
፡፡እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፡፡
የዮሐንስ ራዕይ ጥናት

# እንኳን ደህና መጣችሁ ወደ ዮሐንስ ራእይ

በአሰፋ ጃቴ

2002 (1994 ዓ.ም.)

1ኛ እትም ሐምሌ 1994 ዓ.ም.

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

ስለ መጽሐፉ አስተያየት ቢኖርዎት
በመ.መ.ሣ.ቁ. 16252 አ.አ ይጻፉልን

«እነሆ በቶሎ እመጣለሁ!»

የዮሐንስ ራእይ ጥናት

ጸሐፊና አሳታሚ አሰፋ ጃቴ

እርማት ደረጀ በላይነህ

# ማውጫ


ቁጥር ገጽ

1. የዮሐንስ ራእይ ትርጉም
2. ክርስቶስ የመጨረሻ ውሳኔ አለው 6
3. የክርስቶስ ቃል የፍርድ ቃል ነው 8
4. ከአምላክ የተሰጠ የመጽሐፉ አከፋፈል 10
5. ሰባቱ ቤተ ክርስቲያናት 13
   ሀ/ የኒቆላውያን ትምህርት 18
   ለ/ የኤልዛቤል ትምህርት 18
   ሐ/ የዘመናችን ለብተኝነት 26
6. የዙፋን ክፍል
   ሀ/ ዙፋን በሰማይ 29
   ለ/ አራቱ እንስሶች 38
7. በሰባት ማህተም የተዘጋ መጽሐፍ 40
8. የማህተም መከፈት ወይም መፈታት ፕሮግራም 46
9. የመንፈስ ቅዱስ ዘመን 55
10. ለጥበቃ የተደረገ ምልክት 56
11. በበጉ ደም መንጻት (ነጭ ልብስ መልበስ) 57
12. የማይቆጠር ብዙ ሕዝብ 57
13. የሰባቱ መላእክት ማስተዋወቅ 62
14. ሌላ መልአክ 63
15. የመለከት መነፋት 65
16. ሦስት ወዮዎች 69
17. ጥልቅ ጉድጓድ 70
18. ኤፍራጥስና አካባቢው 74
19. ታናሽ መጽሐፍ 77
20. ባህርና ምድር የእግዚብሔር ነው 79
21. ውስድና ብላት 81
22. ጣፋጭና መራራ 82
23. ሁለቱ የእግዚአብሔር ምስክሮች 84
24. ሦስተኛ ወዮ 95
25. የእግዚአብሔር መቅደስ በሰማይ 97

26. ምጥ የያዛት ሴት 99
27. ቀይ ዘንዶ 101
28. የሰይጣን አወዳደቅ 103
29. ወንድ ልጅ 104
30. ከሳሹ ተጥሏል 105
31. የእርኩስ ሥላሴ አሠራር 109
32. እግዚአብሔርን መሳደብ 111
33. ትልቅ ልዩነት 116
34. ከበጉ ጋር በጽዮን ተራራ 117
35. የዘለዓለም ወንጌል ይሰበካል 121
36. ሦስት ትልልቅ ትእዛዛት እንደተሰጠ 122
37. የባቢሎን መውደቅ 126
38. ሁለት ትልልቅ ማስጠንቀቂያዎች 127
39. አዋጅ ነጋሪ ድምጽ 129
40. ሰባቱ የእግዚአብሔረ ቁጣ ጽዋዎች 135
41. ስለ ባቢሎን 142
42. የሦስት ሴቶች ምሳሌ 145
43. የፖለቲካና የንግድ ባቢሎን ፍርድ 149
44. የክርስቶስ ዳግም መመለስና ፍርድ 154
45. የበጉ ሠርግ 157
46. በሰይጣን ላይ የመጨረሻ ውሳኔ 163
47. የክርስቶስ ሺህ ዓመት መንገሥ 168
48. ለዘለዓለም መኖር ተገለጸ 177
49. የመጨረሻ ቃል ማረጋገጫና ጥሪ 188
50. ተጨማሪ ጥቅሶች 196

# መግቢያ

## የዮሐንስ ራእይ ትርጉም እንዴት ተጀመረ?

ጌታን የግል አዳኜ አድርጌ የተቀበልኩት በ1943 ዓ.ም. በሆሣዕና ከተማ ነው:: ከዚያም በ1947 ዓ.ም. አምቦ ከተማ የሕክምና ሣይንስ ለማጥናት ሄድኩ:: ለሁለት ዓመታት የሚሰጠውን የጤና ረዳትነት ኰርስ ካጠናቀቅሁ በኋላ አምቦ ሆስፒታል ውስጥ ሥራ ጀመርኩ:: በዚህ ሥራዬ ለ13 ዓመታት ያህል ካገለገልኩ በኋላ ፊቴን ወደ ወንጌል ሥራ አዞርኩ:: በመሆኑም በአምቦ ከተማ ለሃያ አምስት ዓመታት የኖርኩት የእግዚብሔር ፈቃድና ጥሪ መሆኑን በመገንዘብ ነው:: በርግጥ ያኔ ሚስዮን ገቢ ካለችው አንድ ጸሎት ቤት በቀር አንድ እንኳ የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን አልነበረም:: የጨለማው ገዢ ዲያብሎስ ጠቅላላ አካባቢውን ተቆጣጥሮት ነበር:: ይሁን እንጂ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለው እግዚአብሔር ነውና ሥራውን አላቋረጠም:: (2ኛ ቆሮ. 4:6)

እንደሚታወቀው ከሚኒዝም ወደ ሀገራችን ከገባ በኋላ ግን እንደማንኛውም ሥፍራ አምቦ አካባቢም ያለን ክርስቲያኖች ለወንጌል ብዙ መከራና ችግር አሳልፈናል:: በካድሬዎች ድብደባ፣ ስድብና ማሥፈራራት ተፈራርቀውብናል:: በመሆኑም የግድያ ደብዳቤዎች በመላክ ልጆቼንም ስላሰቃዩብኝ በ1972 ዓ.ም. ወደ ትውልድ ቦታዬ ወደ ሆሣዕና መመለስ ግዴታዬ ነበር:: እዚያም በጤና ጥበቃ ሌሞ በሌሣ የተባለ ሆስፒታል ለመሥራት ፈልጌ ብጠይቅም ቦታ የለም ተባለኩ:: ይህንን ቦታ የመረጥኩት የሥጋ ዘመዶች ስለነበሩኝ ከአብዮቱ እሳት ለመደበቅ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ግን ከሚነደው እሳት ማዳን እንደሚችልና በዚያም ውስጥ መጠቀሚያ ሊያደርገኝ ስለፈለገ በዋናው እሳት መሃል ሆሳዕና ከተማ ውስጥ አስቀመጠኝ:: እዚያ ከተማ ጤና ጣቢያ በምሠራበት ጊዜ እንዳስተዋልኩት ብዙዎች ክርስቲያኖች ከጌታ ተለይተው እየደከሙና በፍርሀት ጸሎት ከልክሉ እየገደላቸው ነበር:: 1973 ዓ.ም. አካባቢ ጊዜው የቀይ ሽብር ስለ ነበረ ከጥቂት ክርስቲያኖች በስተቀር ብዙዎቹ ሊንቀሳቀሱልኝ አይቻሉም:: ይሁን እንጂ ከአንድ ቤተ ሰብ ጋር የጸሎት ሕብረት

ጀመርን:: በሳምንት ሁለት ቀን ለአዋቂዎች፣ አንድ ቀን ለልጆች እኔ ቤት ውስጥ ቀጠልን:: ከዚህ ተነሥተንም ዕለት በዕለት እየበዛን ሄድን:: እንግዲህ በዚህ የቤት ለቤት ሮግራም ነው የዮሐንስ ራእይን ማጥናት የጀመርነው::

ሥርዐቱ ከሁለትና ሦስት ሰዎች በላይ በአንድ ሥፍራ መሰባሰብ ወንጀል ነው በሚባልበት ጊዜ እኛ የዮሐንስን ራእይ ለማጥናት አርባ ሆነን ተገኘን:: ከዚያም ሕጉ እየጠበቀ ሲሄድ እኛም በቁጥር ስንበዛ፣ «ምን እናድርግ»? ተባባልን:: ጌታ የሰጠን መልስ ለጸሎት ቤት መሥሪያ ጸልዩ የሚል ነበር:: ከዚያን ቀን ጀምሮ ሁላችንም ለመጸለይ ወደ ኋላ አላልንም:: «ጌታ ሆይ ለሰው የማይቻል ለአንተ ይቻልሃል» ብለን ጸሎት ቀጠልን:: ከዚያም የቦቢቾ ቃለ ሕይወትን ጽ/ቤት አማክረን እኔና አቶ አባጉሌ ኑናሞ ደብዳቤዎች አጽፈን የመሬት ጥያቄ ደብዳቤ ወደ ማዘጋጃ ቤት አስገባን:: እግዚአብሔር በድንቅ ሁኔታ 12 ሺህ ካሬሜትር ቦታ በእጃችን አስገባልን:: ቤተ ክርስቲያን ከሠራን በኋላ በ1982 ዓ.ም. ቤተሰቦቼን ይዤ አዲስ አበባ ለሥራ ቅያሬ እስከ መጣሁ ድረስ የዮሐንስን ራእይ ጥናት ቀጥዬ ነበር::

በጊዜው እስከ ራእይ ምዕራፍ 14 ደርሼ ስለ ነበር አዲስ አበባ መጥቼ ይህንኑ ጥናት ቀጠልኩ:: ከሀገር ውጭ አሜሪካም ሀገር ይህንኑ ጥናት ቀጥዬ እነሆ ዛሬ በእግዚአብሔር እርዳታ ለሕትመት በቅቶልኛል::

ከ1973 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓም ድረስ ጊዜ የወሰደ ቢሆንም አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ጌታ ከዘላለም እስከ ዘላለም ምስጋና ይድረሰው:: አሜን!

አሰፋ ጃቴ

# ምስጋና

በአሜሪካ አገር በዳላስ ከተማ ባለች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ ለነበረች ለወይዘሮ ፋፌ በኰምፒተር በመቅረጽና በማረም፣ በማስተካከል የረዳችን እህትና በካንሳስ ከተማ ባለች ቤተ ክርስቲያን በኰምፒዩተር በመቅረጽና በማረም የረዳኝን አቶ ፍጹም ሐዋዝን፣ እንዲታተም ሞራል በመስጠት በነፃ ለሠሩልኝና ላደፋፈሩኝ ሁለቱ ግለሰቦች ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

መጽሐፉን በድጋሚ ያረሙልኝ አቶ ደረጀ በላይነህንና በኮምፒተር በድጋሚ በመጻፍ የረዱኝ ወ/ሮ አልማዝ ወርቁን አመሰግናቸዋለሁ። እግዚአብሔር ይባርካቸው!

አሰፋ ጃቴ

# መግለጫ ወይም መቅድም

የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ከባድና በጣም የተፈራ መጽሐፍ የሚመስላቸው ብዙዎች ናቸው። ሌላው ቀርቶ ብዙ የወንጌል አገልጋዮች እንኳን የዮሐንስ ራእይን ይፈሩታል። የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍን ተከታትሎ ማስተማርና መተርጐም ከባድ ነው ብለውም ያስባሉ። በዳንኤል 8፡26 እና 12፡4 ላይ ትንቢቱን እንዲዘጋ ለዳንኤል ተነግሮታል። ስለዚህ የዮሐንስ ራእይም ዝግ መጽሐፍ ይመስላቸዋል።

ለዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ የተከፈተና የተፈታ መጽሐፍ መሆኑን መርሣት የለብንም። ራእይ 22፡10 ላይ ትንቢቱ ያልተዘጋ መሆኑንና በታረደው በግ ሥልጣን ማህተሙ እንደተፈታና እንደ ተከፈተ በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 5 ላይ ስለምንመለከት መጽሐፉ የተከፈተና የተፈታ ነው። ዝግ አይደለም። በራእይ 1፡3 የተሰጠውን ተስፋ ተመልከቱ። በዚህ መሠረት የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ እንዲጠናና እንድናስተምር ለአብያተ ክርስቲያናት የተላከ መልእክት ነው፤ ራእይ 1፡11።

የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ በብዛት ወደፊት ስለሚመጣው ፍርድ ስለሚናገር የበለጠ ይፈሩታል። በእርግጥ እኔም እንደተመለከትኩት የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ወደ አማርኛ በተተረጐሙ መጽሐፎች ላይ

በእያንዳንዱ ምዕራፍና ቁጥሮች ላይ ሃሳብ ሳይሰጥበት አልፎ የሄደበት ብዙ ቦታ ስለሆነ ራእይን ማጥናት ቀላል አይሆንም። ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት በእያንዳንዱ ቁጥር ሐሳብ መስጠት ስለ ሞከርኩ ወደፊት ለሚያጠኑ ሰዎች ይቀልላቸዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

## ዋቢ መጻሕፍት

1. የኤፒ ትርጉምን (by Theodore H.Epp)
2. የመጽፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (Bible Dictionary)
3. ከዊሊያም ባርክሊ (William Barclay) ስለሆነ ላመሰግናቸው ይገባናል።
4. ዋናው መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው።

## ማሳሰቢያ

ይህ የዮሐንስ ራእይ ትርጉም

1ኛ) ዮሐንስ ራእይን በግል ለሚያጠኑ፣

2ኛ) ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች እንደሚረዳ ተስፋ አደርጋለሁ።

3ኛ) ይህ መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከዮሐንስ ራእይ ጋር አብሮ ካልተነበበ ብዙ አይጠቅምም

አስፋ ጃቴ

# የዮሐንስ ራእይ ትርጉም

ራእይ ማለት ተገለጠ ወይም ታየ ማለት ነው:: የተገለጠው ኢየሱስ ነው:: ለዮሐንስ ታየ (ተገለጠ) ራእይ 1:9-10::

## የመፍሐፉ አከፋፈል

መጽሐፉ 22 ምዕራፎች አሉት:: እነዚህ ምዕራፎች በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላሉ:: ራእይ 1:19 ተመልከት::

1. አንደኛ ክፍል:- «እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን» ይላል:: በምድር ነው ይህ አንደኛ ክፍል ከምዕራፍ 1-3 ያለው ነው::

   ይህ ክፍል የቤተ ክርስቲያን ዘመን በዚህ ዓለም ላይ ያሳያል:: ከሐዋርያት ዘመን አንስቶ እስከ ክርስቲያኖች መነጠቅ ወይም የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ወይም ወደ ጌታ መወሰድ ጊዜ ድረስ ያለውን ሁኔታ ያሳያል:: ቤተ ክርስቲያን አሁንም በምድር አለች ማለት ነው::

2. ሁለተኛ ክፍል:- በምዕራፍ 1:19 ላይ ያለውን ተመልከት፣ «ከዚህ በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን» ይላል:: በሰማይ ማለት ነው:: ይህም ሁለተኛው ክፍል ሲሆን ከምዕራፍ 4-22 ያለውን ክፍል ያጠቃልላል:: «ከዚህ በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን» ይላል:: ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ የሚሆነውን ነገር ማለት ነው::

ራእዩን ያየውና የጻፈው ሐዋርያው ዮሐንስ የስሙ ትርጉም ደስታ ወይም ተድላ ማለት ነው:: ራእዩን የገለጠው ወይም ያሳየው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ወደ ሰማይ ከአረገ በኋላ በ100 ዓ.ም. ላይ ነበር:: ዘመኑ ከ90-100 ዓ.ም. ውስጥ ተብሎ ይገመታል:: ሌላ ጊዜ ደግሞ በክርስቶስ ትእዛዝ ወይም ፈቃድ ልዩ ልዩ መልአኩች ራእዩን ገልጠዋል ወይም አሳይተዋል:: ለምሳሌ ራእይ 22:8-9 ተመልከት::

አንደኛው ክፍል:- ከምዕራፍ 1-3 ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ሲሆን

ሁለተኛው ክፍልም:- ከምዕራፍ 4-22 ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የለችም::

ትእዛዝ ሰጭ ያለውና የነበረው የሚመጣውም ኢየሱስ ነው::

5. ሰባቱ መናፍስት፡ በዮሐንስ ራእይ መናፍስት የሚለው በመጽሐፍ ቅዱስ 54 ጊዜ ተጽፏል:: ራእይ 1:5፤4:5 ሌሎችም ዘካ. 4:2፤ ዘጸ. 19:16 በተለይ ኢሳ. 11:2-3 ላይ ሰባቱን መናፍስት ተመልከት::

ለክርስቶስ የተሰጡት ሦስት ስሞች፤ ቁጥር 5 ተመልከቱ::

ሀ/ የታመነው ምስክር
ለ/ ከሙታን በኩር
ሐ/ የምድር ነገሥታት ገዢ

ሀ/ ኢየሱስ ክርስቶስ የታመነ ምስክር ነው:: አዎን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ሞት ድረስ የታመነ ምስክር ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረና በሠራቸው ሥራዎች ሁሉ በሰው ፊት ለስማያዊው አባቱ ታማኝ ነበር:: ሌሎች ቢክዱም እርሱ አልካደም:: የተላከበትን የአባቱን መልእክት ለሰው አደረሰ:: ስለዚህ ሰማያዊው አባቱም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መሰከረ:: እንዲህ እያለ:- «ይህ ነው ልጄን ስሙት» ማቴ. 3:16-17፤ 17:5፤ ዮሐ. 12:27-28፤ የሐዋ.ሥራ 3:22-23 ይህ የታመነ ምስክር በምድር በነበረበት ጊዜም ሆነ ከሞት ተነስቶ ወደ አብ ከሄደ በኋላም እርሱ ያልገለጸው ምንም ነገር የለም:: እኛም የነመጨረሻ ውሳኔ ያለበትን ቃሉን መጽሐፍ ቅዱስን በእጃችን ይዘናል:: ክብር ለስሙ ይሁን፣ ማቴ 22:35፤ ሉቃስ 19:10::

ለ/ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በኩር ነው:: የሞትና የሲዖል መክፈቻ በእርሱ እጅ ነው:: ቁ.18 ተመልከት:: ክርስቶስ ለእኛ ሲል ሞቶ ነበር:: አሁን ግን ሕያው ነው፤ ሮሜ 6:9፤ 1ኛ ቆሮ. 15:20:: ሌሎች ሞተው በዚያው ቀሩ:: ክርስቶስ ብቻ ነው ሞትን ድል አድርጐ የተነሳ፤1ኛ ቆሮ. 15:51-57፤ ሉቃስ 24:1-12፤ 24-28:: ዛሬ በሞት ፍርሃት የሚገዙትን ነጻ ሊያወጣ ይችላል፣ ዕብ. 2:14-18:: ሞት በሰይጣን በኩል መጣ፤ ክርስቶስ ግን የዲያብሎስን ሥራ ሊያፈርስ ተገለጠ፤ 1ኛ ዮሐ. 3:8:: ዛሬ በክርስቶስ የሚያምኑ ሞትን መፍራት የለባቸውም፤ ዮሐ. 11:25 ከሞት በኋላ ትንሣኤ አላቸው፤ 1ኛ ተሰሎ. 4:13-18፤ 2ኛ ጢሞ. 1:10::

ሐ/ የምድር ነገሥታት ገዢ ነው:: ክርስቶስ ዛሬ የሚነግስባቸው ሥፍራዎች፣

1. ዛሬ በክርስቲያኖች ልብ ይነግሣል፤ ራእይ 3:20፤ ዮሐ.14:23::
2. በአብ ቀኝ በዙፋኑ ይነግሣል፣ ራእይ 3:21፤ ማር. 16:19፤ የሐዋ.ሥራ 7:56::
3. በዓለም ነገሥታት ላይ ገዢ ነው፤ መዝ. 2:1–12
4. ክርስቶስ ወደፊት በዓለም ሁሉ ለሺህ ዓመት ይነግሣል፤ ራእይ 20:1–15፤ 2ኛ ጴጥ. 3:3፤ ዳን.2:1–49 አንብብ:: ያ ድንጋይ ክርስቶስ ነው:: መንግሥቱም ሁሉን ይገዛል፤ መዝ.(103:):19 ክርስቶስ ወደደንና ከኃጢአታችን በደሙ አጠበን፤ 1ኛ ዮሐ.1:7:: ክርስቶስ አማኞችን ለአምላኩና ለአባቱ ካህናትና መንግሥት እንድንሆን አደረገን፤ 1ኛ ጴጥ. 2:9::

1. ዛሬ የሰይጣን መንግሥት አይገዛንም
2. የዓለም መንግሥት አይገዛንም፤ በዓለም እንኖራለን ግን ከዓለም አይደለንም፣ ዮሐ.17:14–16::
3. ከክርስቶስ መንግሥት ግን ተካፋዮች ነን፤ ሮሜ 8:16–17፤ 2ኛ ቆሮ. 5:20 የክርስቶስ አምባሳደሮች ነን (መልእክተኞች ነን) 2ኛ ጢሞ. 2:11–13::

ክርስቶስ አምላክ አይደለምን? አዎን አምላክ ነው፤ ኢሳ. 9:6፤ ዕብ. 1:8–12 ተመልከት:: ዮሐ. 23:28 ታዲያ አባቱ ለምን አምላኩ ሆነ? ቆላ.1:13–14:: ክርስቶስ ፈጣሪ መሆኑን ይናገራል፤ ዮሐ. 1:1–2 ክርስቶስ እግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል:: ግን ክርስቶስ ራሱን አዋርዶ በሰው ምሳሌ ሆኖ እስከ ሞት ድረስ ለመታዘዝ ራሱን ባዶ አደረገ:: እግዚአብሔር ወይም አምላክ መሆን ተወ፤ ፊልጵ. 2:5–11:: ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በእኛ አደረ፣ ዮሐ. 1:14:: ራበው፣ ተጠማ፣ አዘነ፣ አለቀሰ፣ አንቀላፋ፣ ደካማ ሆኖም ሞተ:: የሰውን ባህርይ ሁሉ ወሰደ:: ስለዚህ አምላክ መባልን ተወ:: የሰው ልጅ ተባለ፣ ሉቃስ 19:10::

ቁ. 7 ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ ይመጣል፤ እንደሚመጣ:–
1. ራሱ ተናገረ፣ ዮሐ. 14:3
2. መላእክት ተናገሩ፣ የሐዋ.ሥራ 1:9
3. ሙሽራይቱ (ቤተ ክርስቲያን) ና ትላለች፤ ራእይ 22:17:: ቤተ ክርስቲያን ዛሬም ትናገራለች::
4. መንፈስ ቅዱስ ና ይላል፣ ራእይ 22:17::

5. ፍጥረት ሁሉ ይጠባበቃሉ፣ ሮሜ 8:19–22 ሲመጣ ለሚያምኑት ደስታ፣ ለሚክዱት ዋይታ ይሆናል፣ 2ኛ ተሰሎ. 1:6–7።

ቁ. 8 ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ ስሙን ተመልከት፤

ቁጥር 9–20 እሥር ቤት የሥራ ቤት ነው ያውም:–

ትምህርት ቤት፣ የገለጻ ቤት ነው። ከጌታ ጋር የምንገናኝበት፣ በበለጠ የምንቀራረብበት ቦታ ነው። ዮሐንስ በእሥር ቤት በፍጥሞ ደሴት ነበረ። በእሥር ቤት ለጌታ ወንጌል ሲል ታስሯል። እሥር ቤት ሰው እንዳይገባ በሩ ዝግ ነው። ግን ከጌታ ጋር ለመገናኛ የሰማይ በር ክፍት ነበር። በዚህ ጌታ ራሱን ለዮሐንስ ገለጸ፤ ቁጥር 12 ተመልከት። በምድር ስላለው ቤተ ክርስቲያን ገለጸ። ከዚህ በኋላ ሊሆን ያለውን ሁኔታ ገለጸ።

ቁ. 10 በመጀመሪያው ራእይ ከጌታ ጋር የተገናኘበት ቀን፣ የጌታ ቀን ነበር። ማለትም እሁድ ቀን ነበር። የመለከት ድምጽ በሚመስል ድምጽ ራእዩን ሰማ። ዞር ብሎ ሲመለከት የሰው ልጅ የሚመስል አየ። በራእይ መስማትና ማየት ነበር። ገለጻም ነበረ ማለት ነው።

ቁ.11 ስለ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት (ቤተ ክርስቲያን)

| | ስማቸው | ትርጉማቸው |
|---|---|---|
| 1 | ኤፌሶን | የተወደደ ወይም የሚናፈቅ ማለት ነው |
| 2 | ሰምርኒስ | ከርቤ ወይም መራራ ማለት ነው |
| 3 | ጴርጋሞን | ከፍ ያለ ቦታ ወይም ፎቅ ማለት ነው |
| 4 | ትያጥሮን | ሳያቋርጥ መሠዋት ማለት ነው |
| 5 | ሰርዴስ | ማምለጥ ወይም መሰደድ ማለት ነው |
| 6 | ፍላደልፍያ | የወንድማማች ፍቅር ማለት ነው |
| 7 | ሎዶቅያ | የሰው ግዛት(የሰው ፍርድ) ማለት ነው |

ኢየሱስ ለዮሐንስ ያስተላለፈው መልእክት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መልአክ ጻፍ ብሎት ነው፤ ቁጥር 11:19።

1. ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በዚያ ዘመን የነበሩ ቤተ ክርስቲያናት ሲሆኑ፣
2. ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ጌታ ተመልሶ እስኪመጣና ቤተ ክርስቲያንን እስኪወስዳት ድረስ ያው የቤተ ክርስቲያን ዘመንን የወክላል:: ይህንንም በሚቀጥለው ጥናት ታገኛላችሁ::

ቁ. 12፤13 የሰው ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበረ::

ሳባት መቅረዝ፣ ቤተ ክርስቲያን ነው:: እውነተኛ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ይባላል፣ ማቴ. 5:16:: እውነተኛው ቤተ ክርስቲያን መቅረዝ ነው፣ ያበራል::

ዘይት:- በመቅረዝ ዘይት ነበረ፤ ዘይት መንፈስ ቅዱስን ይወክላል

ዘይት ያዥ:- ዘይትን (መንፈስ ቅዱስን) የሚይዙ አማኞች ወይም ቤተ ክርስቲያን ነው::

<u>መብራት</u>:- ክርስቶስ ነው:: እርሱ የዓለም ብርሃን ነው፣ ዮሐ. 8:12:: ቃሉ ብርሃን ነው፣ መዝ.(119):105:: አማኞችም ማቴ. 5:14-16:: ቤተ ክርስቲያን ብቻዋን ብርሃን ልታበራ አትችልም:: ክርስቶስ ብርሃን ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብርሃን የሚሰጥ እርሱ ነው:: ቤተ ክርስቲያን (አማኞች) ለብርሃኑ ዓይነተኛ ዕቃ ሆነው ለአገልግሎቱ ብቁ መሣሪያ መሆን አለባቸው:: ቤተ ክርስቲያን በረከት ወይም መርገም መሆን ትችላለች:: ለዚህ ጨለማ ለበዛበት ዓለም ብርሃን የሚያበራ ማን ነው? መልሱ ቤተ ክርስቲያን ነው፣ ማቴ.5:13:: የእግዚብሔርን ብርሃን ለምታበራ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ በመካከልዋ አለ፣ ማቴ. 18:20፤ 28:20::

ክርስቶስ በመካከሏ ይመላለሳል
ጌታን በሥጋዊ ዓይን ማየት አንችልም:: ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይመላለሳል:: በምድርና በሰማይ በየዕለቱ በሚሆነው ነገር እንጨነቅ ይሆናል:: ጌታ ግን ልባችሁ አይፍራ ይላል፣ ዮሐ. 14:1-3:: በምድር ስንኖር አንዳንዴ መንገድና ዘዴ ይጠፋብን ይሆናል:: ግን ጌታ በሰማይና በምድር መንገድ እኔ ነኝ ይላል፣ ዮሐ. 14:6::

በቤተ ክርስቲያን መካከል የሚኖርና የሚመላለስ ክርስቶስ አለ:: እርሱ እግዚአብሔር ስለሆነ በአንድ ጊዜ በሰማይና በምድር ሊሆን ይችላል:: ጌታ ሥፍራን ሊያዘጋጅልን ወደ ሰማይ እንደሄደ ተመልሶ

በሥጋው ሊወስደን በሚታይ ሁኔታ ይመጣል። ስለዚህ ራሳችንን በየዕለቱ ማዘጋጀት የእኛ ጉዳይ ነው፣ 2ጴጥ. 3:11–12።

መዘጋጀትን በበጉ ደም በመታጠብ ነው

ዮሐ. 1:29፤ 1ዮሐ. 7:10፤ ራእይ 1:5፤ ቲቶ 3:5። ክርስቶስን ሕይወታችን ማድረግ የምንችለው በእምነት ነው። የእርሱ ሕይወት ለሕይወታችን በእምነት ወስደን ለሰማያዊ ቤት የተዘጋጀንና ክርስቶስን የምንመስል መሆን አለብን፣ 1 ዮሐ. 3:1–2።

ክርስቶስ የመጨረሻ የውሳኔ ቃል አለው፣ ዮሐ. 15:22

ቁ. 13–15 ክርስቶስ የለበሰው ልብስ

የልብሱ ሁኔታ ቁጥር 13 ከባድ ባለ ሥልጣን መሆኑን ያሳያል፣ ማዕረጉን ያሳያል። የእርሱ ማዕረግና ሥልጣኑን ማን ሊሻማ ይችላል? መልሱ ማንም፣ ምንም የለም ነው፣ ማቴ. 28:18፤ ኤፌ. 1:20–21። የልብሱ ሁኔታ ፈራጅ እንደሆነ ያሳያል። በማያምኑት ላይ ቅጣት የተሞላ ፍርድ ይወስናል፣ ማቴ. 25:41–46። ልብሱ ካህን እንደሆነ ያሳያል። ለሚያምኑት አማላጅ እንደሆነ ይገልጻል፣ 1 ዮሐ. 2:2፤ ሮሜ 8:34፤ 1 ጢሞ. 2:5። የሞትና የሕይወት ቁልፍ በእርሱ እጅ ስለሚኖር ማን ያመልጣል፣ ዕብ. 2:3። ስለዚህ ኢየሱስ የመጨረሻ ወሳኝ ቃል አለው ማለት ነው።

ቁ. 14 የራሱ ጠጉር ነጭ

የራሱ ጠጉር እንደ በግ ጠጉርና እንደ በረዶ ነጭ የሆነበት ምክንያት፣ ዳንኤል 7:9 ተመልከት። እረጅም ዕድሜ ያለው መሆኑንና የዘላለም ነዋሪ አምላክ መሆኑን ይገልጻል፣ መዝ (90):1–5፤ 12:25–27። እርሱ ዘላለማዊ አምላክ ነው፣ ዮሐ. 1:1–2 ምዕ. 9:56–58፤ ዘጸ. 3:11–15። ዘመናት ሁሉ የእርሱ ነው።

ነጭ፦ የእግዚአብሔርን ቅድስና ያሳያል። ፍጹምነትን ያሳያል። አንድ ቀን በነጩ ዙፋን ፊት ይቆሙና ፍርድን ይቀበላሉ፣ ራእይ 20:11።

ዓይኖቹ፦ ቁጥር 14 እንደ እሳት ነበልባል የሆነ ሁሉን ያያል። ሁሉን ነገር ግልጥ የሚያደርግ ነው። ዓይኖቹ ምንም ሚስጢር ሳይደብቁ ያያሉ፣ ዕብ. 4:13፤ መዝ.(139):7–12፤ ዘካ. 4:10፤ መዝ. 11:4። በዚህ ዓይኖቹ ፊት ሁሉም ሰው ይቆማል። እኛ ክርስቲያኖች እንኳን ለፍርድ እንቆማለን፣ 1ኛ ቆሮ. 3:11–15፤ 2ኛ ቆሮ. 5:10። ማንም

ሰው በፊቱ ውሸት ሊናገርና ሊዋሽ አይችልም፣ የሐዋ. ሥራ 5:1:: ለሁሉም እንደሥራው ሊከፍል ይመጣል፣ ራእይ 22:12:: ዓይኖቹን ትፈራለህን? እንግዲያውስ ከእርሱ ጋር ታረቅ::

ቁ.15 እግሮቹ በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ

ናስ፡- ምሳሌው የጥንካሬውን ሁኔታ ያሳያል:: በእሳት የነጠረ ስለ ንጽህናና ቅድስና ያመለክታል:: ደግሞም ናስ ፍርድን ያሳያል:: ታላቅ አዳኝ የሆነ ኢየሱስ እንደ እሳት የሚፋጅ ፈራጅ ነው:: የኢየሱስ እግሮች ከሰው እግሮች የተለዩ ናቸው:: የሰው እግር ወደ ፋጥት ይሮጣል፤ (ሮሜ 3:16):: የኢየሱስ እግሮች ግን የደህንነትን ወንጌል ይዘው መጥተዋል፤ ኢሳ. 52:7፤ ሮሜ 10:15:: ስለዚህ በዚህ ቦታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝና ፈራጅ እንደሆነ እንመለከታለን::

ቁ.15 ድምጹ እንደ ብዙ ውኃዎች ድምጽ ነበር

እርሱ ሲናገር የእርሱ ድምጽ እንጂ የሌላ የማንም ድምጽ እንደማይሰማ፣ ጸጥ እንደሚል ያሳያል:: የሌላ ፍጥረት ድምጽ ዝም ይላል ማለት ነው:: ወደ ምድራችን የእግዚአብሔርን ትክክለኛ መልዕክት ይዞ የመጣ እርሱ ብቻ ነው:: ሌላ ሃይማኖት ቢሆን እምነትም ቢሆን በኢየሱስ ፊት ዝም ይላል:: አፍ ሁሉ ይዘጋል ተብሏልና፤ ሮሜ 3:19:: ኢየሱስ ብቻ እውነትም ሕይወትም መንገድም ነው፣ ዮሐ. 14:6፤ ዕብ. 1:1–3፤ 2ኛ ቆሮ.5:8–21:: በዓለም ብዙ ሰባኪዎችና ተናጋሪዎች የኃይማኖት መሪዎች ሁሉ በእርሱ ፊት ዝም ጸጥ ይላሉ፤ ፍርዱንም ይሰማሉ:: ዛሬ የእርሱ ድምጽ በወንጌል አማካይነት ይሰማል:: ዳኑ፤ አማላጃችሁ ልሁን ይላል:: ፍርድም እንኳን ይመጣል ይላል:: በየዘመናቱ ለሰው ልጆች ማስጠንቀቂያ ይሰጣል:: ወንጌልን የሚሰሙት ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው ይላል:: አንተስ የእርሱን ድምጽ ሰምተሃል? ምሳሌ 8:34:: ከሁሉ በላይ ዛሬ የሚነገረው የክርስቶስን የፍቅር ድምጽ ነው:: ዛሬ የጌታን የፍቅር ድምጽ በወንጌል ለሚሰሙትና ለመስማት ለማይፈቅዱት ሁሉ ሳይቀር በምሕረቱና በጸጋ ይጣራል፣ 1ኛ ተሰሎ. 4:16፤ ራእይ 6:15–17፤ 2ኛ ጴጥ.2:23፤ ማቴ. 11:28–29::

ቁ. 16 በቀኝ እጁ ያሉት ሰባት ከዋክብት::

የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ናቸው፤ ቁጥር 20ን ተመልከት:: መዝ. 34:7፤ 1ኛ ቆሮ. 11:10:: ኢየሱስ ሰባቱን ቤተ ክርስቲያናት በቀኝ እጁ ይዟል:: ቀኝ እጅ ሙሉ የእረፍት ሥራ

ነው:: ሙሉ ኃይል፣ ሙሉ ጥበቃ፣ ሙሉ ሰላምና ፍቅር ያለበት ቦታ ነው፤ ዮሐ. 14:27፤ መዝ. 17:5፤ 7,8::

ቁ. 16 በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ
ይህ ሰይፍ የብረት ሰይፍ ሳይሆን የክርስቶስ የቃሉ ሰይፍ ነው፣ ዕብ. 4:12:: ክርስቶስ የሚናገረው ቃል እውነትን ሲያጸድቅ ውሸትን ያፈርሳል::

## የክርስቶስ ቃል የፍርድ ቃል ነው

1. የክርስቶስ ቃል ለአማኞች የፍርድ ቃል ሳይሆን የመዳን ቃል ነው፣ ዮሐ. 5:24:: የአማኞች ፍርድ በጌታ በቀዩ ወንበር ፊት ስለ ሥራቸው ነው፣ 2ኛ ቆሮ. 5:10:: ስለ ሕይወታቸው ፍርድ የለባቸውም፣ ሮሜ 8:1:: ስለ ሥራቸው ፍርድ አለ፣ 1ኛ ቆሮ. 3:11–15:: ይህም ለሽልማት ነው::
2. በጌታ ስላላመኑት የፍርድ ቃል በነጩ ዙፋን ፊት መቆም ሲሆን፣ ስለ አለማመናቸው በሕይወታቸው ሲፈረድ ነው፣ ራእይ 20:15፤ 21:8፤ 19:15::
3. ስለ ክርስቶስ የተነገረ የፍርድ ትንቢት ተመልከት፣ ኢሳ.11:4::
4. ሐሳዊ መሲህን በቃሉ ሰይፍ ሲመታ፣ 2ኛ ተሰሎ. 2:8:: ምንም ፍጥረትና ሰው ክርስቶስ ከተናገራቸው ቃላት ሊያመልጥ አይችልም፣ ዮሐ. 12:48:: የክርስቶስ አፍ የእግዚአብሔርን ቃል ሲናገር፣ የሌላ ሰው አፍ ግን ሐሰትን ያወራል፣ ሮሜ 3:13፤ 14:18:: ሥጋዊ ሰው ውጭን ያያል፣ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል፣ 1ኛ ሳሙ. 16:7:: የሰውን ሁኔታ በመዝሙር 36:1–3 ተመልከት::

ቁ.16 <u>የፊቱ ሁኔታ</u>

ፊቱ እንደ ፀሐይ በኃይል ያበራ ነበር:: የሚያንጸባርቅ የእግዚአብሔር ልጅ ሙሉና የመጨረሻ ሥልጣን አለው ማለት ነው:: ኤር.10:10 ስለ እርሱ ጻፈ:: ዮሐንስ እንደገና ስለ ክርስቶስ ፊት ሲናገር ራእይ 20:11 በዚያ ቀን በክብሩ ፊት የሚቆም አይገኝም:: እርሱ የከተማይቱ መብራት መሆኑ እጅግ ይደንቃል፣ ራእይ 21:23::

ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በመጣ ጊዜ ማንም ቀለደበት። ወደ ፊት ተመልሶ ሲመጣ ግን እንደዚያ አይሆንም። በታላቅ ክብር ይመለሳል። ራእይ 1፡7 ተመልከት።

ቁ. 17 ዮሐንስ በራእይ ክርስቶስን ባየ ጊዜ ወድቆ እንደ ሞተ ሰው ሆነ። ማንም እርሱን አይቶ በሕይወት አይኖርም፣ ዘጸ. 33፡17–23 ተመልከት። በኢየሱስ ትንሣኤ ቀን የሆነውን እይ፣ ማቴ. 28፡2–4። በደማስቆ መንገድ ጳውሎስ ምን እንደሆነ ተመልከት፣ በሐዋ.ሥራ 9፡1–9 ተጽፏል። የእግዚአብሔር ፊት ለሚያምኑት ለጥፋት አይደለም።

ለምሳሌ ሙሴን መጥቀስ ይቻላል፣ ዘጸ. 33፡17–23፤ ራእይ 1፡17፤ የሐዋ.ሥራ 9፡1–9። በእጁ ሽፈናቸው፤ አትፍሩ አላቸው፤ ፈጣሪያቸውና አዳኛቸው ስለሆነ። ያመናችሁትን ታውቃላችሁና አማኝ መፍራት አያስፈልገውም፣ 2ኛ ጢሞ. 1፡2፤ አትፍራ ራእይ 1፡17።

ቁ. 18 ከዘላለም እስከ ዘላለም

የዘላለም ሕይወት ምንድን ነው? ለዘላለም ከጌታ ጋር በደስታ መኖር ነው። ከየት ይመጣል? ከእግዚአብሔር ብቻ ይመጣል። ሰይጣን ነፍሰ ገዳይ ነው፣ ዮሐ.8፡44። ከጌታ ሳይፈቀድ ምንም ሊያደርግ አይችልም፣ ኢዮብ 1፡9–10 ተመልከት።

ሞት ምንድን ነው? ሞት ከእግዚአብሔር መለየት፣ ከእግዚአብሔር ፍርድን መቀበል ነው። ኢየሱስን ለሚያምኑት የሞት መክፈቻ በእርሱ እጅ ስለሆነ።

ቁ. 18 ኢየሱስ ሞትን በሞቱ አሸንፎታል፣ 1ኛ ቆሮ. 15፡55–57።

ጌታ ሞትን መቼ አሸነፈ? በምድር ወረደና ሰው ሆኖ በሞቱና በትንሣኤው ጊዜ። በምን አሸነፈ? በሞቱ አሸነፈ፣ ዕብ. 2፡14–15። ሞት ብዙ ሰዎች እንደሚያስቡት ሁሉ አሸናፊ አይደለም። የተሸነፈ እንጂ።

ሲኦል ምንድን ነው? የሙታን ነፍሳት መቀመጫ ነው። ጌታ ሞቶ ከመነሳቱ በፊት በዚያ የገነት ክፍል የደስታ ክፍል እንዲሁም ላላመኑት የስቃይ ክፍል እንደ ነበረ ሉቃስ 16፡19–31 ይናገራል። ኢየሱስ በሞተ ጊዜ እዚያ ሄዶ ሰብኳል፣ 1ኛ ጴጥ 3፡18–19። ኢየሱስ ከሞት ሲነሳ ግን ከገነት ክፍል ምርኮን ይዞ ወደ ላይ ወጣ፣ ኤፌ. 4፡8–10 ማለትም አማኞችን፣ ኤፌ. 2፡4–7። ከዚያ በኋላ አማኝ ሁሉ የሚሄደው

በሰማይ ወዳለው ገነት ነው፣ 2ኛ ቆሮ. 5፡8፤ 2ኛ ቆሮ. 12፡3–4፤ ፊልጵ 3፡20፤ 1፡23፤ ቆላ. 3፡1:: ዛሬም ሞት ለአማኞች ከሥጋ ተለይቶ ወደ ጌታ መሄድ ማለት ነው፣ ዮሐ. 14፡3:: ዮሐንስ ራእይን እንዲጽፍ ከጌታ የተሰጠ ትእዛዝ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ ብዙውን ጊዜ በጌታ ትእዛዝ እንጂ በሰው ሃሳብ ያልተጻፈ መሆኑን በዚህ ክፍል ልብ እናድርግ:: በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡20–21 ያለውን በሚገባ ማወቅ አለብን::

## ከአምላክ የተሰጡ የመጽሐፉ ክፍሎች

ቁ.19 የመጽሐፉ ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች (ሃሳቦች)

መጽሐፉ በሦስት ዋና ዋና ክፍል ይከፈላል ተብሏል

| | |
|---|---|
| 1. ያየኸውን ጻፍ | ምዕራፍ 1 |
| 2. አሁን ያለውን ጻፍ | ምዕራፍ 2 እና 3 |
| 3. ከዚህ በኋላ የሚሆነው ጻፍ | ከምዕራፍ 4 እስከ 22 |

1ኛ ምዕራፍ 1 ሕያው ጌታን በዘለዓለማዊ ክብሩ ዮሐንስ እንደ አየው

2ኛ በምዕራፍ 2–3 ዮሐንስ በነበረበት ጊዜ የነበረውን ቤተ ክርስቲያንና ዘመኑዋን ዮሐንስ እንደ አየው

3ኛ በምዕራፍ 4–22 ወደ ፊት ከቤተ ክርስቲያን ዘመን በኋላ የሚሆነውን መጨረሻ ያለውን ነገሮች ዮሐንስ እንደ አየው ነው::

ለምሳሌ፣ የመከራ ዘመን፤ የጌታ ወደ ምድር መመለስ፣ የምድራዊ መንግሥቱን ማቋቋም፣ ስለ ፍርድ፣ ስለ አዲስ ሰማይና ምድር ወዘተ. ነው::

በዮሐንስ ራእይ የተገለጠው ኢየሱስ ምን ዓይነት ነው?

ወደ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ወደ ተጻፉት ደብዳቤዎች ስንመጣ የመጽሐፉን አስደናቂ ክፍል እንመለከታለን::

ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን መካከል እንደሚመላለስና እንደሚመረምራቸው፣ ይህም ምን ስህተት እንዳለባቸው ወይም ምን ዓይነት መጽናናትና መልካም ነገር እንዳላቸው ያሳያል:: ለነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ለተባሉት ሁሉ የወሬ ወሬና ሐሰት ሳይሆን

ክርስቶስ ራሱ ነበር የሚናገረው:: በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ስለሚወራው ነገር መደነቅ አይገባንም:: ምክንያቱም ክርስቶስ ራሱ በመካከላቸው ስለሚመላለስ እንደ ተስፋ ቃሉ ሁሉን ያውቃል፣ ማቴ. 28:20::

በአለባበሱም ክርስቶስ ረጅም ልብስ የተጐናጸፈ ነበረ እንጂ እንደ አዳም በኃጢአት ምክንያት ራቁቱን አልነበረም:: በእርግጥ በመስቀል ላይ ራቁቱን የሆነበት ምክንያት በእኛ ኃጢአት የተነሣ እንጂ፣ እርሱ ታላቅ ሊቀ ካህንና ፈራጅ ነው:: ሙሉ ሥልጣን ያለው የክብር ልብስ የለበሰ እግዚአብሔር ነው:: ለእርሱ ሙሉ ሥልጣን የተሰጠው እንደሆነ፣ ፊልጵ. 2:6–11 ተጽፏል:: ይህ በቤተ ክርስቲያን የሚመላለሰው ኢየሱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚሰበሰቡ ብቻ ሳይሆን ግለሰብንም ሆነ ምዕመናንን በግልጽ ያያል:: ምንም ነገር ከእርሱ አይደበቅም፣ ዕብ. 4:13::

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚመላለስ ኢየሱስ ለሁሉም ትክክለኛ ፍርድ ይፈርዳል:: የእርሱ ፍርድ የመጨረሻ ውሳኔ ነው፣ ዮሐ. 5:27–30 ያየውንና የሰማውን ይፈርዳል:: ፍርዱም እውነት ነው::

**ቁጥር 20 የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ምስጢር**

1. ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ናቸው::
2. ሰባቱ የወርቅ መቅረዞች የተባሉት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 2
# ሰባቱ ቤተ ክርስቲያናት

እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን አንድ የቤተ ክርስቲያንን ዘመን ይወክላል።

1. የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን፣ጥሩና መንፈሳዊ ኃይል ያለበትን እንደ የሐዋርያት ዘመን ቤተ ክርስቲያን ዓይነቱን መወከል ይችላል።

2. ሰምርኔስ፣ በቤተ ክርስቲያን ብዙ ሰማዕታት የሆኑባት የሮም መንግሥት የእግዚአብሔርን ሰዎች ያሰቃዩበትና የገደሉበትን ዘመን ይወክላል።

3. ጴርጋሞን፣ የቤተ ክርስቲያን ሕብረትና ነጻነት የነበረውን የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመን ይወክላል

4. ትያጥሮን፣ በቤተ ክርስቲያን በጣም ከባድ ጨለማ የሆነበትን ዘመንና ከባድ ስህተት የገባበትን ይህ ጨለማ ጌታ እስኪመለስ ድረስ በቤተ ክርስቲያን ስም እንደሚቀጥል ያመለክታል።

5. ሰርዴስ፣ ተሐድሶ የሚያመጡትን የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ንቅናቄን ያመለክታል።

6. የቀሩት ሁለቱ ቤተ ክርስቲያናት እስከ ጌታ ዳግም መምጣት ድረስ እውነትና ውሸት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጐን ለጐን እንደሚጓዙ ያመለክታል።

   ፊላደልፊያ፣ እውነትን ሲወክል
   ሎዶቅያ፣ ውሸትን ይወክላል

በእነዚህ በሁለቱ ቤተ ክርስቲያናት ዘመን እውነትም ውሸትም አብረው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይኖራሉ። ስንዴና እንክርዳድ የመከሩ ጌታ መጥቶ እስኪለያቸው ድረስ አብረው እንደሚኖሩ ፣ማቴ.13፡24–30 ተመልከት።

ቁ. 1–3 ሐሰተኞችን የመለየት መንገድ

ሐሰተኞች አስተማሪዎችን መርምረን ለይተን የምናውቅበት መንገድ፣

1. ኃጢአት የሚያደርጉ ከሆነ፣ 1ኛ ዮሐ. 2፡1፤ 3፡4–10

2. ኃጢአት የለብንም የሚሉ ከሆነ ውሸተኞች ሲሆኑ፣ እግዚአብሔርንም ውሸተኛ ያደርጉታል፣ 1ኛ ዮሐ. 1፡8–10።

3. ክርስቶስ አምላክ መሆኑን ወይም አብን የሚክዱ ከሆነ፣ 1ኛ ዮሐ. 2:22::

4. ጠላትነት ወይም ሰውን መጥላት፣ 1ኛ ዮሐ. 4:20::

5. እግዚአብሔር ስለ ልጁ የመሰከረውን አለማመን፣ 1 ዮሐ. 5:10–11 ወይም አብ ያለውን አለማመን፣ ማቴ. 3:17፤ 17:5፤ ወልድ ያለውን አለማመን፣ ዮሐ. 10:30፤ 14:1:: መንፈስ ቅዱስ ያለውን ዕብ. 3:6–7 መካድ ነው::

ቁ. 4 የመጀመሪያውን ፍቅር መተው

1. ከክርስቶስ ጋር ያለውን የቃሉን፣ የጸሎትን፣ የምስክርነትን፣ የማገልገሉን ሕይወት መተው፣ ሉቃስ 10:38–42:: እንደ ማርታ መሆን የለብንም፤ እንደ ማርያም እንጂ:: ደግሞ እንደ ኤፌሶን 3:16–19፤ 4:15::

2. ከሰዎች ጋር ያለውን ሀ)ክርስቲያኖችን ትወዳለህ? ለ) ጎረቤትህን ታፈቅራለህ? ሐ) ሰዎችን ሁሉ ትወዳለህን? ምን አደረግህላቸው? የወንጌል ፍቅር በሕይወትህ አለ? የነፍሳትስ ፍቅር አለህ ወይ?

ቁ. 5 ማስጠንቀቂያ

1. አስብ እንደ ጠፋው ልጅ፣ ሉቃስ 15:11–24
2. ንስሃ ግባ፣ ተመለስ፣ መዝ. 51:1–13
3. አለዚያ እመጣብሃለሁ፣ ራእይ 22:12::

ቁ.6 የኒቆላውያን ትምህርት

የኒቆላውያን ትምህርት ሰውን ማበላለጥ ነው:: የጌታን ቤተሰብ ወይም ቤተ ክርስቲያንን በማዕረግ ወይም በሥልጣን ሰበብ መከፋፈል የለብንም:: አንዳንዱን ተራ ምዕመን ሌሎችን ካህናት ወይም ቄስ በማለት መለያየት ነው::

ለምሳሌ፣ ኒቆ ማለት አሸናፊ ማለት ሲሆን፣ ላውያን ሕዝብ በማለት መከፋፈል ነው፤ መዝ.139:21–22:: መርሳት የማይገባን ሁላችንም በክርስቶስ አንድ ዓይነት ነን፣ 1ኛ ቆሮ. 12:12–30:: ሥጦታና ችሎታ ልዩ ልዩ ነው፣ ያውም ለጌታ ሥራ እንጂ አንዱ ከአንዱ እንዲበልጥ አይደለም:: እንደዚያ ከሆነማ በማቴዎስ 18:1–6፤ ማርቆስ 9:33–37 ሉቃስ9:46–48 ኢየሱስ የተናገረው እኔ ልብለጥ ባይ በመንግሥተ ሰማያት ስፍራ የለውም ማለት ነው::

## ቁ. 8 የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን

ይህ ቤተ ክርስቲያን የነበረው በግምት ከ64 ዓ.ም. እስከ 316 ዓ.ም. ከኔሮ እስከ ቆስጤንጢኖስ መንግሥስት ድረስ ሁለት ክፍለ ዘመንን ያመለክታል። ይህች ቤተ ክርስቲያን ስደተኛ ስለ ነበረች ጌታ ራሱን ሲያስተዋውቃቸው «የመጀመሪያ የመጨረሻ ሞቶ የነበር አሁንም ሕያው የሆነ» እያለ ነው። አዎን ክርስቶስ በእርግጥ ሞቶ ነበር። መሞቱ እንደ ወንጀለኛ ወይም እንደ ሰማዕታት አልነበረም። የእርሱ ሞት በእኛ ፈንታ ነበር። የክርስቶስ መከራና ሞት አሁን መከራ ለሚቀበሉትና በስሙ ለሚሞቱት መጽናኛና ማበረታቻ ነው፣ ራእይ 2:9። ከጌታ የሚደበቅ ምንም ነገር የለም። ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነውን ነገር ሁሉ ገላጭና አራሚ እርሱ ነው።

መከራህን አውቃለሁ፦ በምዕራፍ 2:9 ላይ ያለው መከራና ከምዕራፍ 6 እስከ 19 ድረስ ያለው መከራ በጣም ትልቅ ልዩነት አለው። በዚህ ምዕራፍ መከራና ስደት የመጣባቸው ምክንያት በቁጥር 4 ላይ የቀደመውን ፍቅር ስለተዉ ወይም ስለጣሉ ሲሆን፣ በልባቸው እንዲያስቡና ወደ ጌታ እንዲመለሱ ነበር። ቅጣት እንደነበረ ማሰብ አለብን፣ ዕብ፣ 12:6–11። ስደት ከደረሰባችሁ አለ ኢየሱስ፣ የኔው ዓይነት ስለሆነ አይዟችሁ፣ ዮሐ. 16:33፤ 1ኛ ቆሮ. 10:13። ደግሞ ኢየሱስ የኔ መከራ መቀበል እናንተ ሐብታም እንድትሆኑ እኔ ደኸየሁ ይላል፣ 2ኛ ቆሮ. 8:9። አሁን ሐብታችሁን በላይ ሰብስቡ፣ ማቴ. 6:19:20፤ 2ኛ ጴጥ. 1:5–7። ድህነት የእናንተ ብቻ አይደለም። እኔም በምድር በነበርሁ ጊዜ ለምድራዊ ሃብት ድሃ ነበርሁ ይላል፣ ማቴ. 8:19–20።

## ቁ. 9 አይሁድ ሳይሆኑ ነን የሚሉ አስመሳዮች

በሰርምኔስ ቤተ ክርስቲያን አንድ ሌላ ችግር ነበር። ያውም አስመሳዮች ወይም ሐሰተኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበሩ። አይሁድ ነን የሚሉ ግን የሰይጣን ማኅበረተኞች ነበሩ። ክርስቲያን ነን ባዮች ግን ያላመኑ፣ በውጭ የበግ ለምድ የለበሱ በውስጣቸው ግን ተኩላዎች የሆኑ አስመሳዮች ማለት ነው፣ ማቴ. 7:15። ለምን የሰይጣን ማኅበርተኛ ሆኑ? መልሱ በውስጣቸው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አልተለወጡም ነበር። ወይም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሕይወታቸው አልተቀየረም ማለት ነው፣ ዮሐ. 3:3–5። ምናልባት ለሥጋ ጥቅም ማኅበርተኞች ሆነው ይሆናል። ለወንጌል ግን እንቅፋቶች ነበሩ፣

ሮሜ 8:5–8:: በምን እናውቃቸዋለን? መልሱ በፍሬያቸው ለቃሉ አይታዘዙም ነበር፣ ሉቃስ 6:46:: እንደዚሁም ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋሪያት ነን የሚሉ ውሸተኞች ነበሩ:: ሐዋርያ ለመባል ሐዋርያ የሚል ሥልጣን፣ ጥሪ፣ ስጦታ፣ ከጌታ ማግኘትና ጌታንም ፊት ለፊት መገናኘት አለባቸው:: እነርሱም በቁጥር ትንሽ ናቸው:: እነዚህ ግን ሐሰተኞች ነበሩ:: ብርሃን ከጨለማ ጋር ወይም ክርስቶስ ከሰይጣን ጋር ወይም መንግሥተ ሰማያት ከሲዖል ጋር ምን ግንኙነት አለውና ነው? 2ኛ ቆሮ. 6:14–18::

በሰርምኔስ ቤተ ክርስቲያን የሆነው ነገር ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ካልተገረዘ በቀር፡ በእኛም ቤተ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል:: ጌታ ይጠብቀን::

ቁ. 10 ጌታ የራሱን ሰዎች ሲያጽናና አትፍሩ ይላቸዋል

ጌታ ምንም ስደትና መከራ አይኖርባችሁም ብሎ ተስፋ አልሰጠንም:: መከራ አለባችሁ ነገር ግን፣ እስከ ሞት ድረስ የታመናችሁ ሁኑ አለ እንጂ:: እኔ የሕይወት አክሊል እሰጣችኋለሁ አለ:: በጌታ የሚያምኑ ሁሉ ቀላል ሕይወት፣ ቀላልም መንገድ ይሄዳሉ አላለም፣ ነገር ግን «አይዟችሁ» አለ እንጂ፣ ዮሐ. 16:33::

ሰይጣን ወደ እሥር ቤት ሊያገባችሁ ነው የሚለውን ተመልከት:: ይችላልን? መልሱ:–

1. ሰይጣን ክርስቶስን ሦስት ፈተና በማቅረብ ፈትኖታል፣ ማቴ. 4:1–11::
2. ኢዮብን (የጌታን ባሪያ) እንዲፈተን አድርጓል፣ ኢዮብ ምዕራፍ 1 እስከ 2 ተመልከት:: ነገር ግን አያሸንፍም::

ሰዎችን ሰይጣን እንዲፈትናቸው እግዚአብሔር ለምን ይፈቅዳል?

ታማኝ የሰርምኔስ ቤተ ክርስቲያን አማኞችን ሊፈትናቸው እሥር ቤት አስገባቸው:: ለምን?

1. የእምነታቸው መፈተን ከክቡር ወርቅ ይልቅ እንዲነጥር ያደርጋል
2. ፈተና ወደ ጌታ በበለጠ ያቀርባል፤ እርሱን እንድንመስል ያደርጋል
3. እንደ ኢዮብ ትዕግሥትን እንድንማር ያደርጋል፣1ጴጥ.4:12–19

4. የሚደርስብን ነገር ሁሉ ለመልካም እንዲሆንልን ነው፣ ሮሜ 8:28–29።

ቁ. 11 የሕይወት አክሊል

ይህ የሕይወት አክሊል የዘላለም ሕይወት ማለት አይደለም። የዘለዓለም ሕይወትን የምናገኘው በጌታ በማመን ነው። ከአመንበት ጊዜ አንስቶ የዘላለም ሕይወት እግዚአብሔር ይሰጠናል፣ ዮሐ. 3:16፤ 36። የሕይወት አክሊል ግን የሚሰጠው በክርስትና የድል አድራጊነት፣ የአሸናፊነት ውጤት፣ ወይም የሚሰጥ ማዕረግ ነው፣ 2 ጢሞ. 2:11፤ ራእይ 3:21 ተመልከት። ይህ የነገሥታት ቤተሰብ ማዕረግ ነው።

ቁ. 12 ወደ ጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን የተላከ መልዕክት

ጴርጋሞን ሦስተኛ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን፣ ዮሐንስ በነበረበት ጊዜ ለጣዖት በማምለኪያ ነገሮች በጣም የታወቀች ዋና ከተማ ነበረች። በዚያን ዘመን፣

1. የሮም ነገሥታቶች እንደ አምላክ ይመለኩ ነበር
2. ከሚመለኩበት ነገሮች አንዱ በየጊዜው የሚፈጠሩ መድኃኒቶች ሲሆኑ፣ የእነርሱ ምልክት እባብ ነበር፤ እባብን ያመልኩ ነበር ማለት ነው።

እባብ የሰይጣን አምልኮ ምልክት ነው። ስለዚህ ነው ጌታችን የሰይጣን ዙፋን ያለበት የሚለው። በእኛም ጊዜ ቢሆን ያለ አምልኮ ነን ለማለት አንችልም። ምናልባት ሳናውቅ ያ ሁሉ ጣዖት በፀጉር መያዣ ወይም በልብስ ፋሽን ወይም በሌላ እንጠቀም ይሆን ይሆናል። ስለዚህ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ተያያዥነት ባለው ሁኔታ ሁሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ቁ.12 በሁለት በኩል ስለታም ሰይፍ

በሁለት በኩል ስለታም ሰይፍ በዕብራውያን 4:12 እንደ ተገለጠው የእግዚብሔር ቃል ነው። በአንዱ በኩል የሚያድን ሲሆን በአንዱ በኩል የሚፈርድ ነው። ሰዎች በቃሉ በኩል ጌታን ካመኑ ያድናል፤ ይጠግናል፤ ይፈውሳል። ወንጌል ደህንነት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ቃሉን ቢንቁ ቢጠሉ ይፈረድባቸዋል፣ ዮሐ. 12:48። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ሆይ ቃሉን ከሚያጣምሙት ከሐሰተኞች ትምህርት ተጠንቀቂ፤ ተጠበቂ፣ 2ኛ ጢሞ. 4:2–4፤ 2ኛ ቆሮ. 2:17። ቃሉም

መጽሐፍ ቅዱስ ነው፤ ይህ ቃል ዘለዓለማዊና የማይለወጥ፣ ከእግዚአብሔር አፍ ወጥቶ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ነው። ቃሉ በክርስቶስ አዲስ የተወለዱትንና የሚክዱትን ይለያል።

### ቁ.13 የሰይጣን ዙፋን

የሰይጣን ዙፋን በምድር ላይ በግልጽ የተጀመረው በባቢሎን ነው። ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ንጉሥ ናምሩድ በነበረበት ጊዜ ናምሩድ እናትና ልጅ የተባለ አምልኮ ጀምሮ ነበር። የተጀመረውም በናምሩድና በሚስቱ ነበር፣ ዘፍጥ. 10፡6–12። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ ሃይማኖቶች ሄዶ ሄዶ በእናትና ልጅ ቅርጾችና ምስሎች ይደገፋሉ። ያ ማለት የጌታችንና የማርያምን ስዕል ለሚያመልኩት ሁሉ ጭምር ነው። መልካምነቱ እውነተኛ የክርስትና ኃይማኖት በሥዕልና በቅርጽ ስለማይደገፍ ደስ ይለናል። ክርስትና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ብቻ ይደገፋል፣ ዮሐ. 4፡23–24። ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም በመንፈስና በእውነት ብቻ ነው።

### ቁ. 13 ሃይማኖቴን አልካድህም

(በአዲስ ትርጉም ሃይማኖትህን ይላል) ስለዚህ ስሜን አጥብቀህ ይዘሃል ማለት ነው።

በዚህ ቦታ ኢየሱስ ሃይማኖትህን አይልም። ነገር ግን ሃይማኖቴን ይላል፤ ክርስትና በእውነት የኢየሱስ ሃይማኖት ነው። የእኛ እምነት ከሰው ሳይሆን ከእርሱ ከኢየሱስ መሆኑን በግልጽ እንመለከታለን። ክርስትና የእኔና የአንተ ሃይማኖት ነው ብለን የምናስብ ከሆነ ብዙ መሰናከያ ይኖራል። ነገር ግን ሃይማኖታችን ከጌታ ከኢየሱስ የመጣ ከሆነ ማንም ሊያሰናክለን አይችልም። «የገሃነም ኃይል አይችልም»፣ ማቴ. 16፡18። እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፣ ኤፌ. 2፡8–9፤ ሮሜ 10፡17። ስለዚህ እምነት ሥር መሠረትን አልፎ የሚጠልቅ ነው እንጂ ከወንጌል ተስፋ የሚያነቃንቅ አይደለም፣ሮሜ 8፡38–39።

ከጴርጋሞን አማኞች አንዳንዶቹ በእምነት መንገድ መቀጠል አልቻሉም። ምክንያቱም ከባድ ስደት ስለነበረባቸው እምነታቸውን ትተው ነበር። እምነታቸውን ከጌታ መቀበላቸውን የሚረዱ ሁሉ እስከ መጨረሻ ይጸናሉ። የክርስትና እምነት ጽናት በጌታ ነው እንጂ በሥራ አይደለም። ክርስቶስ በሠራው በአዳኝነቱ ሥራ ነው እንጂ።

## ቁ. 14 በጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ያሉ ስህተቶች

በጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ስህተት የሆኑ ነገሮች መኖራቸውን ጌታ ያውቅ ነበር:: ይሁን እንጂ በጴርጋሞን የነበሩ አማኞች በሙሉ የተሳሳቱ አልነበሩም:: እርግጥ በወንጌል ሥርዓት የማይሄዱ፣ ያውም የበለዓምን ትምህርት የሚያደንቁ አንዳንዶች ቢኖሩም ከእምነታቸው የወጡ ግን አልነበሩም:: ለምሳሌ አንድ በስብሶ የገማ አትክልት ሁሉንም እንደሚያበላሽ ሁሉ፣ በቤተ ክርስቲያንም የበለዓም ትምህርት ሌሎችን የሚያበላሽ ነበር:: የበለዓም ትምህርት ምን ጊዜም ቢሆን የሐሰት ትምህርት፣ የዝሙት ኃጢአት፣ ውሸት፣ ገንዘብ ነክ የሆኑ ትምህርቶችን የያዘ የሐሰት ትምህርት ምንጭ ነው:: ታሪኩ በኦሪት ዘኍልቁ ምዕራፍ 23 እስከ ምዕራፍ 25 ተጽፏል:: ከአብርሃም አንስቶ እግዚአብሔር የባረከውን ሕዝብ በለዓም ሊረግም ይሞክራል:: የሐሰት ትምህርቶች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተረገሙ ናቸው:: ሰይጣን መቼም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተቻለው መጠን የሐሰት ትምህርት እንዲገባ ጥረት ማድረጉን አያቋርጥም:: በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ማለትም በሥላሴ አካል ሦስትነት፣ በመለኰት አንድነት ላይ ክህደትን ማምጣት የሰይጣን ዋና ተግባር ስለሆነ፣ መጠንቀቅ አለብን፣ ያዕ. 4:4፤ ኤፌ. 6:10–12:: የበለዓምን ትምህርት የሚከተሉት ዛሬም እንዲህ ይላሉ፤ ምግብን ብንበላ መጠጥንም ብንጠጣ ከዚያም ሰክረን ከዚያም ብናመነዝር ምንም አይደለም:: አትብሉ አትጠጡ የሚል ሕግ የለም ይላሉ፤ ኢሳ. 22:13–14:: በመጠጥና በምግብ ምክንያት ክርስቶስን ያሳዝናሉ፣ ሮሜ 3:24፤ 14:17:: በለአም ምን ጊዜም የመጠጥና የመብል፣ የዘፈንና የዝሙት ምሳሌ ነው:: እንዲሁም ገንዘብን የመውደድ::

## ቁ.14 የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያንና የበለዓም ትምህርት

በጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን የበለዓም ትምህርት በውስጥ ነበር:: ስለዚህ ጌታ ይነቅፋቸዋል:: አንተም ክርስቲያን ሆይ በምትበላበትና በምትጠጣበት ጊዜ ጌታን የት አስቀምጠሃል? ሮሜ 14:17–23፤ 1ኛ ቆሮ. 10:31::

## ቁ. 15 የኒቆላውያን ትምህርት

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካህናትና ተራ ህዝብ በመባል መከፋፈልን የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በቁጥር 6 እና 7 ላይ ጠልታለች:: ነገር ግን የጴርጋሞንን ቤተ ክርስቲያን ተቀብላ በውስጧ ደብቃለች::

የተደበቀውን የሚያይ ጌታ የምትቅፍብህ ነገር የኒቆላውያንን ትምህርት ነው እያለ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

ቁ. 16 ለንስሐ ይጋብዛል

1. ንስሃ ግባ ሲል እውነተኛ ክርስቲያን ንስሃ ገብቶ ይመለሳል
2. ቶሎ እመጣብሃለሁ ሲል እውነተኛ ክርስቲያን የጌታን መመለስ የጠባበቃል
3. በአፌ ሰይፍ እዋጋለሁ ሲል እውነተኛ ክርስቲያን የእግዚብሔርን ፍርድ አይረሳም።
4. በቁጥር 17 ድል ብታደርግ ሽልማት እሰጥሃለሁ ያለው ክርስቲያን የእግዚብሔርን ሽልማት አይረሳም፣ በተስፋ ይጠባበቃል።

ቁ. 17 ጆሮ ያለው ይስማ

የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን የሚሰማ ጆሮ አለው፤ የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ይሰማል፤ የቃሉን ድምጽ ያውቃል። አንተስ የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ትለያለህ?

የተሰወረ መና

ስለመና ዘጸ.16፡11–15፤ 16፡33፤34፤ ዕብ. 9፡4፤ መዝ.(78)፡25 ለክርስቲያን ግን ዮሐ. 6፡31–35 ስውር መና መንፈሳዊ በረከትን ሁሉ ያመለክታል።

ቁ. 18–19 ትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን

ትያጥሮን ማለት የማያቋርጥ መሥዋዕት ማለት ነው። ወደ ትያጥሮን መልእክት የላከው ሰው ማን እንደሆነ በቁጥር 18 ተመልከት። ስሙ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

ዓይኖቹ፣ ሁሉን ነገር ያያል፣ ይመለከታል፣ ይወጋል፣ ይፈርዳል።

እግሮቹ፣ (እሳት የሆነ) ይፈርዳል፣ ይበቀላል። እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሰው ልጅ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ በማንም አይፈርድም፤ አሞጽ 3፡7፤ ዕብ. 2፡3። ይህ ቤተ ክርስቲያን በብዙ መልካም ነገሮች የታወቀ ነበር።

ቁ. 19 በሥራ፣በፍቅር፣በእምነት፣ በአገልግሎት እንዲሁም በትዕግሥት እንዲያውም ሥራቸው ከፊተኛው ሥራ በላይ ይበዛባቸው ነበር። ዓይኖቹ ሁሉን የሚመረምር ጌታ አይቷቸዋል። ነገር ግን የሚነቅፈው ነገር ነበር። ነቢይ ነኝ የምትለዋ ኤልዛቤል በእነርሱ መካከል ነበረች።

ቁ. 20–23 ስለ ኤልዛቤል 1ኛ ነገሥት 16–31፤ 2ኛ ነገ. 9–22 ተመልከት:: የባዕድ አምልኮ ምሳሌ፣ የዝሙት አገልግሎት ምሳሌና እናት እንደሆነች ያሳስበናል:: በዚህ ቤተ ክርስቲያን የኤልዛቤል ትምህርት ነበር::

1) የዝሙትና የጣዖት አምልኮ ነበረ ማለት ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተደበቀውን ኃጢአት ጌታ አይቷል:: ወንድሞች ሆይ በእኛስ ቤተ ክርስቲያን የተደበቀው ምን ይሆን? የሥጋን ፍላጎት መፈጸም ነውን? የራስ ባል ወይም ሚስት ካልሆነ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለን? ዕብ. 13:4፤ 1ኛ ቆሮ.6:9–11፤ 1ኛ ተሰሎ. 4:3–9::

2) ቅዱስ ያልሆነ የረከሰ መንፈሳዊ መሳይ ትምህርት እንደ ዝሙት ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ጤናማ ያልሆነ ትምህርት ይላል፣ ቲቶ 1:4:: መዳራት አለ? ገላ. 5:19–20 ወንድ ከወንድ ጋር ግብረ ሰዶም አለ? ሮሜ 1:26–27፤ መዝ. 73:27፤1ኛ ነገ.16:18–21፤ 2ኛ ነገ. 9:20:: ኃጢአትን አይቶ ዝም ማለት በደል ነው::

ነቢይ ነኝ ትል ነበር፣ ነገር ግን የሰይጣን ባርያ ነበረች:: አውቃለሁ ማለት፣ እሰብካለሁ፣ አስተምራለሁ፣ እዘምራለሁ ማለት ዋጋ የለውም፤ ነገር ግን በጌታ አምኖ ለቃሉ መታዘዝና ከኃጢአት መራቅ ነው ዋናው ነገር::

ቁ. 21–23 <u>የንስሐ ጥሪ</u>

1. ኃጢአቷን ካልተወች በታላቅ መከራ ላይ እጥላታለሁ ይላል

2. ልጆቿን እገድላለሁ ይላል::

በዘመናችን ኤድስ በሽታ በዝሙት ምክንያት ሰውን እየገደለ ነው:: ክርስቲያንስ እንዴት ይሆን?

ቁ. 24 እና 25 ክርስቲያን ሆይ ኤልዛቤልን አትከተል:: ያላችሁን እምነት፣ መታዘዝን፣ ፍቅርን፣ ንጽሕናን፣ ኃጢአት መጸየፍን አጥብቃችሁ ያዙ::

ቁ. 26–28 መጨረሻ ላይ ከፍ ያለ ዋጋ አለህና

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 3

## ሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ምዕ. 3:1–6 አንብብ

ሰርዴስ ማለት ማምለጥ ወይም መዳን ማለት ነው።

ቁ. 1 ሰባቱ መናፍስት

የእግዚብሔር መንፈስ ኢሳ. 11:2 ተመልከት።

ሰባቱ ከዋክብት፣ የአብያተ ክርስቲያናት መልእክት ነው። ጌታ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰባቱን ቤተ ክርስቲያናት በእጁ ይዟል። ምዕራፍ 1:20 በቤተ ክርስቲያናትና በመልእክቱ ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለው ነው።

ቁ. 2 የሰርዴስ አማኞች ሕይወት የሌላ አፋዊ ክርስትና ብቻ ቀርቶ ነበር። ለምሳሌ የክርስትና ወግ ያላቸው፣ የአምልኮ ሥነ ሥርዓት ያላቸው ግን ሙታን ነበሩ፤ ቁጥር 2 አንብብ። ሞቷል፣ ስም ብቻ ቀርቷል።

<u>የጌታ ምክር</u>፣ የቀረው እንዳይሞት በርታ፣ እሳቱ ሊጠፋ ነው በርታ፣ ዘይት ጨምር በርታ ነው የሚለው።

ቁ. 3 ንስሐ ግባ

በርታ ተመለስ፣ ንቃ እኔ እንደ ሌባ ቶሎ እመጣለሁ እያለ ወደ ራሱ ይጠራል፤ ራእይ 3:3ን አንብብ።

ቁ. 4 ጌታ ሁሉን አዋቂ ስለሆነ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ያለውን አንድ ሌላ ነገር አውቋል። ይኸውም በሰርዴስ ጥቂት ክርስቲያኖች ልብሳቸው ያላደፈ፣ ያልረከሱ ነበሩ። ገና ነጭ ልብስ እንደለበሱ ከጌታ ጋር ይሄዱ ነበር ማለት አንዳንዶች ጌታን ክደዋል። እነርሱ ግን አልካዱም ነበር። አንዳንዶች ኃጢአት ሲሠሩ እነርሱ ግን አልሠሩም ነበር። አንዳንዶቹ መንፈሳዊ የእምነት ልብሳቸው አድፏል። የጥቂት አማኞች ልብስ ግን ገና ነጭ ነበር። አንዳንዶቹ ልብሳቸውን ጥለው ነበር። ያ ነጭ ልብስ ምንድን ነው? መልሱ ከክርስቶስ ያገኘነው የጽድቅ ሥራ ነበር። እነዚህ ክርስቲያኖች በራሳቸው ምንም ጊዜ አልተመኩም። በክርስቶስ ጽድቅ ብቻ ይመኩ ነበር። በክርስቶስ ጽድቅ ተስፋ አደረጉ፤ ስለዚህ ከእርሱ ጋር ሄዱ። ስለዚህ ለእነርሱ የተደበቀ ተስፋና ሙሉ ዋስትና ይሰጣቸዋል።

ቁ. 5 እና 6 ተመልከት

1. ነጭ ልብስ ትጐናጸፋላችሁ ይላል
2. ስሙን ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስሰውም ይላል
3. በአባቴና በመላዕክት ፊት ስለ ስሙ እመሰክርለታለሁ። ጆሮ ያለው ይስማ ይላል።

ቁ.7–13 ስለ ፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን

ቁ. 7 ፊላደልፍያ ማለት የወንድማማች ፍቅር ማለት ነው። የምስጋና ከተማ። ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ጌታ ራሱን ቅዱስና እውነተኛ አድርጐ ያቀርባል። ቅዱስ ማለት የተለየ፣ እርሱን የሚመስል የሌለ፤ ማንም በቀልድ ወይም በቀላሉ ሊደርስበት የማይችል ማለት ነው፣ 1ኛ ጢሞ 6፡16።

እውነተኛ ማለት ጌታ ራሱ እውነት ነው። ቃሉም እውነት ነው። ያለው ቃል ይፈጸማል። ውሸት ወይም ማታለል የለበትም፣ ዘኁ. 23፡29፤ 1 ዮሐ. 5፡20 ተመልከት። የዳዊት መክፈቻ ያለው። ቁልፍ ደግሞ ሥልጣንን ያሳያል፣ ኢሳ. 22፡22፤ 1፡18፤ 3፡7 አንድ ዓይነት ነው፤ ኢየሱስ ባለሥልጣን ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የበላይ ጠባቂ ነው።

ቁ.8 በፊላደልፍያ ያለው ቤተ ክርስቲያን ከጌታ የምስጋና ቃል ይቀበላል። ከሰባቱ ቤተ ክርስቲያን የምስጋና ቃል የተቀበለ ይህ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው። ኢየሱስ ለዚህ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ይላል። ስለ ታማኝነትህ፣ ስለ መልካም ሥራህ፣ በጌታ ብቻ ስለምትተማመን የሕይወትህ ኑሮ በዚህ ዓለም ጌታን ስለመምሰልህ እኔም ዋጋህን እሰጥሃለሁ። ሥራህን ስለማውቅ፣ ስሜን አልካድህም፣ ቃሌን ስለጠበቅህ እኔም የተከፈተ በር ሰጥቼሃለሁ። የወንጌል አገልግሎት በር ከፍቼልሃለሁ፣ ሥራ ይላል። የተከፈተ በር መስጠት ለወንጌል አገልግሎት እንዴት አስፈላጊ መሰላችሁ? የወንጌል ሥራ በር እንዲከፈት ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ ጊዜ ይጸልይና እንዲጸልዩ ያሳስብ ነበር፣ ኤፌ. 6፡19–20። የወንጌል አገልግሎት በር የተከፈተላት ቤተ ክርስቲያን እንዴት የታደለች ናት?

ቁ. 9 አይሁድ ሳይሆኑ የሚዋሹ እንጻሉ

አይሁድ ሳይሆኑ የሚዋሹ እንጻሉ እስታወቀ። የሰይጣን ማኅበርተኞች የሚሆኑ አሉ። በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ሳያምኑ የሚያታልሉ እንጻሉ የታወቀ ነው። ቤተ ክርስቲያን ሳታውቅ በሰይጣን ማኅበረተኞች

እንዳትሞላ መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው። ይህ ሁኔታ በእናንተ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ነው? የተሰጠው ተስፋ አትፍራ በእግሮችህ ሥር እንዲሰግዱ አደርጋለሁ ይላል፣ ሮሜ 16:20።

ቁ. 10 የትዕግሥቴን ቃል ስለጠበቅህ እኔም በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው የፈተና ሰዓት እጠብቅሃለሁ። ይህ የፈተና ሰዓት የተባለው ከምዕራፍ 4–19 ድረስ በራእይ ለዮሐንስ የተገለጠ የመከራ፣ የፍርድና የጭንቀት ጊዜ እንደሆነ ይናገራል። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ወደፊት ከሚመጣው ከሐሳዊ መሲህ ዘመን ወይም 7ቱ የመከራ ዘመን በፊት እንደምትነጠቅና ከጌታ ጋር እንደምትሆን ተብሎ ይታሰባል፤ 1 ተሰሎ 4:13–18፤ 1 ቆሮ. 15:47–51፤ ራእይ 3:11–13። ጌታ ድንገት ቤተ ክርስቲያንን ሊወስድ ይመጣል፤ 1 ተሰሎ. 5:1–11፤ ከዚህ ጊዜ አንስቶ ከጌታ ጋር እንሆናለን፤ የምድር መከራ ሁሉ ያልፋል።

ቁ. 11–13 ቶሎ ብዬ እመጣለሁ

ስለዚህ በርታ፣ ድል አድርግ ማለቱ ነው። በፈተናዎች ድል አድራጊ ብትሆን የተሰጠህ ተስፋዎችን እይ።

1. በአምላኬ መቅደስ አምድ አደርገዋለሁ። ከዚያ አይወጣም ይላል
2. የአምላኬ ስምና የከተማ ስም አዲሲቷ ከተማ ስም በእርሱ ላይ እጽፋለሁ።
3. አዲሱን ስሜን እጽፋለሁ

ጆሮ ያለው ይስማ ማለት አስተውል፣ ልብ አድርግ ማለት ነው።

ቁ. 14–22 ሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን

ሎዶቅያ ማለት የሰው አገዛዝ ወይም የሰው ፍርድ፣ የሰው ድምጽ ማለት ነው። ሎዶቅያ የተፈረደበት ቤተ ክርስቲያን ነው። በዚህ ቤተ ክርስቲያን ምንም መልካም ነገር የለበትም፤ ለብ ያለ ስለሆነ ተገስጸ ወይም ተከሰሰ።

ቁ. 14 ለዚህ ቤተ ክርስቲያንም መልዕክት ያስተላልፍ የነበረው ስሙ አሜን የሚባል ነበር። አሜን ማለት መጨረሻ ማለት ነው፤ አሜን እርሱ አልፋና ኦሜጋ ቀደም ብሎ ያለውን ስም አስብ፤ ራእይ 1:8 ተመልከት። ፊተኛውና የመጨረሻ የሚለውን 1:17ን ተመልከት። የሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን ጀማሪና ፈጻሚ ክርስቶስ መሆኑን

አልተረዳም ነበር:: አሜን ማለት የተጠቀለለ ሲሆን የነገር ሁሉ አጠቃላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የሕይወት ምንጭ ክርስቶስ ነው:: የሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን ግን በክርስቶስ ለብ ያለ ነበረ:: የሕይወት ምንጭ ባለበት የኃይል መጀመሪያ መሆኑን ማለት ነበር፣ ኢሳ. 22:2፤ 3፤ ዮሐ. 4:13፤14::

<u>የታመነ እውነተኛ ምስክር</u>፣ ለኢየሱስ ከተሰጡት ስሞች አንዱ የታመነ ምስክር የሚለው ነው፣ በምዕራፍ 1:5 ተመልከት::

<u>በእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ የነበረ</u>፣ መጀመሪያ ነበር፣ ዘፍጥ. 1:1፤ ዮሐ.1:1–2:: ክርስቶስ ፈጣሪ መሆኑን ይገልጻል:: ለፍጥረት ሁሉ በኵር፣ ዋና ራስ ሲሆን፣ ባለ ሥልጣንም ነው:: ዛሬ በዓለማችን ብዙ ልዩ ልዩ ነገሮችና መሣሪያዎች ይሠራሉ:: ክርስቶስ ግን የእነዚያ ነገሮች ጀማሪና ባለ ሥልጣን ነው:: ያለ እርሱ የሆነ የለም፣ ዮሐ. 1:2:: እርሱ ከሁሉ በላይ ነው፣ ዮሐ. 3:30–32፤ ቆላ.1:15–18::

ቁ. 15–16 አንብብ፣ ይህ ቤተ ክርስቲያን በራድም ትኩስም ሕይወት የለውም:: ለበራድ ተስፋ አለው:: አንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወደ ጽድቅ ይመራቸውና ትኩሶች ይሆናሉ:: በጌታ መንፈስ የሚቀጣጠል ሰው በዓለም ደስተኛ እርሱ ብቻ ነው:: ሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን በራድም ትኩስም ስላልነበረ ደስተኛ መሆን አልቻለም:: ጌታም ከአፌ ልተፋህ ነኝና ስለዚህ በራድ ወይም ትኩስ በሆንህ ይላል::

ቁ. 15–16 <u>ሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን በራድ ወይም ትኩስ አልነበረም</u>

በራድ ማለት ከመንፈሳዊ ሕይወት ውጭ ማለት ነው:: የሚያሞቅ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል በውስጡ የሌለ፣ የእምነት ምስክር የማይገልጽ፣ በክርስትና ኑሮው ውስጥ ሕይወትን የሚያረካ ሕይወት የሌለው ሲሆን፣ በራድ ስለ ክርስትና ሕይወት ግድ የለውም፣ ከቤተ ክርስቲያን ከወንጌል ድርጅቶች ገለልተኛ መሆን ይፈልጋል::

በራዶች እግዚአብሔር ለምን በምድር እንደሚያኖራቸው ዓላማ የላቸውም:: እንዲህ ላሉት መጽሐፍ ቅዱስ በሞትና በፍርድ ጥላ ውስጥ ይመላለሳሉ ይላል፣ ዮሐ. 3:36:: ወደ ጌታ እምነት እስኪመለሱ ድረስ በእግዚአብሔር ቁጣ በታች ይኖራሉ ይላል:: ስለዚህ ያላመኑት ስለ እግዚአብሔር ነገር በራዶች ናቸው:: አንድ ቀን ግን በጌታ ቢያምኑ ተስፋ አላቸው ትኩስ ይሆናሉ::

ቁ. 15 ትኩስ

ትኩስ ስለማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት ምሳሌ ልስጣችሁ

1. ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታን ሳያገኝ በራድ ነበር። ጌታን ካገኘ በኋላ ግን በጌታ እንደተለወጠ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 9 ላይ ተጽፏል። ከዚያ ቀጥሎ የጌታን ሥራ ሳያቋርጥ እንደ ሠራ አንቀሳቀሱ፤ የሐዋ. ሥራ ምዕራፍ 28 እንዲሁም 2ኛ ጢሞ. ምዕራፍ 4ን አንብብ።

2. ዘኬዎስን በሉቃስ 19 ተመልከት፤ በጌታ እንደ ተለወጠ ሥራ ጀመረ። መንፈሳዊ ሕይወት በውስጡ የተዘራ ሰው ያኔውኑ የጌታን ሥራ ይጀምራል፣ ይቀጥላል።

3. ሙሴ በምድያም አገር በጐች ሲጠብቅ እግዚአብሔር ተገለጸለት። ለጊዜው ተከራከረ እንጂ ተለወጠ፤ ዘጸአት 3ን አንብብ። ወደ ጌታ የተመለሱት ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወታቸው እስከ ሞት ድረስ ጠንካራ የማይነቃነቅ ይሆናል። በጌታ ሥራ አይደክሙም፣ ኃይላቸው ዕለት ዕለት ይታደሳል፣ ኢሳ. 40:29–31።

ቁ. 16 ለብታ

ይህ ቃል ዛሬ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተከታይ ቤተ ክርስቲያንን ይመለከታል። ለብተኝነት ራስን የማታለልና የመንፈሳዊነት ምልክት ነው። ለምሳሌ፦ ለብ ያለች ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ጥሪ ትቀበላለች፤ ክርስቲያን ማለት ጥሩ ነው ትላለች፤ ገንዘብ ታዋጣለች፣ ወንጌላዊም ትልክ ይሆናል፤ ጥምቀትም ታጠምቅ ይሆናል፤ አባልነትም ትቀበል ይሆናል። የጌታን ሥራዎችም ልታደንቅ ትችላለች። ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆን ገና ያልደረሰችበት አንድ ነገር ቀርቷል፤ ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወቷ ፍጹም ጌታ አልሆነም፣ ሉቃስ 6:46፤ ዮሐ. 13:13–15። ስለዚህ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያኖሰዎች፣ አማኞች ሳይሆኑ የተቀጠሩ ክርስቲያኖች ስለሆኑ ኢየሱስ በእነርሱ ላይ ጌታ ሆኖ እንዲገዛቸው አልፈለጉም። ለዚህ ነው ለብተኞች የሆኑት።

## የዘመናችን ለብተኝነት

1. በድርጅት መታመን (ዲኖምኔሽን)የለብተኝነት አንዱ ፍሬ ነው:: ክርስቲያን ከሆንን መታመንና መመካት የሚገባን በክርስቶስ መሆን አለበት እንጂ በድርጅት አይደለም፣1 ቆሮ. 1:29–31:: እንዲሁም ክርስቲያንን መክሰስ፣ መፍረድ፣ የእኔ ድርጅት አይደለህም በማለት መጥላት ወደ ለብተኝነት ይመራል:: ወደ ራስ ወዳድነት ያደርሳል፤ 2 ቆሮ. 10:17–18::

2. በመንፈስ አገልግሎትና ፐሮግራም ግድ የለሽ መሆን፣ ትኩስ አይደለንም፣ በክርስቶስ ፍቅር ሕይወታችን አይቀጣጠልም ይሆናል:: ለሌሎች የሚያዝን ልብ፣ የፍቅር ልብ፣ የምህረት ልብ፣ የቸርነት ልብ አለመኖር ለሌሎች አለማሰብ ለብተኝነትን ያመጣል፤ ዘፍ.4:9::

ቁ.17 ሌላው ለብተኝነትን የሚያመጣው በዚህ ቁጥር ተጽፎ ያለው፣

1. ባለጠጋ ነኝ ማለት
2. አንድም እንኳን አያስፈልገኝም ማለት

ቤተ ክርስቲያን በጌታ ጸጋ ሐብታምና የበለጸገች መሆን ያስፈልጋታል እንጂ በምድራዊ ቁሳቁስ ብቻ አይደለም፤ እርሱ ያልፋልና:: ቤተ ክርስቲያን ጌታ ወርሶኛልን? ብላ ራሷን መጠየቅ ያስፈልጋታል:: የእኔ ሐብት ጌታዬ ነው ማለት አለባት፣ 2 ቆሮ. 8:9:: ሕይወቴና ገንዘቤ ሁሉ የጌታ መሆኑን መርሳት የለብኝም:: ቤተ ክርስቲያን አንድም አያስፈልገኝም ማለቷ ልክ አይደለም:: ጌታ አያስፈልጋትም ማለት ነው? በራሷ ትመካለች ማለት ነዋ! ኤር. 9:23–24::

### ቤተ ክርስቲያን

1. የተሰቀለው ኢየሱስ ዕለት ዕለት ያስፈልጋታል፣ 1 ቆሮ.1:22–24::
2. ሕይወቷ የሆነው ኢየሱስ ያስፈልጋታል፣ ፊልጵ. 1:21::
3. ዓላማችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ያስፈልጋታል፣ኤፌ 2:13::
4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታይ ኢየሱስ ያስፈልጋታል፣ ዮሐ. 1:21
5. በክርስቶስ የሆኑት ወንድሞችና እህቶች ያስፈልጓታል:: ማንም አያስፈልገኝም ማለት አይገባትም፣1 ቆሮ. 12:14–28፤ በተለይ ቁጥር 21 ተመልከት::

ቁ. 17 ለቤተ ክርስቲያን የፊት ዕፍረት የሚሆንባት ነገር፣ ለኃጢአቷ የሞተውን፣ ከሞት የተነሳውን፣ ሕይወት የሚሰጥ አዳኟን ክርስቶስን ቸል ብላ በራስዋ በመታመን ስለምትመካና በራስዋ ስለምትደገፍ ነው::

የምትመካው

1. በሐብቷ
2. በንብረቷ
3. በሰዎችና በድርጅቷ ስለሆነ ለብተኛ ናት::

የአሁኑ ዘመን ሎዶቂያን የመሰለች ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ትላለች፣

1. ራሴን ላድን
2. አባል ልሁን
3. ሥራ ላግኝ፣ ለደሞዝ ብቻ ላገልግል፣ ራሴን ልቻል::

ራስ ወዳድ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ከዚህ ዓይነት ሕይወት ጌታ ይጠብቀን:: ስለዚህ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን 5 ነገሮች ደርሰባታል::

ቁ.17ን አንብብ

1. ጉስቋላ ነሽ
2. ምስኪን ነሽ
3. ድሃ ነሽ
4. እውር ነሽ
5. የተራቆትሽ ነሽ ተብሎላታል:: ከዚህ ሁሉ ጌታ ያድነን::

ቁ. 18 ከችግር መውጫ መንገዶች አሉኝና ከእኔ ግዛ ይላል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ::

1. ለጉስቁልና፣ ለምስኪንነትና ለድህነት መውጫ የነጠረ ወርቅ ከእኔ ግዛ ይላል
2. ለእውርነት መድኃኒት የዐይን ኩል ከእኔ ግዛ ይላል::
3. ለራቁትነት ነጭ ልብስ ከእኔ ግዛ ይላል:

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉ አለኝ ወደ እኔ ና ብሎ ጥሪ ያቀርባል፣ ኢሳ. 1፡18፤ ዮሐ. 7፡37፤ 4፡14፤ ሮሜ 13፡14፡፡ ዛሬም ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስን ጥሪ ሰምታ ወደ እርሱ ብትቀርብ ሁሉ ከእርሱ፣ ሁሉ ለእርሱ ነውና ለዘለዓለም ክብር ይሁን አሜን፣ ሮሜ 11፡36፡፡ ሁሉን ከጌታ እንግዛ፡፡ ኢሳ. 55፡1–2፤

ቁ. 19 ቤተ ክርስቲያን የጌታን ተግሳጽ ለመቀበል የተዘጋጀች መሆን አለባት፡፡ ክርስቲያን ሁሉ ለጌታ ግሳጼ ራሱን ማዘጋጀት አለበት፣ ዕብ. 12፡5–11፡፡

ቁጥር 20 የጌታን ድምጽ ስማ

እርሱን ወደ ውስጥህ አስገባ፣ መልካም ይሆንልሃል፡፡ ቃሉን አንብብና ስማ፣ ታዘዝም፣ ኢያሱ 1፡5–9፡፡

ቁጥር 21 የድል አድራጊዎች ተስፋ እንዳያመልጥህ በርታ፡፡

ቁጥር 22 የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ስማ

ዛሬም በቃሉ ይናገራል፤ መንፈሳዊ የልብ ጆሮህን ከፍተህ አስተውል ስማ፡፡

# የዮሐንስ ራእይ 4

## መግቢያ

ራእይ ከምዕራፍ 4 ጀምሮ የዮሐንስ ራእይን ትልቁን ሁለተኛ ክፍል ይጀምራል::

አንደኛው ክፍል፣ የቤተ ክርስቲያን ዘመን በዚህ ዓለም ላይ ይታይ ነበር:: ያውም ከሐዋርያት ዘመን አንስቶ እስከ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ወይም የክርስቲያን ወደ ጌታ (ወደ ሰማይ) መወሰድ ጊዜ ድረስ ያለውን ሁኔታ የሚገልጽ ሲሆን ምዕራፍ 1:19 ተመልከት::

እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ይላል:: ይህ አንደኛ ክፍል ነው::

ከምዕራፍ 4 ጀምሮ ግን ዮሐንስ ሲያይ ያኔ የነበረ አሁን የለም:: እርሱ ምንድን ነው? ቤተ ክርስቲያን ነው:: ቤተ ክርስቲያን አሁን በምድር የለም፤ አሁን በምዕራፍ 4 አይገኝም:: እስከ ምዕራፍ 19 የበጉ ሠርግና ሙሽራይቱ እስከሚል ድረስ አናገኝም:: ምን ሆነ? መልሱ በምዕራፍ 3 እና በምዕራፍ 4 መካከል አንድ ነገር የተፈጸመ ይመስላል:: አልተጻፈም እንጂ ከምዕራፍ 4 ጀምሮ እስከ መጨረሻው የቤተ ክርስቲያን ስም አልተጠቀሰም:: አልፎ በምዕራፍ 19 ቁጥር 7 ላይ በበጉ ሠርግ ግብዣ ላይ ሙሽሪት ስትገኝ እናያለን፣ በዚያ እለት የሚገኝ አማኝ እንዴት ዕድለኛ ነው! እርሱም በሰማይ ነው::

ስለዚህ በምዕራፍ 3 እና በምዕራፍ 4 መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ወደ ጌታ ተወስዳለች ማለት ነው:: ከዚህ ሃሳብ በስተቀር ቤተ ክርስቲያን በዮሐንስ ራእይ መቼ እንደ ተወሰደች እንዴት እንደሄደች አይነግረንም:: በሌላ ቦታዎች ግን በብዙ ተጽፎ እናገኛለን:: ምናልባት ዮሐንስን በምዕራፍ 4 ከሰማይ ድምጽ ወደዚህ ውጣ ባለው ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ወጥታ ይሆናል፣ 1 ተሰሎ. 4:13–18፤ 1ቆሮ. 15:51–57፤ ዮሐ. 14:3::

## የዙፋን ክፍል ምዕራፍ 4:1–11 አንብብ

በቁጥር 1 ዮሐንስ ከምድር ወደ ሰማይ መወሰዱን እናያለን:: ከዚያም በኋላ የሚለውን ልብ አድርግ:: ከምን በኋላ? በምድር ላይ ያያቸው ከነበሩ ከ7ቱ ቤተ ክርስቲያን በኋላ የተከፈተ በር (ደጅ) አየሁ

ይላል:: የተከፈተ በር የት ነበር? በሰማይ ነበር:: በዮሐንስ መጽሐፎች ብዙ በር ወይም ደጅ የሚለውን ቃል እናገኛለን:: ለምሳሌ:-

1. ዮሐ. 10:7–9 ያለው በር የሚያድን በር፣ ከአደጋ የሚጠብቅ በር ነው::
2. ራእይ 3:8 ያለው ስለወንጌል የመመስከር በር፣ ስለ ክርስቶስ የመናገር በር ነው::
3. ራእይ 3:20 የሰው ልብ ደጅ ሲሆን የምርጫ የዕድል ደጅ ነው
4. ራእይ 4:1 በሰማያት በሦስተኛው ሰማይ በእግዚአብሔር ዙፋን የሚገኝ በር ተከፈተ ይላል::
5. ራእይ 19:11 ሰማይ ተከፈተ ለፍርድ የሚወርድበት በር ነው::
6. ራእይ 21 የቅድስቲቱ ኢየሩሳሌም ደጆች (በር) ነው::

በዮሐንስ ራእይ ብቻ ሰማይ ሦስት ጊዜ ተከፍቶ እናያለን::

1. በዮሐንስ ራእይ 4:1 ከምድር መከራ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ስትሄድ
2. በዮሐንስ ራእይ 11:19 በሚያስፈራ በእግዚአብሔር ፍርድ ጊዜ የእግዚአብሔር ኪዳን ለልጆቹ የማዳኑን ደጅ ወይም በር ይከፍታል::
3. በዮሐንስ ራእይ 19:11 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰይጣንና ባላመኑት ላይ ሊፈርድ ሲመጣ ያሉት ደጆች ናቸው::

ታዲያ እኛስ እንዴት እናመልጣለን? ዕብ. 2:3፤ 2 ቆሮ. 6:2:: ማምለጫና መዳኛ ቀን ዛሬ ነው፤ ማቴ. 7:13–14፤ ዮሐ. 10:9::

ከዙፋኑ ፊተኛ ድምጽ

በቁጥር 1 ዮሐንስ ወደ ሰማይ ሲመለከት ሰማይ ተከፍቶ በራእዩ ሲያይ ሳለ ሌላ ነገር ሆነ:: ያውም እንደ መለከት ያለው ድምጽ ሲናገር ሰማ:: የሰማው ድምጽ እንደዚህ የሚል ነበር:– ወደዚህ ውጣ፤ ከዚህ በኋላ ሊሆን ዘንድ ያለውን ነገር አሳይሃለሁ የሚል ነበር::

ይህ ድምጽ ለዮሐንስ አዲስ ድምጽ አልነበረም:: የተለመደ ድምጽ ነበር፤ ዮሐንስ የሚያውቀው ድምጽ ነበር::

ቁጥር 1 ፊተኛው ድምጽ ይላል:-

1. ዮሐንስንና ጓደኞቹን የጠራቸው ድምጽ ዓይነት፣ማቴ.4:19-25
2. ሐዋርያት እንዲሆኑ ለይቶ የመረጣቸው ድምጽ፣ ሉቃስ 6:12
3. ያስተምራቸው የነበረው ድምጽ፣ ማቴ. 5:1 እስከ ምዕራፍ 7
4. በሽተኞችን የፈወሳቸው ድምጽ፣ ማቴ. 12:9-13
5. አጋንንትን ያስወጣ ድምጽ፣ ማር. 1:21-28
6. ለምጻሞችን ያነጻ ድምጽ ዓይነት ነበር፣ ማር. 1:40
7. ሙታንን ያስነሳ ድምጽ፣ ዮሐ. 11:43
8. በሞቱና በትንሣኤው የወደደን የምሕረት ድምጽ ያለ፣ ሉቃስ 23:34፤46፤ ዮሐ. 19:28-30::
9. የባለ ሙሉ ሥልጣን ድምጽ፣ ማቴ. 28:18::

የኢየሱስ ድምጽ ነበር::

ወዳጆቼ ሆይ የኢየሱስን ድምጽ ለይታችሁ ታውቃላችሁን? ዮሐ. 10:16:: የኢየሱስ ድምጽ ሰላምን፣ እረፍትን፣ ሕይወትን ይሰጣል:: እንደ አዳም ጊዜ የፍርሃት ድምጽ አይደለም፣ ዘፍ. 3:9-10:: እንደ እስራኤላውያን የሞት ድምጽ አይደለም፣ዘጸ.19:16-18፤ 20:18-19:: የኢየሱስ ድምጽ ለአንተ እንዴት ይሰማሃል? ምንስ ይመስላል?

ዙፋን በሰማይ

ቁ. 2-3 ሐዋርያው ዮሐንስ ወደ ሰማይ የተጠራበት ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን ዘመን በኋላ ሊሆን የሚገባውን ነገር ለማሳየት ነበር:: ስለዚህ ዮሐንስ ሲገልጽልን ልክ እንደተጠራሁ በመንፈስ ሆንኩኝ ይላል:: ወዳጆቼ ሆይ! እግዚአብሔርን ለመገናኘት በመንፈስ መሆን አለብን፤ በመንፈስ ካልሆንን ማየት አንችልም:: በመንፈስ መሆን ማለት ራስን በፍጹም ለእግዚአብሔር መንፈስ ቀድሶ ማስገዛትና በቁጥጥሩ ሥር መሆን ነው::

1. የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት በመንፈስ መሆን አለብን::

2. ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ለመድረስ በመንፈስ መሆን አለብን::

3. የእግዚአብሔርን ፊት ለማየት በመንፈስ መሆን አለብን፣ ዮሐ. 3:3- 5፤ 1 ቆሮ. 15:50:: እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ዮሐንስ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በመንፈስ መሆን ነበረበት::

ዮሐንስ በቅጽበት ዓይን ነበረ በመንፈስ የሆነው፣ 1ቆሮ. 15:52

1. እግዚአብሔርን ለዘለዓለም ለመገናኘት በቅጽበት ዓይን ውስጣችን መለወጥ ያስፈልገዋል።
2. እግዚአብሔርን ለዘለዓለም ለመገናኘት በቅጽበት ከሥጋችን መውጣት አለብን። ዮሐንስ የእግዚአብሔርን ዙፋን በሰማይ ተዘርግቶ ባየ ጊዜ በመንፈስ ነበር። አካሉ ማለትም ሥጋዊ አካሉ በምድር ፍጥሞ በምትባል ደሴት በእሥር ቤት ነበር፤ ራእይ 1:9። ሕይወቱ ግን በመንፈስ በሰማይ ነበር።

ቁጥር 2 ዮሐንስ ሲመለከት እነሆ ዙፋን በሰማይ ቆሟል ይላል

ዮሐንስ የቆመና የጸና ዙፋን፣ የማይናወጥ ዙፋን፣ የማይለወጥ ዘለዓለማዊ ዙፋን ቆሞ አየ፣ መዝ.(103):19። ደግሞ ዮሐንስ በዙፋኑ ላይ ተቀማጭ ተቀምጦ አየሁ ይላል። ብዙ ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ዙፋን ለመናገር እንፈራለን። ከዚያም በላይ በደንብ ለማወቅ አንፈልግም፤ እንዲያውም እንጠራለራለን። የዮሐንስ ራእይ የዙፋን መጽሐፍ ነው ቢባል አያስፈራም። ምክንያቱም በዮሐንስ ራእይ ብቻ 45 ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል። ለምሳሌ ምዕራፍ 4 እና 5 ተመልከት። በእነዚህ ምዕራፎች እንኳን 17 ጊዜ ስለ ዙፋን ያወራል። ዮሐንስ ወደ ሰማይ ሲወሰድ ወደ ዙፋን ክፍል ተወሰደ። ወደ እዚያ ገብቶ አየ። ስለዚህም ዮሐንስ ያየውን ነገር ለዛሬ ቤተ ክርስቲያን በራእይ መጽሐፍ ያረጋግጥልናል። ደግሞ ስለ ዙፋኑ በአዲስ ኪዳን ወደ 15 ጊዜ ተጠቅሷል። በብሉይ ኪዳን ስንት ጊዜ እንደተጠቀሰ ባላውቅም እነዚህን ጥቅሶች ተመልከት፤ መዝ. (103):19፤ ኢሳ. 6:1፤ዳን. 7:9፤10፤ ሕዝ. 10:1። እንዲሁም በብዙ ቦታዎች እናገኛለን። የእግዚአብሔር ዙፋን ለሚታዩ ነገሮችና ለማይታዩ ነገሮች፣ ሕይወት ላላቸው ነገሮችና ለሌላቸው ለሁሉም ፍጥረት መሃከለኛ ቦታ ሆኖ ይገኛል። የሁሉም መሰብሰቢያ እና መሳቢያ የሆነ የኃይል ሥፍራ ነው፣ ዮሐ. 1:3፤ ቆላ. 1:15–16፤ ዕብ. 1:3፤ ሮሜ 11:36። ዮሐንስ ያየው ዙፋን የፍጥረታት ሁሉ ገዢ ዘለዓለማዊ ኃይል የሆነ እግዚአብሔርን ያመለክታል፤ መዝ.47:8–9። እግዚአብሔር ለዘለዓለም ጸንቶ በቆመ ዙፋን ላይ በመሆን የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ራሱ እግዚአብሔር በአብ ቀኝ መቀመጡን በማሰብ ክርስቲያን በእምነትና በተስፋ እንዲጸና ያደርጋል። ራእይ 4:2 የሚገልጸው እግዚአብሔር ዙፋኑን ከፍ ባለው ሥፍራ በኢሳ. 6:1 መሠረት

የርኩሳት ኃይል በማይደርሱበት ቦታ ያደረገ ስለሆነ እግዚአብሔር ታላቅና ኃያል ከሁሉም በላይ ነው፣ 1 ጢሞ. 6:16::

አዝማች:- ታላቅ ነው ጌታ እጅግ ታላቅ ነው
ክብር ስጡ ክብር ክብር እንስጠው፣
ኢሳ. 66:1፤ማቴ.5:34

ቁ. 2 በዙፋኑ ላይ ተቀማጭ ነበር ይላል

ዮሐንስ ዙፋኑን ሲመለከት በዙፋኑ ላይ የተቀመጠ መኖሩን ይገልጽልናል:: ዮሐንስ በዙፋኑ ላይ ስለተቀመጠው ፎርምና ቅርጽ ምን እንደሚመስል መግለጽ አልቻለም:: ለምን? እርሱ እግዚአብሔር ነውና:: በዘዳግም 4:15-19፤ 23:24፤ ዘጸ. 33:20፤ 1 ጢሞ. 6:16 እንዳለው ሁሉ ለእኛ የተገለጸና የተሰጠን በመልክ ወይም በቅርጽ (ፎርም) አይተን ሳይሆን በማመን እንድንድንና እንድንቀበል ነው፣ 2 ቆሮ. 4:17፤ 18፤ ዮሐ. 4:24-25፤ 20:39:: ዮሐንስ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው እግዚአብሔር መንፈስ ስለነበር መንፈሳዊ አካል እንጂ እኛ የምናውቀውን ዓይነት ሥጋዊ አካል ስላልተመለከተ መግለጽ አስቸግሮታል:: እግዚአብሔርን ያዩት ሁሉ ስለ እግዚአብሔር መልክና ቅርጽ ለመግለጽ እንደተቸገሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽልናል::

ለምሳሌ ቀጥሉ የተጠቀሱትን ቦታዎች ተመልከት:-

1. ሙሴ በቁጥቋጦ እሳት፣ ዘጸ. 3
2. ሙሴ በሲና ተራራ ዘጸ 19
3. ኢሳይያስ በመቅደስ፣ ኢሳ.6
4. ሕዝቅኤል በኪሩቤል፣ ሕዝ. 1 እና 10
5. ዳንኤል ዙፋኖችን፣ ዳን. 7:9
6. ዮሐንስ በራእይ ላይ መልኩን መግለጽ ስላልቻለ እንዲህ የሚል ቃል ተጠቅሟል::

እንደ እሳት፣ እንደ መብረቅ፣ እንደ ደመና፣ እንደ ቀስተ ደመና፣ እንደ አውሎ ነፋስ እያለ ሊገልጽልን ይሞክራል:: ይህ ቃል ወይም ይህ ገለጻ አይበቃምን? ለእኛ በቂ ነው፤ እንዲያውም በዝቷል::

ቁጥር 3 ዮሐንስ በዙፋን ላይ ተቀምጦ የነበረውን ሊገልጽ ስላልቻለ ለእኛ እንደሚገባን አድርጐ እኛ የምናውቀውን ነገር ያመጣና እንደ ብዙ ቀለም እንዳለ ነገር አድርጐ እንቁ፣ መረግድ፣ ቀስተ ደመና፣

እያለ በሰማይ ያለውን መልክ በምድር ባለው አስመስሎ ሲገልጽልን ይሞክራል። አዎን ታላቅ ዙፋን በሰማይ ቆሟል። በዙፋኑም ተቀማጭ አለው። እንደ እውነቱ ለእኛ እንዲገባን በዙፋን ላይ ያለው ማነው?

በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ የነበረው፣ ያለውና የሚኖረው ሕያው እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ እንደነበረ ዮሐንስ ይገልጽልናል።

1. አብ በዙፋን ላይ እንዳለ፣ ራእይ 4:9፤ 5:1–7 ተመልከት።

2. ወልድ በዙፋን ላይ እንዳለ፣ ራእይ 5:6፤ 6:16 ተመልከት።

3. መንፈስ ቅዱስ በዙፋን ላይ እንዳለ ራእይ 4:5፤ 5:6 ተመልከት።

እንግዲህ እግዚአብሔርን እንደ አንድ አካል ብቻ አድርገው የሚያምኑ የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስን ሦስት አካል እንደሆኑ እንደ ቃሉ መሠረት አናምንም፤ እኛ እንደፈለግን ብቻ እየተረጎምን እናምናለን፣ እንሰብካለን የሚሉ የኃይማኖት ድርጅቶች ምን ይቀጣቸው?

ቁጥር 3 በዙፋኑ ዙሪያ መረግድ የሚመስል ቀስተ ደመና ነበር

<u>ቀስተ ደመና</u>፣ የእግዚአብሔርን እውነተኛ የማይለወጥ ታማኝነትን ያሳያል ወይም ያመለክታል። በኖህ ዘመን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ቃል ኪዳን (መሃላ) እንዳደረገ ዘፍጥረት 9:11–17 አንብብ። በምድራችን የሚታይ ቀስተ ደመና ግማሽ ክብ ነው። በዮሐንስ ራእይ 4:3 የሚገኝ ቀስተ ደመና ግን ሙሉ ክብ ነው። ያውም በዙፋኑ ዙሪያ ያለው። ይህ የሚያሳየን የእግዚአብሔርን ሙሉ ታማኝነትና የእውነትን ፍጻሜ መጨረሻ ሲያሳይ ሙሉ ነው እንጂ ጐዶሎ አይደለም። በተለይ እግዚአብሔር ለምድራችን ታማኝ መሆኑን ያሳያል፤ ዘፍጥ. 9:8–11። ለምድር የሚለውን ተመልከት፤ የምድር ቀስተ ደመና የሚያመለክተው ለምድር ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ሲያሳስብ፣

- የእግዚአብሔር ምሕረት በምድር ላይ
- የእግዚአብሔር ይቅርታ በምድር ላይ
- የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በምድር ላይ ስለሚኖር እንኖራለን።

የምድርን ቀስተ ደመና ሕይወት ያለው ነፍስ ሁሉ ያያል አይቷልም። የሰማይን ቀስተ ደመና ግን በክርስቶስ ደም የተዋጁት ብቻ ያያሉ።

በዙፋኑ ዙሪያ ያለው ሰማያዊ ቀስተ ደመና የሚያሳስበው በዘመኑ ያሉትን ለዘለዓለም ሕይወት በጸጋና በእምነት የሚጸኑትን ነው:: ምድራዊ ቀስተ ደመና ሁልጊዜም ምድርን ሲያሳስበን ሰማያዊው ግን ዘለዓለማዊ በረከትን ያመለክታል፣ ኤፌ.1:13–14፤ ፊልጵ.1:6፤ ዮሐ. 6:26፤29::

ቁ. 4 በዙፋኑ ዙሪያ ቀስተ ደመና ብቻ ሳይሆን ሌላ ነገርንም እግዚአብሔር አሳይቷል:: ይኸውም 24 ዙፋኖችና በዙፋኖች ላይ የተቀመጡ 24 ሽማግሌዎች ሲሆኑ፣ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸው ላይ የወርቅ አክሊል ደፍተው በዋናው ዙፋን ዙሪያ ነበሩ ይላል:: ዋናው ዙፋን የአምላካችን የእግዚአብሔር ዙፋን ሲሆን፣ ሌላ 24 ዙፋኖች እንደአሉ በቃሉ ትኩረት እንስጥ::

## 4 ነገሮችን ተመልከቱ

1. በቁጥር 24 ናቸው
2. በዙፋኖቹ ላይ ተቀምጠዋል
3. ነጭ ልብስ ለብሰዋል
4. በራሳቸው ላይ የወርቅ አክሊል ደፍተዋል

እነዚህ 24 ሽማግሌዎች እነማን ናቸው? ከየት መጡ?

የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ልዩ ልዩ ሐሳቦችን ይሰጣሉ

1. አንዳንዶች እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ መላእክቶች ናቸው የሚሉ አሉ፣
2. አንዳንዶቹም 12ቱ እስራኤልን 12 ቤተ ክርስቲያንን የሚወክሉ አማኞች ናቸው ይላሉ::
3. ሌሎቹም የለም 24ቱም የቤተ ክርስቲያን አማኞች ናቸው ይላል::

   ነገሩን ትኩረት ሰጥታችሁ ብትመረምሩት:

1ኛ መላእክት አይደሉም፤ ምክንያቱም:

ሀ) በዮሐንስ ራእይ መላእክት ነጭ ልብስ ለብሰዋል ተብሎ በብዙ ቦታ አልተጻፈም::

ለ) በመጽሐፍ ቅዱስ መላእክት በራሳቸው አክሊል ደፍተዋል የሚል አናገኝም::

ሐ) መላእክት በዙፋን መቀመጣቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ አናገኝም

2ኛ እሥራኤላውያን መሆናቸውንም ያጠራጥራል፤ ምክንያቱም

ሀ) እንደ 1ኛ ተሰሎንቄ 4:12–18 የመነጠቅ ጊዜ በድንገት ስለሆነ እሥራኤላውያን መቼ ተነጠቁና ነው?

ለ) በራእይ መጽሐፍ ወደፊት ስናይ ብዙ ፕሮግራም በእሥራኤል ላይ እንደሚሆን ያሳየናል፤ ጥናቱን ስንቀጥል፣

ታዲያ እነዚህ 24 ሽማግሌዎች እነማን ናቸው? መልሱ እንደሚቀጥለው ነው:

1. በዮሐንስ ራእይ 3:5 መሠረት ልብሳቸው ነጭ የሆነ ቤተ ክርስቲያን ነው:: እንዲሁም ምዕራፍ 19:8፤14 መሠረት ሚስቱ ሙሽራይቱ ናት:: ልብሳቸውን በበጉ ደም አጥበዋል ሲል ልብሱ ጽድቅን ያሳያል፤ ገላ.3:27፤ ቆላ. 3:4፤ ሮሜ 3:24–26፤ 8:27–30፤ ሮሜ 13:14፤ 2 ቆሮ. 5:21::
2. በዙፋን ላይ መቀመጥ ለመላእክት ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን መሆኑን በራእይ 3:21 ተመልከት::
3. የወርቅ አክሊል መድፋትም ለመላእክት ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን መሆኑን በግልጥ ተጽፏል፤ ራእይ 2:11፤ 3:11፤ 2 ጢሞ. 4:8፡ ያዕ. 1:12፤ 1 ጴጥ. 5:4 ተመልከት::

ቁ.4 የእግዚአብሔር ዙፋን በመሃል ሆኖ 24 ዙፋኖችና ሽማግሌዎችም የተቀመጡባቸው ዙሪያ ከበው መላእክትና ሠራዊትም በዙሪያው ሆነው የእግዚአብሔርን ዙፋን ስንመለከት እንዴት ያስፈራል! እንዴት ያለ ኃያል፣ ግርማ፣ ክብር፣ ሥልጣን ያለው አምላክ መሆኑን አድናቆትን አትርፏል::

ቁጥር 8 እና ቁጥር 11ድን አንብብ:: ለምን እንዲህ ባለ ሁኔታ ለዮሐንስ ተገለጠ? መልሱ በቁጥር 5 ይገኛል አንብበው::

መብረቅ ድምጽና ነጐድጓድም እናያለን፤ የምን ምሳሌዎች ናቸው? እንደ መዝሙር 18:13–15፤ 1ኛ ሳሙ፡ 7:10 የፍርድ ምሳሌ ሲሆኑ ከዮሐንስ ራእይ 4:5 ጀምሮ የሚታይ አስደናቂና አስፈሪው ዙፋን ከነሠራዊታቸው ፍርድን ለማሳየት የተገለጸ መሆኑን እናያለን::

የእግዚአብሔር ፍርድ በጠላት ላይ፣ የእግዚአብሔር ፍርድ በዓመጽ ላይ ሆኖ እግዚአብሔር በፍጹም ፍትህ፣ በፍጹም ጽድቅ፣ በፍጹም ቅድስና የሚፈርድበት ጊዜ እንደደረሰ ያሳያል::

በራእይ ምዕራፍ 4 እና 5 የእግዚአብሔር ቅድስና የተሞላ ዙፋንን ክብሩ መኖርን ሲገልጽ ከምዕራፍ 6 ጀምሮ የፍርድ ጉርፍ በፍጥረት ላይ ሲፈስ እናያለን።

ቁ. 5 መብረቅ ድምጽ ነጐድጓድና ሰባቱ የእሳት መብራቶችን ስንመለከት የፍርዱን ከባድነት ያሳስበናል። ለምን የእግዚአብሔር ቁጣ በምድር ላይ ይጐርፋል? መልሱ ስለ ኃጢአት ነው። እግዚብሔር የኃጢአትን አጸያፊነት ክፋት በፍርድ ያሳያል። እስቲ ለትንሽ ጊዜ ምድራችንን እናስብ። በየቤቱ ያለውን ግፍና በደል ባል በሚስት ላይ፣ ሚስትም በባል ላይ፣ ሠራተኛ በአሠሪው ላይ፣ በየመንደሩ ያለውን ግፍ እናስብ፤ ጐረቤት በጐረቤት ላይ ያለውን ሐሜት፣ ጥላቻ፣ ስድብና ጩኸት ብሎም መደባደብና ክስ፣ በየከተማው በፍርድ ቤት ያለው ወንጀል፣ በየገበያው ያለው ሌብነት ቅሚያ በአገር ደረጃና በዓለም ያለውን ግፍ፣ ለቅሶ መንከራተትና ክፋት ስናስብ እንዴት መጥፎ ነው። ለምን ሆነ? ምክንያቱ ኃጢአት ነው። በዚያው ልክ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ትዕግሥት ይቅርታንም እናስብ። እንዴት ድንቅ ነው አምላካችን። ለምን? መልሱ 2ኛ ጴጥ. 3፡9 ሰው በጌታ አምኖ እንዲድን ይታገሣል። ተመለሱ ይላል እንጂ ቢቸኩል ፍርዱን ማን ሊቋቋም ይችላል? ማን ይሸከማል? ዕብ. 10፡29–39።

ቁ. 5 እና 6 ሰባቱ የእሳት መብራቶች ወይም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት

ሐዋርያው ዮሐንስ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ሲመለከት ሰባቱ የእሳት መብራቶች ሰባት መብራቶች ሲበሩ አየ። እነዚህ ሰባቱ የእሳት መብራቶች ሰባት የእግዚአብሔር መናፍስት ነበሩ። አቤት የእግዚአብሔር አምላካችን ኃይሉ ሥልጣኑ ታላቅነቱ፣ ዕብ. 1፡7። መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹን የእሳት ነበልባል ሊያደርግ ይችላል።

ይህ ነገር ዱሮ በአዳም ጊዜ የሆነውን ታሪክ በዘፍጥረት 3፡24 ላይ ያለውን ያሳስበናል። ኪሩቤልን የምትገለባበጥ የእሳት ነበልባል ሰይፍን እናነባለን። ሰው ወደ ገነት ተመልሶ እንዳይገባ የመግቢያው በር እንዲጠበቅ እግዚአብሔር አምላክ ያስቀመጠውን፤ በዙፋኑ ፊት ወደ ዙፋኑ መግቢያ ሰባት የሚበሩ መብራቶችን ስናስብ መብራቶች ዘይት እንደሚያስፈልጋቸው ያሳስበናል፣ ማቴ. 25፡1–12። መብራትና ዘይት የያዙትን በማሰሮዋቸው እናስታውሳቸው።

ይህም መብራት ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው፣ ኢሳ. 11:2:: ምን ይሠራሉ? ብርሃን ይሰጣሉ:: በእግዚአብሔር ዘንድ ጨለማ ከቶ አይኖርም፤ እግዚአብሔር ብርሃን ነው::

የሰው ልጅ ሆይ እንዴት ወደ አምላክ ትቀርብ ይሆን?

በድፍረት አይሆንም፣ ሾልኮ መግባት የለም፤ መግቢያው አንድ በር ብቻ ነው፣ ዮሐ. 10:9፤ 14:6፤ ዕብ. 4:16፤ 10:19–20:: በሩ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: በእርሱ የሚገባ ይድናል:: በክርስቶስ ኢየሱስ ደም መሥዋእትነት በማመን ብቻ ወደ አብ መቅረብ ይቻላል::

ቁ. 6 በዙፋኑ ፊት ያለው የብርጭቆ ባህር:: ሰማይ በውኃዎች መካከል መሠራቱን፣ ዘፍጥ. 1:7፤ መዝ. (148):4 እግዚአብሔር መኖሪያውን ከውኃ በላይ መሥራቱን፣ መዝ. (104):3 የብርጭቆ ባሕር ምናልባት በረዶ ሊሆንም ይችላል ማለት ነው:: ለእርሱ የሚሳነው የለምና:: ፍጥረት ሁሉ ለእርሱ ክብር ተፈጥረዋልና ሁሉም እንደ ፈቃዱ ሆኗል፤ ቁጥር 11ን ተመልከት::

ቁ. 6–8 ስለ አራቱ እንስሶች

ዮሐንስ በራእይ በዙፋን ዙሪያ ሲመለከት አራት እንስሶችን አየሁ ይላል:: እነዚህ አራት እንስሶች ልዩ ፍጥረቶች ናቸው:: ስለ ስማቸውና ስለ ማንነታቸው አልተጻፈም:: ሌላ የተገለጠ ነገር የለም:: ሐዋርያው ዮሐንስ እነዚህን ልዩ ዓይነት ፍጥረት ወይም አራት እንስሶች የሚለውን በተመለከተ ጊዜ ምን እንደሚመስሉ ብቻ ይገልጻል::

በቁጥር 6 ላይ ዓይኖች የሞሉባቸው እንስሶች ይላል እንጂ ምን እንደሆኑ አይናገርም::

በቁጥር 7 ላይ

1. እንደ አንበሳ 2. እንደ ጥጃ
3.እንደ ሰው ፊት 4. እንደ ንስር(አሞራ)ይመስላሉ ይላል::

በተለይ እንደ የሚለውንና ይመስላል የሚለውን ቃል ልብ ብላችሁ ብትመለከቱ ሐሳቡ ይገባል:: ደግሞ ለአራቱም እንስሶች ስድስት ስድስት ክንፍና በዙሪያቸውና በውስጣቸው ዓይኖች ሞልተውባቸዋል ይላል:: ማለት ሁሉን ለማየት አይሳናቸውም ማለት ሲሆን ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም፤ ቁጥር 8 ተመልከት:: እነማን ናቸው? ወይም ምንድን ናቸው? መልሱ ምናልባት ሕዝቅኤል

በእግዚአብሔር ራእይ አይቶ የነበረ ልክ እንደ እናርሱ የሆነ ፍጥረት ልዩ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሲሆኑ ደግሞ ሕዝቅኤል 1:1–28፤ 10:20–21 ስማቸው ኪሩቤል ይባላል:: ዮሐንስ ያያቸው እንስሳት አንዱ አንበሳ ይመስላል:: አንበሳ የአውሬዎች ንጉሥ ነው:: ኃይልንና ግርማን ያመለክታል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በአንበሳ ተመስሏል:: ንጉሥ ነውና፣ ማቴ. 2:2፤ ራእይ 5:5::

ሁለተኛው እንስሳ ጥጃን ይመስላል:: ጥጃ ወይም በሬ ለመሥዋዕትነት የሚጠቅም እንስሳ እንደነበረ በብሉይ ኪዳን ሲገልጽ ወንጌላዊ ማርቆስም ኢየሱስን የሚሰዋ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው ብሎ ያቀርበዋል፣ ማር. 1:1፤ 10:45::

ሦስተኛው እንስሳ እንደ ሰው ፊት፣ ይህ ሦስተኛ እንስሳ ክርስቶስ የሰው ልጅ የተባለውን ሲያሳስብ ሉቃስ ኢየሱስን ፍጹም የሰው ልጅ ብሎ የጻፈውን ያመለክታል፣ ሉቃስ 19:10፤ 9:62፤ 9:51:: እንዲሁም በፊልጵስዩስ 2 ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ሲሆን የእግዚአብሔርን ክብር ትቶ ሰው ሆኖ መከራ መቀበሉን መሞቱን ያሳስበናል:: እርሱ ለኃጢአታችን ሞተ፤ 1 ጴጥ. 2:24–25::

አራተኛው እንስሳ እንደ ንሥር ነበር:: ንሥር ከሚበሩ ወፎችና አሞራዎች ታላቅና ኃይለኛ ንጉሥ መሆኑን ሲገልጽ ነው:: ክርስቶስም ታላቅ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር መሆኑን እናያለን:: እርሱ ንጉሥ ነውና::

እነዚህ እንስሶች የተባሉት ፍጥረቶች ቀንና ሌሊት አያርፉም:: የእግዚአብሔርን ቅድስና ሲገልጹ፣ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ይላሉ:: እኛም ዛሬ እግዚአብሔር ብቻ ነው ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው ጌታ፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው ኃያል፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው ታላቅ፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው እውነተኛ፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው ዘላለማዊ እንላለን:: ስሙ ይክበር! በሁሉ ዘመናት ያለው የነበረውና የሚመጣውም ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክን እናመልካለን፣ ኢሳ.6:1–3፤ ፊልጵ. 2:9–11::

ቁ. 9 ክብር ለሚገባው እግዚአብሔር ክብርን ስጡት፤ ምስጋናም ስጡት፣ መዝ. (29):1–2::

ቁ. 10 ስግደት ለሚገባው ለእግዚአብሔር ስገዱለት አምልኩትም::

ቁ. 11 የሁሉ ፈጣሪ ሁሉን ፈጥሯልና አወድሱት ዘምሩለትም፣ ኤፌ. 1:11–12፤ ቆላ. 1:6፤ መዝ.(100):1–5::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 5

## በሰባት ማህተም የተዘጋ መጽሐፍ

በምዕራፍ 4 ጠቅላላ ራእዩ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ያተኩራል።

በምዕራፍ 5 ደግሞ ጠቅላላ ራእዩ በማህተም በተዘጋ በአንድ መጽሐፍ ላይ ያተኩራል።

በምዕራፍ 4 እግዚአብሔርን በዙፋን ላይ ሆኖ ስናይ፣ በምዕራፍ 5 ደግሞ በጉን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በዙፋን ላይ በግና አንበሳ ሆኖ እናያለን። አንበሣ ከሁሉ በላይ ታላቅና ንጉሥ ሲሆን በግ ደግሞ ለማዳን የሞተልን መድኃኒት መሆኑን እንመለከታን።

በምዕራፍ 5 መጀመሪያ ላይ ኢየሱስ ታላቅና ከሁሉ በላይ ሆኖ ቦታ የወሰደ ስለሆነ እርሱ ብቻ ዋና ሆኖ ይታያል። ከምዕራፍ 4 እስከ 5 የእግዚአብሔርን ቅድስና ሲያሳይ ከምዕራፍ 6 እስከ 19 ድረስ በምድር የሚመጣውን መከራና ፍርድ ያሳያል።

1. በምዕራፍ 4 እግዚአብሔር አብን በሰማይ በዙፋኑ በዙፋኖች ተከቦ እናያለን፣
2. በምዕራፍ 5 ኢየሱስን በሰማይ በዙፋኑ የዓለም በግ የነበረ፣ አሁን የይሁዳ አንበሣ ሆኖ እንመለከታለን።

ሐዋርያው ዮሐንስ በምዕራፍ 4 ላይ የእግዚአብሔር ዙፋን በ24 ዙፋኖችና በ4 እንስሶች ተከቦ እንደነበረ ሲያሳይ በምዕራፍ 5 ቁጥር 1 ደግሞ በዙፋን ላይ ከተቀመጠው በቀኝ እጁ ላይ በ7 ማህተም ታትሞ የተዘጋ መጽሐፍ አየሁ ይላል።

ቁ. 1 በማህተም ታትሞ የተዘጋ መጽሐፍ በቀኝ እጁ ይዞ በዙፋን የተቀመጠ እግዚአብሔር አብ ነው። ይህ በ7 ማኅተም ታትሞ የተዘጋ መጽሐፍ ምንድን ነው? ለዚህ መጽሐፍ ሌላ ስም አለው ወይ? አዎን አለው። ስሞቹ:-

1. አዲስ ቃል ኪዳን መጽሐፍ ሊባል ይችላል። እርሱም ስለ ዓለምና ፍጥረት ያለውን የእግዚአብሔርን ሥራና እቅድ ይገልጻል።
2. የደህንነት መጽሐፍ ይባላል

3. የዓለምን ሁኔታ ስለሚገልጽ የዓለም አድራጐት መጽሐፍ ይባላል።

የመጽሐፉን ሁኔታ ከምዕራፍ 6 ቀጥሎ ባሉት ምዕራፎች የእግዚአብሔርን ፍርድ በዓለም ላይ ሲፈስ ስለሚታይ ነው። ይኸውም:

1. ለሰው ያለውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ፣ ዘፍጥ. 1:26
2. በኃጢአት ምክንያት ሁሉን ያጣና ሁሉ የጠፋበትን አዳም ስናይ፣
3. ሁለተኛው አዳም ክርስቶስ መጥቶ መንገሡ፣ 1ኛ ቆሮ. 15:45፤ ዕብ. 2:5–9፤

የመጽሐፉ ትርጉም አሁን እግዚአብሔር ሁሉን ሥልጣን ለክርስቶስ አሳልፎ ሲሰጥና ሁሉ ነገር በእግሩ ሥር ሲሆን እንመለከታለን። በምዕራፍ 5 በሰባት ማኅተም የተዘጋን ነገር በክርስቶስ ሥልጣን ብቻ የተፈታ እንደሆነ እናያለን፣ ማቴ. 28:18–20። ሥልጣን ሁሉ የእርሱ ሆኗልና ክብር ለእርሱ እንስጥ፣ እንስገድለት።።

ቁ. 1 የመጽሐፉ በሰባት ማኅተም መዘጋት

እንደ ዮሐንስ ራእይ በብሉይ ኪዳንም የተዘጋ መጽሐፍ እናገኛለን። በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የታተመ መጽሐፍ ከማየታችን በፊት ይህ ሰባት ማኅተም ምንድን ነው?

ሰባት ቁጥር ምን ጊዜም ቢሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጨረሻ፣ የማለቂያ፣ የመደምደሚያ ሙሉ ቁጥር ነው ይባላል።

ቁ. 1 በብሉይ ኪዳን ታትሞ የተዘጋ መጽሐፍ በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ነው። የዳንኤል መጽሐፍ ከክርስቶስ ልደት 500 ዓመት በፊት ቀደም ብሎ ተጽፏል። ዳንኤል መጽሐፉን ጽፎ እንደጨረሰ ዝጋ፤ አትም ተብሎ ታዘዘ፣ ዳን. 12:4–9። ይህ እስከ ፍጻሜ ጊዜ ሁሉ ነገር አይገባም ማለት ነው። ነገር ግን ዮሐንስ ራእዩን በጻፈ ጊዜ 90 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነበር። ለዮሐንስ የተነገረው ትእዛዝ ልዩ ነበር፤ (ራእይ 22:10)። በማህተም አትዝጋው ብሎት ነበር። ዝጋ አትም የተባለበት አዳም ያጠፋውን፣ ያጣውን ማዕረግና ክብር ክርስቶስ መጥቶ እስኪመልስ ነበር። ክርስቶስ መልሶ እስኪገዛ፣ አዳኝ እስኪሆን ድረስ ነበር።

አሁን ግን ለዮሐንስ አትዝጋው የተባለው ክርስቶስ ፈጽሞ ከፍኗልና አትዝጋው ማለት ነው። በአዳም ኃጢአት ምክንያት የእርግማን ችግር በዘሮቹ ሁሉ ሞት ሳይቀር ተላልፏል፣ ዘፍጥ. 3፡17–19፤ ሮሜ 5፡12–14። ዛሬ ውጤቱን እያጨድን ነን። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚገልጽልን ይህ እርግማን ከላያችን እንዲወገድ በተስፋ ፍጥረት ሁሉ የሰው ልጅ የክርስቶስን መገለጥ ይጠባበቃሉ ይላል፣ ሮሜ 8፡19–22። ስለዚህ ነው የሰው ልጅ የክርስቶስ መገለጥ የሰባቱን ማኅተም ያለበትን መጽሐፍ መፍታት የሚያጠቃልለው።

ቁ. 2 አንብብ ማን ይገባዋል? ብሎ ብርቱና ኃይለኛ መልአክ ይጠይቃል።

ብርቱ መልአክ እንኳን መጽሐፉን መዘርጋት፣ መክፈት ማኅተሙንም መፍታት አልቻለም። ጌታን ትቶ መልአክን ለሚያምን፣ ሁሉን ነገር የሚችሉ አድርጐ ለሚያስብ ለሰው ልጅ ወዮ!

ብርቱና ኃይለኛ መልአክ መጽሐፉን የመክፈትና ማኅትሙን የመፍታት ሥልጣን ስላልነበረው እንዲህ እያለ በታላቅ ድምጽ ይጮህ ነበር። «የሚገባው ማን ነው? ማን ይችላል? ለማን ይገባዋል መፍታት?» ምን ማለት ነው? ኃይል ያለው ማን ነው? ሥልጣን ያለው ማን ነው? እርግጠኛ ጌታ ማን ነው? ሊገዛን የሚችል ማን ነው? በመልአክ በኩል ከሆነ ተስፋ የለም ወድቋል። ሰይጣንም ከሆነ ተጣለ ወደቀ። በሰው በኩል ከሆነ አዳም በኃጢአት ወድቋል። በሰው በኩል እውነተኛ ፍርድ፣ ፍትህ አልተገኘም፤ ጸድቅ ጠፋ፣ ሰላም ታጣ፣ ፍቅር ጠፍቷል፣ በሰው በኩል የለም። ማን አለ?

ቁ. 3 ለዚህ ጥያቄ መልስ አለ። ቁጥር 3 እንደገና አንብብ።

በምድር በሰማይ ከምድርም በታች ቢሆን ወይም በዓለም ገዢዎች ወይም በቤተ ክርስቲያን ቢሆን፣

1. በሰው በኩል ማንም አልተገኘም
2. በኃይለኞች መላእክት በኩል አልተገኘም
3. ኃይለኛ በሚመስል ሰይጣን በኩል አልተገኘም

በአንዳንድ አገሮች ባህልና ሥርዓት ዋና ባለ ማዕረጉ ሳይመጣ በታውን ቢሆን ክብሩን ማንም ሊነካ አይችልም። የሚገባው እርሱ ነውና። ለዮሐንስ ራእይ ጥያቄ የሚገባ ማንም አልተገኘም። ማንም ባለ ሥልጣን መጽሐፉን ሊከፍት ስላልቻለ ዝም ተባለ።

ቁ. 4 ዮሐንስ ማልቀስ ጀመረ

አ! ዮሐንስ ልቡ የዋህ ነው፤ አዎ ክርስቲያን ልቡ ጠንካራ አይደለም፤ ጨካኝም አይደለም፤ ርኅሩህ ነው እንጂ! ሮሜ 12:15፤ ኢዩ. 2:12–13:: በቁጥር 2 ሊፈታ የሚገባው ማን ነው? ለሚል ጥያቄ መልስ እስከዚህ አልተገኘም ነበር::

ቁ. 5 አንድ ሰው ብቻ ተገኘ::

ሊፈታ የሚገባው ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ እስካሁን አልተገኘም ነበር፤ በቁጥር 5 ላይ ግን መጽሐፉን ሊከፍት ማኅተሙን ሊፈታ የሚገባው ወይም የሚችል አንድ ብቻ ተገኘ:: እርሱም በሞቱ፣ በመሥዋዕቱ፣ በመስቀል ላይ ለሰው ሁሉ የራሱን ደም በማፍሰሱ፣ ሞትን ሞቶ በትንሣኤው ሞትን ድል አድርጐ በመነሣት ሥልጣን ያለው፤ የእግዚአብሔር በግ የሆነው እርሱ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አማላጅ ሊሆን የቻለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው የተገኘ፤ 1 ጢሞ. 2:5፤ ሮሜ 8:34፤ የሐዋ. ሥራ 4:12፤ ዮሐ. 14:6፤ ማቴ. 28:18:: ለሰው ሁሉ ደሙን አፍስሶ ሰውን ሁሉ በደሙ ዋጅቷል ለእርሱ ይገባዋል ተባለ:: የራሱን ሕይወት ለኃጢአተኞች ዋጋ አድርጐ ከፍሏልና ለእርሱ ይገባዋል ተባለ:: ሰላምን በሰው ልብ በተለይም በአማኞች ልብ መሥርቷልና ሰላምን ከእግዚአብሔር፣ ከሰው ጋር እንድናደርግና በልባችን እንዲኖር አድርጓልና ለእርሱ ይገባዋል::

ይህን ማኅተም ሊፈታ የቻለ ጌታ ለወደፊት በዓለማችን ፍጹም ሰላምን ያመጣል:: እርሱ ተመልሶ ይመጣል፣ ኢሳ. 62:25፤ 35:1፤ ሮሜ 8:22፤ ዮሐ. 14:1–3::

ቁ. 5 የይሁዳ አንበሳ ተባለ

ኢየሱስ ከይሁዳ ነገድ ስለ ተወለደና የዳዊት ዘር ስለነበረ የዳዊት ሥር ተባለ:: እርሱ የዘላለም አምላክ፣ ሕያው አምላክ በሰው ዘር መጥቶ ሰው ሆነ ተወለደ፤ ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ሰው ስለሆነ፣ የሰው ልጅ መዳኛ ሆኗል:: ሰው የሚድንበት ዋጋውን ከፍሎታል:: ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ ለመሆን ፈቃደኛ ሆኗል::

ቁ. 6 እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁት

ሐዋርያው ዮሐንስ እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ ይላል:: የታረደ በግ ይወድቃል እንጂ አይቆምም:: ኢየሱስ ግን ቆሟል:: ለዘላለም ሕያው ነው:: ስለዚህ መጽሐፉን ሊከፍት ማህተሙን ሊፈታ የሚገባው

ነው:: ኢየሱስ የሚገባው የሆነበት ምክንያት ፊልጵ. 2:6–11፤ 1ኛ ጴጥ. 1:18–19 ተመልከት:: ኢየሱስ አንበሳ እንደሆነ የሚገልጸው ሁለተኛ በሚመለስበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ ሲሆን፣ እንደ አንበሳ ይነግሣል፤ እንደ አንበሳ ፈራጅ መሆኑን ያሳያል:: ኢየሱስ በግ የሆነበት በአንደኛ ጊዜ በመምጣቱ እንደ በግ ታርዶ ሞተ፤ እንደ በግ ትሁት ሆኖ ራሱን አዋረደ እንደ በግ ጸጋ ይዞ መጣ፣ ዮሐ. 1:18 ዋጋ የከፈለ በግ ኢየሱስ ነው:: የሚፈርድ አንበሳ በአብ ቀኝ ያለው ነው፣ ማቴ. 22:44፤ የሐዋ. ሥራ 7:55–56፤ ኤፌ. 1:20::

ቁ. 6–8 ለመልአኩ ጥያቄ ለመጽሐፉ መከፈትና ለዮሐንስ ለቅሶ ወሳኝ መደምደሚያ የሆነ መልስ ተገኘ:: ለመልአኩ ጥያቄ መልሱ የታረደው በግ ነበር:: ለመጽሐፉ መከፈት የታረደው በዙፋኑ ላይ ያለው በግ ነበር:: ለዮሐንስ ለቅሶ መልስ የታረደው በዙፋኑ ላይ ያለው በግ ነው:: በጉ በዙፋኑ መካከል ነበር::

ቁ. 6 ሰባት ቀንዶች ነበረው::

ቀንድ በምሳሌነቱ ኃይልን ያሳያል፤ ዘኁ. 24:8፤ 1 ነገ. 22:11፤ መዝ. 22:21፤ 131:17:: ቀንድ ሥልጣንን ያሳያል፤ 1 ሳሙ. 2:10:: ክብርን ያመለክታል፤ 1 ሳሙ. 2:1:: ሰባት ማለት ሙሉ መደምደሚያ መፈጸሚያ ማለቂያ ቁጥር ነው:: እንዲሁም ሁሉም ነገር በክርስቶስ ተጠቃሎ ተፈጽሟል ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ራእይና ሥራ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ተጠቃሏል:: በቀንድ ላይ ሙሉ ኃይል እንዳለ ሁሉ በኢየሱስ ላይም ሙሉ ኃይል አለው:: አንተስ በኢየሱስ ደም ያለውን ኃይል ታምናለህ?

ሰባት ዓይኖች:– በምድር ላይ የተላኩ የእግዚአብሔር መናፍሥት ናቸው:: የጌታ ዓይን በምድር ላይ መሆኑን ይገልጻል፤ ዘካ. 4:10፤ መዝ. 11:4፤ 33:13::

ቁ. 7–11 በዙፋኑ ከተቀመጠው (ከአብ) ቀኝ እጅ መጽሐፉን የታረደው በግ ወሰደው:: ማን ይገባዋል ለሚለው ጥያቄ በቁጥር 7–11 መልስ ተገኘለት:: በጉ መጽሐፉን በወሰደ ጊዜ:–

1. ስግደት ነበር 2. ምስጋና ነበር 3. ደስታ፣ ዝማሬ ነበር

ልዩ በዓል እንደሆነ ይመስላል:: ለምን?

1. መጽሐፉን የሚወስድና የሚከፍት ስለተገኘ፣
2. የሚገባው ሰው ስለተገኘ፣

3. ለሰው ብሎ የታረደ ሰው ስለተገኘ፣
4. ከሁሉ ወገንና ቋንቋ ለእግዚአብሔር የዋጀ።

በጉ ስላደረገው መልካም ነገር አንተስ ተደስተህ ዘምረህ ታውቃለህ?

ቁ 9–14 ፍጹም አዲስ መዝሙር ተዘመረ።

በእግዚአብሔር ዙፋን ያሉትን የዘማሪዎች ቡድን እናያለን። በጉ መጽሐፉን በወሰደ ጊዜ በሰማይ ከባድ ዝማሬ ሆነ። ዘማሪዎች እነማን ናቸው? በዝማሬ የተሳተፉትስ?

1. አራት እንስሶች (ቁጥር 8)
2. ሃያ አራት ሽማግሌዎች (ቁጥር 8)
3. ብዙ መላእክት ( ቁጥር 11)

4. በጣም የሚያስገርም በሰማይ ያለው ፍጥረት ሁሉ፣ በምድርም ያለው ፍጥረት ሁሉ፣ ከምድርም በታች ያሉ ሁሉ፣ በባህር ያለው ሁሉ ነበር። በባህር ውስጥ ያለው ሁሉ ይዘምር ነበር፣ ቁጥር 13። መዝሙሩ የትኛው ይሆን?

ሀ) ምድር በተመሠረተ ጊዜ በንጋት ኰከቦች የተዘመረው ዓይነት ይሆን? ኢዮብ 38:7።

ለ) እነ ሙሴ ከግብጽ ባርነት በወጡ ጊዜ የዘመሩት ዓይነት? ዘጸ. 15:1። አይደለም አዲስ ነበር እንጂ።

በሰማይ በዙፋኑ ፊት የነበሩት ዘማሪዎች ዛሬ በቤተ ክርስቲያን የሚዘምረውን ዓይነት መዝሙር ሊሆን ይችላልን? ምናልባት ቁጥር 9 ታርደሃል፤ ዋጅተሃል እያሉ በብዛት ለክርስቶስ ሞት ያወሩ ነበር። ስለ ደሙ ስለ መግዛቱ ያወሩ ነበር፣ ዕብ. 9:22። እናንተስ ስለ ክርስቶስ ሞት ወይም ስለ ደሙ፣ ስለ ሰጠን ነጻነት መዝሙር መዘመር ትችላላችሁን?

ቁ. 10 መንግሥትና ካህናት ሆኖ ይነግሣል

ዮሴፍ ከፈርዖን ጋር እንደ ነገሠ ዳንኤልም ከናቡከደነፆር ጋር እንደ ነገሠ ሁሉ እኛም ከክርስቶስ ጋር እንነግሣለን። መላእክት ሁሉና ፍጥረታት ሁሉ በአንድ ድምጽ ቢዘምሩና ይህንን ቢያወሩ እንዴት ይሆን? ጌታችን ለእኛ ያደረገውን ታላቁን የደህንነት ሥራና የሰጠንን ደስታ አንተስ ታወራለህን? ያንን መላእክት ሊያዩ ይመኛሉ፣ 1ኛ ጴጥ. 1:10–13 ተመልከት።

# የዮሐንስ ራእይ 6

## የማህተም መከፈት ወይም መፈታት ፕሮግራም

ዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 6 ስለ ማህተም መከፈት ከመመልከታችን ቀደም ብለን ኢየሱስ የተናገራቸውን ተመሳሳይ ጉዳዮች ማቴዎስ 24 እንደዚሁም ማርቆስ 13 እና ሉቃስ 21ን አንብብ:: ትኩረት መስጠት አለብን::

በተለይም ማቴ. 24:1–8 አሁኑኑ ሊነብብ፣ ቁጥር 4፣6፣7 ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባ ነው:: ይህ ሐሳብ በልባችን እንዳለ ወደ ዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 6 ስንገባ ብዙ ነገሮች በቀላሉ ሊገቡን ይችላሉ::

### ቁ. 1 እና 2 አንደኛ ማኅተሙ ተከፈተ

ማኅተሙን የከፈተው በጉ ነበር:: በጉ የመከፈት ሥልጣን አለው፤ ምዕ. 3:7:: የገሃነም ደጆች እንኳን አይችሉትም፣ ማቴ. 16:18:: ባለሥልጣኑ ግን ይችላል:: እርሱም በጉ ራሱ ነው::

### አንደኛው ማኅተም በተከፈተ ጊዜ ምን ሆነ?

ነጭ ፈረስ ወጣ፤ ፈረሰኛ ተቀምጦበታል:: ቀስት ይዟል:: ቀስት ተሰጠው፤ ደግሞ አክሊል ተሰጥቶታል:: ድል ተሰጠው:: ይህ ማነው? ስሙስ ማነው? ሐሰተኛው ነብይ ወይም ሐሳዊ መሲህ ነው:: ስለዚህ በነጭ ፈረስ ላይ ስለተቀመጠው ሰው ትኩረት ሰጥተን በጥንቃቄ ብንመረምር፣ አስመሳይና ሃሰተኛ ሆኖ እናገኘዋለን:: ለምሳሌ ያህል ቁጥር 1–2:: በነጭ ፈረስ የተቀመጠ በእነዚህ ቁጥሮች ያለውን እንመልከት::

1. በነጭ ፈረስ ተቀምጧል
2. ቀስት አለው ግን መውጊያ ፍላጻ የለውም፤ ስለዚህ ቀዝቃዛ ጦርነት ይሆን? ደግሞ አያሸንፈውም::

ከዚህ ሌላ ሰው እናያለን፤ በተመሳሳይ መንገድ ራእይ 19:11–16 አንብበን እናመዛዝን:: ከዚህ ሰው ጋር ያለውን ልዩነት በጥንቃቄ ማወቅ አለብን:: በዮሐንስ ራእይ 19 ያለው መውጊያ አለው፣ ዘውድ አለው፣ ድል ያደርጋል:: ይህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስነው:: የምዕራፍ 6ቱ ሐሰተኛ ነው:: ግን ክርስቶስን ለመምሰልና ሕዝቡን ለማታለል በጣም ይጥራል::

3. በምዕራፍ 6 ያለው አክሊል ነው:: አክሊሉ የአሸናፊ ይሁን እንጂ ጊዜያዊ ድል ነው፤ ዘለቄታ የለውም:: ይኸ ሁሉ እውነተኛውን ለመምሰል የሚሞከረው ሙከራ ነው፣ ማቴ. 24:5፤ ዮሐ. 5:43፤ 2 ተሰሎ. 2:9፤10፤ 1 ዮሐ. 2:18:: ጠቅላላ በዓለም ላይ ሰላምን፣ ጸጥታን፣ ዕረፍትን የሚያመጣ ሰው ቢያገኝ ኖሮ በደስታ ይቀበሉታል:: ስለዚህ ይህን ሰው መስሏቸው ይፈልጉታል፣ ማየትም ይመኛሉ:: ለዓለም የሰላም ዋስትና የሚሰጥ ማን ይገኝ ይሆን?

በምዕራፍ 6 ላይ ያለው በነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠው ሰው ሲመጣ እኔ ለዓለም ሁሉ ሰላም ሰጭ ነኝ፤ ዋስትና በእኔ አለ የሚል ስለሆነ አመጣጡ በኃይል ይሆናል:: በውሸት ሰላምን ይዞ የመጣ ይመስላል፣ ዳን. 11:21–23:: በተለይ 36ን ልብ ብለን እንመልከት:: በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ለጊዜው ይፈቅድለታል:: ሰይጣንም ለዚህ ሰው ኃይል፣ ሥልጣን፣ ግዛትን ሳይቀር ይሰጠዋል:: ሁሉን ነገር የሚያደርገው በተንኮል፣ በማታለል፣ በጦርነት ስለሆነ ሕዝብን ሁሉ ያታልላል:: ራሱንም ከአምላክ እኩል ያደርጋል:: ብዙዎችም ይታለሉና ይከተሉታል፣ 2 ተሰሎ. 2:3–12:: ታዲያስ ለሰው ልጅ ማምለጫው ምን ይሆን? መልሱ ዛሬ ክርስቶስን መያዝና ማመን ነው፣ 2 ቆሮ. 6:2፤ ዕብ. 2:3::

ቁ. 3,4 ስለ ሁለተኛው ማህተም መፈታት ወይም መከፈት

በአንደኛው ማኅተም እንዳየነው የሐሳዊ መሲህ ወይም የሐሰተኛ ነብይን መምጣት የሚገልጽ ሲሆን የእርሱ አመጣጥ ክርስቶስን መስሎ ብዙዎችን እንደሚያስት ነው:: ይህ ሰው የሐሰት ሰላምን ይዞ በመምጣት ዓለምን በሞላ ለመግዛት ሥልጣን እንደሚኖረውና የውሸት ሰላም እንደሚሆን አይተናል:: አሁን ሁለተኛው ማህተም በተከፈተ ጊዜ የሚከፍተው አሁንም በጉ ነው:: እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በቁጥር 3 ሁለተኛው ማኅተም ሲፈታ ዮሐንስ አየ፣ ተመለከተ ይላል:: ይህም ቤተ ክርስቲያን (አማኞች) ወደፊት የሚመጣውን ነገር እንድናውቅና በመጣ ጊዜም እምነታችን እንዳይናወጥ፣ ጽኑ እንዲሆን በቅድሚያ እግዚአብሔር በባሪያው በዮሐንስ በኩል እያስተላለፈ ያስጠነቅቀናል ማለት ነው:: በቁጥር 4 ላይ ሁለተኛውን ማኅተም በጉ በፈታ ወይም በከፈተ ጊዜ ዳማ ፈረስ (ቀይ ፈረስ) ወጣ:: በዚህ በዳማ ፈረስ ላይ ለተቀመጠው የተሰጠውን ሥልጣን ተመልከት፡

1. ሰላምን ከምድር ያጠፋ ዘንድ

2. ሰዎች እርስ በእርሳቸው እንዲተራረዱ ያደርግ ዘንድ ታላቅ ሰይፍ ተሰጠው፡፡

ለእነዚህ ባለ ፈረሶች ሥልጣን የሚሰጥ ሌላ መኖሩን መርሳት የለብንም፡፡ ያውም ሥልጣንና ኃይል ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ፈረስ ሁልጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ የጦርነት ምሳሌና ምልክት ነው፡፡ ቀዩ (ዳማ) ፈረስ ሲል የደም ምልክት ነው፡፡ በእነዚህ በቁጥር 3 እና 4 ስንመለከት ፈረሱ ተቀየረ እንጂ ፈረሰኛው በአንደኛው ማኅተም የነበረውን ይመስላል፡፡ አዎን ዓለም ስለ ሰላም ሁልጊዜ ይጮኻል፡፡ ግን እንደ 1ኛ ተሰሎንቄ 5:3 ከጥፋት ማምለጫ መንገድ የለም፡፡ ምክንያቱም ያንን ታላቅ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስን ችላ የሚል እንዴት ያመልጣል? ዕብ 2:3፡፡ ዓለም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን የጠላቸውን ያህል እግዚአብሔር ለክፉ አሳልፎ ይሰጣታል፣ ሮሜ 1:18–32፡፡ ስለዚህ ሰው መምጣት በዳንኤል 11 በተለይም በቁጥር 36–45 እንዲሁም ሕዝ. 38:8፤9፤ 18፤19 እንዲሁም ምዕራፍ 29 ተጽፏል፡፡

ቁ. 5–6 የሦስተኛው ማኅተም መከፈት

ማኅተሙን የሚከፍት አሁንም በጉ ነው፡፡ ዮሐንስ የእያንዳንዱን ማኅተም መከፈት በጥብቅ እንድንመለከት ይጋብዘናል፡፡ እይ ይላል፡፡ አራት እንስሳት እያንዳንዳቸው በየተራ ይጋብዙታል፡፡ በሦስተኛው ማኅተም መከፈት ሦስተኛው እንስሳ ዮሐንስ እንዲነቃና እንዲመለከት ይጋብዘዋል፡፡ ሦስተኛውን ማኅተም በጉ ሲከፍት ጥቁር ፈረስና በፈረሱ ላይ የተቀመጠው ይወጣሉ ወይም ይታያሉ፡፡ በፈረሱ ላይ የተቀመጠው በእጁ ሚዛን ይዟል፡፡ የእህል ሚዛን ነው፡፡ ዮሐንስ ያንን ሲመለከት አንድ እርቦ ስንዴ በአንድ ቀን ደሞዝ፣ ሦስት እርቦ ገብስ በአንድ ቀን ደሞዝ ይሁን የሚል ድምጽ ከአራቱ እንስሳት መካከል መጣ፡፡ ይህ የሦስተኛው ማኅተም መከፈት በምድር የሚሆን የረሃብ ሁኔታ፣ የምግብ ማጣት ፍርድ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በሁለተኛው ማኅተም በቀይ ፈረስ ላይ የተቀመጠው አሁንም በሦስተኛው ማኅተም በጥቁር ፈረስ ላይ ተቀምጧል፡፡ ከጦርነት፣ ከደም ማፍሰስ ቀጥሎ በዓለም ሁሉ ላይ ከባድ ረሃብ ይመጣል ማለት ነው፡፡ በጦርነት ጊዜ ምግብ በቀላሉ አይገኝም፡፡ በጦርነት ጊዜ ገንዘብ ውድ ነው፡፡ ዘይትና ወይንን አትጉዱ ተባለ፡፡ ዘይት የድሎትና የቁንጅና ምሳሌ ነው፡፡ የሽቶና

የቅባትም ምንጭ ነው። ወይን ደግሞ የመጠጥና የስካር ምሳሌ ነው እነዚህ ነገሮች ይብሳሉ፤ ከዚህ ሁሉ ከሚመጣ ከዓለም እርኩሰት ወደ ጌታ ዓይናችንን አንስተን መመልከትና ራሳችንን በጽድቅ ጉዳና ማዘጋጀት አለብን።

ቁ. 7–8 የአራተኛው ማኅተም መፈታት (መከፈት)

አራተኛው ማኅተም የመጨረሻውን ፈረሰኛን ያመጣል። አራተኛው ማኅተም በተከፈተ ጊዜ ከእንስሶቹ አራተኛ ዮሐንስን ና እይ ብሎ ይጋብዘዋል። ዮሐንስ እያየ እነሆ ሐመር ፈረስ ወጣ። ወደ አረንጓዴ ሆኖ ገራጫ ፈረስ ነው። በፈረሱ ላይ ተቀምጦ የነበረው ስሙ ሞት የሚባል ነበር። እርሱን የሚከተል አንድ ሌላ ነበር። ስሙ ሲዖል የሚባል ነበር። ለሞትና ለሲዖል ከባድ ሥልጣን ተሰጣቸው።

ቁ. 8 ላይ በአራተኛው ማኅተም መፈታት 1/4ኛው የምድር ሕዝብ ይገደሉ ዘንድ ይላል፤ ሞትን ተከትሎ የመጣው ሲዖል ነበር። እነዚህ የማይለያዩ ጓደኛሞች ናቸው። ሁልጊዜም ቢሆን ሞት ይቀድማል፤ ከሞት በኋላ ሲዖል ይከተለዋል። ይህ ምን ማለት ነው? መልሱ በዕብራውያን 9:27 ላይ አለ ተጽፏል።

ሞት ማለት ነፍስ ከሥጋ ስትለይ ነው። መሞትን ሁሉም በሥጋው ይሞታል። ከሞት በኋላ ግን በጌታ ያመኑትና ያላመኑት ትልቅ ልዩነት አላቸው።

1/ በክርስቶስ ያመነ ክርስቲያን ሲሞት ሥጋው ወደ መሬት ይቀበራል፤ ነፍሱ ግን በቅጽበት ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሄዳል፣ 2 ቆሮ. 5:1–8፤ ፊልጵ. 1:21–24፤ 3:20፤ ቆላ. 3:1–4፤ ዮሐ. 11:25።

2/ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርጐ ያልተቀበለ ወይም ያላመነ ነፍስ ሲሞት ሥጋው ወደ መሬት ይገባል (ይቀበራል)፤ ነፍሱ ግን በቅጽበት ወደ ሲዖል ይደርሳል፤ ሉቃስ 16:19–31፤ በተለይ ቁጥር 24 – 25።

ሲዖል ማለት የሥቃይ ቦታ፣ የመከራ የእሳት ሥፍራ፣ እረፍት የሌለበት ነው፤ ማር. 9:43–48 ተመልከት። ይህ ብቻ አይደለም፤ ሲዖል ገሃነም እሳትን ያስከትላል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ገሃነም እሳትን ሁለተኛ ሞት ይለዋል፤ ራእይ 20:1415፤ 21:8።

በቁጥር 8 በአራተኛው ማኅተም መከፈት 1/4ኛ የምድር ሕዝብ እንደሚሞቱ ሲናገር ሌላ ጊዜ ደግሞ በራእይ 9:18 ላይ 1/3ኛው የምድር ሕዝብ እንደሚሞት ይናገራል:: በእነዚህ በሁለቱ ቦታዎች ላይ የዓለም ግማሽ ሕዝብ ማለቃቸውን ይገልጻል:: ይህም የሚሆነው:-

1. በጦርነት
2. በረሃብ
3. በብርቱ በሽታ
4. በምድር አራዊት እንዲገደሉ ተደርጐ ነው::

እነዚህ ሁሉ ከባድና አስፈሪ ነገሮች ናቸው:: እስቲ ለጥቂት ጊዜ ይህን አስብ:: ለምሳሌ ዛሬ ለሰው ልጅ የሚገዙት፣ ሰውን ሲያዩ የሚሸሹት የምድር አራዊት በሞላ፣ ነገር ተገልብጦ ጠላቶች ቢሆኑ፣ ሰውን እንዲያጠፉ ሥልጣን ቢሰጣቸው ምድር እንዴት ቀውጢ ትሆን ይሆን? ምን በዋጠን ነበር? እንደ መጽሐፉ የቤት እንስሳት የውጭ አራዊት ሳይቀሩ የሰው ጠላት የሚሆኑበት ጊዜ ሊመጣ ነው:: ከዚህ ሁሉ መከራና እልቂት እንዴት መዳን ይቻላል? መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው:: ዛሬ ነው የመዳን ቀን፤ የሐዋ. ሥራ 4:12፤ 2 ቆሮ. 6:2፤ የሐዋ. ሥራ 16:31 ተመልከት:: ለምን እንዲህ ዓይነት ፍርድ ይደርስብናል? መልሱ እግዚአብሔር ሰው እንዲድን የራሱን አንድ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ምድር ሲልክ አንቀበልም፣ አናምንም እምቢ ብለው በኃጢአት እግዚአብሔርን ስለ አሳዘኑት ፍርድ ደረሰባቸው ማለት ነው፣ ዮሐ. 3:16-19፤ 36፤ 15:22-23:: ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚወድ እንጂ ለሚጠላ ማምለጫ የለውም:: አንተስ ክርስቶስን እንደ ግል መድኃኒትህ አድርገህ ተቀብለሃል? ወይስ ወንጌልን እየናቅህ በኃጢአት ትኖራለህ? እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ጨካኝ ነው:: ኃጢአትን ከአንተ እንዲወስድ ልጁን ልኮታልና ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ልብህ እንዲገባ አሁኑኑ ጋብዘው:: ከኃጢአት ነፃ ትወጣለህ፤ ከእግዚአብሔር ፍርድ ታመልጣለህ:: ከእግዚአብሔር ጋር ትታረቃለህ:: እግዚአብሔር ለብዙ ሺህ ዓመታት ታግሶአል፣ 2 ጴጥ. 3:9:: እግዚአብሔር ትዕግሥቱ የሚያበቃበት ጊዜ ይመጣልና፣ ሚልክ. 4:1-3፤ 2 ጴጥ. 3:10-15:: በጌታ ለሚያምኑና እግዚአብሔርን ለሚታዘዙ እንዲሁም ጌታ ኢየሱስን ትተው በኃጢአትና በእምቢተኝነት ለሚኖሩ ያለውን ሁለት የተለያየ

ሥፍራ ልብ አድርግ። ወደ ጌታ ብትመለስ ዛሬ እንደ ጳውሎስ በሞት ላይ፣ በሲዖል ላይ ትፎክርበታለህና። 1 ቆሮ.15:54–57 ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲዖል ሆይ ማሸነፊያህ የት አለ? ልትል ትችላለህ። ከሞትና ከእግዚአብሔር ፍርድ፣ ስቃይ ነፃ እንድትወጣ እግዚአብሔር ይርዳህ።

ቁ. 9–11 የአምስተኛው ማኅተም መከፈት ወይም ተከፈተ

በጉ አምስተኛውን ማህተም ሲፈታ አየሁ ይላል ዮሐንስ። ከዚህ ቀጥሎ ዮሐንስን መጥተህ እይ የሚሉ የነበሩት በእግዚአብሔር ፊት የቆሙት እንስሶች መጋበዝን ይተዋሉ። ዮሐንስ አየሁ ይላል፤ ይህ ትልቅ ለውጥ ነው። ከዚህ በፊት በራሱ ሊያደርግ ወይም ሊያይ አይችልም ነበር። ሁልጊዜም እየተጋበዘ ነበር። አሁን ግን በራሱ ማየት ቻለ፤ በራሱ ማወቅ ቻለ። በራሱ መተርጐም መቻል ድንቅ ነገር ነው። ለመሆኑ ለማየት የቻለው ነገር ምን ይሆን? በምዕራፍ 6 ቁጥር 9 ያለውን ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክርነት ቃል የታረዱትን ነፍሳት ነው። ለመሆኑ የሞቱ ሰዎች ሥጋቸው ድሮውኑ በምድር የተቀበረና የቆየ ነፍሳቸው ይታወቃልን? በምን ምክንያትስ እንደሞቱ ይታወቃልን? መልሱ አዎን ይታወቃል ነው። ቁጥር 9 ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ሉቃስ 1:37።

ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ እነዚህ በስሙ ምክንያት እንደሚገደሉ ተናግሯል፤ ማቴ. 24:9። ስለዚህ በሐሰተኛው መሲህ ዘመን አማኞች ሕይወታቸውን እንደሚያጡና እንደሚገደሉ በራእይ 6:9 በግልጽ ያሳያል ማለት ነው። በክርስቶስ ሁለተኛ መመለስ ጊዜ ቀድሞ በጌታ የሞቱት ወይም የተገደሉት እንደሚነሱ 1 ተሰሎ. 4:16 ተነግሯል። በዮሐንስ ራእይ 6:9 ላይ ያሉት ነፍሳት ግን በመከራ ዘመን በሐሳዊ መሲሕ ዘመን በጌታ የሚያምኑትና የሚገደሉት ነፍሳት እንደሆኑ ነው። ቃሉ ለምስክርነታቸው የተገደሉት ይላልና። የሐዋ.ሥራ 1:8 እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል። የሐዋ. ሥራ 8:4 ተመልከት። እነዚህ የተገደሉት ነፍሳት ታማኝ ምስክሮች ነበሩ። በቅድሚያ ሰዎች ለጠራቸውና ለአዳናቸው ታማኝ ከሆኑ ለሰውም ታማኝ ይሆናሉ። እንግዲህ ክርስቲያን ሁሉ ለእግዚአብሔርና ለወንጌል ታማኝ አገልጋይ መሆን አለበት።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ እስኪመጣ ወይም እኛ እስክንሞት ድረስ መከራ አይደርስባችሁም ብሎ ተስፋ አልሰጠንም፤ ዮሐ. 16:33።

ቁ. 9 እንግዲህ በኢየሱስ ስም ማመን ብቻ አይደለም መሞትም አለና:: እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን፤ ራእይ 2:10:: በቁጥር 9 ከመሠዊያ በታች አየሁ ይላል:: መሠዊያ በጌታ ፊት ነው:: መሠዊያ ጌታ የተሠዋበት መስቀል ነው:: በዚህ ቦታ ነፍሳት ከመሠዊያ በታች ነበሩ:: በጌታ መስቀል ሥር መሆን ክብር ነው፤ መዝ. (116):15–17፤ ፊልጵ. 3:10–11::

ቁ. 10 በሰማይ ያሉት ሙታን ስለ ምድር ሁኔታ ያውቃሉን?

መልሱ አዎን ያውቃሉ ነው:: ምክንያቱም ጥያቄ ያቀርባሉ፤ እንዲህ እያሉ:– እስከ መቼ አትፈርድም? እስከ መቼ አትበቀልም? በምድር ላይ ስለ ፈሰሰው ደማችን በምድር ላይ በሚኖሩት ላይ ይላሉ:: ለመሆኑ ሙታን መጠየቅ ይችላሉን? መክሰስ ይችላሉን? ስለ ምድርስ ሰው ማሰብ ይችላሉን? አዎን ቁጥር 10ን በደንብ አንብብና ተረዳ::

ቁ. 11 ለነዚያ ታላላቅ ጥያቄዎች ከእግዚአብሔር ሁለት መልሶች ተሰጣቸው::

1. ነጭ ልብስ ተሰጣቸው
2. እረፍት ተሰጣቸውና ታገሱ ተባሉ::

ነጭ ልብስ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ የጽድቅ ልብስ ነው:: ይህም የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጽ ነው::

አዳምና ሔዋን በኃጢአት ከመውደቃቸው በፊት የነበራቸው ዓይነት ልብስ ነው፤ ዘፍጥ. 3:9–11 አንብብ::

እረፍት፣ ገና በምድር እንደ እነርሱ ስለ ክርስቶስ ምስክርነት የሚገደሉ ስለአሉ ታገሱ ተባሉ:: አቤት የእግዚአብሔር ጥበብ፣ ዘዳ. 32:3፣4::

የስድስተኛ ማኅተም መከፈት

ቁ. 12–17

በዚህ ቦታ በጉ ስድስተኛውን ማኅተም ሲፈታ ይታያል:: ይህ ስድስተኛ ማኅተም የእግዚአብሔርን ታላቅ የቁጣ ቀን ይገልጻል፣ቁ. 17 አንብብ::

በጥንት ዘመን ከነቢያቶች ውስጥ አንዱ ስለዚህ ቀን ትንቢት ይናገር ነበር፣ ኢዩኤል 2:30:: ስድስተኛው ማኅተም ሲፈታ በምድር ላይ ስድስት ዓይነት ጥፋቶች ይደርስባቸዋል::

ቁ. 12–17 ስድስቱ ዓይነት ፍርዶች እንደሚከተሉት ናቸው:-

1. ትልቅ የምድር መናወጥ ነው:: ቁ. 12 ከጥንት ነቢያቶች አንዱ ስለዚህ ቀን የተናገረውን በሕዝ. 38:19–23 ተመልከት::

2. ፀሐይ እንደ ማቅ ጸጉር ጥቁር ሆነ:: ስለዚህ ሁኔታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ ተናግሯል፣ (ማቴ. 24:29)::

3. ጨረቃ እንደ ደም ሆነ፤ ቁ. 12:: ትልቅ ደን ወይም ጫካ ሲቃጠል፣ ከጢሱ የተነሳ ሰማይ ጠቁሮ ፀሐይ ቀይ ይሆናል፤ ከቀይነትም ይጠቁራል:: እንደዚሁ ይሆናል ማለት ነው::

4. የሰማይ ከዋክብት በምድር መውደቅ (ቁ. 13):: አወዳደቁም ትልቅ ድንጋይ ከሰማይ እንደሚወድቅ ይመስላል::

5. ሰማይ እንደ መጽሐፍ ተጠቀለለ፣ (ቁ.14):: ሰማይ ሲል ጠፈር ወይም አየር ያለበት ሲሆን፣ ኢሳ. 34:4 ሰማይ ወይም አየር የሰይጣን ግዛት፣ እርሱ የሚገዛበት ስፍራ ስለሆነ ይህ ፍርድ በሰማይ፣ በአየር ወይም በጠፈር ላይ ይሆናል ማለት ነው::

6. ተራሮችና ደሴቶች ከቦታ ተወሰዱ፣ (ቁ. 14):: ሰማይና ምድር እንደሚያልፉ 2ኛ ጴጥሮስ 3:10–15::

ቁ. 15 እና 16 በእነዚህ ቁጥሮች ሰዎች እግዚአብሔርን ስለ ጠሉትና ስለ አረከሱት እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ኃይሉን የሚገልጽበት መሆኑን እናያለን:: በእግዚአብሔር ቁጣ ቀን እግዚአብሔርን የሚክዱትንና የሚጠሉትን የሚሸከም የቀበሮዎች ጉድጓድ እንኳን አይኖርም፤ በዚያች ቀን እውነተኛው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ያውቁታል:: ማምለጫም አይኖርም፣ ቁ. 15–16:: በጌታ ያላመኑት በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ፊት ለመደበቅ ይሞክራሉ፤ ግን ከበጉ ቁጣ ማምለጥ አይቻልም:: ሰዎች ዛሬ ቢክዱም በዚያን ጊዜ ግን መካድ አይቻላቸውም:: ቁጣውን ይገነዘቡታል:: እውነቱ ያኔ እንደ አዲስ ይገባቸዋል::

አንተስ ዛሬ በሕይወትህ ሳለህ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ ቀን ስለ ቁጣው ቀን አስበህ ታውቃለን? የእግዚአብሔር ፍርድ ዛሬ በዓለም ከተሠሩት ከሚያስፈሩት ፊንጂዎች ሁሉ ይልቅ አስፈሪ ነው::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 7

በምዕራፍ 6 የማኅተሞችን መከፈትና በምድር ላይ የፈሰሱ ፍርዶችን መጽሐፍ ቅዱስ አሳይቶናል። በሰባተኛው ማኅተም በምዕራፍ 8 ላይ ያለው ሳይከፈት በፊት ሌላ ሁኔታዎች በመካከል (አንድ ሌላ ነገር) ያውም በምዕራፍ 7 ላይ ያለው ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ከአንደኛ ማኅተም መከፈት ጀምሮ እስከ ስድስተኛ ማሕተም መከፈትን አጠናቅቀን የምንረዳ ከሆነ በዚህ በስድስተኛ ማኅተም መከፈት ምክንያት በምድር ላይ የፈሰሰው ፍርድ እንደዚህ ከባድ ከሆነ ለመሆኑ በምድር ላይ የሚድኑ ይገኛሉን? ብለን ጥያቄ ማቅረባችን አይቀርም። መልሱም በዚሁ በምዕራፍ 7 ውስጥ ይገኛል።

የእግዚአብሔርን ምሕረት፣ የእግዚአብሔርን ይቅርታና ፍቅር በከባድ ፍርድ መካከል ይገልጻል፤ የእግዚአብሔርን ጸጋና ስጦታም እንደዚሁ።

ቁ. 1–3 እናንብብ፣ በነፋስ ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ኃይል ፍርድ ሳይገለጽ በፊት፦

በተለይ በቁጥር 3 ያለውን ቃል እናነባለን። ያውም የአምላካችን ባሪያዎች ይላል፤ እነዚህ ከየት መጡ? በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 4 ላይ አማኞች ወደ ሰማይ ተወስደዋል። በ2ኛ ተሰሎ. 2:7 መሠረት አሁን የሚከለክል በኋላ በገዛ ራሱ የሚወሰድ ይላል። ይህ ማን ይሆን? መልሱ መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱ አስተማሪ መሪ ወቃሽም ነው፣ ዮሐ. 14:14–17፤ ዮሐ. 15:25፣26 እንዲሁም 16:7–11፤ 14:26 እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 የወረደው መንፈስ ቅዱስ እንደ ሐዋርያት ሥራ 1:8 እና ማቴ. 28:18–20 እስከ ጌታ ዳግም መመለሻ ድረስ በምድር ላይ ይሠራል፤ በምድራችን ላይ በአማኞች ልብ ውስጥ ይሠራል። ዛሬ በጌታ አማኞች ለመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ናቸው፤ ዮሐ. 14:17፤ 1 ቆሮ. 6:19።

አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ታትመዋል፣ ኤፌ. 1:13–14፤ 4:30። አማኞች እንዲያጽናናቸው በእምነት ተቀብለዋል፣ ገላ. 3:14። መንፈስ ቅዱስ የተስፋ ወራሾች የርስት መያዣ ቀብድ ሆኖልናል፤ 2 ቆሮ. 1:21–22። በጌታችን ዳግም መመለስ መንፈስ ቅዱስ ይወሰዳል፣ 2 ተሰሎ. 2:6–7። ታዲያስ እነዚህ ሰዎች እንዴት አመኑ?

ለምሳሌ ያህል

1. በብሉይ ኪዳን ዘመን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነበር። በዙፋኑ ላይ ነበር፣ ዮሐ. 1፡1,2።
2. ዘመኑ ሲደርስ ጌታችን ከሴት ተወለደ፣ ገላ. 4፡4፤ ዮሐ. 1፡14፤ ፊልጵ.2፡6።

ቁ. 1–3

3. ጌታችን ኢየሱስ ሥራውን ሲጨርስ ወደ ሰማይ አረገ፣ ማር. 16፡19። ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ከክርስቲያኖች ጋር ይኖራል፣ ዮሐ. 14፡18–24።

የመንፈስ ቅዱስ ዘመን

1. መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን በአንዳንድ ሰዎች ላይ አድሮ ሥራውን ይሠራ ነበር። ለምሳሌ ያህል ለሥራ ሲፈልግ በኃይል ይወርዳል። ሌላ ጊዜ ይሄዳል ማለት ነው። በሳምሶን ላይ መሳፍንት 14፡6 ስለ ሳዖል 1 ሳሙ. 19፡19–24፤ 16፡14፤ ዳዊትም 2 ሳሙ. 23፡2፤ ሕዝ. 2፡1–3፤ 3፡12።
2. መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ዘመን በቤተ ክርስቲያን ዘመን ዛሬ የሚሠራው በበዓለ ሃምሳ ቀን ወደ ምድር በኃይል በሐዋርያቶች ላይ እንደ ወረደ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ሙሉ ይናገራል። ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ያድራል ይኖራል፣1 ቆሮ.3፡16–17፤ 6፡19–20፤ ዮሐ. 14፡16–17።
3. አንድ ቀን ግን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ይወሰዳል፣ 1 ተሰሎ. 4፡13–18፤ 2 ተሰሎ 2፡6–7።
4. መንፈስ ቅዱስ እንደፈለገ ይሠራል፤ ባንድ ጊዜ በዙፋን ላይ እንዲሁም በሁሉ ቦታ ይገኛል። መዝ. (139)፡7–12።

ስለዚህ በዮሐንስ ራእይ 7፡1–3 በዚያ ቀን እንኳን መንፈስ ቅዱስ በሰዎች እንደሚሠራና በከባድ መከራና በእግዚአብሔር ፍርድ መካከልም የእግዚአብሔር መንፈስ ሰዎችን ማዳን እንደሚችል እናያለን።

ቁ. 3 የእግዚአብሔርን ባሪያዎች እስከናትማቸው ድረስ ታገሡ ተባሉ። አቤት የእግዚአብሔር ምሕረትና ትዕግሥት፣ ሰዎችን መውደዱና ፍቅሩ! ሁሉ እንዲድን ይፈልጋል፣ 2ኛ ጴጥ. 3፡9። በዮሐንስ ራእይ ጥናት የምናየው በፍርድ መካከል እግዚአብሔር ለሰዎች የምሕረት

ጊዜና እድል እንደሚሰጣቸው ነው። ሰዎች ግን ወደ እግዚአብሔር መመለስ አይፈልጉም፣ ራእይ 9:20 እና 21 ይህን ይገልጸዋል። ስለዚህ ነው እነሆ የተወደደ ሰዓት አሁን ነው። እነሆ የመዳን ጊዜ አሁን ነው የሚለው 2ኛ ቆሮ. 6:2።

ቁ. 4–8 ለጥበቃ የተደረገ ምልክት

ምዕ. 7:1–3 ባሉት ቁጥሮች ፍርድን ይዘው የመጡ መላእክት በአራቱ ማዕዘን ማለትም በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅና በምዕራብ መቆማቸውንና ሌላ መልአክ ድንገት ቆዩ የእግዚአብሔርን ባሪያዎች በግምባራቸው እስክናትማቸው ብሎ መከልከሉን ትዝ እንዲለን ያስፈልጋል። ለነገሩ በሰው ልጆች ላይ የሚደረግባቸውን ሦስት ምልክቶች ማወቅ አለብን።

1. በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን በልባችንና በሕይወታችን ላይ የመንፈስ ቅዱስን ማሕተም እናገኛለን፣ ኤፌ. 1:13–14፤ 4:30። ይህ የጸጋ ዘመን የምሕረት ዘመን ይባላል።
2. ከመከራ ዘመን ከፍርድ በፊት ለእስራኤላውያን ወገን በግምባራቸው ማኅተም ይደረጋል፤ ራእይ 7:3–8። እነዚህ ወገኖች የሐሰት አስተማሪዎች እንደሚሉት የእነርሱ ወገን ሳይሆኑ የእስራኤል ወገኖች ናቸው። የጆሆቫ መስካሪዎች ነን የሚሉት እንደሚሉት አይደሉም።
3. በኋለኛው ዘመን የሐሰት ነብይ በሰይጣን ሥልጣን መንግሥት ይመጣል። በዚያን ጊዜ ለሕዝብ በግምባራቸው ወይም በቀኝ እጃቸው ላይ ምልክት ይሰጣል። ብዙዎችም ይቀበላሉ፣ ራእይ 13:16–18። ማሕተም ምን ጊዜም ቢሆን የማንነት የዋስትና ማረጋገጫ ነው።

ቁ. 4–8 የታተሙት ከእስራኤል ልጆች ብቻ ናቸው። ቁጥራቸው ከየወገኑ 12 ሺህ ሲሆን ከጠቅላላ እሥራኤላውያን 144 ሺ ይታተማሉ። እነዚህ:–

1. ቅዱሳን ተባሉ፤ ራእይ 13:7–8።
2. ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኲራት ተባሉ፣ ራእይ 14:1–5። ታዲያ እንዴት ሊድኑ ቻሉ።

በምዕራፍ 11 ስንመለከት ሁለት ምስክሮች ተነስተው ይሰብካሉ፤ በዚህ ምክንያት ሊድኑ ቻሉ። በዚያን ጊዜ አመኑ እንጂ። የጆሆቫ

ምስክሮች ነን የሚሉ አስተማሪዎች ይህን ጥቅስ ለራሳቸው ምኞት ስለሚጠቀሙ መታለል የለብንም።

## ልዩ ትምህርት

የእስራኤል ልጆች 12 ወገን መሆናቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እናገኛለን። የ12ቱን ጥናት ብትወስድ በዚህ በራእይ የሁለቱ ስም አልተጠቀሰም። ምክንያቱም ዳን የተባለ ወገን በተስፋ አገር ጣዖት በማምለክ የወደቀ ስለሆነ፣ ኤፍሬምም የርሱ ወገን እንዲሁም፣ መሳፍ 18፤ 1ኛ ነገ. 12 ያብራራል። ስለዚህ በራእይ 7:4–8 በታተሙት ላይ የሉም፤ ጣዖትን እግዚአብሔር አይወድም፣ 1ኛ ዮሐ. 5:21።

### ቁ. 9–14 በበጉ ደም መንጻት ነጭ ልብስ መልበስ

እነዚህ ሰዎች ነጭ ልብስ መልበሳቸውን ልብ ብለን እንመልከት። ልብሱ ነጭ ለመሆን መታጠብ ነበረበት። ልብሱ የታጠበው በበጉ ደም ነበር። የሚነጻውም በበጉ ደም ብቻ ነው። የጽድቅ ልብስ ስለሆነም የቅዱሳን ልብስ ነው። ይህም ልብስ በእግዚአብሔር ዙፋን የሚለበስ ነው። ይህ ዓይነት ልብስ በክርስቶስ ለሚያምኑት ብቻ የሚሰጥ ነው።

ያለ ክርስቶስ ደም ለሰው ይቅርታና ምሕረት አይደረገም። እነዚህ ሰዎች ከመከራ የመጡት ልብሳቸውን በበጉ ደም አንጽተዋል። መንፈሳዊ ንጽሕናና ቅድስና በክርስቶስ ደም ብቻ ነው የሚገኝ። ዛሬ በዓለማችን የሐሰት መንፈስ አለበት። ይህ የሐሰት መንፈስ የሰይጣን መንፈስ ነው። የሰይጣን መንፈስ ሰው በክርስቶስ አምኖ እንዳይድን የተቻለውን ነገር ሁሉ ያደርጋል፣ ያሰናክላል። ለሰው ግን የመዳን መንገድ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም እያበራና እያንጸባረቀ አለ። በወንጌልና በክርስቶስ ደም በማመን ብቻ እምነት ይገኛል።

በ1ኛ ዮሐ. 1:7 እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ሕብረት ይኖረናል። የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻልናል። ደግሞ ሮሜ 3:25 ሮሜ 5:8–9 ጨምረን እናንብብ። በሌላ በማንም መዳን የለም፣ የሐዋ. ሥራ 4:12።

### ቁ. 9 የማይቆጠር ብዙ ሕዝብ

ወደ ዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 8 ከማለፋችን በፊት ዮሐንስ ራእይን ማወቅ ከፈለግን የእግዚአብሔር እቅድ ወይም ፕሮግራም ምን ምን እንደሆነ፣ በሰዎች ዘንድ እንዴት እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅላላና በዮሐንስ ራእይም ቢሆን ሦስት ልዩ ልዩ ዓይነት ሰዎች እንዳሉ ማወቅ ያስፈልጋል።

እግዚአብሔርም ከሦስት ዓይነት ሰዎች ጋር ሥራውን ይሠራል። እነርሱም፡-

1. የእግዚአብሔር እቅድና ፕሮግራም ከእስራኤል ጋር እንዴት እንደ ነበረ፣
2. የእግዚአብሔር እቅድና ፕሮግራም ከአሕዛብ ጋር ነበር፣
3. የእግዚአብሔር እቅድና ፕሮግራም ከቤተ ክርስቲያን ጋር ምን እንደነበረ እንዴት እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

1. እስራኤል በምድር የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ። የእግዚአብሔር እቅድ ለእስራኤል የተጀመረው በአብርሃም ነው፣ዘፍጥ.12፡1–3። ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ ድረስ 2000 ዓመት በላይ ነው። አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ በኋላ እስራኤል የተባለ፤ ሙሴና ኢያሱ መሳፍንትና ነገሥታት ነቢያትና ካህናት ሲሆኑ በ70 ዓመት ወደ ባቢሎን ምርኮ ተወሰዱ። ከዚያም መልሰዋቸዋል። የክርስቶስ መወለድና መሞት የሐዋርያት ሥራ በምድር ሁሉና ከዚያም በ70 ዓ.ም. የኢየሩሳሌም መፍረስ እስራኤል ወደ ዓለም መበተን ሲሆን ታሪኩ ሠፊ ነው፣ ዳን. 9፡24–27 ጠቅለሉ ሁኔታውን ይገልጻል። ትርጉሙንም ካወቃችሁ ኢየሱስም የተናገረውን በሉቃስ 21፡20–24 አንብቡና እግዚአብሔር ፕሮግራሙን ከእስራኤል ጋር እንዴት አድርጉ እንደ ነበር አስተውሉ።

2. አሕዛብ የዓለም ሰዎች የዓለም መንግሥታት ሁሉ እግዚብሔርን ባያምኑም እንኳን ፕሮግራሙን ከእነርሱ ጋር ያካሂዳል፣ ዳን. 4፡17,25። እግዚአብሔር የዓለምን መንግሥታት ሙሉ ፕሮግራም ለነብዩ ዳንኤልና በባቢሎን መንግሥት ጊዜ ለንጉሥ ናቡከደነፆር አስታውቆታል፣ (ዳን. 2፡31–45)። እስቲ በሚቀጥለው ሁኔታ እንመልከት።

ናቡከደነፆር በሕልም ያየው የሰው ምስል ወይም ቅርጽ፣
- ራሱ ወርቅ የሆነ የባቢሎን መንግሥት ሲሆን፣
- ደረቱና ክንዱ ብረት የሆነ የምድያምና የፋርስ መንግሥት፣
- ሆዱና ወገቡ ናስ የሆነ የግሪክ መንግሥት፣
- ጭኖቹ ብረት የሆነ የሮም መንግሥት፣

እግሮቹ ግማሽ ብረትና ግማሽ ሸክላ የሆነ የሁሉ መንግሥት ቅልቅል መንግሥት የሆነና ከዚያም የእግዚአብሔር መንግሥት በድንጋይ ተመስሎ እግዚአብሔር ለዓለም ሕዝብ የራሱ ዕቅድ እንዳለው ያሳያል፣ ይገልጸዋል።

3. ቤተ ክርስቲያን፣ በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የክርስቶስ አካል ነው፣ ኤፌ. 2:23። ለስማያዊ አገር የተጠራ ቅዱስ ሕዝብ ነው፣ 1ኛ ጴጥ. 2:9–10። እስራኤል የእግዚአብሔርን መሲሕ በጣሉትና በተቃወሙት ጊዜ ፕሮግራሙን ወደ አሕዛብ አዞረና ከሁሉ ወገን፣ ከሁሉ ቋንቋ፣ ከሁሉ ነገድ ወደ እርሱ ለመጠጋት ለሚፈልጉ ሁሉ ጥሪውን አስተጋባ ወይም አስተላለፈ። የሐዋ. ሥራ 15:14–18።

ቤተ ክርስቲያን ማለት የተጠሩት ማለት ነው። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ከወረደበት ቀን ጀምሮ እስከ ጌታ መመለሻና ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ቀን ድረስ ሥራውን አያቋርጥም፤ መንፈስ ቅዱስም በሰው ልብ በማደር ሥራውን ይቀጥላል።

ዛሬ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ራሱ ሊያቀርብና ቅድስት እንድትሆን ይፈልጋል፣ ኤፌ. 5:26–27። ዛሬም ክርስቶስ ወንዶችንና ሴቶችንም ይጠራል።

ቁ. 9ና10 ብዙ ሕዝብ፣ ከሁሉ ወገን፣ ዘር፣ ቋንቋ ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል ሕዝብ አየሁ ይላል። እነርሱም:–

1. ነጭ ልብስ ለብሰው
2. በእጃቸው ዘንባባ ይዘው
3. በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆመው
4. በታላቅ ድምጽ እየጮኹ በመጨረሻ በመከራ ዘመንም የእግዚአብሔር ደሕንነትና ምሕረትም ለ144 ሺህ እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን ለሌላም ሕዝብና ወገንም ይሆናል፤ ቁጥር 9።

እነዚህ ህዝቦች እነማን ናቸው? እነዚህ ሕዝቦች የሚያሳዩት ቤተ ክርስቲያንን አይደለም። በዚህ ጊዜ ያለች ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ ተነጥቃለች። በ24 ሽማግሌዎች ተወክሎ በዙፋኑ ዙሪያ በ24 ዙፋን ላይ ተቀምጧል።

ታዲያ እነማን ናቸው? እነማን እንደሆኑ በቁጥር 13 እና 14 ላይ እናገኛለን።

ቁ. 13–14 መልሱ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው ተባለ።

ትልቅ መከራ በምዕራፍ 6:12–17 ያለው ሲሆን 6ኛው ማኅተም በተከፈተ ጊዜ በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሞ የነበረ ብዙ ሕዝብ እንዲሁም በግምባራቸው የታተሙ 144 ሺህ እስራኤላውያንና ሌሎችም ጭምር ናቸው። እንዲሁም ስለ እምነታቸው የሚገደሉ ሁሉ ማለት ነው፤ 6:9–11፤ 7:9,14። አሁንም ላለችው ቤተ ክርስቲያን እንዳልሆነ በራእይ 3:10ና 11 ተመልከት።

ቤተ ክርስቲያንና በመከራ ዘመን ያመኑትን እናወዳድራቸዋለን።

1. ቤተ ክርስቲያን ከመከራ ይጠበቃል፣ ራእይ 3:10።
2. ቤተ ክርስቲያን በ24ቱ ሽማግሌዎች ተወክሏል። በ24 ዙፋን ሆኖ ትልቁን ዙፋን ዙሪያውን ከበዋል፣ ራእይ 4:4።
3. ቤተ ክርስቲያን በራሳቸው የወርቅ አክሊል ደፍተዋል፣ ራእ.4:4።
4. ቤተ ክርስቲያን በበጉ ፊት በገናና ዕጣን የሞላበት የወርቅ ዕጣን ይዘዋል፣ ራእይ 4:4።
5. በቤተ ክርስቲያን አዲስ ቅኔ ይዘመራል፣ ራእይ 5:9።
6. መንግሥትና ካህናት ሆነው ይነግሣሉ፣ 5:10፤1:6።

የመከራ ዘመን (ታላቅ መከራ) ሲሆን ከዚያ የመጡት፤

1. ከታላቁ መከራ የመጡት ናቸው፣ ራእይ 7:14።
2. በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆመዋል፣ 7:9።
3. በእጃቸው የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘዋል፣ ራእይ 7:9።
4. መዝሙር አላቸው፣ ራእይ 7:10።
5. በቀንና በለሊት በመቅደስ ያመልኩታል፣ 7:15።

ልዩ ገለጻ ካስፈለገ፣ ራእይ 7:4 ምዕራፍ 14:1፤ 20:4 ተመልከት።

ቁ. 15–17 ለእነርሱ እግዚአብሔር አምላክ የሚያደርግላቸውን እንክብካቤና መጽናናት አንድ በአንድ ቁጠራቸው። ከዚያም ሌላ:–

1. በዙፋን ፊት የክብር አገልግሎት አላቸው፣ ቁ. 15
2. የበረከትን በረከት የተባረኩ ናቸው፣ ቁጥር 16
3. የልዑልን ጥበቃና እረኝነትን ያገኛሉ፣ ቁጥር 16 ና 17።

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 8

## የ7ኛ ማኅተም መከፈት (በጉ መክፈቱን)

7ተኛው ማኅተም ሲከፈት 7 መለከትና 7 መላእክት ሊነፉ የተዘጋጁትን እናያለን፤ ቁጥር 6 ተመልከት። 6ኛ ማኅተም ሲከፈት የእግዚአብሔር ፍርድ በፍጥረት ላይ አይተን ነበር። አሁንም በሰባተኛው ማኅተም መከፈት 7 መለከት መነፋት ልዩ ልዩ የእግዚብሔርን ፍርድ እንመለከታለን።

1. 7ኛ ማኅትም በመከፈት የእግዚአብሔር ከባድ ፍርድ መጀመሩን ብቻ ያሳያል፣ ቀጥሎ
2. 7 መለከት መነፋት ፍርድ፣ ቀጥሎ
3. 7 ጽዋዎች መፍሰስ ፍርድ ይቀጥላል። ስለዚህ በምዕራፍ 6:7 ላይ የተባለውን ተመልከት። በእንደዚህ ባሉት ቁጣና በእግዚአብሔር ፍርድ መካከል የእግዚአብሔርን ምሕረትና አዳኝነት እንመለከታለን። (ለምሳሌ ምዕራፍ 7 144 ሺህ መታተምና ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል ሕዝብ መዳን አስቡ) እነዚህ የእግዚአብሔርን ፍርድ ስትመረምሩ ሁሉም አዳዲስ ነገር ነው እንጂ የተደጋገመ ዓይነት ፍርድ አንመለከትም። በዚህ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ሥራውን እንመለከታለን፣ እናደንቃለን።

ቁ. 1 ታላቅ ዝምታ በሰማይ

ጸጥታ:– ለ 1/2 ሰዓት ሙሉ ዝምታ፣ ማን ይናገር?

አፍ ሁሉ ይዘጋ፣ ሮሜ 3:19። የንግግር ችሎታ ያለው ቢሆን፣ ታላቅ ሥልጣን ያለው ቢሆን እያንዳንዱ ለራሱ ስለ ራሱ መልስ ይሰጣል።

ታላቅ ዝምታ፣ ጸጥታ፣ ማን ሊናገር ይችላል?

ያስፈራል፣ ማን ሊናገር ይችላል? ኃይል ሁሉ ክብር ሁሉ፣ ምስጋና ሁሉ፣ ግዛትም ሁሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖአል።

«አንበሳ ሲያገሣ የማይፈራ ማን ነው? አሞጽ 3:8።

እግዚአብሔር ሲናገር ዝምታ ሆኗል
አዳምና ሔዋን፣ ዘፍ. 3:9 እና 10።
እስራኤላውያን በሲና ተራራ፣ ዘጸ. 20:19።

ነቢያት፣ ዳን. 8:18፤10:9፤ ዕብራውያን 12:25–29:: የዝምታ ትርጉም ሌላ የሚመጣ ነገር ለማየት በጉጉትና በዝምታ መጠበቅ ነው::

## ቁ. 2 የሰባቱ መላእክት ማስተዋወቅ፤

በእግዚአብሔር ፊት የቆሙትን 7 መላእክት አየሁ ይላል ሐዋርያው ዮሐንስ::

እግዚአብሔር በፊቱ የቆሙትን 7 መላእክት ለዮሐንስ ያስተዋውቀዋል:: እኛም እንድናውቅ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ነው:: በዚህ ቦታ ክርስቶስ የሁሉም ነገር ባለ ሥልጣን እንደሆነ፣ ሁሉን ነገር እንደሚቆጣጠር እናያለን፤ ቁጥር 2 በእግዚአብሔር ፊት የቆሙት ሰባቱ መላእክት የእርሱን ትእዛዝ እንደሚጠብቁ እናስታውስ:: እኛም የእርሱ ፍጥረት ነን፤ የእርሱን ትእዛዛት እንደምንጠብቅ ወይም እንደማንጠብቅ መፈለግ አለመፈለጋችንን አያስገድደንም፤ ነፃ ፈቃድ ሰጥቶናል::

ከፈለግን በፊቱ ልንቆምና በልባችን ለእርሱ ትእዛዝ መታዘዝ እንችላለን:: ባንፈልግም እምቢ ብለን ከፊቱ በመሸሽ ወደፈለግንበት ልንሄድ እንችላለን:: በብሉይ ኪዳን 1ኛ ነገሥት 17:1 እንደሚገልጽልን የጥንቱ ነቢያት በእግዚአብሔር ፊት መቆማቸውን አወቁ:: የመላእክት በእግዚአብሔር ፊት መቆም እርሱን ለመታዘዝ ነው::

ለመታዘዝ በፊቱ የሚቆሙት የእግዚአብሔር ባሪያዎች ነበሩ ::

ሐዋርያት የኢየሱስ ባሪያዎች መሆናቸውን አውቀው ታዘዙ፣ ያዕቆብ 1:1፤ ይሁዳ 1:1፤ 2ኛ ጴጥ. 1:1፤ ሮሜ 1:1:: ጳውሎስም እኛስ የእርሱ ባሪያዎች፣ አሽከሮች፣ አገልጋዮች ነንን? ለመታዘዝ በፊቱ ቆመናል? ሂድ፣ አድርግ የሚለውን እንፈጽማለን? ይለናል::

ቁ. 2 መለከት ሲል፣ ጥሩምባ ማለት ነው፤ የመለከት ትርጉም ልዩ ፍቺ ያለው ነው::

1. የሚመጣውን ነገር ያስተዋውቃል
2. ስለሚመጣው ነገር ያስጠነቅቃል::

ከጥሩምባ በኋላ ገለፃ፣ ማስታወቂያ አለ ማለት ነው:: የሰባቱ መለከት መነፋት የእግዚአብሔር ምስጢር ይፈጸማል ተብሎ ለባሪያዎቹ ለነቢያት ተገልጿል፣ (ራእይ 7:10):: በብሉይ ኪዳን ዘመን እሥራኤላውያን በመለከት ለምን እንደሚጠቀሙ ተነግሮአቸዋል፣ ዘኁልቁ 10:1–10::

1. ለመምረጥ
2. ለማስጓዝ
3. በጦርነት ጊዜ (ጠላትን ለመግጠም)
4. በደስታ (በበዓል ቀን)
5. በወር በሚቃጠል መሥዋዕት ጊዜ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መለከት በብዙ ቦታ ተጠቅሷል።

1. ለጦርነት ጌዴዎን መሳፍንት፣ 7:17–18
2. ኢያሪኮ ሲፈርስ ኢያሱ፣ 6:4–5
3. ትንቢተ ሕዝቅኤል 33:1 ወንጌል መለከትን የመንፋት ምሳሌ ነው።
4. ራእይ 8 የእግዚአብሔር መለከት ነው። ጌታ ሲመለስ 1ኛ ተሰሎ.4:16። ተመሳሳይ መለከት 1ኛ ቆሮ. 15:51–52።

እነሆ የእግዚአብሔር መለከት ሊነፋ ነው እያለ የእግዚአብሔር ቃል ያስጠነቅቀናል። በፍጹምነት በፊቱ ልትቆሙ ተዘጋጁ ይለናል፤ የዮሐንስ ራእይ 8:2 መለከት የሚነፋው ለዓለም ፍርድ ለጥፋት ሲሆን፣ ዛሬ የወንጌል መለከት ይነፋል። በፊቱ ያለ ነውር ልትቆሙ ተዘጋጁ፣ ወደ ጌታ ተመለሱ ነው የሚለው፣ ይሁዳ 1:24–25። የጌታ መለከት ሲነፋ መስማት ትችላለህን? ማለት የክርስቶስ የማዳን ወንጌል ሲነገር ሰምተህ ድነሃል? በጌታ በኢየሱስ አምነሃል? መልሱን አንተው መልስ።

ቁ. 3–4 ሌላ መልአክ

ዮሐንስ ገለጻውን ይቀጥልና ከ7ቱ ሌላ ልዩ ሥልጣን ያለው መልአክ ነበር ይላል። አንዳንድ ሰዎች ይህ ሌላ ሥልጣን ያለው መልአክ ጌታችን ራሱ ነው ብለው ያስባሉ። ጌታችን አለመሆኑን ማወቅ አለብን። ምክንያቱም በጉ በዙፋኑ ላይ ሆኖ ማኅተም ያለበትን መጽሐፍ ይዞ ይገኛል። ስለዚህ ጌታችን አይመስልም። እርግጥ በብሉይ ኪዳን አንዳንድ ቦታ የጌታ መልአክ የሚለው ለእርሱ ማለት ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ ግን እርሱ አይደለም።

ቁ. 3 ምድር ከተፈጠረበት አንስቶ እስከዚህ ድረስ እግዚአብሔር በርኅራኄና በፍቅር መልእክተኞችን እየላከ ምሕረት የተሞላ መልእክቱን አስተላልፏል። አሁን ግን ቁጣው የሚፈስበት ጊዜ ነው።

ቁ. 4 እጣንና ጢስ የቅዱሳን ጸሎት

ይህ ለክርስቶስ የሚገባውን ክብር ያሳያል። ክርስቶስ ሲወለድ ዕጣን የተሰጠበትን እናስብ፣ ማቴ. 2:11። ሰብአ ሰገል የዕጣን ስጦታ አበረከቱ። ክርስቶስ ጣፋጭ ሕይወት የተሞላ ሥራ ስለፈጸመ። በእርሱ ሥራና ሕይወት ምክንያት እኛ አማኞች ጸድቃን ልንባል ቻልን። ጸሎታችንም በክርስቶስ መሥዋዕትነት በኩል ጣፋጭ ሽታ ያለበት ሊሆን ችሏል፣ ኤፌ. 5:2።

ክርስቲያን ሆይ! ጽድቃችን ክርስቶስ ነውን? 1ኛ ቆሮ. 1:31 ቅድስናችንስ? ጸሎታችን ክርስቶስ ካልተቀላቀለበት ጣዕም የለውም። መልካምም ሽታ አይኖረውም። ክርስቶስ ካለበት እምነታችን ዋጋ አለው፣ ጸሎታችንም እንደ ዕጣን ነው።

ዕጣን፣ የክርስቶስ ስም በእኛ ሕይወት፣ የክርስቶስ ሥራ በእኛ ጸሎት ዋጋ ያለው መሆኑን ያመለክታል፣ ዮሐ. 14:14።

ጸሎታችን ዋጋ አለው? ክርስቶስ አለበት?

ቁ. 4 የዕጣኑ ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ወጣ።

ቁ. 5 መሠዊያ የክርስቶስን መስቀል ያመለክታል።

የክርስቶስን ሞትና መሥዋዕትነት ዓለም ስለጠላ፣ ስላልተቀበለ አሁን የነጐድጓድ ድምጽ፣ መብረቅና የምድር መናወጥና ፍርድ ለዓለም ሆነ።

የክርስቶስ መሥዋዕትነት

1. ጸሀንነት
2. ፍርድን ያመጣል፤ መምረጥ የእኛ ጉዳይ ነው፣ 2 ቆሮ. 2:15። ወደ ደህንነቱ ና፣ ከፍርድ ታመልጣለህ፣ ሮሜ 8:1።

ቁ. 5 ነጎድጓድ የሚመጣውን ጉርፍ ያመለክታል።

ድምጽ ከብርሃን ወይም ከመብረቅ ቀድሟል። እንደ እውነቱ ከሆነ ብርሃን ከድምጽ ይቀድማል። ነጎድጓድና ጉርፍ ብርሃንን የቀደመው ከእግዚአብሔር ፊት የወጣ የሚመታ ስለሆነ ነው።

የምድር መናወጥ፤ በምሕረት ዘመን እግዚአብሔር የፈጠራት ምድር ብዙ ነገሮችን ችላለች። ከአዳም እርግማን ጊዜ ጀምሮ እርግማንን

ሁሉ ተሸከማለች፡፡ አሁን ግን ሸክሟን የምታራግፍበት ጊዜ ስለሆነ ጸጥ ልትል አትችልም ትናወጣለች፡፡ እኛ ግን የማትናወጥ መንግሥት ስለምንወርስ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን፣ ዕብ. 12፡28–29፡፡

ቁጥር 6–7 የአንደኛው መለከት መነፋት

ቁጥር 6 ዝግጅት

ቁጥር 7 የመጀመሪያው መልአክ መለከትን ሲነፋ ደም
 የተቀላቀለበት እሳትና በረዶ ወደ ምድር ተጣለ፡፡

<u>የምድር</u> 1/3ኛው (ሲሦ)

የዛፍ 1/3ኛው (ሲሦ)

የለመለመው ሁሉ፣ ዕፅዋትና ሣር ተቃጠለ፡፡

የመጀመሪያው መለከት መነፋት፣ ፍርድን በምድር ላይ አመጣ፤ በዛፎችና በሣር ላይ፡፡

ከ1–4 የተነፋው መለከት በፍጥረት ላይ ሲሆን፣ ምድር፣ ዛፍ፣ ሣር፣ ባህር፣ ወንዞችና በሰማይ ብርሃኖች ላይ፡፡

ከ5–6 የተነፋው መለከት በሰዎች ላይ የሚደርስ ፍርድን ያሳያል፣ ራእይ 4፡4–15፡፡ ምናልባት እግዚአብሔር ለሰይጣን ፈቃድ ይሰጥና ይህ ሁሉ መከራና ጥፋት ሊሆን ይችላል፡፡ የኢዮብን ጊዜ አስብ፣ በረዶ፣ እሳት፣ በሽታና ሞት የሆነበትን፡፡ በፍጥረት ጊዜ በመጀመሪያ የተፈጠሩትን፣ ዘፍጥረት 1፡11–12 ከዚህ ጋር አመዛዝን፡፡ መጀመሪያ የተፈጠሩት መጀመሪያ ይጠፋሉ፡፡ ዓለም ሕያው እግዚአብሔርን ትቶ ፍጥረትን ማምለክና መስገድ ሲጀምር ሮሜ 1፡20–23 ፍርዱን በዛፎችና በሣር ላይ አምላካቸው ሲፈጽም ያዩታል፡፡ በዚህ እግዚአብሔር ይከብራል፡፡ እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑን ያውቃሉ፡፡

ቁ. 8–9 የሁለተኛው መለከት መነፋት

ቁጥር 8 እና 9 አንብብ፡፡ በእሳት የሚቃጠል ታላቅ ተራራን የሚመስል ነገር በባህር ተጣለ፡፡ ባህርም ደም ሆነ፤

1. የባህር 1/3ኛው ደም ሆነ፤ በባህር የሚኖሩ ፍጥረት፣ ሕይወት ካላቸው ሲሦው (1/3) ሞተ፡፡
2. የባህር መርከቦች 1/3ኛው (ሲሦ) ጠፋ (ሰመጠ)፡፡ ይህ ትልቅ ተራራ የሚያህል ከሰማይ የወደቀው ነገር ምንድን ነው?

መልሱ ምን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም። ግን ወደቀ ይላል እንጂ። በሁለተኛው መለከት መነፋት ምክንያት በፍጥረት ጊዜ ሁለተኛ ቀን የተፈጠረው በውኃ ያሉት ነበረ። አሁን በባህር ላይ ፍርድ ደረሰ፣ ዘፍጥ. 1:9–10። እንዴት ሆነ? መልሱ እንዲሁ ሆነ፤ በውኃ ውስጥ ያሉትን ፍጥረታት፣ በውኃው ላይ ያሉትንም መርከቦች ብናይና ብናስብ ቀላል ነገር አድርገን መቁጠር የለብንም። በዓለም ትልልቅ ጦርነት ጊዜ ብዙ መርከቦች በባህር ሰጥመዋል። ብዙ ነገርም ተበላሽቷል። ልክ እንደዚያ ይሆናል።

ቁ. 10–11 የሦስተኛው መለከት መነፋት

ቁጥር 10ን አንብብ። እግዚአብሔር በዮሐንስ በኩል ሲገልጽ ሦስተኛው መለከት ሲነፋ ትልቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ ይላል። የወደቀውም በወንዞችና በውኃ ምንጮች ላይ ነው ይላል።

ውኃው ምን ሆነ? የውኃው 1/3ኛ መራራ ሆነ፤ ማንም መጠጣት ካለበት መሞት ነበረበት። በዚህ ውኃ ምክንያት ብዙዎች ሞቱ።

ቁጥር 10 ተመልከቱ። እንደ ችቦ የሚቃጠል ኮከብ ከሰማይ ሲወድቅ ገና በአየር ላይ እያለ ተቃጥሎ ጹቄት በመሆን በውኃ ውስጥ ተበተነና መርዝ ሆኖ የሰዎችን 1/3ኛ አጠፋ። ያንን ነው ያየሁት ይላል ሐዋርያው ዮሐንስ።

በሁለተኛው መለከት ጊዜ ባህርና በባህር ውስጥ፣ በውጭም ያለው ሁሉም 1/3ኛው ተመትቶ ነበር። አሁንም በሦስተኛው መለከት መነፋት ምክንያት በወደቀው ኮከብ ምክንያት ውኃው ተመርዞ ተበከለ፣ 1/3ኛው ሕዝብ አለቀ።

ይኸንን በትንሹ የሚመስል ታሪክ ከዚህ በፊት በእሥራኤል ዘመን በምድረ በዳ ተደርጓል፣ ዘጸ. 15:22–26 ተመልከት።

ቁጥር 11 የወደቀው ኮከብ ስም እሬቶ ነበር። የምድረ በዳ ውኃ ማራ ነበረ፣ ሁለቱም መራራ ወይም መርዝ ማለት ነው። በዓለም ላይ ካለው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚመር ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ኃጢአት ነው።

መልሱ:–

1. በሙሴ ጊዜ ለመራራ ውኃ መድኃኒት ተገኝቶ ነበር፤ ያውም ዛፍ ነበር።

2. ለኃጢአትም መራራነት መድኃኒት ተገኝቷል። ያውም የኢየሱስ ሞት ነው።

3. በፍርድ ጊዜ ለሚወድቅና መራራ መርዝ ለሚሆን ኮከብ መድኃኒት የለም። ምክንያቱም የምሕረት ጊዜ አልፏል፤ የፍርድ ጊዜ ነው።

ስለዚህ መክብብ 12፡1 አንብብ።

ዛሬ ነው መድኃኒትስ መፈለግ
ዛሬ ካምላክህ ተገናኝ
ዛሬ ነው የምሕረት ጊዜ
ዛሬ ነው የንስሐ ቀን
ዛሬ ነው የመቀበል ቀን
ዛሬ ክርስቶስን ትቀበላለህን?

መራራነትህንና ኃጢአትህን ክርስቶስ አጠበው። የክርስቶስ ሞትና ደም ሕይወትህን ለእግዚአብሔር አጣፈጠው? ስለዚህ ዛሬ ወደ ጌታ ተመለስ።

ቁ. 12–13 የአራተኛው መለከት መነፋት

አራተኛው መለከት በተነፋ ጊዜ የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት ሲሦ (1/3) ሲመታ ለሐዋርያው ዮሐንስ እንደተገለጸ እናያለን።

የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት ሲሶ ይጨልማል፤ መጨለምም ብቻ ሳይሆን ቀን ያጥራል፤ ሌሊትም ያጥራል፤ እንዴት እንደሆነ ቀጥለን እናያለን። ከዚያ በፊት ግን ቁጥር 12ን እንደገና አንብብ። የአራተኛው መለከት መነፋት በፍጥረት ጊዜ በአራተኛው ቀን የተፈጠሩትን ነገሮች ሲመታ እንደሆነ እናስታውስ፣ ዘፍጥ. 1፡4–18 ተመልከቱ። እግዚአብሔር በሰማይ ያሉትን ብርሃን ሰጭዎችን ሲፈጥር ወይም ሲሰጠን ለሥራ፣ ለጉዳይና ለምክንያት ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር በሰማይ ጠፈር ብርሃን ይሁን ያለበት ምክንያት፡–

ቀንና ሌሊትን እንዲለይ፣ ለዕለት፣ ለዓመታትና ለዘመናት ምልክት እንዲሆን ነው፣ ዘፍ. ቁ 14።

12 ሰዓት ወደ 24 ሰዓት፣ 24 ሰዓት ወደ ቀን ወደ ሳምንትና ወር፣ አራት ሳምንት ወይም 30 ቀን ወደ ወር፣ 12 ወር ወደ አንድ ዓመት። 100 ዓመት ወደ ዘመን ይሄዳል። ይህን ሁሉ ሰው

እንዲጠቀምበት እግዚአብሔር ብርሃናትን በሰማይ ፈጠረ (አስቀመጠ)። ይህንንም በፍጥረት አራተኛ ቀን አደረገ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰውም ሆነ፤ ጠቅላላ ፍጥረታት በእነዚህ ብርሃናት ላይ ይደገፋሉ። ለምሳሌ መዝ. (104)፡19–24 ከዚህም በላይ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ወይም ብርሃን ባይኖር በምድር ላይ ምን ያድጋል? ሰውስ ይኖራልን? እፅዋትስ (ዛፍ) ይኖራሉን? ስለዚህ ለፍጥረት ሁሉ የሰማይ ብርሃናት አስፈላጊ ናቸው። ግን በአራተኛው መለከት 1/3ኛው ጨለመ። ኢየሱስም በሉቃስ 21፡25–26 ስለዚህ ተናግሯል። ሰው ግን ይህን የሠራውን (የፈጠረውን) እግዚአብሔርን በአመፃ ተወው፣ ረሳው፣ አላውቅም አለ።

ቁጥር 12ን ተመልከቱ። ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት በእግዚአብሔር ፍርድ 1/3ኛው ስለተመታ ምን ሆነ? ምን አስከተለ? ቀን አጠረ፣ ሌሊት አጠረ ይላል። ምን ማለት ነው? 24 ሰዓት ለአንድ ቀን እንዲሆን ያደረገው እግዚአብሔር አሁን 16 ሰዓት ቀን እንዲሆን አደረገ ማለት ነው። ይኸንን ሊያደርግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። በሰው በኩል አይቻልም። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር በፍጥረት ሁሉ ላይ ባለ ሥልጣንና ተቆጣጣሪ እንደሆነ ያሳያል። ቀን ስላጠረ ሰው ብቻ ሳይሆን ፍጥረት ሁሉ ይሰቃያል። እስቲ ከዚህ በፊት የተማርናቸውን እናስብ፤ ፍርድ፦ በዛፍ፣ በሣር፣ በባህር ውስጥ ያሉትን ሕይወት ያላቸውን ፍጥረታት፣ መርከቦችንና በንጹህ ውኃ ላይ፣ በሰማይ ፍጥረት ላይ። እነዚህ ችግሮች የመጡት የሰማይ መለከት በመነፋቱ ምክንያት ነው። መዝ. 19፡1–6 ስናይ የፍጥረታት ጌታ እግዚአብሔር ስለ ሆነ ሁሉን ሊያደርግ ይችላል። ማን ይከለክለዋል?

ቁጥር 13 ከዚህ በኋላ 3 የመለከት መነፋት ስለሚቀር ስሙ ወዮ ተብሎ 3 ወዮዎች ገና ይቀራል ተባለ።

ቁጥር 13 እናንብብ። ይህ ንስር የተባለው መልአክ መሆኑን እንርሳ። አህያ ያናገረው እግዚአብሔር ቢፈልግ ንስር (አሞራን) ሊያናግር አያቅተውም። (ዘኁልቁ 22)። ኢየሱስም የአሞራዎችን ምሳሌ የተናገረው በማቴዎስ 24፡28 እንመልከት። ቁም ነገሩ ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። ለእርሱ ይታዘዛሉ። እኛም ዛሬ እግዚአብሔርን እንታዘዝ፣ እንገዛለትም። እርሱ አምላካችን ነውና፣ መዝ. (95)፡1–6።

## የቀሩት ሦስቱ መለከቶች ወዮ ተባሉ፣ ራእይ 9

ሦስቱ ወዮዎች በምዕራፍ 9 ያሉት አደገኞች፣ አስፈሪዎችና አሰቃቂዎችም ናቸው:: የእግዚአብሔርን ፍቅርና ቁጣ ብናስተያይ ወይም ብናወዳድር በሰማይና በምድር ያሉትን ነገሮች ሁሉ እርሱን የሚበልጥ ነገር አናገኝም:: ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ናቸው:: ይህም ሁለቱ አስተያየቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድ ጥቅስ ብቻ ዮሐንስ 3:36 ተጠቃሎ ተጽፎ እናገኛለን ። ምርጫው እዚህ ላይ ተጽፏል:: ሕይወት ወይም ቁጣ:: ሰው ሁሉ ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ይችላል:: ሁለቱን አንዴ መምረጥ ግን አይቻልም::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 9

## አንደኛው ወዮ

ቁጥር 1፣2 የወደቀ፣ ወድቆ የነበረው ኮከብ ምንድን ነው? ፊት በተጻፈው ላይ ኮከቡ ከዚህ በፊት የወደቀ መሆኑ ተገልጿል:: ቃሉም ወድቆ የነበረ ይላል:: ደግሞ ያ ወድቆ የነበረውን ኮከብ ሥራ ልብ አድርጉና ተመልከቱ:: «የጥልቁ ጉድጓድ መክፈቻ ተሰጠው» ይህ ማለት መክፈቻ ማለት ሥልጣን ተሰጠው ማለት ነው:: ስለዚህ ይህ ኮከብ የተባለው እርግጠኛ የሰማይ ከዋክብት ውስጥ የሆነ ኮከብ አይደለም:: ለምሳሌ ራእይ 1:20 ላይ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ኮከብ ተብሎ የተሰጠ ስም ታያላችሁ:: እንዲህ ዓይነት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው:: ለምሳሌ ኳስ ተጫዋቾች(ቡድኖች) ኮከብ በማለት ይጠራሉ:: ግን ሰዎች ናቸው:: ስለዚህ ይህ በምዕራፍ 9 ላይ ኮከብ የተባለው ፊት ወድቆ የነበረውን ሰይጣንን ነው:: ይህ ኮከብ ሥልጣን ተሰጠው ይላል:: እንግዲህ ይህ የወደቀ ኮከብ ሰይጣን እንደሆነ የሚገልጹ ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን፣ ኢሳ. 14:12–25፤ ሉቃስ 10:18 ላይ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር «ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁት» አለ:: በ2ኛ ቆሮ. 11:14 እርሱ የብርሃን መልአክ ይመስላል፣ ራእይ 12:7–12 በመጨረሻ ሰይጣን ወደ ምድር እንደሚጣል አይጠራጠርም ይናገራልና::

# ጥልቁ ጉድጓድ 9:1-2

## የጥልቁ ጉድጓድ መክፈቻ

በእውነቱ የዚህ ቁልፍ ወይም መክፈቻ ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ራእይ 1:18:: ይህ ቁልፍ ለሐዋርያው ጴጥሮስ ኢየሱስ እሰጥሃለሁ ካለው ከመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ ማቴዎስ 16:19 የተለየ ተቃራኒ የሆነ ነው::

- ሰይጣን የተሰጠው የጥልቁ መክፈቻ ነው::
- ለጴጥሮስና ለክርስቲያኖች የተሰጠው መክፈቻ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ነው::

የሰይጣን ሥልጣን ጊዜያዊ ነው:: የተሰጠውም ቁልፍ (ሥልጣን) ለአጭር ጊዜ ነው:: ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ይገባና (ይጣልና) ይታሠራል፣(ራእይ 20:3):: ሙሉና ዘላለማዊ ሥልጣን ያለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፣ ማቴ. 28:18፤ ራእይ 1:18::

## ይህ የጥልቁ ጉድጓድ ምንድን ነው?

ጥልቅ ሲል ጉድጓዱ እስከ መጨረሻ የተቀደደ ነው:: በጣም ሩቅ ወደ ታች ጥልቅ ነው:: ለሥሩ መጨረሻ የለውም ማለት ነው:: ጥልቅ ነው፣ ቁጥር 1 ተመልከት::

## ይህ ጥልቅ ጉድጓድ የት ነው?

መልሱ ወደ ታች መሬት ውስጥ እንጂ ወደ ላይ በሰማይ አይደለም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ይህ ጥልቅ ጉድጓድ በመሬት ሆድ ውስጥ በአንድ ስፍራ ተዘግቶ ተቆልፎ ያለው ነው:: ቁጥር 10 ከፈተው ይላል:: ከፈተው ሲል የተቆለፈ ነበር ማለት ነው:: ጥልቁ የአጋንንትና የጋኔን የሰይጣን ጭፍራዎች መድረሻ የስቃይ ቦታ ነው፣ ሉቃስ 8:28-30:: ጥልቅ የሚለው ቃል በዮሐንስ ራእይ ሰባት ጊዜ ሲገኝ በሌላው የአዲስ ኪዳን ክፍል ደግሞ ሁለት ጊዜ ይገኛል:: ይህ ጥልቅ ጉድጓድ የተባለው ቦታ በብሉይ ኪዳን ሲኦል የሚባል ሲሆን ተቃራኒው ደግሞ ገነት ነው:: በአዲስ ኪዳን ደግሞ የሥቃይ ስፍራ ነው፣ ሉቃስ 16:19-31:: ወይም ገሃነም ይባላል፣ ማር. 9:43-48:: በብሉይ ኪዳን ዘመን ይህ ሲኦል የክፉዎች ነፍስ የሚደርስበት፣ ክፉዎች የሚጣሉበት ቦታነው፣ ሉቃስ 16:23:: በሉቃስ 16:19-31 ብናነብ በሲኦል ሁለት ክፍል እንዳለ እንመለከታለን::

1. ባለጠጋው ዓይኑን አንሳና አብርሃምን ከሩቅ አየ:: አልዓዛርንም በእቅፉ ያጽናና ነበር::
2. ባለጠጋው በሲዖል በስቃይ በእሳት ነበልባል ነበረ:: ክርስቶስም ሞቶ እስከተነሳ ድረስ በዚህ ሁኔታ ነው ነፍሳት የሚኖሩት:: ክርስቶስ ከመቃብር ሲነሳ ግን ታሪክ ተለውጧል፣ ሌላ ሆኗል::

በኤፌሶን 4:8–9 እንደምንመለከት ክርስቶስ በአብርሃም እቅፍ በመጽናናት ያሉትን ይዞ ወጣ:: ከዚያን ጊዜ አንስቶ የአማኞች ነፍስ ሥፍራ በመንግሥተ ሰማያት ሆነ፣2 ቆሮ. 5:1–8፤ ፊልጵ. 1:23፤ 3:1–3:: አሁን ጥልቁ ጉድጓድ ምን እንደሆነ እናውቃለን ተገልጾልናል::

ጥልቁ ጉድጓድ 9:1 ሲአል ነው፤ ቁልፉ (መክፈቻው) ለማን ተሰጠ? ለሰይጣን:: ቁልፉን የሰጠው ባለ ሥልጣን፣ ክርስቶስ ነው:: ቁልፉን ተቀባይ ጊዜያዊው ባለ ሥልጣን ሰይጣን በኋላ ራሱ ወደ ጥልቅ እንደሚወርድ አውቀናል::

## ቁ. 3–5 አንበጣዎች

ቁጥር 3–5 እነዚህን ዓይነት አንበጣዎች ቀደም ሲል በመጽሐፍ ቅዱስ ከተነጋገርንባቸው አንበጣዎች የተለዩ መሆናቸውን መረዳት አለብን:: ለምሳሌ ዘጸ. 10:14–15 ተመልከቱ:: በዚህ ቦታ በግብጻውያን ላይ የወደቀውን መቅሰፍት ወይም ፍርድ እንመለከታለን:: በግብጽ አገር የተጣለው አንበጣ ከዚያ በፊትም ከዚያ በኋላም የእርሱን ዓይነት አይሆንም አልነበረምም ተባለ፣ ዘጸ. 10:14–16:: በዚህ ሁኔታ በዮሐንስ ራእይ 9 የተገለጸው አንበጣ እኛ ከምናውቀው አንበጣ ጋር አንድ ዓይነት አይደለም:: ልዩ አንበጣ ነው:: የምናውቀው አንበጣ እንዳልሆነ 8 ዓይነት ገለጻ በዚሁ መጽሐፍ ስለ አለ ለማየት እንችላለን:: ራእይ 9:7–11::

## የአንበጣዎች መልክ

1. ለጦርነት እንደ ተዘጋጁ ፈረሶች ናቸው::
2. በራሳቸው ላይ ወረቅ የሚመስሉ አክሊሎች አሏቸው::
3. ፊታቸው እንደ ሰው ፊት ነበር::
4. ጸጉራቸው የሴቶች ጸጉር ይመስላል::
5. ጥርሳቸው እንደ አንበሳ ጥርስ ነው::

6. የብረት ጥሩር የሚመስል ጥሩር ነበራቸው::

7. የክንፋቸው ድምጽ ወደ ጦርነት የሚጋልቡ ብዙ የፈረስ ሰረገሎች
8. እንደ ጊንጥ ጅራት ያለ ጅራት መውጊያ ያለው::

ለአምስት ወር ሰዎችን ሊያሰቃዩ ሥልጣን ተሰጣቸው:: በእነርሱም ንጉሥ አለቃ አላቸው፣ ቁ. 11:: አለቃቸውም በእብራይስጥ አብዶን፣ በግሪክ አጳልዩን ይባላል:: ትርጉሙ የጥልቅ መልአክ ማለት ነው::

ስለዚህ እነዚህ አንበጣዎች የተባሉት ምን ይሆኑ?

መልሱ አጋንንት፣ ጋኔን፣ ርኩስ መንፈስ፣ የሰይጣን ጭፍራዎች ናቸው:: እንዴት የአንበጣ መልክ ሆኑ? መልሱ የርኩስ መንፈስ ወይም ሰይጣን የራሱ የሚታይ መልክ ወይም ቅርጽ ስለሌለው የሚፈልገውን ነገር፣ መልክ ይዞ፣ ወይም ለብሶ ይታያል ይመጣል::

ለምሳሌ:–

1. ዘፍጥ. 3:1 የእባብን መልክ ይዞ ወደ ሄዋን መጣ::
2. 2ኛ ቆሮ. 11:14 የመልአክን መልክ ሊለብስ ራሱን ይለውጣል::
3. ሉቃስ 8:27 በሰው አድሮ እንደነበረ ይታያል::
4. ሉቃስ 8:32–33 በእርያዎች ገቡ::

በዚህ ምክንያት በልዩ ልዩ ፍጥረቶች በመግባት መልኩን ሊለዋውጥ ይሞክራል:: ክርስቲያን መጠንቀቅ አለበት:: ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በቃሉና በመንፈሱ ካልተሞሉ በስተቀር በምንም ጊዜ፣ ሰዓትና ቦታ በሰይጣን ሠራዊት ሊለከፉና ሊያዙ ይችላሉ:: የሰይጣንን ኃይል የሚያፈርስ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፣ 1 ዮሐ. 3:8::

ወዮ የሰው ልጅ መከራና ሥቃይ፣ ራእይ 9:3–6
እነዚያ አንበጣዎች ሥቃይ የሚያደርሱት ቁጥር 4 በሰዎች ብቻ እንጂ ሌላውን ፍጥረት አይነኩም:: ለምሳሌ፣ ዛፍና ሣር ሌሎች ነገሮችን አይጎዱም:: ሰዎችንም ቢሆን የእግዚአብሔር ማኅተም በግምባራቸው የሌለባቸውን እንዲያሰቃዩ ነው::

ቁ. 5 የሥቃዩ ጊዜ አምስት ወር፣ የሥቃዩ ዓይነት ጊንጥ ሰውን በነደፈ ጊዜ እንደሚያሰቃየው ዓይነት ነው:: ይህን ዓይነት ሥቃይ የሚያውቅ በጊንጥ የተነደፈ ሰው ብቻ ነው::

ቁ. 5 ሥልጣን ተሰጣቸው ይላል:: ለእነዚህ አንበጣዎች ምንም ሥልጣን የላቸውም:: ሥልጣን ያለው በሰጭው ብቻ ነው:: ያውም

እግዚአብሔር ነው:: እዮብ ምዕራፍ 1 እና 2 ስንመለከት የሰይጣን ሥልጣንና ኃይል የተወሰነ፣ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነበር:: ስለዚህ ኃይል ሁሉ ባለው፣ ሥልጣን ሁሉ ባለው በእግዚአብሔር ማመናችን አያስደስተንምን? ተስፋችንን ጽኑ አያደርግምን? ያደርጋል እንጂ::

ቁ. 6 የአንበጣዎች ማሰቃየት ስለሚበዛባቸው ሰዎች ሞትን ፈልገው ይታነቃሉ:: ራሳቸውን ለመግደል ልዩ ልዩ ነገር ያደርጋሉ:: ግን ሞት እምቢ ይላል፤ ሞት ይሸሻል:: ይሁን እንጂ ሰውም ንስሐ አይገባም፤ ራእይ 9:20–21:: በኃጢአቱ አያዝንም፣ እንዲያውም እግዚብሔርን ይሳደባል:: ሰው እግዚአብሔርን ያመሰግናልን? ሰው <u>በችግር</u> ጊዜ እግዚአብሔርን ያመሰግናልን? ሰው በከባድ ሕመም ጊዜ እግዚአብሔርን ያመሰግናልን?

ሰው ሲሞት እግዚአብሔርን ያመሰግናልን? ሁለት ዓይነት አሟሟት አለ፣ ሉቃስ 23:32፣39–43:: ለምሳሌ ሁለት ክፉ አድራጊ ሽፍቶችን ተመልከት::

1ኛው አምኖ ከጌታ ጋር ታርቆ ሞተ::

2ኛው ጌታን ሲሳደብ ሞተ፤ አንተስ? በምን ዓይነት ሞት ልትሞት ነው?

ምንባብ የዮሐንስ ራእይ 9:13–19

<u>ሁለተኛው ወዮ</u>

ቁ. 12 አንደኛ ወዮ አልፏል፤ ገና ሁለት ወዮ ይመጣልና ወዮላችሁ ይላል፣ ቁ. 13–16::

ምዕ. 8:13 እናስብ፣ ምን ይላል? 1ኛ ወዮ በሰይጣን ሠራዊት ተለክፎ መሰቃየት ነበር:: አምስተኛው መለከት ሲነፋ በአንበጣ ዓይነቶች መሰቃየት ነበር:: 2ኛው ወዮ የከፋ ነው:: ያውም ከሰው ፍጥረት ልዩ ከሆነ ሠራዊት ጋር መዋጋት ነው:: መሠቃየት ነው:: ስድስተኛው መለከት ሲነፋ ድምጽ ከዙፋኑ ፊት ካለው መሠዊያ ቀንዶች ነው የመጣ:: ይህ መሠዊያ በእግዚአብሔር ፊት ከዙፋኑ ነበር::

ይህ መሠዊያ የጸሎት ቦታ ነው፤ ምዕ. 8:3:: ጸሎታችን የሚደርስበት ቦታ ነው:: መሠዊያው ለኃጢአታችን የተሠዋውን ክርስቶስን ያሳስባል::

ራእይ 9 ቁ. 13–14 አንብብ፤ ድምጽ፣ ትዕዛዝ ከመሠዊያ ቀንዶች ወጣ:: ምን የሚል? በኤፍራጥስ ወንዝ የታሠሩትን አራቱን መላእክት ፍታቸው የሚል::

<u>የሚፈታ ማነው</u>? 6ኛውን መለከት በእጁ የያዘው መልአክ ነው::

ትዕዛዝ የሚሰጥ ማነው? የተሠዋው ክርስቶስ ነው::

<u>ለምን ይፈታሉ</u>? ቁጥር 15ን አንብብ::

1. ወዮ ከጉድጓድ የወጡ አንበጣ መሳዮች በግምባራቸው የእግዚአብሔር ማኅተም የሌለባቸው ሰዎችን ሊያሰቃዩ ነው እንጂ ሊገድሉ አልተፈቀደላቸውም፣ 9:5፤ 6::
2. ወዮ የሰዎችን ሲሦ እንዲገድሉ ተፈቀደላቸው፣ ዕብ. 2:3::

## እነዚህ አራቱ መላእክት እነማን ናቸው?

ክፉ የሆኑ የሰይጣን መላእክት ናቸው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ስላልተነገረ ስማቸውንም ማንም አያውቅም:: ለምን እንደታሠሩም አይናገርም:: መታሠራቸውን እንጂ:: ርኩስ መላእክት ግማሹ እንደታሠሩ ራእይ 9:14 ይገልጻል::

ግማሹ በድቅድቅ ጨለማ የተጠበቁ፣ የሚንከራተቱ ኮከብ ናቸው ይላል፣ ይሁዳ ቁጥር 13::

### ኤፍራጥስና አካባቢው

9:14 ተመልከቱ:: ለምን በዚህ በተለይም በኤፍራጥስ አካባቢ እነዚህ መላእክት ታሠሩ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: መልሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ስለሚገኝ አንቸገርም:: የመጽሐፍ ቅዱስ ጂኦግራፊና የዓለም ጂኦግራፊ አንድ ስለሆነ፣ ነገሩን በሰፊው ልንመረምር እንችላለን:: ስንመረምርም የአካባቢው ጂኦግራፊና ታሪክ እንዲሁም የዓለም ታሪክ አንድ ሆኖ ይገኛል:: ስለ ኤፍራጥስና አካባቢው መጽሐፍ ቅዱስ ደህና አድርጐ ይገልጻል::

ለምሳሌ:–

1. ዘፍጥረት 2:8፣10–15 ኤደን ገነት የተተከለው በዚያ ነበረ::
2. ዘፍጥ. 3:6–7 ሔዋን ፍሬውን የበላችበት በዚያ አካባቢ ነበረ::
3. የመጀመሪያው ነፍስ ገዳይነት የተጀመረው በዚያ አካባቢ ነው፣ ዘፍጥ. 4:8:: ቃየን አቤልን ገደለ::

4. የመጀመሪያው ንጉሥ በሰዎች ላይ መግዛት የጀመረበትና ልዩ የባዕድ አምልኮ የጀመረው በዚያ ነበር፣ዘፍ.10:8–11::

5. የሰው ልጅ ቋንቋ የተደባለቀበትና ሰዎች ስማቸውን ለማስጠራት የባቢሎንን ግንብ የሠሩበት፣ ዘፍጥ. 11:1–9:: በኋላም ያ ቦታ የባቢሎን መንግሥት ግዛት ከተማ የሆነበት አካባቢ ነበር::

6. የእስራኤላውያን አባት የሆነው አብርሃም ተወልዶ የወጣበት አካባቢ ነው፣ ዘፍጥ. 11:32–33፤ ኢያሱ 24:2::

7. ናቡከደነፆር እስራኤላውያንን ለባርነት ለ70 ዓመታት ማርኩ የወሰደበትና የገዛበት፣ ኤር. 25:12::

8. የኤፍራጥስ አካባቢ የባዕድ አምልኮ የተጀመረበት ነው::

ስለዚህ በኤፍራጥስ አካባቢ የሆነው ሁኔታ ለዓለም በሞላ ችግር መነሻ ወይም የኃጢአት ምንጭ የሆነበት ስለሆነ፣ እግዚአብሔር አካባቢውን ባቢሎን ብሎ ኃጢአቷን የሚፈርድበት ዘመን እንደሚመጣ በዮሐንስ ራእይ 17 እና 18 በግልጽ ተጽፎ ይገኛል::

ስለዚህ በራእይ 9:14–15 የሚገኘው ክፉ የሰይጣን መላእክቶች (4ቱ) የታሠሩበት በእንደዚህ ባለው አካባቢ ነው::

ቁ. 15 እነዚህ ክፉ መላእክት ሊፈቱ የሚጠባበቁ ለሰዓቱ፣ ለቀኑ፣ ለወሩና ለዓመቱ ነው:: በማንኛውም ጊዜ ሊፈቱና መከራ ሊያመጡ የተዘጋጁ ናቸው፣ ይሁዳ 6–7:: በኋላ ሰይጣን ራሱም ለሺህ ዓመት ይታሠራል፣ ራእይ 20:2–3::

## ታላቅ ጭፍራ

## የዮሐንስ ራእይ 9:16–19

እዚህ ላይ የሚናገረው የጭፍራዎችና የፈረሰኞች ቁጥር 200 ሚሊዮን መሆኑን ነው:: ይህ ጭፍራ (ሠራዊት) ከሰው የተለዩ ልዩ ፍጥረቶች ናቸው::

ከሰው የተለዩ ልዩ ፍጥረቶች (ልዩ) ሠራዊት ሁለት ዓይነት አሉ፣

1. የእግዚአብሔር አገልጋዮች (ሠራዊት) ናቸው::

2. የሰይጣን አገልጋዮች (ሠራዊት) ናቸው::

ይህ ሠራዊት (ጭፍራ) ሰው ሊቆጣጠረው ከሚችለው ኃይል በላይ ኃይል አላቸው:: ራእይ 9:17–19::

ይህ የሰይጣን ሠራዊት ከሰው ፍጥረት ልዩ ፍጥረት ነው፤ ፈረሶችና የተቀመጡባቸው አሉአቸው::

1. እሳት:– ቀይ መልክ
2. ያክንት:– ሰማያዊ መልክ
3. ዲን:– ቢጫ የሆነ ኃይልና መልክ አላቸው

በአፋቸውና በጅራታቸው ያለውን እዩ:: ቁጥር 19:: በዮሐንስ ራእይ 9:17–19 ያሉት ልዩ ፍጡራን ከታሠሩት ከ4ቱ መላእክት ተከታትለው የሚወጡ ሲሆኑ የፈረሶችና የእሳት መልክ አላቸው:: እንዲሁም የእግዚአብሔር ቅዱሳን የሆኑ ከሰው የተለዩ ልዩ ፍጡራን ደግሞ አሉ:: (2ኛ ነገሥት 6:8–19):: እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? ሮሜ 8:31:: እግዚአብሔር በእኛ በኩል ስለሆነ በምንም አንፈራም፣ ኢሳ. 41:10::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 10

## ብርቱ መልአክና ታናሽ መጽሐፍ፤ 10፡1–11

ብርቱ ማለት ጠንካራ፣ ኃይለኛ ማለት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ብርቱ መልአክ የሚል ቃል እናገኛለን:: ቁጥር 1ን ተመልከት:: ይህ ብርቱ መልአክ ምናልባትም በምዕራፍ 5፡2 ላይ የተገለጸና መጽሐፉን ሊከፍትና ማኅተሙን ሊፈታ ማን ይችላል? ያለው ወይም በምዕራፍ 8፡3 በመሠዊያው አጠገብ ዕጣን ይዞ ይናገር የነበረው ሳይሆን አይቀርም:: ለምሳሌ በዘፍጥረት 18 ላይ ያለው፣ ዘፍጥረት 21፡17–20፤ ዘጸአት 3 ላይ ያለው፣ ኢያሱ 5፡13–15 ያለውን የሚመስል ክርስቶስ ሥጋ ሳይለብስ ለሕዝብ ይገለጽ እንደነበረ የታወቀ ቢሆንም በዮሐንስ ራእይ 10፡1 ያለው ኢየሱስ አለመሆኑን እናውቃለን:: ምክንያቱም፡–

1. ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ወደ ምድር መጥቶ በመስቀል ላይ ሞቶ ከተነሣ በኋላ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል፣ የሐ.ሥራ 7፡55–56:: እንዲሁም ለሳውልም የሐዋርያት ሥራ 9፡3–5 በክብር ቦታ ተቀምጦ ታየው እንጂ ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን እንደ መልአክ የሚታይበትን አናገኝም:: በዮሐንስ ራእይ 19፡11–21 ከዚያም በኋላ በምድር የሚታይበት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ብርቱ የሆኑ የእርሱ መልአኮች መልእክቱን ይፈጽሙታል እንጂ ክርስቶስን መልአክ ነው ለማለት አንችልም::

በዮሐንስ ራእይ 5፡2 ያለው ብርቱ መልአክ ሲናገር ማነው የሚገባው?

ማኅተሙን ሊፈታ፣ መጽሐፉን ሊከፍት የሚችል ማን ነው? የሚል ነበር:: መልሱ የታረደው በግ ነበር::

### ቁ.1 <u>ደመና ተጎናጽፎ</u>

ይህ ብርቱ መልአክ ደመና ተጎናጽፎ ነበር:: ደመና መጎናጸፍ ለኢየሱስና ለመላእክት የሚነገር ቃል ነው:: <u>ኢየሱስ</u> ከትንሣኤ በኋላ የሐዋ. ሥራ 1፡9፤ ማቴ. 24፡30 የክርስቶስን በደመና መምጣት ሲናገሩ፣ <u>መላእክትም</u> በደመና 1ኛ ተሰሎ. 4፡16፤ የሐዋ. ሥራ 1፡10–11፤ ማቴ. 4፡31 ይናገራል::

ቁጥር 1 በራሱ ላይ ቀስተ ደመና ነበር

ቀስተ ደመናን እግዚአብሔር በጥንት አባቶቻችን ዘመን (በኖኅ ዘመን) ለቃል ኪዳን (ለመሐላ) ቀስተ ደመናን አስቀመጠው፣ ዘፍ. 9:11–13:: ቀስተ ደመና የእግዚአብሔረን ምህረት ያሳያል:: እግዚአብሔር በፍርድ ዘመንም ቢሆን ወደ እርሱ ለሚመጡ ምህረትን እንደሚያሳይ ያመለክታል፣ ዮሐ. 6:37::

ፊቱ እንደ ፀሐይ ያበራል:: የማን ፊት ያበራል?

1. የኢየሱስ ፊት፣ ራእይ 1:16፤ ማቴ. 17:2::
2. የመላእክት፣ ራእይ 10:1፤ 18:1::
3. የእግዚአብሔር ሰዎች፤ ለምሳሌ ሙሴ፣ ዘጸ. 34:29:: የእኛም ማቴ. 13:43::

መልአኩ ይህ ብርቱ መልአክ እግሮቹ የጋለ ብረት ይመስላል ይላል፣ ራእይ 10:1:: የፍርድ ምሳሌ ነው:: የጋለ አምድ የፍርድ መላእክት እንዳሉ ያሳያል:: ይህ ብርቱ መልአክ ጌታችን እንዳልሆነ በቁጥር 5 ና 6 ተመልከቱ:: ለዘላለም በሚኖር ይምላል:: ኢየሱስ አይምልም:: ይህ መልአክ ግን በፈጣሪ አምላክ ስም ይምላል::

ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው፤ ቢምልም በራሱ ስም ይምላል እንጂ በሌላ አይምልም፣ ዕብ. 6:13ን ተመልከቱ::

## የተከፈተች ታናሽ መጽሐፍ

ቁጥር 2 በዮሐንስ ራእይ 10 የሚታየው ይህ ብርቱ መልአክ በእጁ የተከፈተችውን ትንሽ መጽሐፍ ይዞ ነበር:: ይህ ብርቱ መልአክ ያችን የተከፈተችውን መጽሐፍ ይዞ መምጣቱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር፣ ማንነቱን አምላክነቱንና ኃያልነቱን በምድር ላይ ያለውን ሥልጣኑን ለመግለጽ ነው:: ይህች ትንሿ የተከፈተች መጽሐፍ በምዕራፍ 5 በሰባት ማኅተም ተዘግታ ማንም ሊከፍት ያልቻለበት መጽሐፍ ሳትሆን አትቀርም፣ 5:1 እና 2:: በምዕራፍ 5 ያች መጽሐፍ እንደ ተከፈተች አይተናል:: ያቺ መጽሐፍ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ እጅ ላይ ነበረች:: ያቺ መጽሐፍ የዓለምን አዳኝነቱንና የክርስቶስን መንግሥት በምድር ላይ የሚገልጽ ነበር:: ማኅተሙን ለመፍታትና መጽሐፉን ለመክፈት የተገባው ኢየሱስ ብቻ ነው፣5:5–7::

በምዕራፍ 6 የመጽሐፉ አንደኛ ማኅተም መከፈቱንና ፍርድ መጀመሩን ያሳያል። በምዕራፍ 8 የመጨረሻው ማኅተም መከፈት በሰማይ ታላቅ ጸጥታ እንደሆነ አይተናል።

ከዚያም 7 መለከትን በም<sup></sup>ዕ. 10 ይህ ብርቱ መልአክ ያቺን ማኅተሙ ተፈቶ የተከፈተችውን መጽሐፍ ይዞ የመጣ ይመስላል። ይህች መጽሐፍ የኢየሱስን ሥልጣንና ፍርድ በምድር ላይ እንዴት እንደሚሆን ይገልጻል።

ባህርና ምድር የእግዚአብሔር መሆኑን ይገልጻል

ቁ. 2ለ እና 3 አንብብ።

ኢየሱስ የባህርና የምድር ባለ ሥልጣን ነው። ይህ ብርቱ መልአክ የኢየሱስን ሥልጣን ሊገልጥ መምጣቱን አንርሳ። ባህርና ምድር የእርሱ ናቸው፣ መዝ. (95)፡3–5።

በእርግጥ ባህርና ምድር የምን ምሳሌ ነው?

1. ባህር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ የሕዝብ (የሰዎች) ምሳሌ ነው፣ ራእይ 17፡15።

2. ምድር የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እሥራኤልን ነው።
   • እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች ስለ ምድሪቱ ሙሉ ተስፋ ይሰጣቸዋል። እነርሱ ምድር የተሰጣቸው ሕዝብ ይባላሉ። እግዚአብሔር ምድር ይሰጣቸው ዘንድ ተስፋ፣ ቃል ኪዳን የገባላቸው ሕዝብ ናቸው፣ ኢያሱ 1፡3፤ ዘፍ. 12፡7፤ 15፡7፤17፡8፤ 28፡13–14፤ 35፡11–12። ምድር ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። ይህ ብርቱ መልአክ ወርዶ ራእይ 10፡3 አንድ እግሩን በባህር ላይ፣ ሌላውን እግር በምድር ላይ አድርጎ ይጮህ ነበረ። በቃል ምዕራፍ 10፡3–4 <u>ይህ ውኃ</u> ደግሞ <u>ይህ ምድር</u> የእግዚአብሔር መሆኑን ያበስር ነበረ። ቁጥር 5ና6 ተመልከት።

ሕዝብ ቢሆንም ወይም እሥራኤል ቢሆን አምላካቸው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ለሁሉም ማለት ለሕዝበ እሥራኤል ለባህር ወይም ለምድር ታላቅ አምላክና ባለ መብቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ በሰባተኛው መለከት እንደሚሆን ሊገልጽ ነው፣ ቁጥር 11፡15 ተመልከት።

ቁ. 3 ና 4 የመልአኩ ጩኸትና 7ቱ ነጎድጓድ በየድምጻቸው መናገር። በ7ቱ ነጎድጓድ የተነገረውን ዮሐንስ እንዳይጽፍ ተከልክሏል። ነገሩ

ምን እንደሆነ፣ ድምጻቸው እንዴትና ምን እንደነበረ ለማወቅ አንችልም። ምክንያቱም እንዳይጽፍ ተከልክሎ ተዘግቷል። በኋላ ግን በዮሐንስ ራእይ 22:10 ተዘግቶ የነበረው ተፈትቷል። ነገሩ የኢየሱስ አዳኝነትና የዓለም ፍርድ ጉዳይ ነበረ ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ምሥጢር፣ ራእይ 10:7

በዚህ ቁጥር ብርቱው መልአክ በአንድ እግሩ ባህሩን፣ በሌላ እግሩ ምድርን ረግጦ የተከፈተችውን ታናሽ መጽሐፍ ይዞ፣ በታላቅ ቃል ሲጮህ እንዲህ አለ፣

ቁ. 7 መልካም ወሬ ማስታወቂያ የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል አለ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ምሥጢር የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን።

1. የእግዚአብሔር ምስጢር አንዱ ክርስቶስ ነው፣ ቆላ. 1:26–27። ይህ ምሥጢር ለአይሁዶች ተሰውሮባቸዋል፣ ሮሜ 11:25።
2. የአመጽ ምሥጢርም አለ፣ 2ኛ ተሰሎ. 2:7። የሰይጣን ተንኰል ክፉ ሥራም ምሥጢር ነው።
3. የዓለምና የዘመናት፣ የዓለም አገዛዝ ምሥጢር ለዳንኤል የተገለጸው፣ ዳን. 2:19፤ 27–28።
4. የወንጌል ምሥጢር የተሰበከ ምሥራች፣ ራእይ 10:7 የወንጌል አሠራር ስብከቱ፣ ትምህርቱ፣ ትንቢቱ፣ ሮሜ 16:25–26፤ ኤፌ.1:9፤ ምዕ. 3፤ 6:19፤ ቆላ. 4:1–4፤ 1ኛ ጢሞ. 3:16። ይህ ወንጌል ለዓለም ሞኝነት ነው። ለሚያምኑት ግን የሚያድን ኃይል አለው፣ 1 ቆሮ. 1:18፤ 21። ይህ ምሥጢር ከአንደኛው ምሥጢር ጋር ተመሳሳይ ነው።
5. ለታላቂቷ ባቢሎን የሚሰጥ ስም ነው፣ ራእይ 17:5።
6. ያንቀላፉት ይነሳሉ፣ ሌላ ምሥጢር ነው፣ 1 ቆሮ. 15:51–52።
7. የእግዚአብሔር ጥበብ፣ 1ኛ ቆሮ. 2:7፤ ምዕ. 1 ምሥጢር ነው።
8. የጋብቻ ምሥጢር በባልና ሚስት መካከል፣ ኤፌ. 5:32 ምሥጢር ነው።
9. አብያተ ክርስቲያናት መልእክታቸው፣ ራእይ 1:20 ምሥጢር ነው።

የእግዚአብሔር ምሥጢር ለዓለም ተገልጦ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ይሰበካል። በዮሐንስ ራእይ ጊዜና ዘመን በእግዚአብሔር ፕሮግራም (ዕቅድ) ይህ ምሥጢር ይፈጸማል፣ ያበቃል፣ ይቆማል፣ ይቀራል፣ ይደረጋል። ልክ እንደተናገረው ቃል ይሆናል። ዛሬ የሚናገረው ቃል ፍጻሜ ያገኛል ብላችሁ ታምናላችሁ? አዎን ቃሉ ትንቢቱ ፍጻሜ ያገኛል፣ ይፈጸማል ይላል እግዚአብሔር።

ቁ. 8–9 ውሰድና ብላ

ሐዋርያው ዮሐንስ ቁጥር 8 ላይ አንድ ያልተለመደ ነገር ይናገራል። ድምጽ ሰማሁ ይላል። ከሰማይ ድምጽ ሰማሁ፤ እንደገና ድምጽ ሰማሁ ይላል። የተከፈተችውን ታናሽ መጽሐፍ ውሰድና ብላ የሚል፤ (ቁጥር 8 እና 9)።

ዮሐንስ ከሰማይ የሰማው ድምጽ የማን ይሆን?

ቁ. 8 ከዚህ በፊት የተነገረ ድምጽ ነው። ከዚህ በፊት መቼ?

በምዕ. 1:10 በስተኋላዬ ትልቅ ድምጽ በምዕ. 4:1 ፊተኛው ድምጽ ወደዚህ ውጣ የሚል።

ይህ ድምጽ የኢየሱስ ድምጽ ነበር፤ በምዕራፍ 10:9 ላይ መጽሐፉን ውሰድና ብላ የሚል የፊተኛው ድምጽ ነበር። ሐዋርያው ዮሐንስ ይህን ዓይነት ድምጽ ከሰማይ በታች አልሰማም። ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ ይህን ዓይነት ድምጽ ሰምቶ ነበር። ለምሳሌ ያህል ስለ መብል ኢየሱስ ተናግሯል፣ ዮሐ. 6:51። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፣ ዮሐ. 6:54–55። ይህ ቃል ወይም ኢየሱስ የተናገረው ንግግር ለሐዋርያቶች አዲስ ነገር፣ እንግዳ ትምህርት ነበር። አልገባቸውም፣ ዮሐ. 6:63። ሲጠይቁት መልስ ሰጣቸው። ምን ማለቱ ነው? ኢየሱስ እንዲህ ማለቱ ነበር፦ እኔ የምናገረው ስለ ሥጋዊ ወይም ስለ ሥጋና ደም አይደለም፤ ስለ ቃሌ ነው እንጂ። የክርስቶስን ቃል እንደ ምግብ መውሰድ እንዳለብን ነው የተናገረው ወይም የሚናገረው። የኔ ቃል መንፈስና ሕይወት ነው ይላል። ቃሉን ወስደን ለራሳችን እንድናደርግ ነው፣ ዮሐ. 6:63። ነብዩ ኤርምያስ፣ በኤር. 15:16 ልክ እንደዚሁ ቃሉን በልቼ ለልቤ ሐሴትና ደስታ ሆነልኝ ይላል።

ነብዩ ኤርምያስ መጽሐፉን በልቷል ሳይሆን ቃሉን ለራሱ አድርጓል ማለት ነው። እኛስ? የምንሰማውና የምናነበው ቃል በሕይወታችን ይሠራልን? ዳዊት በመዝ. (119)፡103–104 ቃሉ ከሐሰት መንገድ ለየኝ ይላል። ዮሐንስም መጽሐፉን በላና አስፈላጊ ነገር ለሕይወት እንዲያደርግ ፈቅዷል። እኛስ? ብላ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ የተደጋገመ ነው፣ ሕዝ. 3፡1–3፤ ኢያሱ 1፡8–9፤ መዝ. 1፡2–3፤ መዝ. (119)፡105።

## ጣፋጭና መራራ

ብዙ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት ያጠናሉ። ይህን የትንቢት ቃል ባጠኑት መሠረትና ባጠኑት መጠን በሕይወታቸው ሥራ መሥራት ይጀምራል። ሕይወታቸውን ወደ ክርስቶስ እንዲመልሱ ያስገድዳቸዋል። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በቃሉ አማካኝነት ስለሚሠራ ነው። ዮሐ. 16፡7–11 መንፈስ ቅዱስ በኃጢአታቸው ንስሐ ስላልገቡ ስለሚከሳቸው ይተዉታል። ስለ ትንቢት ያላቸው ፍላጐት፣ ስሜትና ጣፋጭነት ይጠፋል፣ መራራም ይሆንባቸዋል።

## ጣፋጭ ክፍል

ስለ ኢየሱስ ዳግም መመለስ ማንበብ ለክርስቲያን ጣፋጭ ነው። በክርስቶስ የሚገኝ የደህንነት ክፍል አርኪ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ተመልሶ ሺህ ዓመት ሲነግሥ በምድር ላይ ሠላም ሲሰፍን፣ ጦርነት፣ ረሐብ አመጽ፣ በሽታ፣ ሞት፣ ቢጠፋ ምን ያህል ደስ የሚያሰኝና መልካምም ነው?

ሰዎች በወንጌል አማካኝነት ከኃጢአት ሲድኑ፣ ከአጋንንት ሲላቀቁ የደስታ ሁሉ ቁንጮ ነው።

የዘላለም ሕይወት የመኖር ተስፋ
የመንግሥተ ሰማያት ቁንጅና
የእግዚአብሔር ዙፋን
የዘለዓለም እረፍት
የመላእክት አገልግሎት ሁሉ ጣፋጭ ነው።

ጌታን በእምነት ተቀብለን ነፍሳችን የሚያርፈው እረፍት ጣፋጭ ነው።
የዘለዓለም ሕይወትና የዘለዓለም ደስታ ከጌታ ጋር መኖር ጣፋጭ ነው።
ችግርና በሽታ፣ ሞት የሌለበት ጣፋጭ ነው።

የኃጢአት ይቅርታ ስላለ፣ በጠላታችን በሰይጣን ላይ ስለ ተፈረደበት፣ የዓለም ጸጥታና ሰላም ጣፋጭ ነው።

## መራራ ክፍል

2ኛ ጢሞ. 3፡12፤ ዕብ. 13፡12–14፤ ማቴ. 5፡11–12፤ ማር. 16፡15፤ መዝ. (123)፡3፣4 መዝ. (126)፡5፣6፤ ማቴ. 19፡29።

ለምሳሌ ያህል፣

1. ስደትን
2. ንቀትን፣ መጠላትን፣ መከራን መቀበል መራራ ነው
3. ለወንጌል ብሎ ቤትን፣ ንብረትን ትቶ መንከራተት
4. እስራትንና ሞትን የመለሰ መራራ በሆድ ውስጥ የሚቆይ የሚመር ትንቢት የወንጌል ትንቢት ለሚያነብ ጣፋጭ ነው፤ የወንጌልን ትንቢት ለሚያደርግ መራራ ነው፤ የወንጌል ትንቢት መፈጸሙ መራራ ነው ማለት።

## ቁ. 11 ከባድ ኃላፊነት

ዮሐንስ በላህ? ለአፍህ ጣፈጠ? ወይስ መራራ ሆነ? «ብላ!» ትዕዛዝ ነው። ከበላ በኋላ አሁን ተነሳና ተናገር። ትንቢት ተናገር___ ስበክ ማለት ነው። መስክር ተባለለት፤ ____ ለማን?

ዮሐንስ ሆይ ለብዙ ወገኖች ለአህዛብ፣_____ ቋንቋ ላላቸው ሁሉ ለነገሥታትም ሁሉ፣ ለትልቁም ለትንሹም ተናገር። ወንጌልን ስበክ። ለሁሉም መስክር፣ ስበክ።

ለምን?

የእግዚአብሔር ፍቅር እንዲበዛ ስበክ። የእግዚአብሔር ፍርድ ሊመጣ ነው። ለበለጠ ዮሐንስ 3፡16 ተመልከት። ቁጣው ሊወርድ ነው፣ ዮሐ. 3፡36። ተናገር፣ አውጅ፣ ቃሉን ለሚቀበሉ፣ ለሚያምኑት እንዲህ ይሆናል፣ 2ኛ ተሰ. 1፡7–10።

1. ለዮሐንስ ትንቢት ተናገር ተብሎ ታዘዘ፣ ምዕ. 10፡11
2. ለሕዝቅኤል ትንቢት ተናገር ተባለ፣ ሕዝ. 3፡18–21
3. ለኛ ትንቢት ተናገሩ ይለናል። እግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ በብዙ መንገድ ነው፣ ሮሜ 10፡14–17።

መንገዱ

1. በመጸለይ
2. ሄዶ ቃሉን በመናገር
3. በገንዘብ፣ አሥራትና ምጽዋት በመስጠት፣ ሚልክ. 3:8–15፤ 1:6–14::
4. በመልካም አካሄድ፣ ማቴ. 5:13–16፤ ቆላ. 4:5::

የእግዚአብሔር መልእክተኞች ነንና ስለ እግዚአብሔር እንናገር፣ 2ኛ ቆሮ. 5:19–21:: ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ እንበል:: እንማልድላቸው:: እንጸልይላቸው:: የእግዚአብሔር ከባድ ፍርድ ሊመጣ ነው:: አንተስ ክርስቶስን ተቀብለሃልን? ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረሃልን? ዮሐ. 5:24::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 11

## ሁለቱ የእግዚአብሔር ምስክሮች

ዮሐንስ ራእይ 11:1–19 አንብብ::

ይህ ምዕራፍ የፍርድ መለከቶች ሲነፉ መሃከል ጣልቃ የገባ ምዕራፍና ነገር ነው::

በምዕ. 9:13 ስድስተኛው የፍርድ መለከት ሲነፋ ምዕራፍ 10 ደግሞ የትንሹ መጽሐፍ ነገር ብላ የሚለው በመሃከል ገባ:: የመጽሐፉ ትንቢት ሊፈጸም ነው፣ 10:7:: ትንቢት ተናገር ተባለለት:: ምዕራፍ 10:11 ሰባተኛ መለከት ገና ሳይነፋ ምዕራፍ 11:15 ያለው መሃከል ምዕራፍ 11 ጣልቃ ይገባል:: ለምን? እግዚአብሔር በፍርድ መሃከል እንኳን ሰው እንዲድን ምኞቱን ያሳያል::

በዚህ ምዕራፍ አራት ነገሮችን እናያለን::

1. ምድራዊ መቅደስ
2. ሁለት ምስክሮች
3. 7ተኛ መለከት
4. ሰማያዊ መቅደስ

ዮሐንስ ከመልአኩ እጅ ወስዶ ትንሿን የተከፈተች መጽሐፍ ከበላ በኋላ፣ ትንቢትም ተናገር ተብሎ ከታዘዘ በኋላ ለዮሐንስ አንድ በትር (ዘንግ) ተሰጠው:: በአዲሱ ትርጉም የሰጠው በትር መለኪያ የሸንበቆ መሆኑን ያወራል፤ ከአዲሱ ትርጉም አንብብ::

ቁ. 1 እና 2 አንብብ

ይህ ለዮሐንስ እንዲለካ የተሰጠው መለኪያ ሸንበቆ ዘንግ ምንድን ነው? ማቴ. 12:18–21፤ ኢሳ. 42:1–4 ተመልከት።

ቁ. 1ና2 መቅደስ

የትኛው መቅደስ? በዚህ በዮሐንስ ራእይ የሚናገረው መቅደስ ወደ ፊት የሚሠራ መቅደስ ነው። መቼ ይሠራል? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያመለክተን ለወደ ፊት ሐሰተኛው መሲህ ሲመጣ ይሠራል ነው የሚለው። የመጽሐፍ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ምሳሌ (ናሙና) ከየት ተገኘ? መጀመሪያ ለሙሴ በሲና ተራራ እግዚአብሔር ምሳሌው ሰማያዊ ዓይነት እንዲሆን ሰጠው፣ ዘጸ. 25:40። ዕብ. 8:5 ሰማያዊ ቤተ መቅደስ መልክ በምድር ስንት ተሠራ?

1. ሙሴ እግዚአብሔር የሰጠውን ዓይነት ምሳሌ ድንኳን ሠርቷል፣ ዘጸ. 25:8–9።

    • የሰለሞን ቤተ መቅደስ 586 ዓ.ዓ. ናቡከደነፆር አፈረሰው

    • እነ ዘሩባቤል የሠሩት ቤተ መቅደስ 70 ዓ.ም. ቄሣር (ሮም) አፈረሰው

    • ከዚያ በኋላ ሆሴዕ 3:4 እና 5 የተባለ በኛ ዘመን አለ ሆኗል።

2. ንጉሥ ሰለሞን በዚያ ዓይነት ቤተ መቅደስን ሠርቷል፤ 1ኛ ነገሥት 6። በኋላ የባቢሎን ንጉሥ አፍርሶ አጠፋው።

3. በነ እዝራና ነህምያ ጊዜ ተሠርቷል፣ ሐጌ 1:4–8:3 በመጨረሻ እርሱን የሮም መንግሥት አፈረሰው።

4. ወደ ፊት የሚሠራው መቅደስ በዮሐንስ ራእይ የሚናገረው ነው፣ 11:1–2።

በሙሴ ዘመን የተሠራው የማደሪያ ድንኳን ምሳሌ ይኸው

# የማደሪያው ድንኳን





ቁ. 11 እና 12 ይህ ምድራዊ መቅደስ በምድር ተጣብቆ ያለውን የሰው ኃይማኖት ይመስላል:: ሰማያዊው መቅደስ ግን ነውር የሌለበት ፍጹም እንደሆነ ያመለክታል:: (ምዕራፍ 11:9):: አሁን በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ፍጹም ንጹህ ቅዱስ የሆነ አምልኮ ሁሉ ለሰማያዊ አምልኮ ምሳሌ ነው::

ምዕ. 11:1 መለኪያና በትር ለዮሐንስ ተሰጠው:: በትሩ ቤተ መቅደስን የሚለካ ነበር:: ቤተ መቅደሱ የመለኪያውን ልክ (ሜትር ልክ) መድረስ አለበት:: የሚለካውም የቤተ መቅደሱን ውስጥ ብቻ ነበር:: እግዚአብሔር የቤተ መቅደሱን ውስጥ ይለካል:: ኢየሱስ ለዮሐንስ ቤተ መቅደሴን በእኔ ልክ፣ በበትሬ ልክ ለካ፤ እኔ እለካለሁ ይላል:: የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እኛ ነን፣ 1ኛ ቆሮ. 3:16–17፤ ምዕ. 6:19ና20:: እግዚአብሔር ቤተ መቅደስን ሁሉ ይለካል:: እግዚአብሔር የራሱን ቤተ መቅደስ እንኳን ይመዝናል (ይለካል):: የእምነታችንና የአምልኮአችን መመዘኛና መለኪያ ምን ያህል ነው? መለኪያውን እንሞላለን ወይ? የማንም ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ መቅደስ የማንም አምልኮ ቢሆን መለኪያውን በትር ካልሞላ ካልደረሰ አምልኮው ከንቱ ነው:: ቤተ መቅደሱ ከንቱ ነው:: በትሩን የማይሞላ አምልኮ ሁሉ ርኩስ ነው:: በትሩን የማይሞላ እምነቱ፣ ዝማሬው፣ ጸሎቱ፣ ምጽዋቱ፣ ስብሰባው፣ ስብከቱ፣ ስግደቱ ዋጋ ቢስ ነው:: ክርስቲያን ሆይ ያንተ ቤተ መቅደስ በትሩን ይሞላል? ይደርሳል? በትሩ ክርስቶስ ነው፤ ሌላ የለም:: በትሩ ሞቱና ትንሣኤው ነው:: ያንተ መለኪያ ልክ እንዲሆን ብትፈልግ ክርስቶስን ብቻ ያዝ:: የኃይማኖት ሁሉ መለኪያ ኢየሱስ ነው:: የአምልኮ ሁሉ መለኪያ ኢየሱስ ነው:: የቅድስና ሁሉ መለኪያ ኢየሱስ ነው:: እርሱ ብቻ ሙሉ ነው:: ሌሎች የእርሱን መለኪያ አይደርሱም::

ቁ. 2 ከቤተ መቅደሱ ውጭ ያለውን ክፍት ቦታ አትለካ፤ ለአረማውያን የተሰጠ ነውና፤ ቁ. 2 እንዲሁም ኢየሱስ በሉቃስ 21:24 የመቅደሱን ውጭ የአረማውያን ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ተወው ይላል:: የአረማውያን ዘመን የሚፈጸመው መቼ ይሆን? ጌታችን ኢየሱስ ዳግም እስኪመጣ ማለት ነው፣ ዳን. 7:9፤ ምዕ. 2:44–45::

ቁ. 3 <u>ሁለቱ ምስክሮች</u>

እግዚአብሔር ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ምን ጊዜም ቢሆን ያለ ምስክሮች የሆነበት ጊዜ የለም፤ የ(ሐዋ. ሥራ 14:17):: በጣም ጨለማ በሆነበት

ዘመን እንኳን ራሱን ያለ አንድ ምስክር አልተወም:: ለምሳሌ አክአብ በእስራኤል ላይ በነገሠበት ዘመን ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት ጨርሳ አስገድላ በነበረበት ዘመን እንኳ፣ ምስክር ይሆን ዘንድ ጌታ ኤልያስን አስቀምጦት ነበር፤ (1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 17 እስከ ምዕራፍ 19):: ምዕራፍ 19:10:: እግዚአብሔር መቼም ቢሆን ከፍርድ በፊት መልእክተኞችን ሳይልክ አይተውም:: ሰዶምና ገሞራን፣ (ዘፍ. 19) ነነዌን፣ ዮናስ ምዕራፍ 1 እግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ አላለፈም፤ በማንም አይፈርድም፤ አልፈረደም:: እግዚአብሔር በፍርድ አይቀልድም:: አለመታዘዝ ባለበት ቦታ ፍርድን ያመጣል:: የፍርድ ምክንያቱንም ዮሐንስ 15:22–25 ላይ ተመልከት:: እነዚህ ሁለቱ ምስክሮች ክርስቲያን በሕይወት መኖር በማይችልበት ዘመን እንኳን ለእግዚአብሔር ነገር ሁሉ ከባድ እንዳልሆነ ያሳያል:: የጊዜ ሁኔታ ምንም ያህል ከባድ ይሁን ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻላል:: (ምዕ. 13:16–17):: እነዚህም ሁለት ምስክሮች ቁጥር 3 ኃይል ይሰጣቸዋል:: በትንቢተ አሞጽ 3:7 እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ይገልጻል:: እግዚአብሔር ራሳቸውን በቅድስና በሚመሩትና የእርሱን ሕብረት ለሚፈልጉት ሁሉ ራሱን ይገልጻል:: የእርሱን መንገድና እቅድ እንድናውቅ ደግሞ ቃሉን ሰጥቶናል:: እነዚህ ሁለቱ ምስክሮች ለምን ያህል ጊዜ ይመሰክራሉ? ምናልባት ለ1260 ቀን ይሆናል:: ስንት ዓመት? ሦስት ዓመት ተኩል ይሆናል:: ምናልባት በእነርሱ ምክንያት ይሆናል 144000 እስራኤላውያን የዳኑት፣ ራእይ 7:4–8 ተመልከት:: ምን ብለው ይመሰክሩ ይሆን? የደህንነት የወንጌል መልእክት እንደ ዮሐንስ 3:3፣ ሉቃስ 13:3–5 ያለ ዓይነት የደህንነት መልእክት ሳይሆን አይቀርም:: ወይም ንስሐ ግቡ ማለት ይሆን ይሆናል::

እነዚህ ሁለቱ ምስክሮች ከየት የመጡና እነማን ናቸው? ራእይ 11:4–6 ስናነብ መልሱን እናገኛለን::

ቁ. 4 እነማን ናቸው ለሚለው ጥያቄ ሲመልስ፣ ቁ. 4 ላይ ይገኛል:: ደግሞ በነብዩ ዘካርያስ ጊዜም ተነግሯል:: ትንቢተ ዘካርያስ 4:1–14:: ሁለቱ የወይራ ዛፎች ዘይት የሚገኝባቸው ናቸው:: ሁለቱ መቅረዞች መብራት የሚሰጡና የሚቀጣጠሉ ወይም ብርሃን የሚሰጡ ምሳሌዎች ናቸው::

ምስክር:– ብርሃን እንደ መስጠት ነው
ዘይት:– የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው

ከመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ ማንም ምስክር ሊሆን አይችልም፣ ዘካ. 4:6:: 1ኛ ቆሮ 4:20፤ 1ኛ ቆሮ. 2:4፤ ሮሜ 15:19፤ 1ኛ ተሰሎ. 1:5:: ወንጌላችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆን አለበት:: እነዚህ ሁለቱ ምስክሮች የሚነሱት ከኢየሩሳሌም ይሆናል ብለን እናምናለን:: «በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ» ዮናስ 1:3፤ 1 ነገ. 17:12፤ 5:16፡ ሉቃስ 2:23 በጌታ ፊት የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ማደሪያ ከሆነ ከቤተ መቅደስ ፊት ማለት ነው:: ስለዚህ ቤተ መቅደስ የነበረው በኢየሩሳሌም ነው:: እነማን ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ልዩ ልዩ ሰዎች ልዩ ልዩ መልስና ሃሳብ አላቸው:: ለምሳሌ ያህል ስማቸው ስላልተጠቀሰ፣

1. ሄኖክ ይሆናል ሌሎችም
2. ኤልያስ ይሆናል ብለው ይገምታሉ::

ምክንያቱንም ሲያቀርቡ የሞት ባህር ሳይሻገሩ ስለሄዱ ተመልሰው ስለምሥክሩ መሞት ይኖርባቸዋል ብለው ያስባሉ፣ ዘፍ. 5:24፤ 2ኛ ነገ. 2:1–11::

ሀ/ ይህ ሃሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ጋር አይስማማም፤ ምክንያቱም ያልሞቱት ሁሉ ተመልሰው ይሞታሉን? በትንሣኤ ቀን ብዙዎች ሳይሞቱ ወደ ሰማይ ስለሚሄዱ 1ኛ ቆሮ. 15:51–52፤ 1ኛ ተሰሎ. 4:17 በሥጋ የተወሰዱት ተመልሰው አይሞቱም:: ስለዚህ በቂ ምክንያት አይደለም::

ለ/ ሔኖክ ደግሞ አሕዛብ ነበረ:: ሲወሰድ የሚነሱት ምስክሮች ግን ከእስራኤል ወገን ነው:: ነገር ግን የሚነሱት ሁለቱ ምስክሮች ስማቸው ባይገለጽ እንኳ ማን እንደሆኑ መገመቻ ተጽፏል፣ ራእይ 11:5::

1. እሳት፣ የእሳትን ነብይ ያሳስባል፣ 2ኛ ነገ. 1:9–12

2. ቁ. 6 ዝናብ የሚከለክል ነብይን ያሳስባል፣ 1ኛ ነገ.17:1፤ ያዕ. 5:17::

ቁ. 6 ውሃውን ወደ ደም የለወጠ፣ ዘጸአት ምዕራፍ 7 እስከ ምዕራፍ 10 ተመልከት:: በመቅሰፍት ምድርን የመታ::

ስለዚህ ሚዛኑን የሚሞሉ ኤልያስና ሙሴ ስለሚመስሉ ምናልባት እነርሱ ይሆናሉ:: ደግሞም ሌላው ትንቢት ስለ ኤልያስ የሚናገር በሚል. 4:5ና6 እንድናስብ ያደርጋል::

ሐ/ ሙሴና ኤልያስ በምድር ላይ በነበሩ ጊዜ ያደረጉት ምስክርነታቸው ሥራቸው ቀጥታ በዮሐንስ ራእይ 11:4–6 ያለውን የሚመለከት ነው። እነዚህ ምስክሮች ራሳቸውን ለመጠበቅ ልዩ ኃይል አላቸው። በልዩ ኃይል ታምራትና ምልክቶች ይሠራሉ።

ቁ. 5 ማንም ሊጐዳቸው ቢፈልግ (ቢያስብ)

1. ኤልያስን፣ 2 ነገሥት 1:9–12

2. ሙሴ በቆሬና ዳታን ላይ ምድር ዋጣቸው፣ዘኁልቁ 16:29–33። 250 ሰዎችም እንደጠፉ ተጽፏል።

ይህ ጠባይ ለሙሴና ለኤልያስ ሰዎች የነበራቸው ስለሆነ እነርሱ ይሆናሉ ተብሎ ይገመታል። ለእነርሱ ለምስክርነታቸው ከባድ ጠላት ይነሳባቸዋል። እነርሱ ግን በእግዚአብሔር ኃይል ምስክርነታቸውን ይፈጽማሉ። በእውነት ላይ ለሚቆሙ ሁሉ እግዚአብሔር ወዳጃቸው ነው።

ሰይጣናዊ ውጊያ በሁለቱ ምስክሮች ላይ፣ ራእይ 11:7

ቁ. 7 የሁለቱ ምስክሮች ሥራና የምስክርነታቸው ጊዜ ሳያልቅ ሕይወታቸው ከዚህ ዓለም እንዲወሰድ (እንዲሞቱ) እግዚአብሔር ይፈቅዳል። ገዳዩም ጠላት ሰይጣን ነው።

የአማኞች ሞት፤ ይህን ቁጥር ስንመለከት እንዴት ያድነናል? የሚል ጥያቄ ሊኖረን ስለሚችል መልሱን በጥቂቱ ለመመለስ:–

1. እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ተቆጣጣሪ ስለሆነ

2. እግዚአብሔር የአገልጋዮቹን ሕይወት ሥራቸውን እስኪፈጽሙ ድረስ ከክፉ እንደሚከላከልና እንደሚጠብቃቸው በቃሉ ስላረጋገጠልን፣ እርሱ ካልፈቀደ በየትኛውም የሚያስፈራ ቦታና ዘመን እንደምንጠበቅ እንደሚፈልግም ለማድረግ የሚችል አምላክን መሆኑን ስለምናምን ከመቅሰፍት ያድነናል።

ለምሳሌ

1. የጳውሎስን ሕይወት አስቡ። በመጨረሻም ጊዜ እንዲሄድ ጊዜው በደረሰ ጊዜ፣ 2ኛ ጢሞ. 4:7–8 አንብብ። የጌታ በሪያ የሚሞትበት ጊዜ ሲደርስ:–

ሀ/ መልካም ገድል ተጋድያለሁ
ለ/ ኃይማኖቴን ጠብቄአለሁ
ሐ/ሩጫዬን ጨርሻለሁ ይላል እንጂ አይፈራም።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ባለ ጊዜ በእስር ቤት ነበር። ክፉ ጨካኝ ንጉሥ ኔሮ ነበረ በግዞት ያስገባው። ጳውሎስ ግን ሞትን አይፈራም ነበር፤ ለምን? በየቀኑ ሕይወቱን በእግዚአብሔር እጅ አደራ ይሰጥ ስለነበር። ስለዚህ ቀኑን አውቆታል፣ 1 ጴጥ. 4:19።

2. ደግሞ ንጉሥ ዳዊትም መዝ. 39:4«የመጨረሻዬን ቀን አስታውቀኝ» ይላል እንጂ አይፈራም፤ መዝ. (102):23።

3. ኢዮብም ያንን የመጨረሻ ቀን ለማወቅ ፈለገ፣ ኢዮብ 7:1፤ 14:5– 14። ጻድቅ የመጨረሻ ቀጠሮ ቀንን ማወቅ የፍልጋል፣ ይለምናል፣ ይናፍቃል አይፈራም። እኛስ ስለ ራሳችን ሞት ቀን ምን እናስባለን? የማያምን ኃጢአተኛ ግን እንደ ኢየሱስ ጊዜ ባለጠጋ ሉቃስ 13:19–21 ይሆናል። ሊኖር ቢፈልግም አይፈቀድም ይወሰዳል፣በግድ ይሞታል። ሰው ከዚህ ዓለም ሞት ቀጠሮ በኋላ ሌላ የሞት ቀጠሮ እንዳለ 3መርሳት የለበትም፣ ዕብ. 9:27። ዛሬ ኢየሱስን ለሚጠሉት የሚጠብቃቸው ገሃነመ እሳት ነው፣ ራእይ 20:15፤ 21:8። ዛሬ ኢየሱስን ጌቸቸውና መድኃኒታቸው አድርገው ለተቀበሉት ግን የሚጠብቃቸ ሌላ ክብር ነው፣ የዘላለም ሕይወት ነው፣ ዮሐ. 5:24፤ ሮሜ 8:1። የዮሐንስ ራእይ ሁለቱ ምስክሮች ግን እግዚአብሔር ሲፈቅድ እንደሞቱ በቁጥር 7 ላይ እናገኛለን።

1. ጠላት ለጊዜው ያሸነፈ ቢመስልም
2. ጨለማ ብርሃንን ያሸነፈ ቢመስልም
3. ክፉ ጻድቅን ያሸነፈ ቢስልም
4. ሲያል መንግሥተ ሰማያትን ያሸነፈ ቢመስልም
5. ለጊዜው ሰይጣን እግዚብሔርን ያሸነፈ ቢመስልም

ሁሉም ድል ጊዜያዊ ነው። ሁሉን የሚችል አምላክ ለጊዜው ፈቀደ።

የሞቱትም ሁለት ምስክሮች ነገር እውነት ነው። የሚገድል የጥልቁ አውሬም ያለ ነው። ታዲያ ክርስቲያን በዚህ ነገር እንረበሻለን? አይደለም ምንም ቢሆን ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር እጅ ነው፣ ሮሜ 8:28።

ሁለቱን ምስክሮች የሚገድላቸው አውሬ ደግሞ ሰው ነው። ደግሞም የሚሞቱት ምስክሮች ሰዎች ናቸው። እነዚህ ገዳዮች የሚሞቱና የሚበሰብሱ ናቸው እንጂ የማይበገሩ ኃይላት አይደሉም። ስለ እነዚህ አውሬዎች በምዕ. 12 እና 13 ላይ ስንደርስ በደንብ እናጠናቸዋለን።

## ሁለቱ ምስክሮች የሚሞቱበት ስፍራ፣ ራእይ 11:8

ቁ. 8 አንብብ እንዴት አስፈሪ ሥራ፣ እንዴት አዋራጅ ሁኔታ፣ እንዴት የተናቀ ዝቅተኛ ስድብ የሞላበት አሟሟት ነው አውሬው የሚሠራውና የሚያደርገው። ከገደለ በኋላ ሬሳቸው እንዳይቀበርና እስኪበሰብስ፣ እስኪተላ፣ እስኪፈነዳ እንዲገማ በውጭሜዳ በአደባባይ ይቀመጣል። ሰይጣን ምድር ላይ እንዲገዛ በሚፈቀድበት ጊዜ እንዲህ ያለ ርኩስ ሥራ ነው የሚሠራው። ሰይጣን በኛ ዘመን ወይም በቤተ ክርስቲያን ዘመን የብርሃንን መልአክ ሊመስል ይሞክራል። በዚያን ዘመን ግን እንደዚያ አይሆንም። ያኔ የሚያደርገው በቀጥታና በግልጽ የርኩስነት ሥራ ነው። አለበለዚያ ዛሬስ ቢሆን ስንት ክርስቲያኖች ሬሳቸው እንዳይቀበር ማድረግ መቼ ተወ?

ለመሆኑ ሥፍራው የት ይሆን? ቁ. 8 ላይ እግዚአብሔር ሥፍራው የት እንደሚሆን ይገልጽልናል።

1. በመንፈሳዊ ምሳሌ አነጋገር ሰዶምና ግብጽ ይባላል።
2. ወይም የኛ ጌታ የተሰቀለበት ቦታ ይላል እርሱም ኢየሩሳሌም ነው። 3ቱን ቦታ እናስተውላቸው።
   1. በሰዶምና ገሞራ ምን ተደረገ? ዘፍጥ. 18:20–21፤ 19:4–7።
   2. በግብጽስ ምን ተደረገ? ዘጸ. 1:11–16።
   3. በኢየሩሳሌምስ? ማቴ. 23:37፤ ሉቃስ 13:34።

በስቅለት ጊዜ የሆነውን በ4ቱ ወንጌል ተመልከት።

## ቁ. 9–10 የሁለቱ ምስክሮች ሬሳ እንደማይቀበር

ቁ. 9 ዓለም ሁሉ የእነዚያ ምስክሮችን ሬሳ በሜዳ ወድቆ ያዩታል። በመገናኛ ብዙሃን ማለትም፣ በቴሌቪዥን በሬዲዮ ወሬውም በአለም ሁሉ ይታያል ይሰማል። ይህም የሚሆነው ለሦስት ቀን ተኩል ነው። ለሦስት ቀን ተኩል ሬሳቸው አይቀበርም።

የዓለም ሕዝብ ሁኔታ እንዴት ይሆናል?

ቁ. 10 እናንብብ፣ ምድርን ሁሉ አሰቃይተው ስለነበሩ በምን? በስብከታቸው፣ በፍርዳቸው፣ ቁ. 5ና6 ተመልከት:: ታዲያ ስብከት ምድርን ያሰቃያልን?

ቁ. 10 አዎ ጻድቅ ሰው ምንጊዜም ቢሆን ኃጢአተኛን ወይም ኃጢአተኞችን በሕይወቱ፣ በምስክርነቱ፣ በስብከቱና በኑሮው ያሰቃያል:: ስለዚህ ይህ ኃጢአተኛ ትውልድ በጻድቃን ኑሮ ይሰቃያል፣ ይደነግጣል፣ ምክንያቱም ኃጢአተኞች ኃጢአትን መሥራትን ቢወዱም፣ ኃጢአታቸው ግን እንዲገለጽ፣ እንዲታይና እንዲሰማ አይፈልጉም:: ይልቅ ኃጢአታቸው እንዲሸፈን ይፈልጋሉ:: ጌታ ኢየሱስ ግን የተሰወረ ሳይገለጽ አይቀርም ብሏል:: እነዚህ ሁለት ምስክሮች የዓለምን ጥፋት ስለገለጹ ወይም ዓለም ክርስቶስን መጥላቷ ስለገለጹ አዳኛቸውን አለመቀበል ፍርድ የሚያመጣ እንደሆነ በመግለጽ ስለተገደሉ ኃጢአተኞች ደስ አላቸው:: የእውነት ምስክሮች በሞት ጸጥ ቢሉም እውነት ግን አይሞትም:: ለምሳሌ ማርቆስ 15:27-32:: ጸፎችና ፈሪሳውያን በክርስቶስ ሞት እውነት የሚሞትና የሚቀበር መስሏቸው ቢደሰቱም ደስታቸው ለሦስት ቀን ብቻ ነበር::

በኃጢአት የሚገኝ ደስታ አጭር ነው:: እንዲሁም በሐዋርያው ጳውሎስ መታሠር ሰዎች ተደስተዋል:: እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር መልእክት ከእስር ቤት ሆኖ ይልክ ነበር:: ይህ ደግሞ ባይገባቸውም ለቅዱሳን ጥቅም ነው:: ደግሞ የዮሐንስ መታሰር በዮሐንስ ራእይ 1:9 ዮሐንስ ራእይን ወደ እውነት ለመግለጽ ወይም ለማውጣት ረድቷል:: ስለዚህ እውነት ቅንጣት ያኽል እንኳን አታልፍም፣ ማቴ 24:35:: ስለዚህ ጻድቃንንና ክርስቶስን የሚጠሉ መጨረሻቸው ወደ እሳት ባህር ይሆናል፣ ዕብ. 9:27 ራእይ 20:15::

## ትንሳኤና እርገት፣ ዮሐንስ ራእይ 11:11-12

የሕይወት መንፈስ የገባበት ሁሉ ይቆማል:: በኋለኛው ዘመን ስለሚነሱ ሁለቱ ምስክሮች ስናይ እግዚአብሔር ያሸንፋል እንጂ አይሸነፍም::

ቁ. 11፣ በመሞታቸው ዓለም ሁሉ ሲደሰትና ስጦታ ሲለዋወጡ ድንገት አንድ ነገር ሲሆንባቸው ይታያል:: እግዚአብሔር በመካከል ገባ:: የዓለም ደስታ ድንገት ተቋረጠ:: ዓለም በቴሌቪዥን በሬዲዮና በሌላም በሚታይ ነገር የሁለቱ የእግዚአብሔር ምስክሮች መሞታቸውን

እያዩና እየሰሙ ደስታቸው ጣሪያ ደረሰ የነበሩ ሁሉ ድንገት ሁለቱም ምስክሮች በእግሮቻቸው ብድግ ብለው ይቆማሉ:: በዚህ ጊዜ ትልቅ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ ዓለምን ይይዛል:: ቁ. 11::

ቁጥር 12 ተነሥው እንደቆሙ ድምጽ ከሰማይ መጣላቸው:: ድምጹም ወደዚህ ውጡ፣ ኑ የሚል ነበር:: በዚያች ሰኩንድ ጠላቶቻቸው እያዩዋቸው ወደ ሰማይ ወጡ:: ምናልባት ወደዚህ ውጡ የሚለውን ድምጽ ዓለም ሁሉ ሳይሰማ አይቀርም:: እነዚያ ሁለቱ ምስክሮች ሁሉ እያዩዋቸው ወደ እግዚአብሔር ክብር በደመና ተነጠቁ:: በቀረው ዓለም ላይም ፍርሃት ወደቀባቸው:: ከሃሰተኛ ነቢይ በላይ የሆነ እንዳለ አውቀዋልና ዓለም የከዳቸው ትንሳኤና እርገትን ይሰብኩ የነበሩት በራሳቸው ትንሳኤና እርግት የእግዚአብሔርን መኖርና ታላቅነት መሰከሩ ማለት ነው:: እግዚአብሔር አምላካችን ተናጋሪ ብቻ አይደለም:: የተናገረውን አድራጊም ነው፣ ዘኍ. 23:19:: ዛሬስ የክርስቲያን ስብከት ስለምን ይሆን? የሐዋርያው ጳውሎስ ስብከት ግን 1ኛ ቆሮ. 2:2 ላይ እንደምንመለከት የክርስቶስ ሞት፣ ስቅለትና ትንሣኤ ነበር:: በስብከታችን የክርስቶስ ሞት ደምና ትንሣኤ ኃይል ከሌለ ደካማና ዓላማውን የሳተ ይሆናል:: በዮሐንስ ራእይ 11 ያሉት ምስክሮችም ይሰብኩ የነበሩት ዓለም የናቀውን፣ ዓለም የካደውን ኢየሱስንና የትንሣኤውን ኃይል ነበር:: አንተስ ስብከትህ ስለምንድን ነው? ሰባኪ ሆይ ስብከትህ የጌታ ሞትና ትንሣኤው ይሁን::

## ክለሳ

7 ማህተምን 7 መለከት ይከተላል፤ ከሰባት መለከት መሃከል 3 ወዮዎች አሉ ከሦስቱ ወዮዎች ቀጥሎ 7 የቁጣ ጽዋዎች መፍሰስ ይጀምራሉ::

ቁ. 13 የእግዚአብሔር ፍርድ

ቁጥር 13 የሁለቱ ምስክሮች ተልዕኮ አልቆ ከሙታን ተነስተው ወደ ሰማይ ተጠርተው እንደወጡ ከባድ የምድር መናወጥና መንቀጥቀጥ ይደርሳል ይላል ዮሐንስ:: የምድር ሁኔታ አስፈሪ ይሆናል፣ ዕብ. 10:30–31:: በዚህ በምድር መናወጥ የተነሳ 7 ሺህ ሰው ተገደለ:: የከተማይቱም አሥረኛ እጅ ወደቀ:: ከሰይጣንና ከሃሰተኛ ነቢይ የሚበልጥ ማንም የሌለ መስሏቸው ለነበረ፣ ሕዝብ ከሁሉ በላይ የሆነና ከማንም የሚበልጥ ሥራ ሊሠራ የሚችል የሰማይ አምላክ

እግዚአብሔር እንደሚኖር ይገነዘባሉ:: በዚያን ጊዜ ክብርን ለእርሱ ይሰጣሉ፣ ፊልጵ. 2:10–11:: ጉልበት ሁሉ ለእርሱ ይንበረከካሉ፣ ምላስም ሁሉ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክራሉ የሚለው ቃል ይፈጸማል:: ይሁን እንጂ ሰዎች በእግዚአብሔር ያምናሉ የሚል ቃል አናገኝም:: የሚያድን እምነት ሊኖር የሚገባ አሁን ነው፣ 2ቆሮ. 6:1–2:: አንተስ አሁን በክርስቶስ እምነት አለህ? ጊዜው ካለፈ በኋላ የንስሃ ጊዜ አይኖርም:: የእምነትና የንስሃ ጊዜ አሁን ነው:: የምድር መናወጥ የእግዚአብሔር አንዱ መግሪያ ነው:: እግዚአብሔር በምድር መናወጥ ለምድር ሕዝብ እየተናገረ ነው::

1. ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ የምድር መናወጥ ነበረ፣ ማቴ. 27:51–53
2. በጌታችን ትንሣኤ ጊዜ የምድር መናወጥ ነበረ፣ ማቴ. 28:3

ይህ የምድር መናወጥ እግዚአብሔር በምድር መናወጥ ለሕዝብ እንደሚናገር ያስረዳል::

በኢሳይያስ 1:2 ላይ «እግዚአብሔር ተናግሯልና ሰማያት ስሙ ምድርም አድምጪ» ይላል:: ደግሞ የምድር መናወጥ ሰው የእግዚአብሔርን ፍርድ ፊት ለፊት እንደሚገጥም ያሳስበናል:: ከዚህ ቀደም የምድር መናወጥ በ1978 ዓ.ም. በሜክሲኮ ከተማ፣ በሕዳር 7/79 በታይዋን በካሜሩን የሆነውን፣ በዓለማችን በልዩ ልዩ ቦታዎች በየጊዜው የሚሆነውን ማስታወስ እንችላለን:: ጌታ እየተናገረ ነው ማለት ነው::

ሰዎች እግዚአብሔርን ባይፈሩና በእምነትም ባይከተሉ የሚያስፈራ ፍርድ ይጠብቃቸዋል፣ ዕብ. 9:27፤ 10:27፤ 12:29::

3ኛ ወዮ ይመጣል

የ7ኛተው መለከት መነፋት ራእይ 11:14–19

ታላቅ መግለጫ ከሰማይ ስለ ክርስቶስ መንግስ

ቁ. 14ና15፣ ክርስቶስ ለዘላለም ነገሠ የሚል ነበር:: ክርስቶስ ሊነግሥ ነው፤ የሰማይና የምድር ሥልጣን ለክርስቶስ ሊሆን ነው፤ በዳንኤል 2:44 የተባለው ገና ሊፈጸም ነው፤ በኢሳይያስ 9:6–7 ያለው ሙሉ በሙሉ ገና ሊፈጸም ይገባዋል:: በስልጣንና በታላቅ ኃይል ይነግሣል:: ታዲያ ክርስቶስ በሥልጣን በሚነግሥበት ሰዓት ወዮ ይኖራል ወይ? አዎን ክርስቶስ በሥልጣን በሚነግሥበት ጊዜ እርሱን ለማያምኑት፣ እርሱን ለሚጠሉት ከባድ ወዮ ይሆንባቸዋል:: ምክንያቱም ንጉሡ

በጐችንና ፍየሎችን ይለያቸዋል፣ ማቴ. 25:31–46:: ስንዴንና እንክርዳድን ይለያቸዋል፣ ማቴ. 13:24–30::

ቁ. 16ና17 በታላቅ ዙፋን ፊት ያሉት ሽማግሌዎች የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ይወክላሉ:: እየሰገዱ እንዲህ አሉ፣ «ስለ ነገሥህ እናመሰግናለን::» የክርስቶስ መንገሥ ለቤተ ክርስቲያን ደስታ ይሆናል፣ ክብርና ምስጋና ይሆናል:: የታመኑትንና ይጠብቁ የነበረውን ያገኛል::

ቁ. 18 አሕዛብ ግን በክርስቶስ መንገስ ይቆጣሉ:: በክርስቶስ መንገስ አይደሰቱም:: ክርስቶስ በሚነግስበት ጊዜ ምድርን ያጠፉትን፣ በኃጢአት ያበላሹትን ያጠፋቸውና በምድር ላይ ሰላምን ያመጣል:: ስለዚህ አሕዛብ ይቆጣሉ:: ቁጣቸው እስከ ጦርነትና ጥፋት ያደርሳቸዋል፣ ምዕራፍ 19:19:: የእግዚአብሔር ቁጣ እንጂ የሰው ቁጣ ቀላል ነው:: የሰው ቁጣ ደካማና ኃጢአተኛ ሲሆን የእግዚአብሔር ቁጣ ግን ቅዱስና እውነተኛ ነው:: ከእግዚአብሔር ቁጣ ለማምለጥ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፣ አንተና ቤተሰብህ ትድናላችሁ፣ የሐዋ. ሥራ 16:31::

ቁ. 18 ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ አሉት:: የምድር አሕዛብ፣ ዘመን የማይመጣ፣ ክርስቶስ የማይመጣ፣ አድርገው ይገምታሉ:: እግዚአብሔር ዓለምን እንዲድን ዘንድ እንደሚታገሳቸው አልተረዱም ነበርና፣ 2ጴጥ. 3:9:: እግዚአብሔር አሁንም በምህረት ይመለከታል:: የምሕረት ጊዜ ገና አላለቀምና ክርስቶስ ግን አሕዛብን ይገዛ ዘንድ ይቀጠቅጣቸው ዘንድ ጊዜ ይመጣል፣ መዝ. 2:9:: ወንድሞቼ ሆይ ለጥቂት ጊዜ በዓለም ያለውን ግፍና ጦርነት እርኩሰትንም አስቡ:: በዓለም አሳዛኝ ሁኔታዎች ይፈጸማሉ:: ዓለም በዚሁ ሁኔታ እያለች ጌታ በድንገት ወደ ምድር ቢመለስ ወይም የዓለም ፍጻሜ የሚያደርግ ክርስቶስ ቢገለጥ፣ የዓለም ሕዝብ ክርስቶስን እንደ ቶማስ ጌታዬ አምላኬ መድኃኒቴ ብሎ ይቀበልና ይሰግድ ይመስላችኋል? ዮሐ. 20:28:: አያደርጉትም፣ አይሉም፣ አይፈልጉም:: እንዲያውም ይቆጣሉ፣ ለጦርነት ይነሳሉ እንጂ፣ ምዕ. 19:19:: ስለዚህ ነው በዙፋኑ ላይ ያሉት ሽማግሌዎች ቁጣህ መጣ ያሉት፣ ቁ. 18:: ሐዋርያው ጳውሎስም ሮሜ 1:18–19 የእግዚብሔርን አምላክነት ግዛቱን ስለማይፈልጉ፣ ቁጣ ከሰማይ ይገለጣል ይላል፣ ሮሜ 2:4–5፤ ኢሳ. 13:7–11::

1. ክርስቶስ በማያምኑት ሲፈርድ፣ በነጭ ዙፋን ፊት ሲሆን፣ ራእይ 20:11–15::

2. ክርስቶስን በሚያምኑት ሲፈርድ፣ በፍርድ ወንበር ፊት ይሆናል፣ 2 ቆሮ. 5:10።

ራእይ 11:18 ላይ ለባሪያዎችህና ለነቢያት ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ ይላል። ለአገልጋዮቹ ዋጋ አላቸው

ቁ. 19 በዚህ ቁጥር ላይ የሚታየው ነገር በጌታችን መንግሥና በዓለም ፍርድ በቅዱሳንም ዋጋቸው መከፈል ስለ መግለጫ በመካከል ይገባና ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን መቅደስና በውስጡም ያለው የቃል ኪዳን ታቦት ለዮሐንስ ይታያል። ከዚያም መብረቅ፣ ከባድ ድምጽ ነጐድጓድ፣ የምድር መናወጥና ታላቅ በረዶ ይሆናል። በምድር ላይ ከባድ ቁጣና ፍርድ ሲሆን ሰማይና የቃል ኪዳን ታቦት መቅደሱም ተከፍቶ መታየቱ የእግዚአብሔር ቸርነት፣ ፍቅርና ቅድስና እውነተኛ ፍርድ በሰማይ ባለው በእግዚብሔር ዘንድ እርሱን ለሚወዱት እንደሚሆንላቸው ሲያመለክት፣ መቅደሱና የታቦቱ ስርዓት ክርስቶስን ያመለክታል።

እግዚአብሔር የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ ዮሐ. 1:29 ወይም የኃጢአት ዕዳ እንዲከፍል የላከውን ልጁን የኢየሱስ ክርስቶስንና በመስቀል ላይ ያፈሰሰውን ደም፣ የዓለም መሥዋዕት የሆነው በግ ክርስቶስን ያመለክታል። እግዚአብሔር እስካሁን በክርስቶስ ለሚያምኑት በስሙም ንስሃ ለሚገቡት ፍቅሩንና ምሕረቱን የኃጢአትን ሥርየት እያደረገ ነው። የእግዚአብሔርም ቁጣ ከእነርሱ ያልፋል። ደሙንም አያለሁ ከእናንተም አልፋለሁ መቅሰፍትም አይሆንባችሁም ይላል፣ ዘጸ. 12:13።

ቁ. 19 የእግዚብሔር መቅደስ በሰማይ

ለዮሐንስ በሰማይ የታየው የእግዚአብሔር መቅደስ፣ የምድርን መቅደስ በሙሴ ዘመን፣ በሰለሞን ዘመን፣ በነህምያና በዕዝራ ዘመን የተሠራውን ምድራዊ መቅደሶችን ያሳስበናል። በእነዚህ ሰዎች ዘንድ የሠሩት መቅደሶች የሰማያዊው መቅደስ ምሳሌ ነበር። በምድር የተሠሩ በሰማያዊው ምሳሌ ነው፣ ዕብ. 8:5። በተለይ ለሙሴ በመጀመሪያው የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ በተራራ ላይ ተመልከት፣ ዘጸ. 25:40። በዮሐንስ ዘመን በራእይ ሰማያዊው መቅደስና የኪዳኑ ታቦት የታየበት፣

1. የእግዚአብሔርን ቅድስና ያሳያል፣ ዘሌ. 19:2፤ 1ጴጥ.1:15–16

2. የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በደም ያለውን ያሳስበናል። ያውም በክርስቶስ ደም፣ ዕብ. 9:23–26። እግዚአብሔር ከአማኞች ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ኢየሱስ ይህ አዲስ ኪዳን ነው ብሎ አሳስቧል፣ ሉቃስ 22:17–20፤ 1ኛ ቆሮ. 11:23–26።
3. የክርስቶስን መሥዋዕትነት ያሳስበናል፣ ዮሐ. 1:29፤ ኢሳ. 53:4–12
4. እኛ አማኞች መሥዋዕት መሆን እንደሚገባን ያሳየናል፣ ቆላ. 3:3፤ ሮሜ 6:11፤12:1:3
5. ለጌታ ማቅረብ የሚባንን መሥዋዕት ያሳስበናል፣ ሮሜ 12:1፤ ዕብ. 13:15።
6. የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና የታቦቱ ሥርዓት በብሉይ ኪዳን ዘመን የሚያሳየው የእግዚአብሔርን ምሕረት በሰዎች ላይ እንደሆነ ነው።

## ምሕረት እንዴት ይገኛል?

ምሕረት እንዲገኝ አንድ ወገን መጐዳት አለበት። ያውም እግዚአብሔር ስለ እኛ ተጐዳ፣ ዮሐ. 3:16።

በዮሐንስ ራእይ 11:19 ላይ መብረቅ፣ ነጎድጓድ፣ የምድር መናወጥና ታላቅ በረዶ ይታያል። ያ ሁሉ የእግዚብሔርን ፍርድ ያሳያል። የእግዚአብሔር ፍርድ በሁሉ ላይ አለ ይመጣል። ይሁን እንጂ መሥዋዕት በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ በኩል አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፣ ለሚቀበሉት በሙሉ ምሕረት ይገኛል፣ 2ኛ ቆሮ. 5:14–15፤ 21:3 መሥዋዕት ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ይቅርታና ምሕረት፣ ሰላምና እርቅን ያሳያል። በክርስቶስ መሥዋዕትነት በኩል ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ሊታረቅ ችሏል።

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 12

## ሐዋርያው ዮሐንስ በሰማይ አስደናቂ ነገር እንደ ተመለከተ

የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 12 በደንብ ካልገባን ወይም ካላወቅን፣ ራእይ መጽሐፍን በሙሉ ወይም መጽሐፍ ቅዱስን በሞላ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው ማለት ይቻላል። የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 12 የሚገልጸው እውነትን ከእኛ ዘመን ጀምሮ ወደ ኋላ ወደ እነ አብርሃም ተመልሶ ከእኛ ዘመን ወደ ፊት እስከ ክርስቶስ ዳግም መመለስና የዓለም ፍርድ መጨረሻ ደርሶ ሁሉን በክርስቶስ ይጠቀልላል።

የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 12 ማወቅ ሙሉ ራእይ ከዚያም አልፎ መጽሐፍ ቅዱስን በውስጡም ያለውን ታሪክ በሞላ ማወቅ ማለት ነው። በዚህ ምዕራፍ ጦርነትና ጥል፣ በሰይጣንና በክርስቶስ መካከል ተቃውሞ፣ እንዲሁም በእሥራኤል ልጆች መካከል ያለውን ነገር ይገልጻል። በተጨማሪም ከዚህ በፊት የነበረውንና ወደ ፊት የሚኖረውን ጠላትነትንና ጦርነት በሴቲቱና በዘንዶው መካከል ያለውን በግልጽ ያሳያል።

ቁ. 1፡2 ምጥ የያዛት ሴት

እዚህ ቁጥር ላይ ምጥ የያዛት ሴት ማን ናት? ይህችስ ሴት እውነተኛ ሴት ናት ወይ? ወይስ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው? ምሳሌያዊ ንግግር ማለት ስለ አንድ ነገር በቦታው ገብቶ ወይም በፈንታው የሚጠራና የሚነገር ነገር ሲሆን፣ ለምሳሌ ራእይ 2:2 ኤልዛቤል የተባለች ሴት ምሳሌ አለ። የዚህች ሴት ታሪክ በ1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 16 እስከ ምዕራፍ 20 ላይ ሲገኝ ኤልዛቤል የዝሙትና የጣዖት አምላኪዎች ምሳሌ ነች። እንዲሁም ዮሐንስ ራእይ 17 ላይ ታላቂቱ ጋለሞታ (አመንዝራ ሴት) እናገኛለን። እርሱም ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን ልዩ የባዕድ አምልኮ የሚያደርጉትን ያመለክታል። በዮሐንስ ራእይ 19 ሌላ ሴት ትታያለች። ይህች ሚስት የተባለችውን እናገኛለን። ያውም የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ወይም ሙሽራይቱ ተብላ በዮሐንስ ራእይ 21:9 ላይ እናገኛለን። ስለዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር እንደሆነ እንወቅ።

ለነገሩ ራእይ 12:1–2 ላይ ያለችው ን ሴት ሰዎች በልዩ ልዩ መንገድ ይተረጉማሉ።

1. አንዳንዶች የኢየሱስ እናት ማሪያም ናት የሚሉ አሉ:: ግን መጽሐፉን ስንመረምር የኢየሱስን እናት ድንግል ማሪያምን አትመስልም:: ምክንያቱም ማሪያም ሰው ስትሆን፣ በዮሐንስ ራእይ 12:1–2 ላይ ሴት የተባለችው ግን ሰው ተብሎ ከተፈጠረ ከሰብአዊ ፍጡር በላይ የሆነች ስለሆነች ነው:: ፀሐይን መጎናጸፍ፣ ጨረቃን ከእግሩ በታች፣ 12 ኩከብ በራሱ ያደረገ ሰው ስለማይገኝ ለማሪያም ይህን ምሳሌ ማድረግ አይገባም:: ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ቦታ ምንም ተመሳሳይ ጥቅስ ለማሪያም የተጠቀሰ ነገር ስለሌለ እርሷ አትሆንም::

2. ሌሎች ደግሞ ይህች ሴት የተባለች ቤተ ክርስቲያን ናት የሚሉ አሉ:: ግን ቤተ ክርስቲያን አትመስል:: ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ሴት ተብላ አልተጠራችም:: ሙሽራይቱ ወይም ድንግል ተብላ ከምትጠራው በስተቀር 2 ቆሮ.11:2፤ ራእይ 19:7፤ 21:9:: ስለዚህ ይህች ሴት ቤተ ክርስቲያን አይደለችም::

3. ሌሎች ደግሞ የእሥራኤል ነገድ እንደሆነ ይናገራሉ:: የእሥራኤል ነገድ በብሉይ ኪዳን መሠረት ከሆነ እውነትም እንደ ሚስት እንደ ሴት ተጠርታለች:: እግዚአብሔርም እንደ ባል ተጠርቷል፣ ኢሳ. 54:5፤ ኤር. 3:6–14፤ ሆሴዕ 2:4 ጀምሮ ተመልከት ኤር. 31:32፤ ሚክያስ 4:9–10:: ስለዚች ሴት ተጨማሪ ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፀሐይና ኩከብ፣ ስለ 12 ኩከቦች መኃልየ መኃልይ 6:10፤ መዝ. (104):2 በማየት ማጥናት ይቻላል::

መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ራሱን ይተረጉማል:: ስለዚህ ይህ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ 12 ኩከብ ማን እንደሆነ ወይም የማን ነገድ እንደሆነ ዘፍጥ. 37:9–11 ስለምናይ ቀጥታ ይህች ሴት የእሥራኤል ነገድ ምሳሌ መሆኗን እንረዳለን:: በተጨማሪ አዲስ ኪዳን ውስጥ በዮሐ. 4:22፤ ሮሜ. 9:4–5፤ ዕብ. 7:14 ተጽፏል::

ቁ. 2 <u>ምጥና ጭንቀት</u>

ሴትየዋ በምጥ ተይዛ ስትጨነቅ ትታያለች:: የሚወለደውን ልጅ ቤተሰብ ሁኔታ እናስብ:: የዚህ ልጅ ቤተሰብ ሁሉ በጭንቀትና በመከራ በጥበት መጻተኞችና ስደተኞች ሆነው በዚህ ዓለም ላይ እንደሚኖሩ ያስገነዝባል::

1. ዓለም እግዚአብሔር አብንና እግዚአብሔር ወልድን ጠላ፤ ዮሐ. 15:23–25::

2. ሥጋ ለብሶ የመጣው እግዚአብሔር ወልድ በዚህ ዓለም ራሱን የሚያስጠጋበት አልነበረውም፤ ሉቃስ 9:58፤ ማቴ. 8:20፤ የሐዋ. ሥራ 9:1–5::

3. ምድራዊ የእምነት አባቶች የሆኑ እነ አብርሃም፤ ይስሐቅና ያዕቆብ ሌሎቹም በዓለም ባይተዋር ሆነው ኖሩ፤ ዘፍጥ. 23:4:: 1ኛ ዜና 29:15፤ መዝ 39:12፤ ዕብ. 11:13–16፤ 1ኛ ጴጥ. 2:11::

ለምሳሌ በግብጽ፤ በፍልስጥኤም፤ በከነዓን፤ በከለዳውያን፤ በባቢሎንና በአሦርያ ስንት ጊዜ መጻተኞች ሆኑ? ዛሬ እኛም በእምነት የአብርሃም ዘር ነን፤ ገላ. 3:29፤ ፊልጵ. 3:20፤ 2ኛ ቆሮ. 5:2–10:: በዚህ ዓለም የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሁሉና የምድር ፍጥረት ሁሉ ይቃትታል::

1. ፍጥረት ሁሉ ይቃትታል፤ ሮሜ 8:22
2. እኛ የጌታ ልጆች እንቃትታለን፤ ሮሜ 8:23–25
3. መንፈስ ቅዱስ ራሱ ይቃትታል፤ ሮሜ 8:26–27
4. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ተመልሶ በመምጣት ፍጥረትን ሁሉ ጻጥ እስከሚያደርግ ድረስ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ውስጥ በጭንቀትና በምጥ ትኖራለች፤ ማቴ. 24:8፤ 1ኛ ተሰሎ. 5:3–4፤ ሉቃስ 21:34–35፤ መክብብ 9:12:: በዛሬ ዘመን የጌታ ልጆች ሁሉ ይሰደዳሉ፤ 2ኛ ጢሞ. 3:12፤ ዮሐ. 15:20፤ የሐዋ. ሥራ 14:22፤ 2ኛ ቆሮ. 4:9::

ቁ. 3ና4 <u>ታላቅ ቀይ ዘንዶ</u>

በዚህ ቦታ ሐዋርያው ዮሐንስ እንደገና በጣም አስደናቂ ነገር በሰማይ እንደተመለከተ ያሳያል:: እግዚአብሔር ድንቅ ነገር ያሳየዋል፤ ቁጥ 3ና4 እንደገና አንብብ:: ቁጥር 3 ሐዋሪያው ዮሐንስ በሰማይ ሌላ ምልክት ተመለከተ:: ዮሐንስ ያየው ምልክት መልኩ ቀይ ዘንዶ ነበረ:: ይህ ቀይ ዘንዶ ማን ነው? መልሱን ቁጥር 9 ላይ ተመልከት:: በዮሐንስ ራእይ 12 ላይ ይህ ቀይ ዘንዶ የተባለው ዲያቢሎስ ሰይጣን የቀድሞ እባብ ነው:: እግዚአብሔር ሰይጣንን እስካሁን ጊዜ ድረስ የዓለም ገዢ የዚህ ዓለም አምላክ እንዲሆን ፈቅዷል፤ ኤፌ. 2:2:3 በአየር ሥልጣን ያለውና የጨለማ ዓለም ገዢ ተብሎ ተጠርቷል፤ 2ኛ ቆሮ. 4:4፤ ኤፌ. 6:12::

ሰይጣን ኢየሱስን ይህ ዓለም የእኔ ነው ለኔ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ዓለም ለአንተ እሰጥሃለሁ ያለው (ማቴ. 4:8–9) በዚህ ምክንያት ነው። ይህንን ዓለም በኃይል የሚገዛ በራእይ 12 ላይ ያለው ቀዩ ዘንዶ (ሰይጣን) ምን ያደርጋል? ቁጥር 4 ተመልከት።

ከሴቲቱ የሚወለደውን ሕጻን ሊውጥ ወይም ሊገድል ይቆማል። እርሱ ማለት ዘንዶው ደም ፈላጊ ነው። ደም ጠጪ ነው። ነፍሰ ገዳይ ነው። እርሱ ማንንም አይምርም። ስለዚህ ነው ኢየሱስ በዮሐንስ 8:44 ላይ ከጥንትም ነፍሰ ገዳይ ነው ያለው። ከእርሱ ለመዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ ነው የሚያዋጣው። በያዕ. 4:7–8 በጌታ ኢየሱስ ስናምን ከእኛ እንደሚሸሽ ተናግሯል። ስለዚህ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

ዮሐንስ ሲመለከት የሚወለደውን ልጅ ሊውጥ በሴቲቱ ፊት ቆሞ ነበር። ሰይጣን ለማንም ሕይወት አይገደውም፣ አይራራም፣ ጨካኝ ነው። የእግዚአብሔርን ልጅ ሕይወት እንኳን ሊያጠፋ ይፈልግ ነበር። ነገር ግን ኃይል የለውም አይችልምም።

ቁጥር 4 ስለ 7 ራሶችና አስር ቀንዶች
ቁ. 4 ላይ ያሉት 7 ራሶችና አስር ቀንዶችን የሚመለከት በዮሐንስ ራእይ 13 ተመልከቱና መርምሩ። ደግሞ ምዕ. 17:9 ላይ ትርጉም አለው።

1. 7 ራሶች:– ሰይጣንና ሃሳዊ መሲህ ያላቸውን ግንኙነትና ሁኔታን ያሳያል፣ ምዕ. 13 በደንብ ተመልከት። ሰይጣን ደግሞ ከዓለም መንግሥታት ጋር ያለውን ግንኙነትና ሁኔታ ያሳያል፤ ምዕ. 17 ተመልከት።

2. 10 ቀንዶች ቁጥር 3 ላይ አስር ቀንዶች በዘንዶው ላይ ነበረ። እንዲሁም ደግሞ በሐሳዊ መሲህ ላይም አለው፤ ምዕ. 13:1 ተመልከት። አስሩ ዘውዶች አስር የዓለም መንግሥታትን ያሳያል። ሰባት ዘውዶች በራሱ ላይ ያለው በቁጥር 3 ሥልጣንንና ገዢነትን በሰይጣንና በሐሳዊው መሲህ አማካይነት የሚሰጣቸውን የዓለም መንግሥታት ያሳያል።

ሐሳዊ መሲህ የዲያቢሎስ ባለሥልጣን ሆኖ የሚነሳ ሰው ሲሆን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ሥራ ከምድር ጨርሶ እንዲያጠፋ የሚሞክር የራሱና የዲያቢሎስን መንግሥት እንዲያጸና የሚያደርግ ነው። ግን ኃይሉ፣ መንግሥቱና ሥልጣኑ ወድቋል፣ ተጣለ ይላል ራእይ 12:9–12።

ቁ. 4 የሰይጣን አወዳደቅ

ጅራቱ የሰማይን ከዋክብት ሲሦ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው ይላል:: ከሴቲቱ የሚወለደውን ሕፃን ሊበላ በፊቷ ቆሞ የነበረው ዘንዶ ከመላእክቱ ጋር እንዴት እንደ ወደቀ ዮሐንስ ሲያስረዳን የሰማይን ከዋክብት ሲሦ (1/3ኛ) እጅ በጅራቱ ወደ ምድር እንደጣላቸው ይናገራል:: ራእይ 12:7:: በእግዚአብሔር መልአክ አለቃ ሚካኤልና በሠራዊቱ፣ እንዲሁም የሰይጣን መልአክ ራሱና በሠራዊቱ መካከል ጦርነት እንደነበረ ይናገራል:: ወይም በቅዱሳን መላእክትና በክፉ መላእክት መሃከል የነበረ ጦርነት በሰማይ እንደነበረ ይገልጻል::

በዮሐንስ ራእይ 12:4 ከዋክብት የሚለው መላእክት መሆኑን የሚገልጽ በኢሳ. 14:12–17 ስታነቡ ታገኛላችሁ:: በተለይ ቁጥር 13 ላይ የሰይጣንን ፍላጐት ታገኛላችሁ:: በእግዚአብሔርና በመላእክት ላይ ዙፋኑን ከፍ ከፍ አደርጋለሁ የሚለውን ቃል አስተውሉ:: 5 ጊዜ አደርጋለሁ ይላል:: በቁጥር 14 በ5ኛው ጊዜ በልዑል እመስላለሁ ሲል እንደ እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ እሆናለሁ ማለቱ ነው:: የእግዚአብሔርን ቦታ መውሰድ ፈለገ:: ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ከሦስተኛው ሰማይ ተጣለ:: በዚህ ምክንያት ከመላእክት ሲሦው (1/3ኛው) እርሱን ተከትለዋል:: 2/3ኛ ማለት ሁለት እጅ የሚሆኑ የሚበልጥ ቁጥር ግን ሰይጣንን ሳይከተሉ ከእግዚአብሔር ጋር ቀርተዋል:: ከእግዚአብሔር ጋር የቀሩት መላእክት ብዙ ስለሆኑ ማንም ሊቆጥራቸው አይችልም፣ ዮሐንስ በራእይ 5:11 ሲገልጽልን እንዲህ ይላል::

የወደቁትም 1/3ኛ ማለት ሲሦው ቢሆንም ጥቂት ሠራዊት አይደሉም ብዙ ናቸው:: እነርሱ የሰይጣን ሠራተኞችና አገልጋዮች ናቸው:: ሰይጣን በአንድ ጊዜ ሁሉ ቦታ ስለማይደርስ የእርሱ መላእክት የሆኑትን እርኩሳን ሠራዊት በልዩ ልዩ ቦታ ወክሎ ያስቀምጣቸዋል፣ ይሰድዳቸዋል ማለት ነው:: ሰይጣን በራሱ ብቻ ክፉትን ለዓለም ሁሉ ሊያዳርስ አይችልም:: ብዙ ወኪሎች በየቦታው ይኖራሉ:: በዚህ ምክንያት ነው ክፋት በዓለም ሁሉ የሚሞላው::

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገልጽልን ከክፉ መላእክት መካከል የታሠሩ እንዳሉ ነው:: ይሁዳ፣ 6፤ 2 ጴጥ.2:4፤ ራእይ 9:14:: ይህ 1/3ኛ የሆኑ ከዋክብት የነበሩት መላእክት ዛሬ በዓለም ላይ የሚሠሩትም ቢሆን ወይም የታሠሩት ቢሆኑ መጨረሻቸው ምን ይሆን? ማቴ. 25:41

ተመልከት:: ሌላ ማስተዋል የሚገባን ነገር በዚህ ቁጥር 4 ሰይጣን በሴቲቱ ፊት መቆሙን ነው:: ይህ ጠላት ምንም ጊዜ በክርስቶስና በሴቲቱ ፊት በመቆም እንቅፋት መሆን ይፈልጋል:: የእርሱ ሃሳብ ላጥፋቸውና እኔም ራሱ ልጥፋ ስለሆነ እነርሱን አጥፍቶ ሊጠፋ ይሞክራል:: በዘፍጥረት 3:15 ላይ በሴቲቱና በእባቡ መካከል ጠላትነት እንደ ተደረገ አንርሳ:: ይሁን እንጂ ሰይጣን የሚወለደውን ወንድ ልጅና ሴቲቱን ሊያጠፋ ቢሞክርም ጥፋት በራሱ ላይ ተመለሰበት እንጂ ሊያጠፋቸው አልቻለም:: ከሴቲቱ የተወለደው ልጅ ግን በመስቀል ላይ በመሞት የሰይጣንን ራስ ቀጥቅጧል፣ ዕብ. 2:14፤ 1ኛ ዮሐ. 3:8፤ ሮሜ 16:20:: በመጨረሻ ደግሞ እንዲህ ይሆናል፣ ራእይ 20:10 ተመልከት::

ቁ. 5 ተመልከት

## ወንድ ልጅ

በዚህ ቁጥር እንደምንመለከተው እግዚአብሔር በዮሐንስ በኩል ለቤተ ክርስቲያን ስለ ልጁ ጠቅላላ የሕይወቱን ታሪክ በአንድ ቁጥር አጠቃሎ ያሳያል:: ያውም ስለ እግዚአብሔር ልጅ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ከመወለዱ አንስቶ እስከ ትንሳኤው ያለውን ታሪክ ነው የሚያወራው:: ልጁ ከሴቲቱ ተወልዶ ወደ ሰማይ እስኪነጠቅ ድረስና በእግዚአብሔር ዙፋን በቀኙ እስኪቀመጥ ድረስ ያለውን ቁጥር 5 አንብብ:: ደግሞ ለወደፊት በምድር ላይ ሺህ ዓመት እንደሚነግሥና አሕዛብንም በብረት በትር እንደሚገዛቸው ሲገልጽ በተለይም በመዝሙረ ዳዊት 2:9 ላይ ያለውን ትንቢት በሰማይ እንዴት እንደሚፈጸም ይገልጻል:: ያ ቀይ ዘንዶ የእግዚአብሔርን ልጅ ለመዋጥ እንዴት እንዳሳደደው በሕይወቱ ታሪክ እናውቃለን:: ማቴዎስ 2 በሔሮድስ በኩል፣ ማቴዎስ 4 በፈተና፣ በሐዋርያት በኩል ማቴ. 16:22፤ ሉቃስ 2:2–3፤ ዮሐ. 15:27፣ ሉቃስ 22:31፣ በካህናት በኩል ማቴ. 27:41–44 በተለይም በስቅለቱ ጊዜ በጲላጦስ፣ ዮሐ. 18:28፤ በሄሮድስ፣ ሉቃስ 23:6፤ በመቃብር ላይም ማቴ. 27:62–66 ተመልከት:: ልጁ ግን ሁሉን ድል አድርጐ ተነሣ፣ ማቴ. 28:1–10:: ከዚያም 40 ቀን እየታያቸው ቆይቶ ወደ ሰማይ አረገ፣ የሐዋ. ሥራ 1:9–11:: ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በመውጣቱ ዛሬ ጠላት ዘንዶ ተዋረደ፤ ተሸነፈ:: ድል ሆነ:: ድሉ የአምላካችን፣ ድሉ የጌታችን ነው ድሉ ዘምሩ ክርስቲያን ሃሌሉያ!!

ቁ. 6 እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ ይመግባል።

ሴቲቱ ወደ ምድረ በዳ ተነጠቀችና ተመገበች። እግዚአብሔር ለግብግ ይጠራናል፣ ኢሳ. 55፡1–2። ይህ የእግዚአብሔር ወገን እግዚአብሔር የመገበውና ያደረገውን ነገር ያሳስበናል።

1. እሥራኤልን በምድረ በዳ እንደመገበ መዝ. (78)፡23–28፤ (105)፡40።
2. ኤልያስን በምድረ በዳ እንደ መገበ ያሳስበናል፣ 1ኛ ነገ. 17፡1–7፤ 19፡1–8።
3. ማርያምና ዮሴፍ ከሕፃኑ ከኢየሱስ ጋር ወደ ግብጽ በሸሹ ጊዜ በምድረ በዳ ምን ደርሶባቸው ይሆን? ማቴ. 2፡13።
4. ኢየሱስ ክርስቶስ በምድረ በዳ አንድ ጊዜ አራት ሺህ ሰው (4000) መገቧል፤ ማቴ. 15፡32–39። ሌላ ጊዜ አምስት ሺህ (5000) ሰው መገቧል፣ ዮሐ. 6፡1–14።
5. እግዚአብሔር ዛሬም ለተራበችና ለተጠማች ነፍስ የሕይወትን ምግብ ይመግባል፣ዮሐ.4፡11–14፤ ዮሐ. 6፡35፤ ዮሐ.7፡37–39።

ቁ. 7–9 ከሳሹ ተጥሏል

1. ከሳሽ ማለት ባላጋራ ነው፤ ቁ. 9። የጥንት ጻድቃንን ይከሳቸው ነበር።

ሀ/ ኢዮብን ከሷል፣ ኢዮብ 1፡6–22፤2፡1–6

ለ/ ኢያሱን ከሷል፣ ዘካ. 3፡1–2፤ መዝ. (109)፡6

ሐ/ ዛሬም የክርስቶስን ወገኖች ሊከሳቸው ቢሞክርም በክርስቶስ ደምና በክርስቲያኖች ምስክርነት ይሸነፋል ራእይ 12፡10–11።

ቁ. 10–12 ታላቅ ዜማ በሰማይ የድል ዜማ ነበር።

የዝማሬው ምክንያት፡–

1. ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስ ስለ ሆነ
2. ወንድሞች ማለት ክርስቲያኖች ስለ አሸነፉ ታላቅ ድምጽ በሰማይ ይሰማ ነበር፣ ቁጥር 10።

ጠላታቸው ሰይጣን ክርስቲያኖችን የተዋጋበት መንገድ

ሀ/ በማታለል መንገድ ክርስቲያኖች እንዲስቱ ያደርጋል፣
ለ/ በማስፈራራት መንገድ ክርስቲያን እንዲክድ ያደርጋል፣
ሐ/ በማሰቃየት መንገድ ክርስቲያንን እንዲክድ ያደርጋል፣

3. ይዘምሩ የነበሩት የጸኑትና ያሸነፉት ጻድቃን በሰማይ የነበሩት ናቸው።

በምን አሸነፉ?

1. ከበጉ ደም የተነሳ፣ በደሙ ባለው ኃይል ነበር። ክርስቶስ በመስቀል መሞቱ፣ በመቃብር መቀበሩ፣ በሦስተኛው ቀን መነሳቱ ሰይጣን መቋቋም የማይችለው ትልቅ ኃይል ነው።

አዝማች:–አ ግሩም ኃይል ነው
አ ግሩም ኃይል ነው ጌታዬ ሆይ!
ሀ/ በክንድህ ውስጥ ያለው አ ግሩም ኃይል ነው
ለ/ በልብህ ውስጥ ያለው አ ግሩም ኃይል ነው
ሐ/ በደምህ ውስጥ ያለው አ ግሩም ኃይል ነው
መ/ በሞትህ ውስጥ ያለው አ ግሩም ኃይል ነው።

በክርስቶስ ሞት ዲያቢሎስ ተሸንፎ ወድቋል።

2. ከምስክርነታቸው የተነሳ፣ አማኞች ነፍሳቸውን እስከ መጨረሻ እስከ ሞት አሳልፈው ሰጥተዋል። በእርሱም ታምነዋል። ስለዚህ ሙሉ የኃጢአት ይቅርታ ስለአገኙ ይዘምራሉ። እነዚህ የሚዘምሩት ፃድቃን ከሕይወታቸው በላይ ለጌታቸው ሕይወታቸውን ለመስጠት፣ ለመገዛትና ለመታዘዝ ጌታን ስለመረጡ አይበገሩም ነበር፣ ዮሐ. 12፡25፤ ማቴ. 10፡39፤ 16፡25፤ ማር. 8፡35፤ ሉቃስ 9፡24፤ 17፡33።

ሰይጣን በሰማይ መብቱን ተገፎ ኃይሉ ተወሰደበት። ከሰማይም ወደ ምድር ተጣለ። ኃይሉና ሥልጣኑ በምድር ብቻ ስለሆነ፣ እርሱ ከመጥፋቱ በፊት ምድርን ሊያጠፋ ይፈልጋል። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ ሰይጣን ክርስቶስን ለማጥፋት የሞከረው። ክርስቶስ ቢሞት መልካም ነው። ክርስቶስን አስገድዬ ማረፍ አለብኝ፣ እርሱን ካስገደልሁ በቃ ሁሉም በእጄ ይሆናል ብሎ ተነሳና:–

ሀ) በሔሮድስ በኩል ሥራውን ጀመረ፣ ማቴ. 2:16

ለ) በምኩራብ ሕዝብ ሊያስገድለው ሞከረ፣ ሉቃስ 4:28–29

ሐ) በራሱ ሞከረ፣ ማቴ. 4:1–11

መ) በአውሎ ነፋስ ለማጥፋት ሞከረ፣ ሉቃስ 8:22–24

ሠ/ ከጌቴሰማኔ እስከ ጉልጐታ፣ ማር. 14:30፤ ምዕ.15 ለማሰቃየት ሞከረ:: ኢየሱስን በወንጀለኛ ሁኔታ እንዲሞት አደረገ::

ኢየሱስ ከሞተም በኋላ በሰይጣን ከባድ ፍርሃት ገባበት:: በኢየሱስ ሞት ሰይጣን እንደሚሸነፍ እግዚአብሔር ያውቅ ነበረና ኢየሱስ እንዲሞት የእግዚአብሔር ፈቃድ እቅድ ይፈጸም ዘንድ ኢየሱስ እስከሞት ታዘዘ፣ ፊልጵ. 2:6–11::

ሰይጣን ኢየሱስ የሞተ እንደሆነ የሚያሸንፍ መስሎት ክርስቶስን በማሰቃየት እንዲገድሉት ጭፍሮችን ሰደደ:: ኢየሱስ ቢቀበርም እንኳን ሰይጣን እረፍትን አላገኘም:: ስለዚህ ነው መቃብሩ በጥብቅ እንዲጠበቅ ያደረገው (ማቴዎስ 27:62–66) ሙከራው ብዙ ቢሆንም ሰይጣን ተሸነፈ:: ስለዚህ ነው በዮሐንስ 12:24–25 የእግዚአብሔር እቅድ በክርስቶስ ሞት የሰይጣንን ድል መመታት የሚገልጸው:: ኤፌ. 1:20–21፤ ፊልጵ. 2:9–11፤ መዝ. (110):1:: ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ:: ጠላታችን ተዋረደ:: በሁለት ቦታ ተሸነፈ::

1. በሰማይ፣ ራእይ 12:7–9
2. በምድር፣ ራእይ 12:11::

ቁ. 13–17 ዘንዶ ሰይጣን ነው:: ወደ ምድር መጣሉን ባየ ጊዜ ሴቲቱን ማሳደድ ይጀምራል:: ሴቲቱ የቤተክርስቲያን፣ የእግዚአብሔር የተመረጠ ሕዝብ፣ ክርስቶስ የመጣለት ቅዱስ ወገንን ይመስላል:: የዘንዶው ሙከራ፣ ሕዝቡን የሚያድን ከሴቲቱ የተወለደውን ወንድ ልጅ ሊያጠፋ ነበር፣ ቁጥር 4–6 አይተናል:: አሁን ግን ሰይጣን ሃሳቡን ቀይሮ ሴቲቱን ማሳደድ እንደ ጀመረ እናያለን:: ሰይጣን ሴቲቱን ማሰቃየት ልጁን ማሰቃየት፣ ሴቲቱን ማሳደድ ልጁን ማሳደድ ነው ብሎ ያምናል ያደርጋልም::

የሐዋርያት ሥራ 9:4 ላይ በደማስቆ መንገድ ጳውሎስን የተገናኘው ኢየሱስ እንዲህ አለው:–

- ክርስቲያኖችን ማሳደድ ክርስቶስን ማሳደድ ነው።
- ቤተ ክርስቲያንን ማሳደድ ክርስቶስን ማሳደድ ነው
- ቤተ ክርስቲያንን ማበላሸት ክርስቶስን ማበላሸት ነው።
- ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ክርስቶስን ማገልገል ነው።
- ቤተ ክርስቲያንን መርዳት ክርስቶስን መርዳት ነው።

በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች ሴቲቱን (ቤ/ክንን) በምን ሁኔታ እንመለከታለን? እንደ ኢየሱስ ነው ወይ? ሴቲቱ ወደ ምድረ በዳ ተወስዳ እንደ ተመገበች በቁጥር 6 አጥንተናል። ቁጥር 14 ላይ ለሴቲቱ ሁለት የንስር ክንፍ እንደተሰጣት ተጽፏል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የንስር ክንፍ የሚል በርካታ ቦታ እናገኛለን። ምሳሌውም ታላቁ የእግዚአብሔር ክንድ አማኞችን እንደሚሸከም ያመለክታል፣ ዘጸ. 19፡4፤ ዘዳ. 32፡11–12፤ ኢሳ. 40፡31፤ 46፡3–4፤ 60፡4፤ ኢሳ. 63፡9። ዛሬም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል እጆቹን ዘርግቶ ኑ እንደሚለን ያሳየናል፣ ማቴ. 11፡28–30፤ ኢሳ. 65፡2፤ ሮሜ 10፡21።

ቁጥር 15–17 ዘንዶው ወንዝ የሚያክል ውኃ ከአፉ እንደፈሰሰ በቀጣና በንዴት ስደትን በሴቲቱ (በቤ/ክ) ላይ ማንሳቱን ዳዊት እንዲህ ይላል፣ መዝ. 42፡7፤ 32፡6፤ (124)፡2–8፤ ኢሳ. 43፡2። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው።

ምድሪቱ ሴቲቱን ረዳቻት፤ እግዚአብሔርን ለሚፈልግ ሰው፣ ሁሉ ነገር ወዳጅ ነው። ለበጎ ይሆናል፣ ሮሜ 8፡28። ፍጥረት ሁሉ ደስ ይለዋል። ፍጥረት ሁሉ ይረዳዋል፣ ይጋርደዋል፣ መዝ. 34፡7–10፤ ራእይ 12፡16 ተመልከት።

ቁጥር 17 ጌታ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ችግር፣ ስደት በቤተ ክርስቲያን ላይ የመኖሩና የመቀጠሉ ምክንያት ጠላት ስለማይተኛ ነው። እንወቅ ሰይጣን ጠላት እንደ አንበሳ ይዞራልና እንጠንቀቅ፣ 1ኛ ጴጥ. 5፡8።

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 13

በዚህ ምዕራፍ ብዙ ልዩ ልዩ ነገሮችን ስለምናይ በትዕግሥት እንከታተል:: ሰይጣን በመጨሻው ዘመን የሚቀጠምባቸውን ዘዴዎች ይገልጽልናል::

## የእርኩስ ሥላሴ አሠራር

ሰይጣንና ሁለቱ ከባህር የሚወጡት አውሬዎች ከተባሉት ወኪሎቹ ጋር በመሆን ሦስቱ አብረው ይሠራሉ:: በመጀመሪያ በዚህ ክፍል የምናየው ሦስቱ የጽድቅ ጠላቶች፣ ዲያብሎስና ሁለቱ አውሬ የተባሉትን የክፋት ሥሉስ እንላቸዋለን:: ሦስቱ ሥልጣንን አንዱ ከአንዱ እየተቀባበሉ ስለሚሠሩ የእርኩሳን ሥሉስ ክፋትና ሥራቸው ሲሆን በአሠራር እንደ ሥላሴ ለማስመሰል ይሞክራሉ፣ 2ኛ ቆሮ. 11:14–15፣ 2ኛ ተሰሎ. 2:4::

<u>ለምሳሌ</u> በቅድስተ ሥላሴ እግዚአብሔር አብ አንዱ አካል ሲሆን፣ ሁለተኛው እግዚአብሔር ወልድ፣ ሦስተኛው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ናቸው:: በርኩሳን ሥሉስ አንደኛው ዘንዶ ሰይጣን ምዕ. 12:9 በርኩሳን ሥላሴ፣ ሁለተኛው መካል የመጀመሪያ አውሬ መሆኑን ምዕ. 13:1–10 ስናይ ሦስተኛው የርኩሳን ሥላሴ ሦስተኛ አውሬ ወይም ምዕ. 13:11–18 ያለውና ሐሰተኛው ነብይ መሆኑን እንመለከታለን:: በዚህ ሁሉ ሰይጣን የዓለምን ሕዝብ የመጨረሻ እድሉን ተጠቅሞ እንደሚያስታቸው ያመለክታል::

ሐዋርያው ጳውሎስ በመጨረሻ የክርስቶስ ተቃዋሚ እንደሚነሳ በ2ኛ ተሰሎ. 2:9–10 በራሱ ጊዜ እንደሚሆን ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ያሳስባቸው ነበር:: ሐዋርያው ዮሐንስም የዚህን የሐሳዊ ወይም የአውሬ መንፈስ በዮሐንስ ዘመን እንኳን እንደሚሠራ ገልጾልናል:: ሰውየው ባይነሳም እንኳን መንፈሱ ይሠራ ነበር ማለት ነው፣ 1ኛ ዮሐ. 2:18–22፣ 1ኛ ዮሐ. 4:3 ተመልከት::

ባህር የተባለውን ትርጉም ምዕ. 13:1 እንዲሁም ምዕ. 17:15 አወዳድራቸው::

በሉቃስ 21:25–26 ላይ ኢየሱስ ከባህርና ከሞገድ (ሕዝብ) የተነሳ ይጨነቃሉ ብሏል፣ ኢሳ. 57: 20 የሰውን ልብ በፍርሃትና በስጋት በሚያስጨንቅ ዘመን፣ ሰይጣን የራሱን ሰው ለዓለም ሰላምን፣ ጸጥታንና

ዋስትናን የሚሰጥ አስመስሎ ያቀርበዋል:: ይህም ሰው አውሬ የተባለው ገዢ የራሱን ፕሮግራምና እቅድ ይዞ ለዓለም ስለሚቀርብ ብዙዎቹ ይስቱና ይከተሉታል::

ቁ. 1–9 አንድ ሰው በሚኖርበት ዘመን ለእግዚአብሔር ወይም ለሰይጣን መሣሪያ ወይም ሠራተኛ መሆን እንደሚችል በዚህ ቦታ ያመለክተናል:: እኔና እናንተ ለማን ቆመን እናገለግል ይሆን? በዮሐንስ ራእይ 12 መጨረሻ ላይ በቁጣ ወደ ምድር የተጣለው ወይም የወረደው ጠላት ዲያብሎስ፡ በቁጣ በባህርና በአሸዋ ላይ መቆሙን ቁጥር 17 ይገልጽልናል::

በምዕ. 13 ላይ ባህርና ምድር የተጨመቁ ይመስል አውሬዎችን ሲያወጡ ተመልከቱ::

1. በቁጥር 1 አንደኛው አውሬ ወጣ
2. በቁጥር 11 ሌላው አውሬ መጣ ይላል::

ስለዚህ ሁለት አዲስ አውሬዎችና የፊተኛው አንዱ ዘንዶ የተባለውን ሲጨምር 3 አውሬዎች መሆናቸውን እናስተውል::

<u>ዋናው ነገር</u> ሰይጣን እንደ ተጣለና ጊዜው አጭር መሆኑን ስለተረዳ ክፉትን አፍጥኖ የሚሠራበትን መንገድ ይከፍታል:: ስለዚህ ሁለት አውሬዎችን ሊወክል ነው ማለት ነው:: ዮሐንስ በራሱ ዘመን የተመለከታቸው አውሬዎች በዳንኤል 7:3–7 ከተመለከታቸው አውሬዎች ጋር ስለሚመሣሠሉ ራእይ 13:2 በዳንኤል 4 ትላልቅ አውሬዎች የሚለው የትልልቅ መንግሥታት ምሳሌ እንደሆኑ ልብ እንበል:: በእነዚያ ዘመን የዓለም ግዛትና ኃይል በእነርሱ እጅ ነበር::

1. እንደ አንበሳ፣ የባቢሎን መንግሥት
2. እንደ ድብ፣ የሚድያን መንግሥት
3. እንደ ነብር፣ የፔርገርያ መንግሥት
4. የግሪክ መንግሥት ሆኖ ሲታይ ዮሐንስ በቁጥር 2 ልዩ ልዩ አካል ክፍል የሚወክለውን ጨካኝ የሮም መንግሥት ራሱ ነው ብሎ ሳያስብ አይቀርም::

ራሱንና ቤተ ክርስቲያንን ሊበሉ የቀረቡ የሮም መንግሥት ገዢዎችን ሲያስብ ለምሳሌ:–

1. ቄሣር ጢቢረስ ከ 14–37 ዓ.ም.
2. ቄሣር ካልጎሉ ከ 37–41 ዓ.ም.

3. ቄሣር ክለወይስ ከ 41–54 ዓ.ም.
4. ቄሣር ኔሮ ከ 55–68 ዓ.ም.
5. ቄሣር በስጴስን ከ 69–79 ዓ.ም.፣
ቲቶ ከ 79–81 ዓ.ም.

ዲሞትን የተባለው ከ 81–96 ዓ.ም. ያሉትን መንግሥታት መስሉት ነበር:: ያም ሆነ ይሀ፣ ይህ አውሬ የተባለው ሰው መሆኑን እናስብ::

1. ሰይጣን
2. ሰይጣናዊ ሥልጣን የሚሰጠውን ሐሳዊ መሲህን
3. ሥልጣን የተቀበለውን ሐሰተኛ ነብይን ሲያመለክት

አውሬው በጅምሩ የሞተና የቆሰለ መስሉ ሲታይ የክርስቶስን ምሳሌ መሞቱና ትንሳኤውን ለመምሰል ያስመስለዋል:: ደግሞ አብ ሥልጣንን ለወልድ እንደ ሰጠው፣ ዘንዶውም በቁጥር 4 ላይ ሥልጣን ለአውሬው ሲሰጥ ይታያል:: በዚህም ዓለም በሙሉ ይከተለዋል:: ስለዚህ አንደኛው አውሬ ገናና ስለሆነ ታላቅ ስምና ግዕረግ ያገኛል:: በቁጥር 4 ላይ ማን እርሱን ይችላል? ይላል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ማን ይችላል? ማን እርሱን ይመስላል? የተባለና የተደነቀ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: በሌላ ፍጥረት ውስጥ አልተደረገም፣ ዘጸ. 15:11:: በዮሐንስ ራእይ ግን አውሬው ያንን ግዕረግ ለመውሰድና ለማግኘት ይሞክራል:: ሰውም እርሱን እንደ አምላክ ያመልከዋል:: በዳንኤል 7:8–20 ላይ እንደሚያመለክተው ይህ የሰይጣን መሣሪያ የሚሆን አውሬ የተባለው ሰው ወይም መንግሥት መሆን እንደሚችል ነው::

ቁጥር 5–9 <u>እግዚአብሔርን መሳደብ</u>

1. እግዚአብሔርን መስደብ ማለት ለእግዚአብሔር ብቻ መሆን የሚገባውን አምልኩ፣ ስግደት፣ ክብር መስጠትን የመሰለ ነገር ለሌላ መስጠት ማለት ነው:: ለኔ ብቻ ስገዱ፣ እኔን ብቻ አምልኩ ማለት በዳንኤል 3 ላይ ያለውን ዓይነት ያመለክታል::

2. የድር የሮም መንግሥታት ሕዝቡን በማስገደድ እነርሱን እንዲያመልኩ አድርገዋል:: እምቢ የሚል ሁሉ ከባድ ቅጣት ይደርስበት ነበር:: ለምሳሌ:–

ሀ) በመግደል
ለ) በእሳት በማቃጠል
ሐ) ለአራዊት በመስጠት
መ/ ሌላም ልዩ ልዩ ስቃዮች ይደርስባቸው ነበር::

ቁ. 6-7 ከ 37-41 ዓ.ም. የነበረው ንጉሥ ቄሣር ካሊጉለ የተባለው እንደ እብድ ያደርገው ስለነበረ ራሱን እግዚአብሔር ነኝ በማለት ሰዎች እንዲያመልኩት አድርጓል:: ለእሥራኤል ልጆች በቅዱስ ቦታ ላይ የራሱን ቅርጽ በማስቀመጥ እንዲያመልኩት ሥቃይ አሳይቷቸዋል:: የእግዚብሔርን ማደሪያ ከተሳደቡት ቄሣሮች አንዱ እርሱ ነበር:: አሁንም በአውሬው ኃይልና ሥልጣን ሰይጣን ብዙ ይጠቀማል ማለት ነው::

ቁ. 8 ሥልጣን ለተሰጠው ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፈ ሁሉ ይሰግዱለታል:: ስለ ሕይወት መጽሐፍና ስሞች በራእይ በብዙ ቦታ ይገልጽልናል:: ለምሳሌ፣ ምዕ. 3:5፤ 13:8፤ 17:8፤ 20:12-15፤21:27 አዲስ ኪዳን በሚጻፍበት ዘመን የነበረው የሮም መንግሥት የራሱን ዜጎች የሚመዘግብበት መዝገብ ስለነበረው በጥብቅ ይጠበቅ ነበር:: የእርሱ ዜጎች ዜግነታቸውን የሚያጡት፣

1/ ሲሞቱ 2/ ከጠፉ ወይም ሳይገኙ ሲቀሩ ነበር::

እንደዚሁም የእግዚአብሔር ወገን የሆኑትን የእርሱ መዝገብ ያውቃቸዋል:: የሕይወት መጽሐፍ ያውቃቸዋል:: ጌታን ክርስቶስን ሲቀበሉ ይመዘገባሉ፣ ሉቃስ 10:20:: ስለዚህ ጳውሎስ በኤፌ. 1:4 መጠራታቸውን መመረጣቸውን፣ ደግሞ 1ኛ ጴጥ. 1:19-20 የክርስቶስ መሥዋዕት ከዓለም ፍጥረት በፊት ለምርጦቹ መሞቱን ይገልጻል:: አንተስ ተመርጠሃል? በሕይወት መጽሐፍ ተመዝግበህ ይሆንን? ስለዚህ ነው በሮሜ 8:35 ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል የሚለው:: ከክርስቶስ ፍቅር የሚለይህ ነገር አለን? በክርስቶስ አምነህ ከሆነ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፈሃል ደስ ይበልህ!

ቁ. 10 ጆሮ ያለው ይስማ

በዚህ ቦታ የተጻፈው ቃልና ሐሳብ በጥንት ነቢያት ዘመን ለኤርምያስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ቃል ያለበት ሲሆን፣ ኤርምያስ 15:2 እንብብ:: ኤርምያስ የተነገረውን ለእሥራኤል ያስተላልፍ ነበር:: ለሞት የሚሆን፣ ወደ ሞት:: ለሰይፍ የሚሆን፣ ወደ ሰይፍ:: ለረሃብ የሚሆን፣ ወደ ረሃብ:: ለምርኮ የሚሆን፣ ወደ ምርኮ:: የሚማረክ ይማረክ፣ የሚገደል ይገደል:: ሐሳቡ ሲጠቃለል ከእግዚብሔር ኃይል የሚያመልጥ ምንም ነገር የለም ማለት ነው::

ኢየሱስ በማቴዎስ 26:52 ላይ ሰይፍ የሚያነሱ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና አለ::

በዚህ ቦታ ሦስት ነገሮችን ያሳስበናል፤ እንመልከት:-

1. ክርስቲያን በእምነቱ ምክንያት የሚደርስበትን ሁሉ በትዕግሥት መቀበል እንዳለበት ሲያስተምረን የሚታሠር ካለ በመታሠር፣ መከራ የሚቀበል ቢኖር ሳያጉረመርም ክርስቶስን በመከተል ምክንያት የሚመጣውን ሁሉ በእምነት ጸንቶ መቀበል አለበት።

2. ክርስቲያን በእምነት ምክንያት ለሚመጣበት ነገር ሁሉ ሰይፍን መምዘዝ ወይም ጠርነትን ማንሳት ወይም በጥላቻ መመልከት የለበትም። ወንጌላችን የፍቅርና የሰላም ነው እንጂ የጥልና የጦርነት ወንጌል አይደለም። ወንጌላችን የሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር ስለሆነ፣እግዚአብሔር በቃሉ የሚለውን መቀበል አለብን። በወንጌል ምክንያት የሚመጣውን ለመቀበል መዘጋጀት ይገባናል።

3. በወንጌላችን ክርስቲያን ከጠላት ጋር እንዲዋጋ የተሰጠ መሣሪያ በቁ. 10 ያለው ይሆናል። የቅዱሳን መሣሪያ ትዕግሥትና <u>በእምነት</u> መጽናት መሆኑን ያሳስበናል። ስለዚህ ይህን አዋጅ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማው፣ ራእይ 2:7፤ 3:6፤ 3:13፤ 3:20፤ 3:22።

ቁ. 11–14 ይህ አውሬ የተባለው፣ የበግ መልክና የዘንዶ ሁኔታ እንዳለው አስታውስ። የበግ ቀንዶች ሲል፣ እንደ በግ የዋህ መሆን ሊያስመስል ሲሆን፣ ይህ አውሬ በውጭ የበግ መልክና ምሳሌ አስመስሎ፣ በውስጥ ግን የዲያቢሎስ መልክ መኖሩን ያሳስበናል፣ ማቴ. 7:15 ተመልከት።

ቀንድ፣ ቀንዶች ምን ጊዜም በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ <u>ኃይልን፣</u> ጉልበትንና ሥልጣንን ያመለክታል። ይህ አውሬ የተባለው ሁለተኛው አውሬ ሐሰተኛ ነቢይ ተብሏል። ራእይ 13:11 እንዲሁም 16:13፤ 19:20፤ 20:10 ተመልከት። ይህ አውሬ የተባለው ሰው መሆኑን አንርሳ። የሰይጣን መኖሪያ ስለሆነ ሁሉን ነገር የሚሠራበትን ኃይልና ሥልጣን ከፊተኛው አውሬ ይቀበላል (ያገኛል)። በምዕ. 13:1 ላይ ያለው አውሬ ሐሳዊ መሲህ ሲሆን፣ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ መሲህ ለመምሰል ሁለት ነገሮችን ያደርጋል። ቁጥር 3 እና 12 አንብብ።

1. ለሞት የታረደና የቆሰለ /

2. ለሞቱ የሆኑ ቁስሎች መፈወስ ስለሆነ፣ የኢየሱስን መቁሰል፣ መሞትና መነሳትን ሊያስመስል ይሞክራል ማለት ነው።

ቁጥር 11 ላይ ያለው ሐሰተኛ ነቢይ ነው። ይህ ሁለተኛው አውሬ የተባለው ሰው ወይም ሐሰተኛው ነቢይ ስለ አንደኛው አውሬ ወይም ስለ ሐሳዊ መሲህ ኃይለኛና ጠንካራ ሠራተኛ ወይም ወኪል ይሆናል። ቁጥር 12 ተመልከት። የተሰጠው ዘመንና የሚኖረው ረጅም ጊዜ ባይሆንም እንኳ ለሰው ጭንቅ ፈጣሪና ለፊተኛው አውሬ ፍጥረት ሁሉ ቢሰግድለት ይፈልጋል።

ነገሩ የቅዱስ ሥላሴ አንድነትና ሦስትነትን አብ ወልድን እንደላከው፣ ወልድም አብን እንዳስተዋወቀና መንፈስ ቅዱስን እንዳስተዋወቀ፣ መንፈስ ቅዱስም የወልድ ወኪልና አክባሪ ሆኖ በምድር እንደሚሠራ፣ ወልድ እንዳስተዋወቀ ዮሐ. 16፡13–15 እንዲሁም የእርኩስ ሥላሴ ምሳሌ ያንን ሊያስመስል ነው። እባብ ሥልጣኑን ለአንደኛው አውሬ ወይም ለሐሳዊ መሲሕ ሲሰጠው፣ ሐሳዊ መሲህ ወይም አንደኛው አውሬ ሥልጣኑን ለሐሰተኛው ነብይ ወይም ለሁለተኛው አውሬ ሲሰጥ፣ ሁለተኛው አውሬ ሁሉን ተወክሎ በክፋት እንደሚሠራና ሁሉም ሰው ለሐሳዊ መሲህ እንዲሰግዱና ክብር እንዲሰጡለት ያደርጋል። በእነዚህ ዘመናት እግዚአብሔርን የሚያመልኩት በምድር ቢኖሩ እንዴት ያለ ጭንቅና መከራ ይሆን መሰላችሁ! እግዚአብሔርን የሚያመልኩት ሁሉ ለሐሳዊ መሲህና ለዘንዶ ምስል ክብር መስጠትና ማምለክ ስለማይፈልጉ ስደት ይበዛባቸዋል፤ ቁጥር 16–17 ተመልከት።

## ቁጥር 13–14 ታላላቅ ተአምራቶች

ይህ አውሬ የዓለምን ሕዝብ ሊያስት ወይም ሊያሳምን ብዙ ታላላቅ ተአምራቶችንና ምልክቶችን እንዲያደርግ ለሐሰተኛው ነቢይ ሥልጣን ይሰጠዋል። ተአምራቶቹ ምን ዓይነቶች ይሆኑ? ለምንስ እንደዚህ ይሠራሉ? መልሱ 2ኛ ተሰሎ. 2፡9–11 ተመልከት።

## የአውሬው ምስል መናገር

ቁጥር 15 ላይ ለሐሳዊው መሲህ ምስል በመሥራት ሰው ሁሉ እንዲሰግድለት፣ በሁሉ ቦታ ላይ ያደርጋል (ያስቀምጣል)። ያ የተሠራው ምሥል እንዲናገርና ትንፋሽ እንዲኖረው ያደርጋል። ይህ ሁሉ የሚደረገው የዓለም ህዝብ እንዲስትና እንዲያመልከው ነው። እንግዲህ ኢየሱስ በማቴ. 24፡15–16 የተናገረውን እንዲሁም በዳንኤል 9፡27 ያለውን ተመልከትና አመዛዝነው። በዚህ ጊዜ የሚሆን ይመስላል። ጊዜውም አንድ ሱባኤ ማለት ሰባት ዓመት መሆኑ

ነው:: ይህን ዓመት ለሁለት ብታካፍለው ሦስት ዓመት ተኩል ወይም 42 ወር ይመጣል:: ይህ ግማሹ ጊዜ መሆኑን ያሳያል::

ምስሉ ሕይወት ማግኘትና መነጋገር መቻሉ ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ፣ 2ኛ ቆሮ. 4:4 የእግዚአብሔር ምሳሌ፣ ዘፍጥ. ለመሆን እግዚብሔር ሰውን እንደ ፈጠረ ሰይጣንም ፈጣሪ ለመምሰልና ለመመለክ ይሞክራል:: እንግዲህ ይህ ሁሉ ቢሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን ፈጠረ ወይም መፍጠር ይችላል የሚልበት ቦታ ስለሌለ፣ ክርስቲያን ሁሉ መሳት የለበትም:: እውነተኛ ፈጣሪና አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነውና::

**ቁጥ 15–17 ምልክት ስለ መቀበል**

በዚህ ቦታ በሐሳዊ መሲህና በሐሰተኛ ነቢይ ወይም አውሬ በተባሉት በሁለቱ ሰዎች ዘንድ ሰው ሁሉ በቀኝ እጁ ወይም በግምባሩ ላይ ልዩ ምልክት እንዲያደርግ ይገደዳል:: ምልክቱም የአውሬው ስም ወይም ቁጥር ይሆናል:: ያንን ቁጥር ወይም ስም በቀኝ እጁ ወይም በግምባሩ ያላደረገ ሰው ቢኖር ሊገዛና ሊሸጥ አይችልም:: ማለት በረሃብ እንዲሞት ይደረጋል ማለት ነው:: ምልክቱም የእግዚአብሔርን ስም የሚሳደብና ጣዖትን የማምለክ ምልክት ነው:: ይህ ምልክት ወይም ቁጥር እንደመታወቂያ ካርድ ስለሚሆን፣ ብዙ ሰው ካርዱን ረስቶ ስለሚሄድ፣ በእጁ ወይም በግምባሩ የሚሆን ምልክት ግን ከወሰደው ጋር አብሮ ስለሚሄድ በግልጽ ቦታ ስለሚሆን ለሁሉ ይታያል:: ይህ ምልክት ከሌለ ግን መግዛትና መሸጥ አይችልም::

**ቁ.18 ይህ ቁጥር ነው የሚጻፈው 666**

የቁጥሩን ሚስጥር የሚያውቅ ጥበበኛ ሰው ብቻ ነው:: ለምሳሌ 1:7፤ መዝ.(111):10፤ ኢዮብ 28:28 ያውም ጥበበኛ ሰው የእግዚብሔር ሰው ብቻ ነው:: ይህ ቁጥር የሰው ቁጥር ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ 6 ቁጥር ሰው የተፈጠረበት ቀን ነው፣ ዘፍጥ. 1:26–31 ተመልከት:: 666 ይህ ቁጥር ገና በመሠራት ላይ ያለ ቁጥር ነው:: ይህ ቁጥር የሰው ቁጥር ነው:: ሰው ደካማ መሆኑን ይገልጻል:: ይህን ቁጥር የሚሰጥ ደግሞ ሰው መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: ሰው ራሱ ምንም መሥራት የማይችል መሆኑን ነው:: ለምሳሌ 7 ቁጥር በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሌር ቁጥር ነው:: ወይም ሙሉ ቁጥር ይባላል:: ሁሉንም የመቻል ቁጥር ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉን ፈጥሮ ከጨረሰ በኋላ ያረፈበት ቀን ነው፣ ዘፍጥ. 2:1–3::

666 ቁጥር የሚሰጥ ሰው ወይም ሐሳዊ መሲህ ሰው እንደሆነ አምላክ እንዳልሆነ ማሰብ አለብን። ሰው ጉዶሎ ነው። እግዚአብሔር ግን ሙሉ ነው። ሰው በእግዚአብሔር ሚዛን ሊቀመጥ አይችልም። አዎን ሰው ሊያታልልና እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ሊመስል ይሞክር ይሆናል። እውነተኛ ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው፣ ኤር. 17:5–10። ሰው ግን ውሸተኛ ነው። በውሸተኛ ሰው ወይስ በእውነተኛ እግዚአብሔር በየቱ ታምናለህ? ማንን ታገለግላለህ? ለማን ትሰግዳለህ? ለማንስ ትመሰክራለህ? በማን ሥራ ላይ ትደነቃለህ? ከሁሉ የሚበልጠውን እግዚአብሔርን ምረጥ!

## ትልቅ ልዩነት

በምዕራፍ 13 እና በምዕራፍ 14 መካከል ትልቅ ልዩነት አለ

1. ዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 13
   ጨለማ አስፈሪና ለሰው ልጆች መራራ ታሪክ፣ አሰቃቂ ሁኔታ ያለበት፣ የሰይጣን መንግሥት ተንሰራፍቶ የሚሠራበትና የሚታይበት ምዕራፍ ነው። ምዕራፍ 13 ስናነብ በምድር ላይ ምን ዓይነት ጊዜ ይሆናል ብለን የምንጠይቅበት ምዕራፍ ነው። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ሰዎች እንዴት ይሆናሉ? የሚለውን ጥያቄ መልስ ለማግኘት አስቸጋሪ የሚሆንበትም ነው።

2. <u>ወደ ምዕራፍ 14</u> ላይ ስንገባ ግን በጉን በጽዮን ተራራ ስናይ ያ ሁሉ ፍርሃትና ሰቀቀን ችግር ሁሉ ያበቃል። 14:1። የሚያድንህ በግ ክርስቶስ ሊያድንህ ቆሞ ይታያል፣ ደስ ይበልህ! ወደ በጉ ወደ ኢየሱስ ብትመለከት እረፍት ታገኛለህ፤ ከጭንቀት ሁሉ ታርፋለህ፣መጽናናትም ይሆንልሃል፣ኢሳ. 40:1–2።

3. ሰይጣን እግዚአብሔርን የሚወዳደር ይመስላል

1. በምዕራፍ 7:3–8 የእግዚአብሔር ባሪያዎች 144000 በግምባራቸው ታትመው ነበር። በምዕራፍ 13:16 ላይ ሰይጣን ማየት የሚያመልኩትን በግምባራቸው ወይም በቀኝ እጃቸው ሲያሳትም እንዳየን በምዕራፍ 14 ላይ ደግሞ የእግዚአብሔር ባሪያዎች በግምባራቸው የታተሙትን በጽዮን ተራራ በድል አድራጊነት ከጌታቸው ጋር (ከበጉ ጋር) እናያቸዋለን። ቁጥር 1ን አንብብ። በምዕራፍ 7 በመከራ ጊዜ የታተሙት በምዕራፍ 14 ከቁጥራቸው

አንድ እንኳን ሳይጠፉ ከመከራ በኋላ በድል ቦታ ተገኝተዋል። እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን አይረሳቸውም፣ ያቆማቸዋል እንጂ አይጥላቸውም።

2. ሰይጣን ያተማቸው መጨረሻቸው ምን ይሆን? የት ይገኙ ይሆን?

መልስ ምዕራፍ 19:20–21። የሰይጣን መጨረሻው ምን ጊዜም አያምርም። ድል መሆን ነው። ቅጣትና ፍርድ ያስከትላል፤ ሞትን ያመጣል። ስለዚህ ነው ኢየሱስ በማር. 9:34–48 ትልቅ ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያ የሚሰጠን፣ ማቴ. 25:41 እና 46።

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 14

## መግቢያ

1. ይህ ምዕራፍ ለእግዚአብሔር ልጆች ትልቅ መጽናኛ ነው። በዚህ ምዕራፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ሙሉ አሸናፊነት እናያለን። ይህ ምዕራፍ ክርስቶስ ለልጆቹ ሥራ ሲሠራና ክርስቶስን በጣም በበለጠ ልንተዋወቅ እንደምንችል እናያለን። መዝ. 2:6፤ ዕብ. 12:2፤ ራእይ 3:2፤ መዝ. (132):13።

2. ምዕራፍ 14 ለቀሩት ምዕራፎች እንደ አጠቃላይ ማውጫ ሆኖ ይታያል። በዚህ ምዕራፍ ወደ ፊት የምናያቸውን ነገሮች ዋና ዋና አድርጉ ያቀርብናልናል። ለምሳሌ ያህል፣

   ሀ) በጉ (ክርስቶስ) ከ144 ሺ ቅዱሳን ጋር በጽዮን ተራራ ላይ፣ ቁ.1–5
   ለ) የዘላለም ወንጌል የሚሰብክ መልአክ፣ ቁጥ 6–7
   ሐ) የታላቂቱ ባቢሎን መውደቅ፣ ቁ. 8
   መ) ለአውሬው በሚሰግዱበት ላይ ያለው ፍርድ፣ ቁጥ 9–11
   ሠ) በጌታ ለሞቱት ያለው ብፅዕና (ዕድለኞች) ቁ. 12–13
   ረ) የአርማጌዶን ጦርነትንና የመሳሰሉትን ይዟል፣ ቁ. 14–20

ቁ. 1 ከበጉ ጋር በጽዮን ተራራ ላይ ነበሩ። ከበጉ ጋር የሚቆሙት ድል አድርገው ነበር ። ዛሬ ለኛስ? 2ኛ ቆሮ. 2:14 በድል አድራጊነት ያዞረናል።

መታተም፣ መታተም ምንን ያመለክታል?

1. የእርሱ የባለቤቱ መሆኑን ያመለክታል:: በዘመናዊ ሁኔታ የተያዙ ከብቶች የባለንብረቱን ማህተም በጆሮዎቻቸው ይሸከማሉ:: የማን መሆናቸውን ይገልጻል:: የክርስቶስ የሆኑትም እንዲሁ ነው::
2. እንደሚገዙለት ያመለክታል:: ማን ይገዛል?
3. ዋስትና ወይም ደህንነት ይሰጣል:: ዋስትና ለባለቤቱ የመኖር ምልክት ነው::
4. የምትደግፈውን የምትመካውን ያሳያል::
5. የሚያድን አለ ማለት ነው::

የማህተሙ ባለቤት ውድ እህቴና ወንድሜ ሆይ ለአንተስ (ለአንቺስ) ዋስ የሚሆን ማን አለ? በማንስ ማህተም ታትመሃል? ማንስ አተመህ? ኤፌ. 4:30፤ 2ኛ ቆሮ. 1:22::

ቁ. 2–3 በዚህ ጥቅስ መሠረት ዮሐንስ ይህንን ራእይ ካየ በኋላ እኛንም ወደ ታላቁ ዙፋን ፊት ይወስደናል:: ቁጥር 3 ተመልከት:: ታላቅ ዝማሬ በዙፋኑ ፊት ምን ጊዜም በዮሐንስ ራእይ ወደ ታላቁ ንጉሥ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ስንቀርብ ዝማሬና ስግደት ይቀድማል:: ይህ የሚሆንበት ምክንያት መደረግ ያለበት ነገር ነው:: ምክንያቱም ጌታና ንጉሥ ስለሆነ ነው:: በምዕራፍ 4 እና 5 ላይ የእግዚብሔርን ዙፋንና የሚሆነውን ነገር ልናይ እንችላለን:: አሁንም በምዕራፍ 14:2–3 ላይም የዳኑትና ድል ያደረጉት ማለት ከመከራ የወጡት በዙፋን ፊት ታላቅ የዝማሬ ጊዜ እንዳላቸው ይታያል:: የዝማሬ ድምጽ በመሣሪያ ነበር:: መሣሪያው ምን ዓይነት እንደሆነ አይነገረንም:: ግን እንደ በገና ደርዳሪዎች ድምጽ ያለ ነበር::

ዝማሬ የምን ምልክት ነው? ያዕ. 5:13 ተመልከት:: እነዚህ 144 ሺ ከመከራ የዳኑት፣ በመከራ የጸኑትና አሸናፊዎች በደስታ ይዘምራሉ:: መዝሙራቸውን ሌሎች አይችሉትም:: ይህ ለኛም ለቤተ ክርስቲያን ትልቅ መጽናኛ ነው:: በልዩ ልዩ መከራ ለሚያልፉ ክርስቲያኖች ሁሉ የደስታ ጊዜ ይመጣል:: የዝማሬ ጊዜ ይመጣል:: የመጽናናት ጊዜ ይመጣል:: በዙፋኑ ፊት የምንገለጥበት ጊዜ ይመጣል:: አንተ ክርስቲያን ወይም አንቺ ዛሬ ለጌታህ/ሽ/ በልብህ/ሽ/ ውስጥ ወይም በቃል የምትዘምረው/ምሪው/ መዝሙር አለህን?/አለሽ?/ መዘመር ትችላለህ?/ትችያለሽ?/ በምድር በመዝሙርና በዝማሬ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማመስገን ለምደሃልን?/ለምደሻል?/ ቆላ. 3:16–17::

ቁ. 4-5 ስለ ድንግልና፤

እነዚህ 144 ሺ ድንግሎች እንደሆኑ ይነገራል።

1. ይህ ድንግል የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሴቶች ብቻ አያወራም። ለጠቅላላ ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እንጂ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ወንድና ሴት ሳይለይ ለሁሉም በክርስቶስ ያመናችሁ ድንግል ናችሁ ይለናል፣ 2ኛ ቆሮ. 11:2 ተመልከት። እንዲሁም ደግሞ በማቴ. 25:1-13 ላይ ያለውን ስንመለከት ድንግል የሚል ቃል በጾታ በወንድና በሴት ሳይሆን ድንግልና ማለት ንጽህናና ቅድስና መሆኑን እናያለን። «በሴቶች ያልረከሱ» የሚለውን ሐሳብ ስንመለከት፣ ስለ መጋባት ሳይሆን ድንግልና ማለት ስለ ቅድስና፣ በክርስቶስ ፊት ያለ ነውር መኖርን ያመለክታል። ብዙ ሰዎች ይህን ጥቅስ ይዘው ሳያገቡ የሚኖሩትን ሰዎች ያደንቃሉ። ይህ ሐሳብ ያላቸው ሰዎች እንዳይሳሳቱ መጠንቀቅ አለባቸው። ጋብቻ ቅዱስ መሆኑን እንዳይረሱ አሳስባለሁ፣ ዕብ. 13:4። እግዚአብሔር ጋብቻ ለሰው ልጅ ጀማሪ ሆኗል። ዘፍጥ. 1:26-28፣31። ዘፍጥ. 2:18-25 ደግሞ ኢየሱስ ጋብቻን አክብሯል። ዮሐ. 2ን በሙሉ። ማቴ. 19:4-6። መንፈስ ቅዱስም በሐዋርያው ጳውሎስ በኩል ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ፍቅርና ንጽሕና በባልና ሚስት ምሳሌ ተመስሏል (አስመስሏል)። ስለ ድንግልና ሁለት ሃሳብ አለ:-

1. የጋብቻ ቅድስናን ወደ እርኩሰት የተረጐሙት ሰዎች ነበሩ። 1ኛ ጢሞ. 4:3 ሐዋርያው ጳውሎስ በኋለኛው ዘመን ይሆናል ይላል።

በዮሐንስ ዘመን

ሀ. ኖስትክስ የተባሉት በሐዋርያት ዘመን የነበሩ ስለ ጋብቻ ተቃውመዋል። ጋብቻና ትውልድ የሰይጣን ነው ብለው ያስተምሩ ነበር።

ለ. ታይታን የተባለ ሰው ጋብቻ ርኩሰት ነው፣ ዝሙት ነው ብሎ ያስተምር ነበር።

ሐ. ኦሪጀን የተባለው የቤተ ክርስቲያን (አባት) ታላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረው ራሱን ከጋብቻ ዓለም አገልሎ ድንግል ሆኖ መኖትን መረጠ፤ እንዲሁም ሌሎች።

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ ሌላ አምልኮ መመለስ እንደ ዝሙት ተቆጥሯል። ድንግል መሆን ቀርቶ እንደ አመንዝራ ሆኖ

ይታያል:: ያንንም ብዙ ጊዜ እሥራኤል አደረገች፣ ዘጸ. 34:15፤ ዘዳ. 31:16፤ መሳ. 2:17፤ መሳ. 8:27–33፤ ሆሴዕ 9:1 ተመልከቱ::

ቁ. 4–5 በጉ ወደሚሄድበት ሁሉ ይሄዳሉ::

1. ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ተስፋ፣ 1ኛ ተሰሎ. 4:17–18 ተመልከት::

2. እነዚህም 144000 በዚያ ይሳተፋሉ፣ ዮሐ. 12:26፤ 17:24፤ 14:3:: እነዚህን ቁጥሮች አመዛዝን::

በጉን የሚያጅቡት እነዚያ ዛሬ በፍጹም የሚከተሉት ናቸው:: ኢየሱስም ፊልጶስን ተከተለኝ አለው፣ ዮሐ. 1:44፤ ማቴዎስን፣ ማር. 2:14፤ ባለጠጋውን ማር. 10:21 ደግሞ ሉቃስ 9:59 ለጴጥሮስ ዮሐ. 21:19–22:: በኋላ ጴጥሮስ 1ኛ ጴጥ. 2:21::

ዮሐንስ በዚህ ቦታ ሲገልጽልን ኢየሱስን ወይም በጉን የሚከተሉት ሦስት ነገር ያደርጋሉ፣ ወይም ይሆናል ይላል::

1. ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኩራት እንዲሆኑ ነው፣

   በኩራት የመጀመሪያ የእግዚአብሔር ነው፣ ዘጸ. 13:1–2፣12፤ ዘፍጥ. 4:3–4:: መሥዋዕት ከበኩራትና ከተባዕት ይደረግ ነበር:: በአሪት ዘመን የሌዋውያን በኩር ተመረጠ፣ ዘኁ. 3:11–13፣40፤ ለቤተ ክርስቲያን ሮሜ 12:1–2፤ 1 ቆሮ. 6:19–20 ያለውን ተመልከት::

2. በአፋቸው ውሸት አልተገኘም (አይገኝም) ስለ አፋችን ተመልከት

- በዳዊት እንዲህ ተባለ፣ መዝ. 32:2
- በኢሳይያስ እንዲህ ተባለ፣ ኢሳ. 53:9
- በሶፎንያስ እንዲህ ተባለ፣ ሶፎ. 3:13
- ኢየሱስ ምሳሌያችን፣ 1ኛ ጴጥ. 2:22

እንዴት ይቻለናል? ለኢየሱስ ሁሉ ይቻለዋል:: ኢየሱስ ጻድቅ ብቻ በደሙ ካጠበን ክርስቶስ እንነጻለን:: ስለዚህ ይቻላል፣ኤፌ.5:26–27፤ ቆላ. 3:3::

3. ነውር የለባቸውም

ነውር የሌለበት የመሥዋዕት በግ ብቻ ነበር፣ ዘሌ. 3:1–6:: እኛ በበጉ ምክንያት እንዲህ ነን፣ ኤፌ. 1:4:: ቅዱስና ነውር የሌለን ሆነናል፣ ቆላ. 1:22:: ነውርና ነቀፋ የሌላችሁ ቅዱሳን አድርጓል::

ኤፌ. 5:27 ቤተ ክርስቲያን ያለ ነውር ትሆን ዘንድ፣ 1ኛ ጴጥ. 1:19 ነውርና እድፍ በሌለው በክርስቶስ ደም በማመን ልንነጻ ችለናል:: ኢየሱስ ራሱን ለእኛ ንጹህ የመሥዋዕት በግ አድርጐ ስለ ቀደሰን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፤ ክብርን እንስጠው::

ቁ. 16–17 የዘላለም ወንጌል ይሰበካል፣ ማቴ. 24:35፤ ኢሳ. 40:8

1. ወንጌል ይሰበካል፤ ወንጌል ዛሬም ነገም ይሰበካል፣ ወንጌል እንዳይሰበክ የሚከለክል ኃይል የለም:: ወንጌል ይሰበክ ያለው እግዚአብሔር ነው፣ ማቴ 28:28–20፤ ማር. 16:15፤2 ቆሮ.4:3–6:: በወንጌል ስብከት ሞኝነት ሰዎች ይድናሉ፣ 1 ቆሮ. 1:21፤ ማቴ. 11:25:: ዛሬ በወንጌል ስብከትና በሰዎች መዳን እድል ፈንታ አለህ? ስለዚህ በዓለም ሁሉ ወንጌል መሰበክ፣ የዓለም መጨረሻ ምልክት እንደሆነ፣ ክርስቶስ ተናግሯል፣ ማቴ. 24:14:: ዛሬ ወንጌል ወደ ዓለም ሁሉ የሚደርስና የሚሰበክ በክርስቶስ ተከታዮች በኩል ነው:: በዮሐንስ ራእይ 14 ላይ እንደሚገኝ ወንጌል በዓለም መጨረሻ ዘመን የሚሰበከው በመልአክ እንደሚሆን ይናገራል፣ ምዕ. 14:6–7 አንብብ:: ለአህዛብ ሁሉና ለነገድ ልዩ ልዩ ቋንቋ ላላቸው ሁሉ ለወገን ሁሉ ይሰበካል:: መልአኩ የዘላለምን ወንጌል ይዞ ይመጣል:: የዘላለም ወንጌል ማለት ለወንጌል መጨረሻ የለውም ማለት ሲሆን፣ ይህ ወንጌል የዘላለም ሕይወት ፍሬ ያፈራል:: ሰዎች ለዘላለም እንዲኖሩ ያደርጋል፣ ዮሐ. 11:25–26፤ ምዕ. 6:47 ቁ.50፣ 51፤ ምዕ. 8:51፤ ምዕ. 5:24::

2. የወንጌል እውነት በፍጥረት ሁሉ (ለሰው) ይተላለፋል::

   ሀ) በሰው በኩል ለ) በመልአክ በኩል

   ሐ)እግዚብሔር ራሱ ሲሆን የሚሰበከው ነገር ተደብቆ የነበረ ምስጢር ክርስቶስን ነው:: ክርስቶስ አዳኝ እንደሆነ ነው፣ ሮሜ 16:25::

ወንጌል በመልአክ ተሰብኮ ያውቃል ወይ?

1. በጥንት ዘመን ወንጌል በመልአክ ተሰብኳል፣ ዕብ. 1:1–3:: ለምሳሌ ወደ አብርሃም መልአክ ተልኳል፣ ዘፍጥ. 18:: ወደ ሎጥ ዘፍጥ. 19:: ወደ ዳንኤልም 9:20–23:: ወደ ዘካሪያስ፣ ሉቃስ 1:: ወደ ማሪያም፣ ሉቃስ 1:26:: ለእረኞች ሉቃስ 2:10–11:: ሌላም ብዙ እናገኛለን::

2. በሰው ነቢያትን አስቡ፣ ዕብ. 1:1–3

3. ክርስቶስ ራሱ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ማር. 1:14–15

4. ሐዋርያትና ወንጌላውያን፣ ኤፌ. 4:11፤ ማር. 16:15

5. በኋለኛው ዘመንም በመልአክ ይሰበካል፣ ራእይ 14:6–7::

ይህ ሁሉ የሚሆነው ወይም ወንጌል የሚሰበከው ሰው እንዲድን ነው፣ ቲቶ 2:11–14:: ሰው ሁሉ ወንጌልን ሰምቶ እንዲድን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው:: ስለዚህ ወንጌል ክርስቶስ ነው:: ማንም ቢሰብክ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ መንገድ አንድ ብቻ ነው፣ ዮሐ. 14:6:: ያም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ማንም ይስበክ ወደ ክርስቶስ አዳኝነት የማያመጣ፣ ወደ ክርስቶስ ደምና ሞት የማያደርስ ወንጌል ከሆነ እውነተኛ ወንጌል አይደለም:: ይህ ወንጌል በሁሉ በኩል ለሰው እየተሰበከ ሰዎች ግን በክርስቶስ ባያምኑ ወይም በእምነት ባይቀበሉ ወደ ፍርድ ይሄዳሉ፣ ሮሜ 8:1:: የመላእክት ስብከት ራእይ 14:7 እና የነጳውሎስ ስብከት በሐዋ. ሥራ 14:15 አመዛዝን::

ቁ. 7 ሦስት ትልልቅ ትእዛዛት እንደ ተሰጠ

1. እግዚአብሔርን ፍሩ
2. ለእግዚአብሔር ክብር ስጡ
3. ለእግዚአብሔር ስገዱ የሚል ሲሆን፣

## 1. እግዚአብሔርን ፍሩ

ይህ ቃል ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ይሰበካል:: በመጨረሻ ዘመንም መልአክ ይሰብክ የነበረው ይህንኑ ቃል ነው:: እንዲህ እያለ፦ ቁጥር 6 እና 7 አንብብ::

በምድር የምትኖሩ ሁሉ

ሕዝብ የሆናችሁ ሁሉ

ነገድ የሆናችሁ ሁሉ

ቋንቋ ያላችሁ ሁሉ

ወገን(ዘር) የሆናችሁ (ያላችሁ) ሁሉ እግዚአብሔርን ፍሩ::
እንደ ኢዮብ 1:1፣5ና8፤ ምሳ. 2:2፤ መዝ. 34:11–14፤ ቁ. 9::

1. የኖህን ዘመን አስቡ፤ ኖህ ግን ያንኑ ስብከት እግዚአብሔርን ፍሩ፣ ክብርን ስጡ፣ ስገዱለት ሳይል አልቀረም፣2 ጴጥ. 2:5::

2. የሎጥን ዘመን አስቡ፣ ሎጥ ግን ያንኑ ሰበከ፣ 2 ጴጥ. 2:6–10:: በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉት ሰባኪዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ፍሩ፣ ክብርን ስጡት፣ ስገዱለትም ሳይሉ አላለፉም::

3. ኢየሱስም እግዚአብሔርን መፍራት አስተምሯል፣ ሉቃስ 12:4–7፤ ማቴ. 10:28::

4. ሐዋርያትም እግዚአብሔርን ፍሩ ብለዋል፣ያዕ.4:6–10፤ 1 ጴጥ. 5:5–6::

መልእክቱ ሁላችሁ እግዚአብሔርን ፍሩ የሚል ነው:: ምሳሌ 1:7 የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው:: ሰነፎች ግን ይንቃሉ፣ ምሳሌ 9:10 ተደግሟል:: የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው:: አስተዋይ ግን ቅዱስ ይሆናል፤ እኔ እግዚአብሔርን እፈራለሁ የሚል ሰው እርሱ አስተዋይ ነው::

እግዚአብሔርን መፍራት ንጹህ ነው፣ መዝ. 19:9፤ 34:7፤ 91:11፤ ዳን. 6:22:: እግዚአብሔርን አንፈራም የሚሉ አሉ:: ብዙ ናቸው፤ መዝ. (36):1–3፤(14):1–6:: አልፎ ተርፎ አምላክ የለም፣ አያይም፣ አይሰማም ይላሉ:: ሰው ይበድላል፣ ባልንጀራውን ይገፋል፣ ይዘርፋል፣ ያስለቅሳል፣ በዓለማችን ላይ ግፍ ሞልቶባታል:: ነቢዩ ኢሳይያስ 1:17–19 ተመ. እግዚአብሔርን ፍሩ ይላል:: ባል ሚስቱን፣ ሚስት ባሏን በግፍ አታታልሉ፣ ሚልክ. 2:16:: በጠቅላላ እግዚአብሔርን የሚፈራ ማን አለ? ወንጌላዊ? ዘማሪ? የቤተ ክርስቲያን መሪዎች? ቤተ ክርስቲያን ድርጅት ነውን? በትምህርት ቤት? በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ማነው?..... ማንም የለም፤ ባዶ ነው:: አፍ ሁሉ ይዘጋ፣ሁሉም ከፍርድ በታች ነው፣ ሮሜ 3:10–19:: እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል፣ ኑ ወደ እኔ ልጆቼ ሁኑ፣ መዝ. (34):11–18:: ስሙኝ ይላል፣ እኔ አስተምራችኋለሁ፣ ማቴ.11:28–30፤ መክብብ 12:13:: የሰይጣን ዓይነት ፍርሃት አትፍሩ፣ ያዕ. 2:19::

2. ለእግዚአብሔር ክብርን ስጡ፣1ኛ ዜና 16:28–29፤ መዝ.(29):1–2

እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ ወደ ንስሃ እንዲገቡ፣ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ጥሪውን እያስተላለፈ ነው:: እግዚአብሔርን በማክበር

(ክብርን በመስጠት) ቦታ በመስጠት እንድናከብረውና እንድንፈራው ይፈልጋል:: እግዚአብሔርን አክብሩ:: በፍርሃትም ተገዙለት ታዘዙ:: እርሱ ነውና ሰማይንና ምድርን፣ ባህርንም፣ የውኃ ምንጮችን በውስጣቸው ያለውን ሁሉ የሠራ፣ ኃይል ሁሉ ያለውን እግዚአብሔርን አክብሩ::

ዛሬ እኛ የምንኖርበት ዘመን ክብርን፣ ምስጋናንና ታላቅነትን ሰው ለራሱ በሚፈልግበት ዘመን ውስጥ እንኖራለን:: የወንጌል መልእክት ግን አይለወጥም:: ክብርን ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ስጡ ይላል:: በኋለኛው ዘመንም መላእክት ይህንኑ ያውጃሉ:: እግዚአብሔርን አክብሩት ይላሉ:: እግዚአብሔርን እንዴት ማክበር (ክብር) መስጠት ይቻላል? መንገዱስ? መንገዱማ አንድ ነው:: መንገዱማ ግልጽ ነው፣ ዮሐ. 14:6:: ክብር ምስጋና ፍርሃት ስግደት የሚደርሰው በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው:: በሌላ በኩል፣ በሌላ ስም አይቀበልም:: አይደርሰውምም:: የሐዋ. ሥራ 4:12 የእግዚአብሔር ክብር ክርስቶስ ነው:: የእግዚአብሔር ክብር በክርስቶስ ተገልጧል፣ ዮሐ. 1:14፤ ዕብ.1:3::

ክርስቶስ የሌለበት እምነት
ክርስቶስ የሌለበት ጸሎት
ክርስቶስ የሌለበት ስግደት ምንም ወደ እግዚብሔር አይደርስም::

እግዚአብሔርን ማክበር ብንፈልግ መንገዱ ክርስቶስ ነው:: የእግዚአብሔርን ክብር እንመልከት::

1. የክርስቶስ ክብር በተዓምራቱ፣ ዮሐ. 2:11
   የክርስቶስ ክብር በተራራ፣ ማቴ. 17:1–8
   የክርስቶስ ክብር በሕማማቱ፣ ዮሐ. 12:23–38
   የክርስቶስ ክብር በትንሳኤውና በእርገቱ፣ 1ጴጥ. 1:20–21

በሚመጣው በዳግም ምጽአቱ የሚገለጠው፣ማር. 8:38 ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ፣ ሮሜ 13:7፤ ይሁዳ 25፤ መዝ. 24:7–10........ ስለዚህ መዝ. (103):1–22:–

| | |
|---|---|
| <u>ልቤ</u> ያመስግን | <u>አፌ</u>. ያመስግን ክብርን ይስጥ |
| <u>ኃይሌ</u> ያመስግን | ነፍሴ ያመስግን ክብርን ይስጥ |
| <u>ከንፈሬ</u> ባርኪ | ምላሴ ያመስግን ክብርን ይስጥ |
| <u>እጀ</u> ክብርን ይስጥ | <u>እግሬ</u> ያመስግን ክብርን ይስጥ |

ሁለመናዬ ክብርን ይስጥ፣ 1ኛ ቆሮ. 6:20፤ ምዕ. 10:31::

### 3. ለእግዚአብሔር ስገዱ

እግዚአብሔርን በማክበር ስገዱ፤ ትክክለኛ ስግደት፣ ዮሐ. 4:20–24

ሀ) ሰብአ ሰገል በሕፃኑ በኢየሱስ ፊት ዝቅ ብለው ወድቀው እንደ ሰገዱ ሁሉ ለጌታ ስገዱ፣ ማቴ. 2:11:3

ለ) ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዮሐንስ ራእይ 4:10–11 እንደ አደረጉት አድርጋችሁ ስገዱ:: እንደ ጴጥሮስ፣ ማቴ. 14:33፤ መዝ. (95):6 ኑ እንስገድ ለእርሱም እንገዛ ይላል:: ዕብ. 1:6 መላእክት ሁሉ ይስገዱለት:: ፊልጵ. 3:3 እኛ በመንፈስ ለእግዚአብሔር እንሰግዳለን፣ ዮሐ. 4:20:: እግዚአብሔር በመንፈስ እንድንሰግድ ይፈልጋል:: ስግደት ማለት አምልኮ ማለት ነው፣ ኢያሱ 24:14–15:: በዚህ ዘመን ክርስቲያን በዚህ ዓይነት መንገድ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል (ያመልከግል)::

የስግደቱ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው:

1. በጸሎት 1ጢሞ. 2:8
2. ቃሉን በማንበብ፣ ዕብ. 1:22
3. መዝሙር በመዘመር፣ ኤፌ. 5:19
4. በስብከትና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ሐዋ. ሥራ 20:7
5. በምጽዋት፣ 1ቆሮ. 16:1–2፤ ዘዳ. 16:16
6. በጥምቀትና በቅዱስ ቁርባን፣ 1ቆሮ.11:18–34፤ ሮሜ 6:3–4::
7. እግዚአብሔርን በመውደድና ፈቃዱን በማድረግ፣ ማር.12:30–31፤ ማቴ. 7:21::

እርስ በርሳችን ሕብረት ማድረግ፣ ዮሐ. 13:34:: እውነተኛ ስግደት ወይም አምልኮ ከልብ ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንጂ በቦታ ሁኔታ አይወሰንም:: በእነዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን አክብር፣ 1ቆሮ. 10:31::

የአንተና የአንቺ ስግደት እንዴት ነው? ራእይ 14:7:: ለሌላ የሚሰግዱትን አጠፋለሁ ይላል እግዚአብሔር፣ ሶፎን. 1:5::

ቁ. 8 የባቢሎን መውደቅ

ሌላ መልአክ ባቢሎን ወደቀች ወደቀች ይላል። እግዚአብሔር በባቢሎን የሚፈርድበት ጊዜ ይመጣል ማለት ነው።

ባቢሎን ምንድን ነው? ከየት መጣ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባቢሎንን በሦስት መንገድ እንመለከታለን።

1. በምድር የነበረ አሁንም ያለ ከተማ ነው። እርሱም የሚገኘው በምስራቅ አገር በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ያለው ቦታ ወይም ከተማ ነው። በአብርሃም ዘመን ባቢሎን ታላቅ ከተማ ነበረ። ስለ ባቢሎን ዘፍጥረት 11:1–9፤ ዳን. 4:30 ተመልከት።

2/ የዓለምን የኃይማኖት ሁኔታ ያመለክታል። (በአምልኮ) ስንት ዓይነት አምልኮ። በአምልኮ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይበደላል። በዓለም ስንት ዓይነት ኃይማኖት ይኖራል?

ስፍር ቁጥር የሌለው ነው። እውነተኛውስ የትኛው ነው? ራእይ ምዕራፍ 17 ስንደርስ እንመለከታለን። ከእግዚአብሔር የሚለት የሐሰት አምልኮ የተጀመረው በባቢሎን ነበር፣ ዘፍጥ. 11:4 ተመልከት።

3. የዓለምን አገዛዝና የፖለቲካ ሁኔታ ያመለክታል። በአስተዳደር የሚበድሉትን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። በዓለም ስፍር ቁጥር የሌለው የፖለቲካ ሁኔታ ሲታይ በኃይል መግዛትና ማስጨነቅን ያጠቃልላል። ዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 18 ስንደርስ እንመለከታለን። ግዛትና ኃይል በባቢሎን እንደ ጀመረ ዘፍጥ. 10:10 ተመልከት። ስለዚህ ባቢሎን የክፋትና የዓመጽ ቦታ ሆኖ እናገኛለን። ባቢሎን ከእግዚአብሔር የሚለይ ኃይማኖትና እግዚአብሔር እንዳይገዛ የክፋት አገዛዝ የተጀመረበት ቦታ ስለሆነ እግዚአብሔርን የሚቃወም መሠረት የተጣለበት መስሎ ይታያል።

ባቢሎን ወደቀች፤ ሁለት ጊዜ መልአኩ ይደጋግመዋል። የክፋት መጨረሻም በዚያ ይጀምራል። ባቢሎን የኃይል፣ የመደሰቻ፣ ምኞት መፈጸሚያ፣ የዝሙት ምሳሌ ሆኗል። ስለ ባቢሎን ወይም ስለ እርኩሰቷ በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ተጽፏል። ለምሳሌ ኢሳ. 21:9፤ መዝ. (75):8፤ ኤር. 51:8፤ ኤር. 25:15 ዝሙትን መለማመድ የእግዚአብሔርን ቁጣ ያመጣል፣ ኢዮብ 21:20። እግዚአብሔር ይፈርዳል።

## ትልልቅ ሁለት ማስጠንቀቂያዎች

1. በራእይ 14:9–11 ላይ ያለው የጥፋትና የፍርድ ጊዜ ሊሆን ነው የሚል፣

2. ራእይ 14:12 የእረፍትና የልፋታችሁን ብድር የመቀበል ጊዜ ሊሆን ነው የሚል ነበር።

ቁ. 9–11 ለሐሳዊ መሲህ ለሚሰገዱለት ሁሉ ፍርድ

እንደኛውን እንመልከት። አውሬው (ሐሳዊ መሲህ) ነው። በሁሉ ሰው ላይ በሥልጣን መቀመጥ ወይም መኖር (መግዛት) እንደሚፈልግና እንደሚሆንለት በምዕራፍ 13 ተመልክተናል። በዚያ በመከራ ጊዜ ለሚወድቁትና ለሚክዱት ሁሉ ትልቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። ቤተ ክርስቲያን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከዚያ ድረስ ቤተክርስቲያን የተጨነቀችበት፣መከራ የተቀበለችበትና የተሰቃየችበት ዘመን ሲያልቅና ሲያበቃ ሲሆን፣ ለሐሰተኛ ተከታዮች ግን ታላቁ የመጨረሻ ፍርድ ደርሷል፣ 14:7። ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰገዱት ሁሉ ምልክቱንም በእጃቸውና በግምባራቸው የወሰዱት ሁሉ ያልተቀላቀለ የቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣሉ። ምን ማለት ነው ያልተቀላቀለ ማለት? ምንም ምህረት የሌለው ምንም ይቅርታ የሌለው፣ ምንም ፍቅር ያልተጨመረበት የእግዚአብሔርን የቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣሉ፣ ፍርድ ይቀበላሉ ማለት ነው። እርግጥ ሥጋቸው ይሞታል፤ ነፍሳቸው ወደ ስቃይ ወደ ሲኦል ይወርዳል ማለት ነው። ለምሳሌ በሉቃስ 16:19–31 ኢየሱስ ያስቀመጠውን ዓይነት አለ። ከዚህም ሌላ በመጨረሻው ፍርድ ጊዜ ከሲኦል ወጥተው ወደ እሳት ባህር ይጣላሉ፣ ራእይ 20:11–15።

ሥቃያቸው ለዘላለም ቀንና ሌሊት ይሆናል፣ ራእይ 14:11። ይህን የሥቃይ ቦታ ያዩት:

1. መልአክ ያውቃል፣ ራእይ 14:9።
2. ኢየሱስ ያውቃል፣ ማቴ. 13:41–43፤ ማር. 9:43–48።

በዚህ በዮሐንስ ራእይ ጊዜ በዙፋኑ ላይ የተቀመጡት 24 ሽማግሌዎች እንኳን አላዩም። አያውቁምና። (ቤተ ክርስቲያን ወኪሎች) ራእይ 14:9–11፤ ዘፍጥ. 19:28፤ ምሳሌ ሲሆን ኢሳ. 34:8–10 ተመልከት። ከዚህ ሁሉ ፍርድ መውጫ መንገድ የሚሆን፣ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ዛሬ ምህረትን ይዞ አለና በእምነት ምህረትን ተቀበል።

የምህረት ጊዜ አላለፈም አሁንም አለ። ኢየሱስ ለኛ መሥዋዕት በመሆን የእግዚአብሔር በግ ስለሆነ እርሱን በእምነት ተቀበል፣ዮሐ. 1:29፤ 3:16–18፤ 3:36።

ቁ. 12–13 እረፍትና ብድር የመቀበል ክፍል እንመለከታለን። ሁለተኛው ክፍል ከፊተኛው ትልቅ ልዩነት ያለው ነው። በዚህ ክፍል የእረፍትና የልፋታቸውን ዋጋ የሚከፈላቸው ስለሆነ የመጽናናት ጊዜ ይሆናል። ስለዚህ ብጹአን ናቸው ተብለዋል። ደስ ይበላችሁ እድለኞች ናችሁ ተብለዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ብጹአን ናችሁ የሚለው ለሁለት ዓይነት ሰዎች ነው።

1. በምድር ላሉት ሳይሞቱ በሕይወት በጌታ አምነው ላሉት ሲሆን፣ በሥጋ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ስለ ጌታ እምነት ሲሉ መከራና ችግር ስለቀመሱ ብጹዕ ይላቸዋል፣ ማቴ.5:3–10፤ሉቃስ6:20–23።
2. በጌታ እምነት የሞቱትን ነው። ከሞት በኋላ ስለሚጠብቃቸው ደስታ እያሰበ ራእይ 14:12–13 ብጹአን፣ ዕድለኞች ይላቸዋል። ለምን?
   - ሀ) የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የምትጠብቁ ስለሆነ፣
   - ለ) በጌታ ስም በማመን እስከመጨረሻ የሚጸኑ ስለሆነ
   - ሐ) በድካማቸው ስለሚያርፉ ብጹአን ናቸው
   - መ) ወደ ዘላለማዊ እረፍት ሥፍራ ስለሚሄዱ፣ አንተ ታማኝ ባሪያ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ ስለሚባሉ፣ ማቴ. 25:21።
   - ሠ) ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብለው የሠሩት መልካም ሥራቸው ሁሉ ይከተላቸዋል። ለጌታ የሠሩበትን ዋጋ እንዲቀበሉ ሥራቸው ይከተላቸዋል፣ 2ቆሮ. 5:10፤ ዕብ. 6:10።
   - ረ) ብጹአን ናቸው፤ በጌታ የሆኑት አልሞቱም፤ አንቀላፍተዋል እንጂ፤ 1 ቆሮ. 15:18እና51፤ 1 ተሰሎ. 4:16።

እዚህ ላይ የእነርሱን ማለት የሞቱትን ሁኔታ የሚገልጽልን፣ እኛ ዛሬ በሥጋ ሕይወት ያለን እንድናውቅና የወደፊት ሁኔታችንን እንድንረዳ ሲሆን፣ ዝግጅት እንድናደርግ በሕይወት ሳለን እኛን ለማጽናናት ለማጠንከር በድል አድራጊነት በተስፋ እንድንጓዝ ሊያደርገን ነው።

አንተስ ክርስቲያን ከሞት በኋላ ተስፋ አለህን? ከድካም ተርፈሃል? ወይስ ትሰቃያለህ? ወይም አታውቅም ይሆን? ታዲያ ከሞት በኋላ

ምን ይጠብቅሃል? ወይም መጨረሻህ ወዴት ነው? ዛሬ መድረሻህን ወደ ክርስቶስ አድርግ።

ቁ. 14–20 አዋጅ ነጋሪ ድምጽ

አዋጅ ነጋሪ ይጮኻል እንዲህ እያለ፣ መከሩስ ደርሷል (እህሉ በስሏል) አጨዱት የሚል ነበር። አጨዱት እያለ ትእዛዝ ይሰጣል።

ቁ. 14–16 አዋጁን ተመልከት

የአጨዳው ኃላፊ (ባለቤት) የሰው ልጅ ነው። ሌላ ማንም አይደለም። እህሉ ደርሷል ወይም በስሏል፤ መብሰሉን በምን እናውቃለን? በቁጥር 15 እና በቁጥር 18 እህሉ ደርሷል መከር በስሏል ይላል። ወዳጆች ሆይ እህል እስኪደርስ ባለቤቱ በብዙ ትእግስት እንደሚጠብቅ ሁሉ እግዚአብሔር በብዙ ታገሰ። አሁን ግን ጊዜው ስለደረሰ የቀጣው ጊዜ ሊሆን ነው። አሁን ዘመኑን ስናይ ምድሪቱ እህል እያደረሰች ትመስላለች። ኢየሱስ በማቴ. 24፡3–15 ምልክትን ገለጸ። ስለዚህ እነዚህን ተከታይ ቁጥሮችልብ ብለን እንመልከታቸው።

1. መሳት ነው፣ ክርስቲያንን እንኳን የሚያስት ብዙ ነገር በኃይማኖት ድርጅት የሐሰት ትምህርት ስላለ፣ ቁ. 5 እና 11
2. የጦርነት ወሬና ሁኔታ ነው፣ በዓለማችን ያለውን የጦርነት ብዛት አስብ፣ ቁ. 6።
3. ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥት በመንግሥት ላይ መነሳት፣ ሰላም መጥፋት፣ ቁ. 7።
4. ረሐብ፣ በዓለም ያለውን የረሐብ ሁኔታ አስብ ይቀጥላል፣ ዘሌዋ. 26፡26።
5. ቸነፈር፣ ዓለም ዛሬ በኤድስ መቅሰፍት ምን እየሆነ ነው?
6. ፍቅር ትቀዘቅዛለች፣ ቁ. 12 ክርስቲያን ራእይ 2፡4 ተመልከት።
7. ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፣ ቁ. 14። ዛሬ ወንጌል በሬድዮና በጋዜጣ፣ በልዩ ልዩ መገናኛዎች ዛሬ ይሰበካል። እንዲሁም ሉቃስ 21፡20፡29፡34 አንብብ። 1ጢሞ. 4፡1–2፤ 2ጢሞ. 3፡1–9፤ ሮሜ 1፡26–32 አመዛዝን። ሰዎች ግን በዚህ ሁሉ የንስሃ ልብ የላቸውም። ይልቁንም ይሳደባሉ፣ ራእይ 15፡9–11 ተመልከት።

ቁ. 14 የሰው ልጅ በደመና የሚለውን ልብ አድርጉ። በአዲስ ኪዳን ሁልጊዜም የሰው ልጅ የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስን ሲሆን፣ የሰው ልጅ በደመና የሚል በብዙ ቦታ ተጠቅሷል። የሐዋ. ሥራ 1:9 በደመና ተነጠቀ፤ የሐዋ. ሥራ 1:11 በደመና ይመለሳል፣ በማቴ. 24:30 ምልክት በደመና ይታያል፤ ራእይ 1:7 እነሆ በደመና ይመጣል፣ 1ኛ ተሰሎ. 4:13–18 ተመልከት። ስለ ኢየሱስ ፈራጅነት በብሉይ ኪዳን የተነገረውን መዝ. 2:7–9 ትንቢተ| ኢዩኤል 3:13–14። ይህ ሁሉ ፍርድ የሚሆንበት ምክንያት የዓለምን መድኃኒት ክርስቶስን አናምንም አንቀበልም እምቢ ስላሉ ሲሆን፣ ለዓለም ማምለጫ አይኖርም፣ ዕብ. 2:3።

ቁ. 17–19 የእሀሉ ባለቤት መላእክትን (አጫጆችን) ይልካል፤ እነርሱም ሲያጭዱ ይታያሉ፣ ማቴ 13:39–43 ተመልከት።

ቁ. 19 እህሉ ታጭዶ በመጭመቂያ (ገንዳ) ውስጥ ተጣለ፤ የዚህ መጭመቂያ (ገንዳ) ስም የእግዚአብሔር ቁጣ ተብሏል። እህሉ (ሕዝብ) ለእግዚአብሔር ፍርድ እንዴት ይሰበሰባሉ የምትሉ ካላችሁ ኢዩኤል 3:9–15 አንብቡና አመዛዝኑ።

ቁ. 20 በመጭመቂያው ውስጥ የተጣለ እህልን (መከር) እንደ ወይን ያስመስላል። ወይን በጥንት ዘመን በገንዳ ገብቶ በእግር ይረገጣል፣ ይጨመቃል። ጭማቂው ውሃ ከታች ይፈሳል። ይህ የተረገጠው ወይን ከከተማ ውጭ ማለት ከኢየሩሳሌም ከተማ ውጭ ሜጊዶን (አርማጌዶን) የተባለ ሸለቆ ላይ ይሆናል። የተረገጠው የደም ፈሳሽ እስከ ፈረስ ልጓም አንገት ይደርሳል። እርዝመቱም እስከ 300 ኪ/ሜትር ይደርሳል። ይህን ብዙ ሰዎች የአርማጌዶን ጦርነት እያሉ ያስተምራሉ። የደም ፈሳሽ ከፍታው እስከ ፈረስ ልጓም ርዝመቱ እስከ 300 ኪ/ሜትር ሲሆን፣ ይህ እንዴት ይሆናል ካላችሁ በተጨማሪ ትንቢተ ዘካርያስ 14:1–4 አንብቡ።

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 15

ዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 15 ላይ ስንደርስ የምናተኩርበት ነገር አለ። ያውም በኋለኛው ዘመን በመጨረሻ ሊሆን ያለውን የእግዚአብሔርን ፍርድ በፍጥረት ላይ ሲሆን ነው።

ከዚህ በፊት የተጠቀሰውን ለማስታወስ ያህል

1. በምዕ. 6:1–17 ስለ ሰባቱ ማህተም ይናገርና በመጨረሻው ላይ ሌላ ቀጥሏል።
2. በምዕራፍ 8:1–9፤ 21 ምዕ. 11:15–19 ስለ ሰባቱ መለከት መነፋት ይናገርና በመጨረሻው ላይ ሌላ ቀጥሏል።
3. ምዕራፍ 15:1፤ ምዕ. 16:1–21 ድረስ አሁን የምናነበውንና ቀጥሎ ስላሉት መጨረሻ ሰባት የቁጣ ጽዋዎች ማፍሰስ ይናገራል።

ማፍሰስ የሚለው ቃል አንድ ጊዜ ጭልጥ ወይም ገልብጥ ብሎ እስከ መጨረሻው ማፍሰስ ሲሆን፣ የ7 ጽዋዎች መፍሰስ ድርጊት በምዕራፍ 16 ጠቅላላውን ቢገልጽም ከእነዚህ የጽዋዎች ማፍሰስ ፍርድ ቀጥሎ ባሉት ጊዜያት የዲያቢሎስ መታሠርና የክርስቶስ ሺህ ዓመት በምድር ላይ መንገሥ እንደሚቀጥል ይገልጻል። ምክንያቱም በምዕራፍ 6:17 ላይ በመጀመሪያ በሰባቱ ማህተም መፈታት ጊዜ ማን መቋቋም ይችላል ብሎ ነበር።

ቁ. 1 የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ስለሚፈጸም ይላል፤ መፈጸም ማለት ማለቅ ሲሆን፣ በቅድሚያ ስለ ሦስት መፈጸም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናስባለን። እነርሱም፦

1. ዘፍጥ. 2:1–2 እግዚአብሔር በሠራቸውና በፈጠራቸው ነገሮች መፈጸምን ይገልጣል።
2. ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በነበረ ጊዜ፣ ዮሐ. 19:28–30 የዓለምን ኃጢአት በራሱ ተሸክሞ የኃጢአትን ዋጋ በከፈለ ጊዜ ተፈጽሟል ያለው ሲሆን፣ እርሱ በፈጸመው ሥራ መዳን በእርሱ አግኝተናል፣ ዮሐ. 1:29። በዮሐንስ 19:35 ኢየሱስ ተፈጸመ ብሏል።
3. ዮሐንስ በራእይ እያየ እንደገና ኃጢአትን የፈጸመውን ኢየሱስን በሚጠሉትና በማይታዘዙት ላይ የሚፈጽመውን የእግዚአብሔር

ቁጣ ጽዋ በኃጢአትና በኃጢአተኞች ላይ ሲፈስ ያያል። እርሱም የኋለኞቹ ሰባቱ መቅሰፍቶች የተባለውን ጽዋ የሞላ ፍርድ ሊፈርዱ ሰባት መላእክት ተዘጋጅተው ይታያሉ።

ቁ. 2–8 ያለው ሐሳብ መካከል ያለውን ነገር ይገልጻል። ለምሳሌ ቁጥር 1 ስለ ሰባቱ መላእክት ዝግጅትና ስለ ሰባቱ የቁጣ መቅሰፍት ጽዋዎች መፍሰስ መግቢያ ያስተዋውቃል። በምዕራፍ 16 ላይ የጽዋዎች መፍሰስ እስኪያመጣ ድረስ በመካከል ሌላ ነገር ዮሐንስ ያያል። ያውም የአውሬውና የምስሉ፣ እንዲሁም የስሙን ቁጥር፣ ደግሞ ድል ያደረጉትን መዘምራን ይመለከታል። እነዚህ መዘምራን በእሳት በተቀላቀለ በብርጭቆ ባህር አጠገብ የእግዚአብሔርን በገና ይዘው በባህር ላይ ቆመዋል፣ ቁ. 2 ተመልከት። የእነዚህንም መዘምራን ዝማሬያቸውን ማንም ሊያውቅ አይችልም ነበር፣ ምዕ. 14፡3። እነዚህ አውሬውንና ማታለሉን ሌላም የአውሬውን ሽንገላ ድል አድርገዋል። ድል ያደረጉትም እስከሞታቸው ድረስ ነው፣ ምዕ. 2፡10። እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን የተባለው ተፈጽሞባቸዋል። እነርሱ ለጌታቸው ታማኝ ሆነዋል። አንተስ ለጌታህ ታማኝ ነህን? በታማኝነት ትሞታለህን?

ቁ. 3–4 የሙሴና የበጉ ቅኔ ነበር ዝማሬያቸው። ጌታ ታላቅ ነው አሉ። ሁሉን ነገር ይገዛል፣ የሁሉ ንጉሥ ነው። መንገዱና ጽድቁ እውነት ነው፣ የማይፈራውና የማያከብረው ማነው? ቅዱስ ስለሆንህ ሁሉም ላንተ ይሰግዳሉ። ሁሉም ያመልኩሃል እያሉ ነበር። ፊልጵ. 2፡9–11፡3 እኛም ዛሬ ለጌታ እየሰገድን ክብርን እንሰጣለን።

ቁ. 5–8 የጭስ መቅደሱን መሙላት

በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር የምስክር ድንኳን ወይም መቅደስ በምድር ላይ ነበረ፣ ዘጸ. 38፡21፤40፡34–35። በሰማይ መቅደስ መከፈት የሚያሳየው እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ የጸና ታማኝ መሆኑን ነው፣ ራእይ 11፡19። በእነዚህ ቦታዎች የእግዚአብሔርን ፍርድ ሁኔታ ይገልጻል። እግዚአብሔር ቅዱስ ፈራጅ መሆኑን እናስታውስ። ፍርዱ ትክክለኛ ነው። በኃጢአት የረከሰች ዓለምን በቅድስና ይፈርዳል፣ መዝ. (96)፡13።

ቁ. 8 ጭስ መቅደሱን እንደሞላ

በዚህ ቦታ የሚያሳየው የእግዚአብሔርን ክብርና ግርማ ነው። ማንም መቅደሱ ሊገባ አልቻለም ነበር። በብሉይ ኪዳን የሆኑትን ልናስታውስ ይገባናል። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አንብብ።

1. በሲና ተራራ እንዴት ነበር? ዘጸ. 19፡18
2. በመገናኛ ድንኳንስ? ዘጸ. 40፡34–35
3. በሰለሞን ዘመን በተሠራው ቤተ መቅደስስ? 1 ነገ. 8፡10–11
4. በኢሳያስ ዘመንስ? ኢሳ. 6፡3
5. ኢየሱስ በተራራው ላይ በተለወጠ ጊዜ፣ ማቴ. 17፡1–8
6. ኢየሱስ በዮሐንስ ራእይ፣ ራእይ 1፡12–20
7. ለእኛስ? ዕብ. 12፡18–20

የእግዚአብሔር ክብርና ኃይሉ እንደዚህ አስፈሪ ከሆነ ማን መጠጋት ይችላል? ማንስ ይቋቋም ዘንድ ይችላል? ዕብ. 12፡28–29። በጌታ የሚያምኑትን በእምነት በኩል እንዲቀርቡ ስለ ተፈቀደ እግዚአብሔርን እጅግ አድርገን ማመስገን ይገባናል፣ ዕብ. 10፡21–22። በክርስቶስ ዳግም ምጽአት፣ ማር. 8፡38 ምዕመናን የእግዚአብሔር ክብር ሙሉ በሙሉ ይታይላቸዋል፣ 2 ቆሮ. 3፡18። ከእግዚአብሔር ክብርን ይቀበላሉ። ከክብሩ ይካፈላሉ፣ ዮሐ. 17፡22–24፤ ሮሜ 8፡17–21፤ 1 ቆሮ. 15፡43፤ ማቴ. 13፡43።

የእግዚአብሔር ክብር ከሰው ሲለይ አደገኛና አስፈሪ ነው።

1. በሳምሶን ጊዜ፣ መሳ. 16፡19–21፤ ዘኁ. 12፡9–11
2. በኤሊ ዘመን፣ 1 ሳሙ. 1፡21–22
3. በሕዝቅኤል ዘመን፣ ሕዝ. 9፡3፤ 10፡4፤ 11፡22–23። ይህ ተከስቶ ነበር።

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 16

እግዚአብሔር ፈራጅ አምላክ ነው። ፍርዱም ትክክለኛ ነው፣ ያዕ. 5:8–9።

በራእይ ምዕራፍ 16 ላይ የእግዚአብሔር የፍርድ ውሳኔ ድምጽ ከመቅደሱ ሲወጣና ለመላእክት ትእዛዝ ሲሰጥ ይታያል። <u>የኃጢአተኞች ፍርድ ጊዜ ነው</u>።

1. በቀድሞ ዘመንም እግዚአብሔር እምቢተኞችን ቀጥቷል። ግብጻውያን እንኳ በሚከተሉት ቅጣቶች ተቀጥተዋል፦

   ሀ) ውኃውን ወደ ደም በመለወጥ፣ ዘጸ. 7:20–25።
   ለ) በእንቁራሪት(ጓጉንቸር) ቀጣቸው፣ ዘጸ. 8:5–14።
   ሐ) በቅማል ዘጸ. 8:16–18።
   መ) በዝምብ፣ ዘጸ. 8:20–24።
   ሠ) በከብት በሽታ፣ ዘጸ. 9:3–6።
   ረ) በቡግንጅ ቁስል፣ ዘጸ. 9:8–11።
   ሰ) በመብረቅና በበረዶ፣ ዘጸ. 9:22–26።
   ሸ) በአንበጣ፣ ዘጸ. 10:12–19።
   ቀ) በጨለማ፣ ዘጸ. 10:21–23።
   በ) በበኩር ልጆች ሞት ቀጣቸው፣ ዘጸ. 12:29–30።

2. እግዚአብሔርን የማይሰሙና የማይፈሩ፣ የማያምኑና እምቢተኞች እንደሚቀጡ ሲያሳያቸው ነበር። ደግሞ በዮሐንስ ራእይ 8 በተመሳሳይ ቅጣት እንደሚቀጣቸው ለባሪያው ለዮሐንስ አሳይቷል።

   ሀ) ዕጽዋትን በበረዶ እሳትና በደም ሲቀጣ፣ ራእይ 8:7።
   ለ) ባህርንና ፍጥረቱን በእሳት ተራራ በሚመስል ነገር ሲቀጣ፣ ራእይ 8:8።
   ሐ) ውኃንና ምንጮችን በኩከብ መውደቅ፣ ራእይ 8:10–11
   መ) ለፍጥረት ሁሉ በጨለማ፣ ራእይ 8:12
   ሠ) ሰውን በቁመናው የሚበሉ አጋንንት በመላክ፣ራእይ 9:1–12
   ረ) ለሰዎች የታሠሩትን 4 መላእክት በመፍታት፣ 9:13–21
   ሰ) ከዚህ ሁሉ በላይ ድሉ የክርስቶስ ሆኖ ይታያል፣ ራእይ 11:15

3. በራእይ ምዕራፍ 16 ላይ ሦስተኛው ተመሳሳይ ፍርድ በኃጢአን ላይ ሲበየንባቸው ይታያል።

ሀ) በቁስል፣ ራእይ 16:2።
ለ) በባህር ደም፣ ራእይ 16:3።
ሐ) ምንጮችና ወንዝ ደም መሆን፣ ራእይ 16:4።
መ) በፀሐይ መጥቆር፣ ራእይ 16:8።
ሠ) ጨለማ፣ ራእይ 16:10
ረ) በኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅ፣ ራእይ 16:12
ሰ) በአየር መበከል፣ መሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅና በረዶ፣ ራእይ 16:17–21።

ይህን ሁሉ መሸከም ይቻላልን? ዛሬውኑ ንስሐ መግባት ይበጃል። ኢያሱ 10:11

ቁ. 1–21 ሰባቱ የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋ

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ስለሆነ ኃጢአትን ይቅርታ መስጠት አይችልም። በኃጢአት ላይ ምህረት አያደርግም። እግዚአብሔር ለረጅም ጊዜ ታጋሽ እንኳን ቢሆንም ኃጢአትን አይምረውም። በኃጢአት ላይ ቁጣውን ያፈሳል እንጂ። ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ ላይ እግዚአብሔር ሰባት የፍርድ ጽዋ ሲያፈስ እናያለን።

የእግዚአብሔር ፍርድ እንደታወጀ በምዕ. 15:1። ሰው የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት መቀበል እምቢ ስላለ የእግዚአብሔር ቁጣ ጽዋ በፍጥረት ላይ ሊፈስ ነው።

ቁ.1 ለሰባቱ መላእክት፣ ሂዱና አፍሱ የሚል ትእዛዝ ተሰጣቸው። ከዚህ በፊት በምዕራፍ 6 ላይ ማህተሞች በተከፈቱ ጊዜና ከምዕራፍ 8 ጀምሮ መለከቶች በተነፉ ጊዜ ተራ በተራ ነበር ትእዛዝ የተሰጣቸው። አሁን ግን በምዕራፍ 16 ላይ የቁጣ ጽዋዎች እንዲፈሱ የተነገራቸው በአንድ ጊዜ ነው። ሰባቱም የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋዎች ከአንዱ አንዱ ተከታትለው እንዲያፈሱ ተነገራቸው። ለምሳሌ በምዕ. 9:5 ተመልከት። አምስቱ መላእክት መለከት እስኪነፉ ድረስ 5 ወር እንደፈጀ ሲታይ፣ የቁጣን ጽዋ ለማፍሰስ ግን ጊዜ አልተወሰነም። የቁጣ ጽዋ በቀጥታ በምድር ላይ እንዲፈስ በትልቅ ድምጽ ከመቅደሱ ተነገረ። በምዕ. 15:8 ላይ ዮሐንስ ሲነግረን መቅደሱ ክፍት እንደነበረና በእግዚብሔር ክብርና ኃይል የተነሳ ጢስ መቅደሱን ሞልቶ ነበር። መቅሰፍቶቹ እስኪፈጸሙ ድረስ አንድም መግባት

እንዳልተቻለ ተመልክተን ነበር። እንግዲህ ማንም ወደ መቅደሱ መግባት ካልቻለ ይህ የትእዛዝ ድምጽ ቀጥታ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የወጣ ድምጽ ነበር። ሌላ ጊዜ ግን አንዱ መልአክ ለሌላው መልአክ መልእክትን ያስተላልፍ ነበር፣ ምዕ. 7:1–3። ይህ የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋ የሚፈሰውም በፍጥረት ሁሉ ላይ ነው። በዚህ የቁጣ ጽዋዎች መፍሰስ ላይ የምናየው ጉዳይ እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ብቻ ሳይሆን ኃጢአትን የሚጠላ አምላክ መሆኑንም ጭምር ነው፣ ሚልክ. 2:16።

## ቁ. 2 የአንደኛው ጽዋ መፍሰስ

ለሰባቱ መላእክት የእግዚአብሔርን የቁጣ ጽዋ እንዲያፈስሱ ከተነገረ በኋላ በቁጥር ሁለት ላይ የመጀመሪያው መልአክ ሄዶ የቁጣውን ጽዋ በምድር ላይ ሲያፈስስ ሐዋርያው ዮሐንስ ያያል። ልክ የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋ አንደኛው በምድር ላይ ሲፈስስ የአውሬውም ምልክት ባለባቸውና ለአውሬው ምስል በሚሰግዱ ሰዎች ላይ መጥፎና የሚያሰቃይ ቁስል ወጣባቸው። ይህን ዓይነት ቁስል ሰው በምድር ላይ ከተፈጠረበት ዘመን አንስቶ እስከዚያ ድረስ በፍጹም ታይቶ የማይታወቅ ዓይነት ነበረ። ይህ ዓይነት ቁስል፣ ከነቀርሳ (ከካንሰር) ቁስል የሚበልጥ፣ ከቁምጥና በሽታ ቁስል ይልቅ የሚያሰቃይ ልዩ ዓይነት ነው። ብዙ ተአምራትን በመሥራት ኃይሉን ያሳይ የነበረው አውሬው (ምዕ. 13:13 ተመልከት) እንኳን ሊፈውሰው ወይም ማንም ሊረዳዳበት የማይችል ዓይነት ነበር። ሰዎች በዚህ ዓይነት ቁስል ቢሰቃዩም እንኳን ንስሐ አልገቡም። እንዲያውም እስከ አምስተኛው የእግዚብሔር የቁጣ ጽዋ ድረስ ስንመለከት እግዚአብሔርን ይሳደቡ ነበር። ይሰቃዩ የነበሩት ለአውሬውና ለምስሉ ይሰግዱ የነበሩት ብቻ ናቸው። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? በዘጸ. 10:21–23 መልስ አለው። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። እርሱ የሚፈቅደውን ሁሉ ያደርጋል።

## ቁ. 3 የሁለተኛው ጽዋ መፍሰስ

የመጀመሪያው የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋ በምድር ላይ ሲፈስስ ቀጥሎ ሁለተኛውን የቁጣ ጽዋ በባህር ላይ አፈሰሰው። ሁለተኛው መልአክ የቁጣ ጽዋ በባህር ላይ ባፈሰሰ ጊዜ የባህሩ ውሃ ወደ ደም ተለወጠ። እንደ ሞተ ሰው ደም ሆነ። በባህሩ ውስጥ የነበሩት ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት ሁሉ ሞቱ። ከዚህ በፊት በምዕ. 8:9

ላይ ሁለተኛው መለከት በተነፋ ጊዜ የባህር 1/3ኛው ወይም ሲሦው በውስጡ የነበሩት ሕይወት ያላቸው ነፍሳት ሞተው ነበረ። በዚህ በሁለተኛው የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋ መፍሰስ የባህሩ ሁሉ ሕያው ነፍሳት አለቁ። ይህ ፍርድ ዓለምን ሁሉ ይጐዳል። ምክንያቱም ዓለም በሞላ በባህር ውስጥ ተከቧልና ብዙ ይጠቀማል። ባህር ጨዋማ ስለሆነ ሕይወት ያለውን ነገር የመጠበቅ ባህርይ ስላለው፣ በሁለተኛው የቁጣ ጽዋ ደም መፍሰስ ግን ሰው ከተፈጥሮ በነፃ ያገኛቸው ከነበሩት ነገሮች ለምሳሌ ንጹህ አየር፣ የመጠጥ ውሃ፣ ጋዝ እንዲሁም ኤሌክትሪክ ወይም መብራትን እንዲሁም በብዛት በባህር ላይ ያለውን የንግድ መስመር በሞላ ያወድማል። ክርስቶስን ለሚጠሉት መጨረሻቸው አስፈሪና አስከፊ ነው። ዛሬም በክርስቶስ ለሚያምኑ ተስፋቸው እግዚብሔር ነው፣ ዕብ. 10:39።

## ቁ. 4–7 የሦስተኛው ቁጣ ጽዋ መፍሰስ

ሦስተኛው መልአክ የቁጣ ጽዋውን በወንዞችና በውኃ ምንጮች ላይ አፈሰሰ። እርሱም ደም ሆነ። ከዚህ በፊት ሦስተኛው መለከት በተነፋ ጊዜ በምዕ. 8:10 ላይ ንጹሕ ውኃ 1/3ኛው ወይም ሲሦው ወደ ደም ተለውጦ ነበር። አሁን ግን የምድር ንጹህ ውኃ በሞላ ወደ ደም ተለወጠ። ከዚያ በኋላ በውኃ ላይ ሥልጣን ያለው መልአክ ገለጻ ሲሰጥ ቁጥር 5 እና 6 ላይ ተገልጧል። ገለጻውም የጌታ ፍርድ ቅዱስ ፍርድ ነው ይላል። ትክክለኛ ነህ፤ እውነተኛ ነህ ሲል ዮሐንስ ይሰማዋል። ዮሐንስ እያየ መልአኩ ምክንያቱን ይገልጻል። ሰዎች የቅዱሳንና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ፣ ደም አጠጣቸው፤ ይህም የሚገባቸው ነው ይላል። የጻድቃን ደም በከንቱ ስለ ፈሰሰ አሁን ብድር መላሽ ጌታ ደም ያጠጣቸዋል።

ቁ. 7 ሌላ ድምጽ ከመሠዊያው ተሰማ። አዎን ሁሉን የምትችል ጌታ አምላክ ሆይ፣ ፍርድህ እውነትና ትክክል ነው እያለ። ጌታ ኢየሱስን ያላመኑት ስለሚያደርጉት ኃጢአት በሙሉ ደም የሚጠጡበት ጊዜ ይመጣል። ምን ያደርጉ ነበር ለሚለው ጥያቄ ምዕራፍ 13:10 ተመልከት። የፈለጉትን ሁሉ ያደርጉ ነበር። አሁን ግን ኃይል ሁሉ ሥልጣን ሁሉ የጌታ ሆነ። ጉልበት ለጌታ ይንበረከካል፤ ምላስም ሁሉ ጌትነቱን ይናገራል፣ ፊልጵ. 2:11።

## ቁ. 8–9 የአራተኛው ቁጣ ጽዋ መፍሰስ

አራተኛው መልአክ የእግዚአብሔርን የቁጣ ጽዋ በፀሐይ ላይ አፈሰሰ። በዚያን ጊዜ ሰዎችን በግለት እንዲያቃጥል ኃይል ተሰጠው። ሰዎችም በፀሐይዋ ትኩሳት የተነሳ ተቃጠሉ። ሰዎችም በመቅሰፍቶች ላይ ሥልጣን ያለውን የእግዚብሔርን ስም ተሳደቡ። ስለ ኃጢአታቸው ንስሃ መግባትና ለእግዚአብሔር ክብር መስጠትም እምቢ አሉ።

ከዚህ በፊት በምዕራፍ 8:12 ላይ አራተኛው መለከት በተነፋ ጊዜ የፀሐይ 1/3ኛ ወይም ሲሦ ተቃጥሎ ነበር። አሁን ግን በዚህ በአራተኛው የቁጣ ጽዋ መፍሰስ ምክንያት ፀሐይ በሙሉ እንደ ተቃጠለች እንመለከታለን። በዚህ ምክንያት ሰዎች በፀሐይዋ ትኩሳት ተቃጠሉ። ስለዚህ ጉዳይ ኢየሱስም በሉቃስ 21:25 ተናግሯል ። በመጨረሻም ምልክቶች በፀሐይ፣ በጨረቃና በከዋክብት ላይ እንደሚሆን ገልጿል። እንደዚሁም ሐዋርያው ጴጥሮስም ስለ እነዚህ ቀናት መፈጸምና ሁኔታቸው ትንቢት ተናግሯል። 2ጴጥ. 3:10–12። ስለ መጨረሻው የዓለም ፍርድ እግዚአብሔር ለዓለም በፈጠረው ነገር ዓለምን መልሶ ሊፈርድ እንደሚችል መመልከት እንችላለን። ፀሐይና ጨረቃ፣ ከዋክብትም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በእግዚአብሔር ምህረት ዓለምን ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ነገር ግን ሰዎች ከኃጢአት ንስሐ መግባት፣ እንዲሁም እግዚአብሔርን ማክበርና መፍራት እምቢ ስላሉ ለቅጣት እንደሚበቁ ነው። ይህ ሁሉ ቅጣት ለእምቢተኞች ሲሆን፣ እግዚአብሔርን ለሚፈሩት ዛሬ ክብሩንም ለሚሰጡት፣ በዳንኤል 3:19–25 ለእግዚአብሔር ልጆችና ለጠላቶች እንደሆነ ሁሉ፣ እንዲሁም በሙሴ ጊዜ በግብጽ ለእሥራኤል ልጆችና ለግብጻውያን እንደ ተደረገ ሁሉ፣ ዘጸ. 10:21–23 ተመልከት። የእግዚአብሔር ጥበቃ በጌታ ልጆች ላይ ይሆናል፣ መዝ. (121):6። ምናልባትም በምድር ላይ የጌታ ልጆች በምድር ላይ አሉ ከተባሉ የእሥራኤል ለእግዚአብሔር ታማኝ ቅሬታ ሊኖሩ ይችላሉ። በዚያ በመከራ ዘመን ሰዎች ግን ለኃጢአታቸው ንስሐ አይገቡም፤ ቁ.9። ስለዚህ ነው ኤርምያስ በምዕራፍ 17:9 የሰው ልብ እጅግ ክፉ ነው ያለው።

## ቁ. 10–11 አምስተኛው የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋ መፍሰስ

አምስተኛው መልአክ የእግዚአብሔርን የቁጣ ጽዋውን በአውሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ። የአውሬውም መንግሥት ጨለማ ሆነ፤ ሰዎችም

ከሥቃያቸው የተነሳ ምላሳቸውን ያኙኩ ነበር:: ከሥቃያቸውና ከቁስላቸው የተነሳ የሰማይን አምላክ ተራገሙ:: ከሥራቸውም ንስሐ አልገቡም::

ይህ አውሬ የተባለው ሐሳዊ መሲህ፣ ሐሰተኛው ክርስቶስ ነው:: ዛሬ የእርሱ ዙፋን የጨለማ ግዛት ዙፋን በዓለማችን ተዘርግቶ ይታያል፣ 1 ቆሮ. 4:4፤ ኤፌ.6:12:: በምድርና በአየር ላይ የአውሬው ዙፋን ላይ የቁጣው ጽዋ በፈሰሰ ጊዜ ሰዎች ከባድ ሥቃይ ያገኛቸዋል:: ምላሳቸውንም እንደሚያኙኩ ዮሐንስ ያይ ነበር:: በቁስልም ተወረሩ:: ነገሩ ቀላል አልነበረም:: ከባድ ሥቃይ ነው:: ይሁን እንጂ ሰዎች ንስሐ አልገቡም:: ከኃጢአታቸው ወደ እግዚአብሔር ምህረት አልተመለሱም:: እንዲያውም አብዝተው ተራገሙ እንጂ:: ስለዚህ ለፍርድ ጊዜ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 2:4–5 ላይ የተነገረውን አንብብ:: እንዲሁም ምህረት የሌለው ኃጢአት በመንፈስ ቅዱስ ላይ መናገር ሲሆን፣ ዛሬ የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ አለመስማት የእግዚአብሔርን ልጅ ክርስቶስን በእምነት መቀበልን እምቢ ማለት ለዚህ ዓይነት ቅጣት ይዳርጋል:: ዛሬ እውነተኛውን አምላክ በመንፈስ ማምለክ ትተን ለምስልና ለልዩ ልዩ ምልክቶች ብንሰግድ ቅጣትን ያመጣል:: አሁን ግን የእግዚአብሔር የምህረት ጊዜ ስለሆነ ማንም ሰው ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቢመጣ በምህረት ይቀበለዋል፣ የሐዋ. ሥራ 16:31::::

## ቁ. 12–16 ስድስተኛው የቁጣ ጽዋ መፍሰስ

ስድስተኛው መልአክ የእግዚአብሔርን የቁጣ ጽዋ በኤፍራጥስ ወንዝ ሲያፈስስ ዮሐንስ በራእይ ይመለከት ነበር:: የእግዚአብሔርን የቁጣ ጽዋ በኤፍራጥስ ወንዝ ባፈሰሰ ጊዜ ትልቁ የኤፍራጥስ ወንዝ ውኃ ደረቀ:: ከምሥራቅ በኩል የሚመጡ ነገሥታት ለጦርነት እንዲመጡ መንገድ ተዘጋጀላቸው፣ ቁ. 12:: ይህ ነገር ምሳሌያዊ ንግግር ብቻ ሳይሆን በእርግጥ የሚደረግ ነገር ነበረ:: በዚህ በስድስተኛው የቁጣ ጽዋ መፍሰስ ምክንያት የመጨረሻው የአርማጌዶን ጦርነት ዝግጅት መንገድ ይከፈታል::

ቁጥር 16 አርማጌዶን ታላቁ የዓለም መጨረሻ ጦርነት የሚደረግበት ጊዜና ቦታ ነው ተብሎ ይታመናል:: የወንዙ መድረቅ ከምሥራቅ በኩል ለሚመጡት ጦር ሠራዊት ሁኔታውን ቀላልና ምቹ ያደርገዋል:: የዓለም ሥልጣኔ በኤፍራጥስ ወንዝ አካባቢ እንደ ጀመረ እንዲሁም

የዓለም ሥልጣኔ በዚያ ወንዝ አካባቢ እንደሚፈጸምና እንደሚደመደም ይመስላል። ይህ ኤፍራጥስ የምሥራቅና የምዕራብን ወሰን የሚለይ ስፍራ ነው። ለአብርሃም ዘር ጌታ ቃል ሲገባ የውርስ ምድራቸው ድንበር በዚያ ነበር፣ ዘፍጥ. 15:18። የወንዙ ርዝመት ከ2896 ኪሎ ሜትር በላይ ሲሆን፣ ጎኑ ሰፊና በጣም ጥልቀት ያለው ነው። ለወታደሮች መሻገሪያነት ከባድ ስለሆነ፣ እግዚአብሔር ወንዙ ይድረቅ አለ ማለት ነው። በዚህ ምክንያት ለምሥራቅና ለምዕራብ መካከለኛ ድንበር መከፈት ለጦር ሠራዊት መተላለፊያ የተመቻቸ ስለሆነ፣ ለምሥራቅ ሠራዊት ወረራ ክፍት ይሆናል። ይህም የሚሆነው የምሥራቁ ሕዝብ ብዛት ስላለው ነው። ለምሳሌ ያህል የጃፓንና የቻይና እንዲሁም የሕንድን ሕዝብ ብዛት መገመት ይቻላል። እንዲሁም ትንንሽ መንግሥታትን፡፡ ይህ ወደ መጨረሻው የሚያመራ ጦርነት ሳይሆን አይቀርም። በቁጥር 13–16 ድረስ ያለው ሦስት ርኩሳን መናፍስት በእንቁራሪት መልክ ያለው ከእርኩሳን ሥላሴዎች አፍ ወጣ።

አንዱ ርኩስ መንፈስ ከዘንዶ አፍ፣ ሌላው ከአውሬው አፍ ሲወጣ፣ ሌላው ከሐሰተኛው ነቢይ አፍ ውስጥ ሲወጣ ዮሐንስ ይመለከታል። እነዚያ ሦስቱ እንቁራሪት የሚመስሉ ርኩሳን መናፍስቶች ወደ ዓለም ሁሉ፣ ወደ ነገሥታቶች ሁሉ ወጡና ለጦርነት ሰበሰቧቸው። ይህ ጦርነት የታላቁ ኃያል እግዚአብሔር ጦርነት ቀን ነው ይባላል። ድሉ ግን የጌታ ነው።

እነሆ እንደ ሌባ በድንገት እመጣለሁ ተጠንቀቁና ተዘጋጁ ይላል ጌታ። ከእነዚያ ከርኩሳን ሥላሴዎች አፍ የወጡት ሦስቱ ርኩሳን መናፍስት ለምድራችን በጣም ከባድ የሆነ መከራና የአርማጌዶን ጦርነት ሰብሳቢዎች ናቸው። ይህን የጦርነት ጊዜ ሰይጣን በተቻለው መጠን ከፋት የተሞላበት ጦርነት እንዲሆን ያደርጋል። ይህን ታላቅ ጥፋት ያለበትን ጦርነት ሰይጣን ወደ እሥራኤል ያደርግና እሥራኤልን በሙሉ ለመደምሰስና ከምድርም ለማጥፋት ምኞቱ ሲሆን፣ ከምድር የእግዚአብሔርን ሰዎች ለመደምሰስም ሙከራ ያደርጋል። ግን አይሳካለትም። እግዚአብሔር የዓለምን ሕዝብ በሙሉ እንዲሰበስብ ፈቀደለት እንጂ። ቁ. 16 ተመልከት።

ይህ ጦርነትና የሰይጣን ሙከራ እሥራኤልን ፈጽሞ አንዱንም በምድር ላይ የማያስቀር ዓይነት ነው። ለእሥራኤል ተስፋ የሚያስቆርጥ ዓይነት ነው። በዚያ ውስጥ ግን እግዚአብሔር አልተጨመረም። በዚህ

በመከራው ዘመን ለእሥራኤል ጨለማ ቢመስልም እግዚአብሔር ብርሃናቸው ይሆናል። እግዚአብሔር ጣልቃ ይገባል፣ ዘካ.14:1–3። ስለዚያች ሰዓት የተጻፈውን ተመልከት። ጌታ ለሕዝቡ ሲዋጋ በዮሐንስ ራእይ 19:11 ላይ እንደ ተጻፈው፣በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ይመጣል። በዚህ በከባድ ጦርነት እሥራኤል ወደ ሰሜን ወይም ወደ ደቡብ እንዲሁም ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ለእርዳታ የሚመለከትበት አይኖረውም። እሥራኤል ዓይኖቹን አቅንቶ ወደ ሰማይ ንጉሥ ብቻ ይመለከታል። በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ ይወርዳል። ከመከራቸውም ያወጣቸዋል፣ ዘካ. 14:4–5። በዚያን ጊዜ በክርስቶስ እጆች ስላሉት ቁስሎች ይጠይቃሉ፣ ዘካ. 13:6። ጌታም በወዳጆቹ እንደቆሰለ ይመልስላቸዋል። እነርሱም ያለቅሳሉ። በዚያ የቃሉ ትንቢት ይፈጸማል። ከዚያ ወዲያ ወደ ጌታ ይመለሳሉ፣ ዘካ. 12:10። ከዚያም ጌታ ለዘላለም እንደሚገዛቸው በመዝሙር 2 የተጻፈው ይፈጸማል። መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 2 አንብብ።

ቁጥር 17 የሰባተኛው የእግዚአብሔር ቁጣ ጽዋ መፍሰስ

ስለዚህ ስለ ሰባተኛው የቁጣ ጽዋ መፍሰስ ዮሐንስ ሲጽፍ ጽዋው በአየር ላይ ፈሰሰ ይላል። ጽዋው በአየር ላይ እንዲፈስ ከሰማይ ከቤተ መቅደስ ከዙፋን «ተፈጸመ» የሚል ቃል ተሰማ። ይህ ሰባተኛው ጽዋ የፈሰሰው በአየር ላይ ነበር። አየር የክፉ መናፍስት ግዛትና የዲያብሎስ ዙፋኑም ስለሆነ፣ ኤፌ. 6:12፤ ዮሐ.12:31፣ፍርዱ በአየር ላይ ሆኗል። ድምጽ ከእግዚአብሔር ዙፋን ከመቅደሱ ሲሆን፣ ወደዚያ ማንም ሊገባ አይችልም ነበረ፣ ምዕ. 15:8። ስለዚህ ጌታ ራሱ ነበረ ተፈጸመ ያለው። ከዚህ በፊትም ጌታ በመስቀል ላይ በነበረ ጊዜ ተፈጸመ የሚል ቃል ደህንነታችንን ሲፈጽም ተናግሯል፣ ዮሐ. 19:30። አሁን ግን በዮሐንስ ራእይ ፍርድ ሲፈጸም ማምለጫ አይገኝም፣ ክርስቶስ ራሱ ፈራጅ ነው፣ ዕብ. 2:3።

ቁጥር 18 በዚሁ በሰባተኛው የቁጣ ጽዋ መፍሰስ ታላቅና ከባድ የምድር መናወጥ ሆነ። ታላቂቱ ከተማ በሦስት ቦታ ተከፈለች፣ ዘካ. 14:4። ታላቂቱ ባቢሎንም በእግዚአብሔር ዘንድ ታሰበች።

ቁጥር 19 ስለ ታላቂቱ ባቢሎን ምዕራፍ 17 እና 18 ስንደርስ እናጠናለን።

ቁጥር 20 ከምድር መናወጥ ክብደት የተነሳ በባህር ያሉት ደሴቶችና ተራሮች እንደጠፉ እንመለከታለን:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምድር መናወጥ የእግዚአብሔር ፍርድ አንዱ መንገድ እንደሆነ እናያለን፤ ሕዝ. 38:: እንዲሁም በኢሳያስ 24:1 ደግሞ ተጽፏል:: ደግሞ ወደፊት አንድ ቀን ሰማይና ምድርን አናውጣለሁ ይላል ጌታ:: በምድር ላይ እስከ አሁን አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታ የምድር መናወጥ አለ:: ዓለምን ወይም ምድርን በሞላ አይደለም:: በዚያን ጊዜ ግን በምድር ሁሉ ላይ ይፈርዳል::

ቁጥር 21 በዚያኑ ጊዜ ከሰማይ ሌላ ፍርድ በሰዎች ላይ ሲወርድ እናያለን:: እርሱም እያንዳንዱ አርባ ኪሎግራም የሚመዝን በረዶ ከሰማይ በሰዎች ላይ ወረደባቸው:: ይህም እጅግ አሰቃቂ ፍርድ ነበረ:: ሰዎች ግን እግዚአብሔርን ተራገሙ እንጂ ንስሐ አልገቡም:: ዛሬ የእግዚአብሔርን የጸጋ ሥጦታ ከመቀበል መናቅ እንዴት አደገኛ ነው!

## የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 17 እና 18

## የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ በባቢሎን ላይ

እነዚህ ሁለት ምዕራፎች ለጥናት በጣም ከባድና አስቸጋሪ፣ ለሰውም የማይገቡ ምዕራፎች ይመስላሉ:: ቢሆንም የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን መርሳት የለብንም:: ስለዚህ ማንበብና ማጥናት አለብን፤ ራእይ 1:3::

ዮሐንስ ራእይ 17 እና 18 ሁለቱ ምዕራፎች ከምዕራፍ 16 ጋር ተከታታይነት የሌላቸው ናቸው:: ምዕራፎቹ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ታላቅ ፍርድ በባቢሎንና በምድር ላይ ሲሆን ያሳያል:: በቅድሚያ እነዚህን ምዕራፎች በዝርዝር ከማየታችን በፊት የእያንዳንዱን ምዕራፍ አመጣጥ እንመልከት::

የምዕራፍ 17ን አጀማመር ስንመለከት ከሰባቱ የቁጣ ጽዋ በምድር ላይ ከሚያፈሱት መላእክት አንዱ ሐዋርያው ዮሐንስን በራእይ 17:1 ላይና በብዙ ውሃዎች ላይ የተቀመጠችውን የታላቂቱን ጋለሞታ አመንዝራ ሴት የቅጣት ፍርድ አሳይሃለሁ ሲል እናያለን:: መልአኩ ዮሐንስን እንደ ጠራው፣ ዮሐንስ በመንፈስ ሆኖ ወደ ምድረ በዳ ወይም ወደ በረሃ ይወሰዳል:: ከዚያም ታላቂቱን አመንዝራ ሴት

እንደ አየ በቁጥር 3–5 አንብብ። በዚያ በበረሃ ዮሐንስ ሲያይ ሴትየዋ ምን እንደሆነች በቁጥር 6 አንብብ። ሴቲቱ በቅዱሳን ደም ሰክራ ነበር። ዮሐንስም ሴቲቱን ሲያይ በጣም ተደነቀ። መልአኩ ግን ለምን ታደንቃለህ? እርሷን የሚሸከማትን ምስጢር እኔ እነግርሃለሁ ይላል፣ ቁጥር 7 አንብብ።

በምዕራፍ 18 ደግሞ ታላቅ ሥልጣን ያለው መልአክ ከሰማይ ትልቅ ብርሃን እያበራ ሲወርድ በብርቱ ድምጽ ሲጮህ ዮሐንስ ያያል። ለታላቂቱ አመንዝራ ባቢሎን የሚናገረውን በቁጥር 9–10 አንብብ። ከዚህ በላይ በምዕራፍ 17 እና 18 በተመለከትናቸው ቁጥሮች ባቢሎን የሚል ቃል በጣም የታወቀና ቋሚ ቃል ነው። ይህ ባቢሎን የሚለው ቃል ለአንድ ከተማና የአንድ ነገር አሠራርና ሥርዓት የተሰጠ ቃል ነው። የእነዚህን ምዕራፎች ትርጉም ለማወቅ ቁልፉ፣ እነዚህን ባቢሎን ማለት አንድ ከተማ ወይም የአንድ ነገር አሠራርና ሥርዓት መሆኑን ማወቅ ነው።

ይህ ባቢሎን የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱሳችን ሲጠቀስ ኢየሩሳሌም ከሚለው ቃላት ያንሳል እንጂ በቁጥር ብዙ ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ስለ ሥርዓትና አሠራር ትርጉም የሚሰጥ ምን እንደሆነ የሚያብራሩ ሁለት ከተሞች አሉ። ያውም በምዕራፍ 17 እና 18 የሚያሳየው ባቢሎንና ሮም ናቸው። ሁለቱም ባቢሎንን ያሳስባሉ። አንዱ ባቢሎን ሲል ሮምን ሲያመለክት፣ እርሱም የኃይማኖትንና የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና አሠራርን ሲያመለክት፣ ሌላው ደግሞ ባቢሎን የሚል የፖለቲካና የንግድ አሠራር ሥርዓትን ያመለክታል ማለት ነው።

ራእይ 17 የቤተ ክርስቲያን በባቢሎን ሥርዓትና አሠራር ሲገለጽ

ራእይ 18 ደግሞ ፖለቲካ በባቢሎን ሥርዓትና አሠራርን ይገልጻል።

በእነዚህ ምዕራፎች መሠረት በኃይማኖት፣ በፖለቲካና በንግድ አሠራር ላይም የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚሆን እናያለን። ምዕራፍ 17 ሲገልጽ በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 13 የነበረው የሐሰተኛ ነቢይ አሠራርን መለስ ብለን መመልከት ይጠቅማል። ምዕራፍ 18 ደግሞ በዮሐንስ ራእይ 16፡17–21 ላይ ያለውን እግዚአብሔር በምድር ላይ ያፈሰሰውን የቁጣ ጽዋ ያመለክታል።

## ባቢሎን እንዴት እንደ ተጀመረ

ዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 17 እና 18 የእግዚአብሔር ፍርድ በባቢሎን እንደሚሆን ሲገልጽ ድንቅ እንዳይመስለን። ምክንያቱም ባቢሎን የኃጢአትና የባዕድ አምልኮ ጣዖትና የአመጽ አገዛዝ በምድር ላይ፣ አመጽ በእግዚአብሔር ላይ የተጀመረበት ቦታ ስለሆነ ነው። ሰዎች ከኤደን ገነት ከተባረሩ በኋላ ቃየን በኖድ ምድር ከተማ ሠርቶ ተቀመጠ፣ ዘፍጥ. 4:16። የከተማውን ስም በልጁ ስም ሄኖሕ ብሎ ጠራው፣ ዘፍጥ. 4:17። ያም ትውልድ አመጸኛ ትውልድ ሆነ፣ (ዘፍጥ. 4:19–24)። ያ ትውልድ በጥፋት ውኃ ተደመሰሰ። ከጥፋት ውኃ በኋላ የኩሽ ልጅ ናምሩድ ኃያል ሆኖ እንደተነሳ ዘፍጥ. 10:8 ተጽፏል። ኃያልነቱ በእግዚአብሔር ላይ ነበር። እግዚአብሔርን የማይፈራና የማይታዘዝ፣ በኃይሉ የሚመካ ሆኖ በሰናዖር ምድር ባቢሎንን መሠረተ፣ ዘፍጥ. 10:9–10። የናምሩድ ሚስት ሳመርማስ የተባለች ጣዖትና ባዕድ አምላክን አምላኪ የሆነች፣ ከኤልዛቤል የባሰች ሴት ነበረች። በባቢሎን መቅደስ ተሠርቶ የጣዖት ዋና ካህን ሳመርማስ ስትሆን፣ ጣዖቶቹም <u>አስታሮት</u> የሰማይ ንግሥት የተባለችና <u>በ</u>ዓል የተባለውን የፀሐይ አምላክ ያመልኩ ነበር። ናምሩድ ከሞተ በኋላም ሰመርማስ በዝሙቷ ወንድ ልጅ ወለደችና የሞተው ናምሩድ ተመልሶ ተወልዷል በማለት ሕዝቡ ልጇን ታሙዝን እንዲያመልኩ በማድረግ፣ ሕፃኑንና እናቱን ሕዝቡ እንዲያመልኩ የተደረገው በመጀመሪያ በባቢሎን ነበር፣ ሕዝ. 8:14። በኋላ ይህ አምልኮ ለእሥራኤላውያንም ደርሷል። ስለዚህ የሐሰት አምልኩና ኃይማኖት እንዲሁም የአመጽ አገዛዝና የፖለቲካ ሥርዓት ለዓለም ያበረከተበት ቦታ ስለሆነ ፍርድ ከእግዚአብሔር ይሆናል። ይህ ባቢሎንና አሰራሯ በቤተ ክርስቲያን ገብቶ ስለነበረ ኢየሱስ ክርስቶስ ለትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ይቺን ኤልዛቤልን ከመካከልህ አስወጣ እያለ መልእክትን ልኮለታል፣ ራእይ 2:18–29። በተለይም በምዕ. 17 ላይ ቁ. 1–5 ይህች የባቢሎን ምስጢር የሆነችው ጋለሞታ በምስጢራዊ አሠራር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መግባቷን በግልጽ ያሳስበናል።

ስለ ባቢሎን ፍርድ፣ ኢሳ. 13፤ ኤር. 50:35 እስከ ምዕ. 51:24–26፤ ራእይ 18:18። በተለይም ራእይ 17 እና 18 ምዕራፎችን አጥና።

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 17

ወደ ዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 17 ስንመጣ በመጀመሪያ የምናየው ስለ ጋለሞታ ሴት ምሳሌ ነው:: ይህ ምዕራፍ የሚያሳስበን በዮሐንስ ራእይ ያሉትን የሦስት ሴቶች ምሳሌና ምንን እንደሚያመልኩ ነው::

1. አንደኛዋ ሴት በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 17:1 በብዙ ውኃዎች የተቀመጠች፣ ታላቂቱ ጋለሞታ ሴት፣ በዝሙቷ ነገሥታትን ያሰከረች፣ የስድብ ስሞች የሞሉባት፣ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉዋት፣ ቀይ ልብሶችን ለብሳ በቀይ አውሬ ላይ የተቀመጠች፣ በግምባሯ የምስጢር ስም ታላቂቱ ባቢሎን ተብሎ የተጻፈባት ነበረች:: በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ ምስክሮች ደም የሰከረች ሴት ናት፣ (ቁ.1–6):: ይህች ሴት የሐሰት ቤተ ክርስቲያንን ትወክላለች:: ይህች ሴት በትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ኤልዛቤል ተብላ እንደምትገኝ ኢየሱስ ገልጿል፣ (ራእይ 2:20)::
2. <u>ሁለተኛዋ ሴት</u> በዮሐንስ ራእይ 12:1 የምትገኝ ሲሆን፣ ፀሐይን ለብሳ፣ ጨረቃን በእግሮቿ ረግጣ፣ 12 ኮከቦች በራሷ የደፋች ሴት ነበረች:: እርሷ የእስራኤልን ልጆች የምትወክል ናት፣ ራእይ 12:1–6፤ 13–17::
3. <u>ሦስተኛዋ ሴት</u> በዮሐንስ ራእይ 19:7 እንዲሁም 21:9 ላይ ራሷን ያዘጋጀች የበጉ ሚስት ሙሽራይቱን ነው:: ይህች ሴት እውነተኛ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የምትወክል ናት:: ስለዚህ መልአኩ እነዚህን ሴቶች በየጊዜው ለዮሐንስ ያሳይ ነበር::

ቁ. 1 እና 2 ስለዚህ በምዕራፍ 17:1 እና 19:1–2 ቤተ ክርስቲያንን መስላ ሐሰትን ትዘራ የነበረችው በዝሙት የተሞላች ጋለሞታ ሴት ባቢሎን ፍርድ ስትቀበል እናያለን:: እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅ ነው:: ይህች ሐሰተኛ ሴት ለራሷ ብዙ ሕዝብን፣ ብዙ ወገኖችን፣ ብዙ ስዎችንና ቋንቋዎችን ማለትም ብዙ ኃይማኖቶችን እንደምትይዝ፣ እንዲሁም አስር የዓለም ታላላቅ ነገሥታትንና ቀንዶች የተባሉትን እንደምታቅፍ ምዕ. 17:15 ተጽፏል::

እኛ ዛሬ ከእነዚህ ከሦስቱ ሴቶች የትኛዋን እንመስላለን? ከየትኛዋ ጋር ነን? የትኛዋን እያገለገልን ነው?

ቁ. 3 መልአኩ ዮሐንስን ወስዶ ያሳየው በበረሃ በቀይ አውሬ ላይ የተቀመጠችውን ሴት ነበረ:: የስድብ ስሞችና ሰባት ራሶች እንዲሁም

አሥር ቀንዶች ያሉት ማን እንደሆነ ከዚህ በፊት በምዕ. 13 ላይ ያየነው ሐሳዊ መሲህን ነበር። ምዕ. 17:1 እና 13:1ን ስንመለከት ያው አንድ ዓይነት አውሬ ነው። ሴትዮዋም በመጨረሻው ዘመን የሐሰትን ኃይማኖት ሥርዓት የያዘች መሆንዋን እንረዳለን። ያም ሐሰተኛው ቤተ ክርስቲያን ነው።

ቁ. 4 ይህች ውጭዋ ሲታይ የከበረችና ሐብታም ስትመስል ውስጥዋ ግን ባዶና ራቁት፣ ደሃም እንደሆነች ኢየሱስ አመልክቶ ነበር፣ ምዕ. 3:17። በእጅዋም የያዘችው የወርቅ ጽዋ የሐሰት ወንጌል መሆኑን ያሳያል። ከራእይ 1:20 ጋር አመዛዝን።

ቁ. 5 የሴትየዋ ስም የምስጢር ስም ነበር። ታላቂቱ ባቢሎን የጋለሞታዎችና የምድር እርኩሳት እናት ተብላለች። የዛሬ የእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ስምም ምስጢር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በብሉይ ኪዳንና በነቢያት የተሰወረ፣ በአዲስ ኪዳንና በሐዋርያት የተገለጠ የክርስቶስ ምስጢር የሆነ ቤተ ክርስቲያን በኔ ተገለጠ ይላል፣ (ኤፌ. 3:2–6)። ስለዚህ ሰይጣን ሐሰትን ይዞ በተቻለው መጠን በየትኛውም ዘዴ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ሊመስልና ሊያስመስል እንደሚፈልግ በዚህ ልናውቅ እንችላለን። 2ቆሮ. 11:13–15። ምንም ታድርግ ምንም ትምሰል እንጂ፣ የእግዚአብሔር ፍርድ በርሷ ላይ ይሆናል፣ ራእይ 17:1።

ቁጥር 6 እና 7 በመከራ ዘመን ታላቅ ስደት በምዕመናን ላይ ይሆናል። ዮሐንስ ሲያያት ሴቲቱ በቅዱሳንና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ ነበር ይላል። ነገሩ ዮሐንስን ያስደንቅ ስለነበረ መልአኩ ተርጉሞ ሲገልጽለት እናያለን። ከታላቁ የመከራ ዘመን ቀደም ብሎ ክርስቶስ እውነተኛዋን ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ ስለሚነጥቅ በምድር የሚቀረው የሐሰት ቤተ ክርስቲያን ይሆናል። ይህች ቤተ ክርስቲያን በቀይ አውሬ ላይ ተቀምጣ ነበረ። መሪዋ አውሬ ነው። እርሱም ሐሳዊ መሲህ ነው። በዚያ ዘመን ከሐሰተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ብዙዎቹ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነት ስለሚመለሱ፣ ብዙዎችም ስለሚያምኑ ይገደላሉ። ይህንንም በምዕ. 13:15 ተመልክተን ነበረ። ለምስሉ አንሰግድም ያሉት ተገደሉ። እንዲሁም በምዕራፍ 6:10 አምስተኛው ማኅተም ሲከፈት የተገደሉት ቅዱሳን ሲጮኹ አይተናል። አሁን ግን ፍርድ በፍጥነት መጣባቸው። እነዚያ የተገደሉት ሰማዕታት ነጭ ልብስ ለብሰው በዙፋኑ ፊት ቆመው፣ በምዕ. 7:9–14 ተመልክተናል። በምዕ. 17:7 በቅዱሳን ደም የሰከረችው ሴትና የተሸከማት አውሬ፣

ሴቲቱ የሐሰት ቤተ ክርስቲያንን ስትወክል፣ የተሸከማት አውሬ፣ 7 ራሶችንና 10 ቀንዶችን፣ የፖለቲካ አገዛዝ ሥልጣንን እንደሚይዝና አውሬው ኃይማኖትንም ፖለቲካንም በቁጥጥሩ ሥር እንደሚያደርግና ለእውነተኛ አማኞች መከራ እንደሚበዛ እናያለን።

## ቁ. 8 የአውሬው መጨረሻ

ከቁጥር 8 ጀምሮ የአውሬውን ማንነትና ከየት እንደመጣ፣ ወዴት እንደሚደርስና ያችን ጋለሞታይቱን ሴት እንደሚያጠፋ መግለጫ ተሰጥቶናል። መልአኩ ለዮሐንስ ከተረጐመ ለቤተ ክርስቲያን ተገለጸ ማለት ነው። ያየኸው አውሬ አስቀድሞ ነበረ፣ አሁን ግን የለም። ከጥልቁ ዘንድ ይውጣ አለው፤ ወደ ጥፋት ይሄዳል አለ። ይህ ገዢ ወይም ባለ ሥልጣን ይምጣ እንጂ በጌታ መምጫ ይጠፋል። የዓለም ሕዝብ ግን ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፈ ሁሉ፣ ስለ አውሬው አስቀድሞ የነበረ አሁን የሌለ፣ ከጥልቅም ይወጣ ስለ አለው፣አድናቆትን ሲያበዙ እንመለከታለን። ዓለም በሆነውና በሚሆነው ነገር ሁሉ ይደነቃል እንጂ ወደ ክርስቶስ እውነት አይመጣም።

ቁ. 9–11 ጥበብ ያለው ስለ ስምንቱ አገዛዝ (ነገሥታት) ያስተውል። አንዳንዶች፣ ሰባት ራስና አስር ቀንዶች፣ ከሮም ከሰባቱ ተራራዎች የሚነሱ ገዢዎች ናቸው ብለው ይተረጉማሉ። ሌሎች ደግሞ ልክ ለዳንኤል እንደተባለው የዓለም ገዢዎች የነበሩትን ነገሥታት ለምሳሌ፣ ግብጽን፣ አሶርን፣ ባቢሎንን፣ ሜዶንና ፋርስን፣ ግሪክን፣ ሮምን፣ ሰባተኛው የአውሮፓ የተባበሩት መንግሥታትንና የመጨረሻው ሐሰተኛ መሲህን ራሱን የሚያወራ ነው የሚመስል ይላሉ። ይህ ስምንተኛው ሐሳዊ መሲህ ጋለሞታይቱን ሴት የተሸከመ ራሱ ነው።

ቁ. 12 መልአኩ ለዮሐንስ ሲገልጽ አሥሩ ቀንዶች ገና መንግሥት ያልተቀበሉ ነገሥታት ናቸው አለው።

ቁ. 13 አውሬው ለአንድ ሰዓት፣ ለአጭር ጊዜ ሥልጣን ይሰጣቸዋል። እነርሱም እርሱን ያገለግላሉ። እነዚህ አስሩ የተባበሩት መንግሥታት ለአውሬው ኃይላቸውን፣ ሥልጣናቸውንና አገልግሎታቸውን ይሰጣሉ።

ቁ. 14 እነዚህ የተባበሩት አስር መንግሥታት በጉን ይዋጋሉ። ነገር ግን የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌቶችም ጌታ የሆነው ድል ይመታቸዋል። ከእርሱም ጋር ያሉት የተጠሩት፣ የተመረጡትና የታመኑም ድል ያደርጋሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የነገሥታት ንጉሥ ወይም የጌቶች ጌታ ብቻ ሳይሆን የሁሉ ፈጣሪና አምላክ መሆኑን በቆላስይስ 1:16 ተጽፏል።

ሰይጣንና ሠራዊቱ ማለት ነገሥታት ሁሉ በአርማጌዶን ለጦርነት እንደሚሰበሰቡና በነጩ ፈረስ ላይ የተቀመጠውን የእግዚአብሔርን ልጅ እንደሚዋጉ በምዕራፍ 19:19 ወደ ፊት እንመለከታለን::

ቁ. 15 መልአኩ ለሐዋርያ ዮሐንስ ገለጻ ሲያደርግ፣ በቁ. 1 ያየሃት በውኃዎች የተቀመጠች ጋለሞታ፣ ውኃዎች ማለት ብዙ ወገኖች፣ ብዙ ሕዝብና ቋንቋዎች ናቸው ተብሏል::

ቁ. 16–18 የጋለሞታይቱ መጥፋት

አውሬውና እነዚያ አስሩ የተባበሩት ነገሥታት ጋለሞታይቱን ሴት እንደሚጠሉና እንዲያጠፏት ተደረገ:: ያም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈጽሙ ነበር:: ባዶዋን፣ ራቁቷን አድርገው ሥጋዋን በሉና በእሳት አቃጠሏት:: ይህ ዕድል ለሐሰተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ይጠብቃታል:: በክርስቶስ ደም ያልተዋጀች፣ ግን ቤተ ክርስቲያን ነኝ ለምትለዋ ወዮላት::

እግዚአብሔር የራሱን ዓላማና ፈቃድ እርስ በእርሳቸው በማጣላት እንኳ ይፈጽማል:: ከዚህ በፊት በጣዖት መሪዋ በኤልዛቤል እግዚአብሔር እንዴት እንደሠራ በ2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 9 ልንመለከት እንችላለን:: እንደዚሁም በመጨረሻው ዘመን አውሬውና ዘንዶው ከነገሥታቱ ጋር በሐሰተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተነስተው እንደሚያጠፉዋት ልብ በሉ::

ሰይጣን ከብዙ ዘመናት ጀምሮ የእግዚአብሔርን ዓይነት አምልኮና ስግደት ለራሱ ሊወስድ ይፈልግ የነበረውን፣ አሁን ዘንዶው ከአውሬው እንዲሁም ከነገሥታት ይቀበላል፣ ምዕ. 13:4 ተመልከት::

ስለዚህ ነገር ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2:1–12 ያለውን አስቡ:: ሰይጣን ቀድሞ በኤደን ገነት፣ ቀጥሎም የባቢሎንን ግምብ ሲሠሩ ቋንቋቸው በተዘበራረቀበት ጊዜ፣ በክርስቶስ መስቀል ጊዜ መልካሙን አጥፍቶ የዓለምን ጥፋት በማምጣት ለራሱ ክብርና አምልኮ ከሰዎች መውሰድ የፈለገውን በዚህ ምዕራፍ ለአጭር ጊዜ ሲወስድ እናያለን:: መጨረሻው ግን የእርሱም ጥፋት ነው፣ ራእይ 20:10 ተመልከት::

በምዕራፍ 17 የኃይማኖት ወይም የቤተ ክርስቲያን ባቢሎን ተደምስሷል:: አሁን በምዕራፍ 18 ደግሞ የፖለቲካና የንግድ ባቢሎን ሲፈረድበት እንመለከታለን::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 18
# የፖለቲካና የንግድ ባቢሎን ፍርድ

ዮሐንስ ራእይ 18፡1 «ከዚህ በኋላ» በሚል ቃል ይጀምራል። ያም ማለት የኃይማኖትና የሐሰት ቤተ ክርስቲያን ባቢሎን ከተፈረደባት በኋላ ማለት ነው።

ሐዋርያው ዮሐንስ ሌላ ሥልጣን ያለው መልአክ ሲወርድ በታላቅ ድምጽ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች ሲል ይሰማል፣ ያያል።

በምዕራፍ 18 የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የንግድ ሐሰተኛው ባቢሎን መፈረድ እንዳለበት ይገልጻል። ይህም ፍርድ በክርስቶስ ሁለተኛ ወደ ምድር መመለስ ጊዜ የሚሆን እንደሆነ ያስረዳል። የምዕራፍ 17 ባቢሎን የሐሰተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ፍርድ በዓለም በታላቁ መከራ መካከል ወይም ከ3 ዓመት ተኩል በኋላ ሲሆን፣ የምዕራፍ 18 ባቢሎን ማለት ግን የአስተዳደርና የንግድ፣ የኢኮኖሚ ባቢሎን ብልግና ወይም ኃጢአቷ በክርስቶስ መመለስ ላይ ሆኖ ከዓለም መከራ መጨረሻ ላይ መሆኑንና ሰባቱ ዓመት እንደተፈጸመ ይሆናል። ፈራጁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ይሆናል፣ ራእይ 18፡8።

ዋናው ነገር ራእይ 17 እና 18 ስለ ባቢሎን መውደቅ ቢያወሩም ሁለቱም ልዩነት አላቸው። አንዱ የኃይማኖት ባቢሎን፣ ሁለተኛው የአስተዳደር ባቢሎን ሆኖ፣ ጌታ የሚፈርድበት ጊዜ ይሆናል። ምዕራፍ 18፡8 ተመልከት። የኃይማኖት ባቢሎንን አውሬውና ነገሥታት እንዲቀጡ ጌታ ሲፈቅድ፣ የአስተዳደር ባቢሎን ግን ጌታ ራሱ ይቀጣል፣ ሮሜ 6፡23።

ቁ. 1 ከዚህ በኋላ ማለት በምዕ. 17 ያየናት የሐሰት ቤተ ክርስቲያን ወይም የኃይማኖት ሥርዓት መፈረድ በኋላ ማለት ነው፣ ከክብሩ የተነሳ ምድርን የሚያበራ ታላቅ ሥልጣን ያለው መልአክ ስለ አስተዳደር ሥርዓት ፍርድ ያበስር ነበር።

ቁ. 2 ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፣ ወደቀች ብሎ ስለ ፍርዷ ጮኸ። አንዳንዶች እንደሚያስቡት ይህ ቦታ በመጨረሻው ዘመን የዓለም አስተዳደር የሆነችው ከተማ ባቢሎን በኤፍራጥስ ወንዝ አካባቢ እንደምትሠራና የዓለም አስተዳደር ወደዚያ ሳይጠቃለል አይቀርም፣ ይህ ባይሆንና ያቺ ከተማ ባትሆንም የዓለም የሰው አስተዳደር በርኩሰት የተሞላ እንደሚፈረድበት ያሳያል። ቁጥር 2 ለዚህ ምዕራፍ ዋና

ቁልፍ ነው:: ስለ ባቢሎን ከተማ መውደቅ በዚህ ምዕራፍ ያሉትን ቁጥር 2,10,16,18,21 ተመልከት:: በእነዚህ ቁጥሮች ምክንያት የባቢሎን ከተማ የዓለም አስተዳደር የሚሆንበት ሳይሠራ የሚቀር አይመስልም::

ዛሬ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ዓይኑን ዘይትና ማዕድን በሚያወጡት በመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች ላይ ሲያተኩር ያስደንቃል:: መካከለኛው ምሥራቅ በብዙ ነገሮች ትኩረት እየተሰጠው ነው:: ለምን ይሆን? ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢትና የዓለም ዓይን ወደዚያ ስለሆነ ነው:: የመጨረሻው የክርስቶስ መምጫ ትንቢቶች የሚፈጸሙት በዚያ ነው:: የባቢሎን መውደቅ ጉዳይ በኢሳያስ 13 እና በኤርምያስ 50 ላይ ያለው ትንቢት መፈጸሚያ ይሆናል::

ቁ. 3 መልአኩ ለዮሐንስ የገለጸለት የባቢሎን መውደቅ ዋና ምክንያት፣ አሕዛብን በክፋት የተሞላ ነገር በማስለመዷ ነበር::

ቁ. 4 <u>የመለየት ጥሪ</u>

እግዚአብሔር ለሕዝቡ በየዘመናቱ ጥሪውን እንደሚያስተላልፍ ሁሉ በዚሁ ጥቅስም ጥሪውን ያስተላልፋል:: እግዚአብሔር ከኃጢአት ጋር ሕብረት ስለሌለው እኛንም ከኃጢአት ጋር አትተባበሩ ይለናል::

1. በሙሴ ዘመን ለእሥራኤላውያን በፍርድ መካከል ጥሪ አስተላለፈ፣ ዘዳ. 4:29-31::
2. ዛሬም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሰይጣናዊ ሥራዎችና ሥርዓት እንድንለይ በጥብቅ እየገለጸ ከእነርሱ መካከል ውጡ ይለናል፣ 2ኛ ቆሮ. 6:14-18::
3. ለክርስቲያን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ፣ 1 ዮሐ. 2:15-17፤ እንዲሁም ያዕ. 4:4 ከዓለም ተለዩ ይለናል::
4. ክርስቲያን ራሱን እንዲመረምርና ንስሐ እንዲገባ 1ዮሐ. 1:9::

ቁ. 5 በዚህ ቁጥር የኃጢአት ደረጃ ምን ያህል ከፍ ብሎ እንደሚሄድ በግልጽ ያሳያል:: የኃጢአት ሁሉ ደረጃ በተለይም በታላቁ በሰባቱ ዓመት የመከራ ዘመን ኃጢአት ወደ ሰማይ እንደሚደርስ ነው:: በእግዚአብሔርም ዘንድ ይታሰባል:: በሎጥ ዘመንም የሰዶምና የገሞራ ኃጢአት ጩኸት በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ሆኖ ነበር፣ ዘፍጥ. 19:13:: እግዚአብሔር የባቢሎንን ኃጢአት ለብዙ ዘመናት እየመዘገበ እንደ ቆየና በመጨረሻም የፍርድ ጊዜ እንደ ቀረበ ይገልጻል::

እንዲሁም ሰው በክርስቶስ ስም አምኖ ኃጢአቱ በክርስቶስ ደም ካልተደመሰሰ በስተቀር፣ ዮሐ. 1:9 የሁሉ ሰው ኃጢአት ወደ እግዚአብሔር ፍርድ ይመጣል። እግዚአብሔርም ስለሚታገስ፣ 2ኛ ጴጥ. 3:9 ኃጢአትን የረሳ መስሎት ሰው ይዝናና ይሆናል። አንድ ቀን ግን በጌታ ፊት ያገኘዋል፣ ዘኍ. 32:23።

ቁ. 6 ክርስቶስን የሚጠሉትን ኃጢአታቸውን በላያቸው ላይ የሚጨምሩትን፣ የኃጢአት ብድራት እንደሚከፈላቸው ቢያውቁና ያም ኃጢአት መራራ መሆኑን ቢረዱ በፍጥነት ወደ ጌታ በሸሹ ነበር። በመጨረሻ በሕይወት መጽሐፍ ያልተገኘ ሁሉ እንደሥራቸው መጠን በፍርድ ዙፋን ፊት ይከፈላቸዋል፣ ራእይ 20:12። ከባድ ፍርድ ይጠብቃቸዋል፣ ሮሜ 2:4–11። ማምለጫ አይኖርም፣ ዕብ. 2:3፣9:27።

ቁ. 7 ራሷን የምታመሰግን ባቢሎን

ራሷን ከፍ አደረገች፣ ኰራች፣ ከእኔ ሌላ የለም አለች፣ ራሴ ለራሴ አምላክ ነኝ አለች። እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል፣ 1ኛ ጴጥ. 5:5፤ ያዕ. 4:6–7። ራሷን ለጌታ ዝቅ ማድረግ እምቢ ካለች የሥራዋን ዋጋ ታገኛለች፣ ገላ. 6:7።

ቁ. 8 በኃጢአተኞች ላይ የሚፈርድ እግዚአብሔር ብርቱ ነው፣ ዕብ. 10:31። በሰዶምና ገሞራ ከንዱን ያሳየ እግዚአብሔር ብርቱ ነው፣ዕብ. 12:25–29። ኢየሱስ ለሞኙ ሐብታም ያለውን አስብ፣ ሉቃስ 12:19–20። የእግዚአብሔር ፍርድ እንዴት አስፈሪ ነው።

ቁ. 9–10 የዓለም ነጋዴዎችና ባለጠጎች ጩኸት

1. እግዚአብሔር በምዕ. 17 ላይ የባቢሎንን ምስጢር በፈረደ ጊዜ የዓለም ነገሥታትና ገዢዎች እጅግ ደስ አላቸው። ምክንያቱም ጋለሞታይቱ ሴት ለእነርሱ እንቅፋት ነበረች።

2. እግዚአብሔር በምዕ. 18 ላይ በታላቂቱ ባቢሎን የንግድና የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ባቢሎን ሲፈርድ ግን የዓለም ነጋዴዎችና ሐብታሞች ሁሉ ትልቅና ትንሽ ሳይቀር ያለቅሱና ያዝኑ ነበር።

ዮሐንስ እያየ በአንዲት ሰዓት ማለት በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍርድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዶ እቃጥሉ ጨረሳት። የጭሱንና የፍርዱን ሁኔታ በዓለም ያሉት ሁሉ በቴሌቪዥን ያዩ ነበር። በምድር ወይም በባህር ያሉት ይመለከቱ ነበር።

ቁ. 10 ታላቂቱ ከተማ ባቢሎን ወዮልሽ ወዮልሽ በአንድ ሰዓት ፍርድ ደርሶብሻል ይላል።

በመስከረም 1/94 ዓ.ም. በአሜሪካን አገር በኒውዮርክ ከተማ የነበረውን የዓለም ንግድ ማዕከል ፎቆች፣ በጀት አውሮፕላን በተመታ ጊዜ የፎቆቹን መደርመስ ዓለም ሁሉ አይቷል። በትንሽ ጊዜ ውስጥ እንዴት እንደ ጠፉ፣ በውስጡም የነበሩት እንዴት እንዳለቁ በዓይናችን አይተናል፣ በጆሯችንም ሰምተናል። እንዲሁ ይሆንን? የወርቅ፣ የብር፣ የከበረ ድንጋዮችና ልዩ ልዩ ልብሶች ከከተማዋ ጋር ወደሙ። ከምድር ከርስ የሚወጡ፣ ከምድር ላይ የሚገኙ ውድ የንግድ ቁሳቁሶችና ሰዎች፣ ከባህር የሚገኙ ሳይቀሩ ተቃጠሉ። እነዚህ ነገሮች በሙሉ ከሰይጣን አምልኮ ጋር የተነካኩ ነበሩ። እግዚአብሔር በእነዚህ ዕቃዎችና ገገርዎች እንዲሁም ነጋዴዎች አይከብርም ነበር። ክብርን ሁሉ ሰይጣንና ሰው ለራሱ ስለ ወሰደ እግዚአብሔር መቅጣት ነበረበት። ስለዚህ ቅጣት ደረሰበት።

ዛሬ ክርስቲያን የዓለምን ሐብትና ባለጠግነት ክብር ስታይ ልብህ ምን ያስባል? ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ የዓለምን ድሎት ትፈልጋለህ? ክርስቲያን ሆይ ልብህን መርምር። ዛሬ በዓለም መጨረሻ ጫፍ ላይ እንደምንኖር አትርሳ። ልብህ በዓለማዊ ሐብትና ምኞት ብቻ አይሙላ። ነገር ግን በማያልፍ በጌታ ፍቅርና ቃል ይሙላ፣ ማቴ. 24:35። ልብን ከሚሰርቅ ከዓለማዊ ባለጠግነት ምኞትና ጉድጓድ ውጣ ነጻ ሁን። ለሁለት ጌታ ማገልገል አትችልምና፣ ማቴ. 6:24።

ቁ. 20 በባቢሎን ፍርድ የሰማዩ ሁኔታ እንዴት ነበር

ሰማይ ሆይ ደስ ይበልህ ተባለ። እናንተም ቅዱሳን ደስ ይበላችሁ። ሐዋርያት፣ ነቢያትም ደስ ይበላችሁ ተባለ። ምክንያቱም ለካ እነርሱን በምድር ታሳድድና መከራ ታሳይ የነበረች ይህች ባቢሎን ናትና ነው። ቅዱሳን አማኞችን፣ ሐዋርያቶችንና ነቢያትን የፈጀች እርሷ ናትና። አሁን ግን ተፈረደባት። የርሷን ፍርድ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ዙፋን ሆነው ይጠባበቁ ነበር ማለት ነው። እግዚአብሔር ይታገሳል እንጂ ለፍርድ አይዘገይም። እርሱ እውነተኛና ጻድቅ ፈራጅ ነው፤ የበቀል ጊዜ ነውና ራእይ 18:24። እግዚአብሔር የቅዱሳንን ደም የሚበቀልበት ጊዜ መጣ፣ ደስ ይበለን። ጊዜ መጣ፣ በዓለም የነበሩት፣ ይስቁና ይደሰቱ የነበሩት ደግሞ የሚያለቅሱበት፣ በምድር ሥቃይን እያዩ ያለቅሱ የነበሩት ቅዱሳን የጌታ ልጆች የሚደሰቱበት ጊዜ

መጣ:: ቅዱሳን የሚደሰቱበት ምክንያት የእግዚአብሔር ቅድስናና የእግዚአብሔር ትክክለኛ ፍርድ ስለ ተፈጸመ ነው:: የምድር ሕዝብ ሲያለቅሱ ባዶ ሲቀሩ፣ ኢዮብ 1:21፣ ቅዱሳን ሲደሰቱ፣ ዕንባ. 3:18፣ ፊልጵ. 4:4 ምን ይሰማሃል? አንተስ በየትኛው ክፍል ነህ? ጊዜያዊ ደስታ ወይም የዘለዓለምን ትፈልጋለህ?

ቁ. 21 የፍርዱ ዓይነት

ይህ ቁጥር እንደሚገልጽልን መሠረት አንድ ብርቱ መልአክ ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ የሚያህል አንድ ትልቅ ድንጋይ አንስቶ ወደ እሳት ባህር ወረወረና ታላቂቱ ባቢሎን እንዲህ ተገፍታ ወደቀች፣ እንግዲህም ወዲህ ከቶ አትገኝም አለ:: ወደ ፍርድ ባህር ተወረወረች:: ከዚህም በፊት በምዕራፍ 16:17–21 ፍርዷን ተመልክተን ነበር:: በዚህን ጊዜ ድንጋይ የሚያህል ነገር ከሰማይ ሲወድቅባት ከተማዋ ትታይ ነበር:: አሁን ግን በዚህ ምዕራፍ ከተማዋ ከቦታው ስትጠፋ እንመለከታለን:: በባህር ወይም በእሳት ባህር ተዋጠች:: ከከተማዋ የቀረ ምንም ነገር የለም:: የድንጋዩን ትርጉምና ምሳሌ ማወቅ ከፈለጋችሁ 1ኛ ቆሮ. 10:4፣ ከዳን. 2:34–35፣44፣45:እንብቡ::

ቁ. 22–24 የምድር ደስታዎች ያበቃሉ:: በዚህ ቦታ 6 የደስታ ምንጮችን ተመልከት

1. የስሚት ደስታዎችና ምንጭ ያበቃል:: ያውም የበገናና የዝማሬ፣ እምቢልታና፣ የመለከት ድምጽ፣ የሙዚቃ ድምጽ ያበቃል::
2. የአንጉልና የእጅ ጥበብ ደስታ ምንጭ ያበቃል:: ያውም የእጅ ጥበብና ብልሃተኝነት ድምጽ::
3. የእህልና ምግብ ደስታ ምንጭ ያበቃል:: ያውም የወፍጮ ድምጽ::
4. በብርሃን መደሰት ምንጭ ያበቃል:: ያውም የመብራትና የብርሃን ድምጽ::
5. በጋብቻ የመደሰት ድምጽ ያበቃል:: ያውም የሙሽራውና የሙሽራይቱ ድምጽ፣ ሠርግ፣ ዘፈንና ግብዣ ወዘተ ወይም የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ድምጽ በዚያ አይገኝም::
6. የገበ ምንጭ ደስታ ያበቃል:: ያውም ንግድና ነጋዴዎች የምድር መኳንንት በአስማት ሕዝብን አሳስተው ነበር:: ስለዚህ ከእንግዲህ ምንም አይኖርም:: አይሰማም ያበቃል::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 19

## የክርስቶስ ዳግም መመለስ

**ቁጥር 1**

ይህ ምዕራፍ ሲጀምር «ከዚህ በኋላ» ብሎ ይጀምራል። ምን ማለት ነው? ያቺ ነጋዴዋ ባቢሎን ፍርድ ከተቀበለች በኋላ የሚቀጥል ነገር ነው ማለት ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ እየሰማና እያየ በሰማይ የብዙ ሰዎች ድምጽ ሰማ። እንዲህ እያሉ ነበር፡—

**ቁጥር 2**

ሃሌሉያ ማዳንና ክብር ኃይልም የአምላካች ነው። ምክንያቱም ምድርን በዝሙቷ ያጠፋችውን ያችን ታላቂቷን ጋለሞታ ሴት እግዚአብሔር ስለፈረደባት፣ የባሪያዎቹንም ደም ከእጅዋ ስለተበቀለ ፍርዶቹ እውነትና ጽድቅ ነው አሉ። ይህ 19ኛው ምዕራፍ የመከራ ዘመን ማለቂያ እንደሆነና ደስ ብሏቸው በሰማይ ዝማሬ እንዳደረጉ ያሳየናል፣ ራእይ 18፡20። በምዕራፍ 19፡1 በደስታቸው ምክንያት ለጥሪው መልስ ሲሰጡ እንመለከታለን። አሸናፊና የፍጥረት ገዢ የሆነው ኢየሱስ በአውሬውና በዘንዶው የሚፈርድበት፣ ለሺህ ዓመትም የሚገዛበት ዘመን ስለ ደረሰ ነው። ያቺ ክፉ ባቢሎን ተፈረደባት። ጨለማው ወደብርሃን ተለወጠ፣ ፍርድ ወደ በረከት መለወጡ ነው።

በምዕራፍ 19 የምንመለከታቸው ሁለት ትልልቅ ነገሮች፣ የበጉ ሠርግና የጌታ ዳግም መምጣት ጉዳይ ነው። እንዲሁም በዚህ ምዕራ ሁለት ትልልቅ ግብዣዎችን እናያለን። ያውም የበጉ ሠርግ ግብዣና በአርማጌዶን ጦርነት ለሰማይ አሞራዎችና ወፎች የተሰጠ የሥጋ ግብዣ ነው። ያም ማለት በሮሜ 8፡18–23 ድረስ የተጻፈው የተስፋችን ዘመን መጣ፣ የእግዚአብሔር ልጆች የነጻነት ዘመን ስለ መጣ በሰማይ ደስታ ሆነ ማለት ነው።

**ቁጥር 2–3 በሰማይ ታላቅ ሃሌሉያ**

እነዚህ ምስጋና የሚያቀርቡ ቅዱሳን አሁን ነገሮችን ከእግዚአብሔር አቅጣጫ እግዚአብሔር እንደሚያይ ዓይነት አድርገው ስለሚያዩ ነገሮቹ ልዩ ሆነዋል። እነዚህ ቅዱሳን ለእግዚአብሔር ማዳንና ክብር ኃይልም ይሁን ሲሉ፣ ምክንያት አላቸው። እርሱ እግዚአብሔር እውነተኛ፣ ጻድቅ ፈራጅ ስለሆነና ያቺን ጋለሞታ በርኩሰቷ ምድርን በሞላ ያበላሸችውን እንዲሁም ጌታ የቅዱሳንን ደም ስለ ተበቀለ

ምስጋናና እልልታ በሰማይ ስለሆነ ነው:: ደግሞ የፍርዷ ጢስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ስለ ወጣ ነው::

ታላቅ ሃሌሉያ የሆነበት ምክንያት

1. ጋለሞታዋ ሴት ስለ ተፈረደባት
2. ጌታ ማንም ሊቃወም በማይችል ሁኔታ ስለሚነግሥ ነው::
3. የቅዱሳን ደም በከንቱ የፈሰሰውን ስለ ተበቀለላቸው ነው::
4. የበጉ ሠርግ ሥፍራውን ስለሚወስድና የሐሰት ሙሽራይቱ መንገድ ስለለቀቀችና ስለ ተወገደች ነው:: በቁጥር 3 ላይ የጢስ መውጣት ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚለው በራእይ 14:9–11 ስለተገለጸ ተመልከት::

ቁ. 4 ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በሰማይ ሠራዊት ደስታ አብረው ተደሳቾች ሆነው በታላቅ ዝማሬ ውስጥ ሲገኙ እናያለን:: ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ወደ ሰማይ የተነጠቁ ቤተ ክርስቲያንን የሚወክሉት ናቸው:: 4ቱ እንስሳትና ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ሃሌ ሉያ ብለው ለእግዚአብሔር ሲሰግዱ ይታያሉ:: በዮሐንስ ራእይ ስለ 24ቱ ሽማግሌዎች የሚያወራው የመጨረሻ ቦታ ራእይ 19:4 ነው:: ከዚህ በኋላ ስለ ቤተ ክርስቲያን በተለይም የተነጠቁትን ምዕመናን የሚወክል 24 ሽማግሌዎች የሚለው ይቀርና ሙሽራይቱ ወይም ሚስቱ በሚል ቃል ተተክቶ እናያለን::

ቁ. 5–6 ድምጽ ከዙፋኑ ወጣ፣ እንዲህ እያለ፣ እግዚአብሔርን የምትፈሩ ባሪያዎች ሁሉ አምላካችንን አመስግኑ የሚል ኃይለኛ ድምጽ፣ ከባድ ድምጽ፣ ሃሌ ሉያ ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላካችን ነግሦአልና፣ ኃይል ሁሉ ብርታት ሁሉ የእርሱ የሆነ ጌታ ነግሦአልና ይሉ ነበረ:: እንግዲህ ሙሽራው ከነገሠ ሙሽራይቱም የመንግሥዋ ጊዜ መጥቷል ማለት ነው:: እንግዲህ የበጉ ሠርግ ደርሦአልና፤ ይህ የበጉ ሠርግ ከጌታ ወደ ምድር መመለስ ቀደም ብሉ በሰማይ ይሆናል::

ቁ. 7–10 የበጉ ሠርግ ሥነ ሥርዓት

ከሃሌ ሉያ ኳየር (መዘምራን) ቀጥሎ የተሰጠ መግለጫ:: መግለጫውም የበጉን ሠርግና እራት የሚመለከት ጉዳይ ነበረ:: ስለ ሠርግ አይሁዶች የሚያደርጉት ሥርዓት ነበራቸው:: ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ጭምር ስለ ሠርግ እንመለከታለን::

1. ሠርግ ሁልጊዜ በአባት ማለት በሁለቱ ሙሽራና ሙሽራይቱ ወላጆች የሚደረጉ ሥርዓቶችን ያሳስበናል። ለምሳሌ ያህል የማርያምና የዮሴፍ ጋብቻ ጉዳይ በማቴ. 1:19–25 ላይ ያለውን ማንበብ ነው። ስለ ሁለቱ እጮኛሞች ጉዳይ በጥልቅ ማየት ይቻላል። ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳለች፣ ይህ መታጨት ማለት በወላጆቻቸውና በቤተሰባቸው እንዲሁም በሕብረተሰባቸው የመታጨት ፕሮግራም ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ ማርያም የዮሴፍ ሚስት ትባል ነበረ። ወንዱ እጮኛዋ ለሴቷ ባልዋ ይባል ነበረ። ሠርግ ተደርጐ ሳይጋቡ ወይም በግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳይኖራቸው እንኳን ባልና ሚስት ይባሉ ነበር። ይህን ከማቴዎስ ወንጌል ልንገነዘብ እንችላለን። በዚህ መካከል ሳሉ መልአክ መጥቶ ለዮሴፍ ስለ እጮኛው ወይም በአይሁድ ሕግ ስለ ሚስቱ ከመንፈስ ቅዱስ ማርገዟን ገለጸለት።

2. በዚሁ ዓይነት ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምዕመናን በ2ኛ ቆሮ. 11:2 ላይ ለክርስቶስ ለአንድ ባል ለማቅረብ እንደ አጯቸው ይናገራል። ስለዚህ ይህች የታጨች ድንግሊቱ ለወንዱ ሚስት ናት። ያም ክርስቶስ ባል ሆኖ፣ ቤተ ክርስቲያን ሚስቱ ድንግሊቱ ሆና እናገኛለን።

3. በኤፌሶን 1:3–4 ላይ ስንመለከት እግዚአብሔር አብ ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ሚስት እንድትሆን እንደ መረጣት እንመለከታለን። እኛ አማኞች ሳንወለድ በፊት ተመርጠናል፣ ታጭተናል፣ እንግዲህ በአይሁድ ሕግ ወንድ ልጁ ለአባቱ እጮኛዬን አምጡልኝ ብሎ ሲናገር፣ አሁን አገባለሁ ብሎ ራሱን አዘጋጅቶ ሲቀርብ ሙሽራይቱ ትመጣለች። የሙሽራይቱ መቅረብ ጊዜ ይባላል። የልጅቷ አባት ወደ ልጁ ወይም ወደ ሙሽራው የሚስቱን ወይም የሙሽራይቱን እጅ ይዞ ይመጣና ለልጁ አባት ሲያስረክብ፣ የልጁ አባት ተቀብሎ ለልጁ ለሙሽራው ሙሽራይቱን ይሰጣል። ወይም ያስረክባል። ያኔ ሙሉ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ተፈጸመ ይባላል።

4. የሙሽራይቱ ወደ ሙሽራው መቅረብ ጉዳይ በኤፌሶን 5:25–27 ባሎች ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ይላል። ራሱን ለቤተ ክርስቲያን አሳልፎ ሰጥቷል። በውኃ አንጽቷት ቤተ ክርስቲያንን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ ይላል። እንግዲህ ይህ ወደ ራሱ ማቅረብ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ

በአየር ስትወሰድ 1ኛ ተሰሎ. 4፡16–17 ላይ እንደተገለጸው ይፈጸማል። በዚያም በሰማይ የሠርጉ ቃል ኪዳን የሚደረግና የሚፈጸም ይመስላል። በዚያ በሠርጉ ጊዜ ምናልባት ቶሎ ወደ ሠርጉ እራት መሄድ ሳይሆን ሙሽራው ሙሽራይቱን ለተጋበዙት ጉባኤ የማስተዋወቅና የሽርሽር ፕሮግራም ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። ከዚያም ሁልጊዜ ሙሽራይቱ ከሙሽራው ጋር ትሆናለች፣ 1ኛ ተሰሎ. 4፡17–18። ይህ የደስታ ጊዜያቸው ይሆናል። ስለዚህ ፕሮግራም አንተ ራስህን አዘጋጅተሃል ወይ?

ቁ. 8–9 የበጉ ሠርግ

ሚስቱ ራስዋን ስለ አዘጋጀች ደስ ይበለን ይላል። ቤተ ክርስቲያን ምን ጊዜም ራስዋን በቅድስና መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ርኵሰትን መጸየፍ አለባት፣ ዕብ. 12፡14፤ ይሁዳ 1፡24–25። ሚስቱ ምን ጊዜም ያማረና ያጌጠ ልብስ መልበስ ያስፈልጋታል። ቀጭን ያጌጠ ልብስ የተባለው የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ ነው። በክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ከነጻን በኋላ ለመልካም ሥራ ተጠርተናል። የጽድቅ ሥራ እንሥራ፣ መልካም ሥራ ሁልጊዜም ያስፈልገናል፣ ማቴ. 5፡16፤ ኤፌ. 2፡10።

ቁ. 9 ወደ በጉ ሠርግ እራት መጠራት።

የዓለም ሕዝብ ሁሉ ተጠርቷል። በወንጌል እየተጠራ ነው። እናንተ ደካሞች ወደ እኔ ኑ ይላል፣ ማቴ. 11፡28–30።

የግብዣው ሁኔታ

ሰው ሁሉ እንደ አቅሙ፣ እንደ ባለጠግነቱ መጠን ነው የሚያደርገው። ድግሱ ለአጭር ጊዜ ሊሆን ይችላል ወይም ለሙሉ ሳምንት ወይም ከዚያም በላይ ለረጅም ወራት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ በዮሐንስ 2፡1–12 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ተጠርተው ነበረ። ከዚያም ድግስ እንደነበረና በዚያ እንደ ተካፈለ እናያለን።

## 5. ስለ በጉ ሠርግ ግብዣ

ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 22፡1–14 ያለውን መርምር። ይህ ንጉሥ ያዘጋጀው የልጁ ሠርግና ግብዣ፣ እግዚአብሔር ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያዘጋጀው ሠርግና ድግሥ ይመስላል። ደግሞ ወደ ሠርጉ እንመጣም ብለው የቀሩትን አይሁዳውያንን ያመለክታል፣ በማቴ. 25፡1–13 ድረስ ያለውን የሠርግ ቦታ ተመልከትና አመዛዝን።

ሙሽራው ከሙሽራይቱ ጋር ስለሚመጣ ተዘጋጅተው ይጠባበቁ ነበር። የተዘጋጁት ከሙሽራው ጋር ሺህ ዓመት ሊነግሡ ወደ ሠርጉ ገቡ። ያልተዘጋጁት አይሁዶች ግን በውጭ ቀሩ። ዘይቱ መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል፣ (ሮሜ 8፡9)።

## ልዩ ልብስ

ሙሽራው የለበሰው የራሱን ቅድስና የተባለውን ልብስ ሲሆን፣ ሙሽራይቱ የለበሰችው የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ ይባላል። ስለዚህ ነው በቁጥር 9 ላይ ወደ በጉ ሠርግ የተጠሩ ብጹአን ናቸውና ጻፍ የተባለው። ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው ይላል። የበጉ ሠርግ ግብዣ ጊዜ እንደ ራእይ 21፡9–10 መሠረት ከክርስቶስ ጋር ለሺህ ዓመት ስንነግሥ የሚሆን ይመስላል። ደስ ይበላችሁ፣ በታውም ከሰማይ የምትወርድ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ይሆን ይሆናል። በበጉ ሠርግ እራት የሚገኙት እንግዶች በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፡–

1. ዮሐንስ መጥምቁ እንደ ዮሐንስ 3፡29
2. እንደ ሉቃስ፣ 13፡28–29 የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ሁሉ ነው።
3. እንደ ራእይ 20፡4 መሠረት በመከራ ዘመን ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም የታረዱትና የተገደሉት ቅዱሳን ሁሉ፣
4. በመከራ ዘመን የሚድኑ ሕዝብ በሙሉ፣
5. ምናልባት ቅዱሳን መላእክት በሙሉ፣ ዕብ.1፡6።

ቁ. 10 የዮሐንስን ሁኔታ እንመልከት፤ ስለ በጉ ሠርግ እራት ገለጻ ላደረገው መልእክት መስገድ ሲሞክር መልአኩ መልሶ፣ አታድርገው አለ። ማለት አትስገድልኝ፣ እኔም አንተም የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነን። ለእግዚአብሔር ስገድ። የሚሰገድለት እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኔ ቅዱስ መልአክ ስግደትን ከእግዚአብሔር ልወስድና ለራሴ ለማድረግ አልችልም። እኔም ለእግዚአብሔር ብቻ እሰግዳለሁ። እኔም ፍጡር ነኝ። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ስገድ አለው መልአኩ፣ ራእይ 22፡8–9። ክብር ምስጋና ስግደት የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ቁ.11 <u>የሰማይ መከፈት</u>

ሐዋርያው ዮሐንስ ሰማይ ተከፍቶ አየሁ ይላል በዮሐንስ ራእይ 4፡1–2። ሰማይ ተከፍቶ ዮሐንስን ወደላይ ሲያስወጣው ወይም ሲያስገባ ነበረ። አሁን ግን ልዩ ነበረ። ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ምድር የሚመልስ ሰማይ ተከፍቶ ነበረ። ዮሐንስ ወደ ሰማይ ሊገባ ሲሆን፣ በዚህ ቦታ

ግን ኢየሱስ ከሰማይ ሲወጣ ወደ ምድር ሲወርድ ይታያል:: ቁ. 11ን አንብብ:: ጌታ ከሰማይ ወደ ምድር ከቅዱሳንና ከመላእክት ጋር ሲወርድ ይህን ምድር ባበላሸው በሐሳዊ መሲህና በምድር ነገሥታት ላይ ልክ በዳንኤል መጽሐፍ ምዕ. 2:34-45 እንደተጻፈ ከሰማይ የተወረወረ ድንጋይ ይወርድባቸዋል:: የጌታ መውረድ ለሰይጣንና ለሐሳዊ መሲህ፣ እንዲሁም ለክፉ ሰዎች የመጨረሻ ጥፋታቸው ይሆናል:: ክርስቶስ ሺህ ዓመት መንገሥ ከመጀመሩ በፊት የክፋት ሠራዊት በሞላ መንገድ መልቀቅ አለባቸው:: ከዚያ በኋላ ነው የጽድቅ መንግሥት የሚቋቋመው::

<u>ነጭ ፈረስ</u>፡- ክርስቶስ በነጭ (አምባላይ) ፈረስ ላይ፣ ፈረስ የጦርነት ምሳሌ ነው:: ከዚህ በፊት በምዕ. 6:2 ላይ ሐሳዊ መሲህ ክርስቶስን መስሎ ሕዝቡን ሊያስት በነጭ ፈረስ ተቀምጦ መጣና አታለላቸው:: ክርስቶስ ግን እውነተኛ ነው:: በመጀመሪያ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ ራሱን ዝቅ አድርጎ፣ አዋርዶ፣ ሠላማዊ ሆኖ፣ በአህያ ላይተቀምጦ ነበር፣ ማቴ.21:1-11:: አሁን ግን በፈረስ ላይ ተቀምጦ ሲመጣ በጦርነትና በድል አድራጊነት ይመጣል፣ ቁጥር 11 ተመልከት:: በነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠው ታማኝና እውነተኛ ይባላል:: ፊልጵ. 2:8-11:: በመጀመሪያ መምጣት ራሱን አዋርዶ፣ በሁለተኛው መምጣት ግን ራሱን ከፍ ያደረገ፣ ኃያሉ እግዚአብሔር እርሱ ብቻ ነው:: እርሱ ከሁሉ በላይ ነው:: እርሱ ክብር ይገባዋል:: እርሱ ሊነግሥ ይገባዋል:: እርሱ ድል አድራጊ ነው:: እርሱ እውነተኛና ታማኝ ነው:: በእውነትም ይፈርዳል::

ቁ. 12 ዓይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ናቸው::

በምዕራፍ 1:14 ላይ አይተናል:: ማለት አንዳችም ነገር ከዓይኖቹ ማምለጥ አይችልም:: ማንም ከእርሱ መደበቅ አይችልም፣ ምዕ. 6:12-17 ተመልክተናል::

- በራሱ ላይ ብዙ ዘውዶች አሉ ይላል:: ከዚህ ጊዜ አንስቶ ክርስቶስ ወሰን የሌለው የምድር ሁሉ ገዢዋ ባለ ሥልጣን እርሱ መሆኑን ያሳያል:: እስከዚያ ድረስ ሰይጣን ሁልጊዜ እየተቃወመው ነበር:: አሁን ግን ክርስቶስ ሰይጣንን ስለፈረደበት የዘላለም የምድርና የሰማይ ገዢ ይሆናል::
- ደግሞ ከራሱ በቀር ማንም ሊያውቅ የማይችል የተጻፈ ስም አለው::

## ቁ. 13 በደም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፏል

ለዓለም ሕዝብ ደሙን አፈሰሰ፣ ኢሳ. 63:2–6:: እርሱ በዓለም ሊፈርድ ይመጣል:: ስሙም የእግዚአብሐር ቃል ተብሏል፣ ዮሐ. 1:1:: እስከዚህ ድረስ ክርስቶስ በዙፋኑ ሆኖ ፍርድን ወደ ምድር ይልክ ነበር:: አሁን ግን ወደ ምድር ይወርዳል:: ኢየሱስ ወደ ምድር ሲወርድ ወደ ሰማይ ሲያርግ ባረገበት፣ የሐዋ. ሥራ 1:10–12 ወደ ደብረ ዘይት ተራራ እግሮቹ ይወርዳል፣ ዘካ. 14:4:: ከዚያም የተከማቸውን የምድር ገዢዎችን ሠራዊት በሥልጣኑ ይዋጋል፣ ድልም ያደርጋል::

## ቁ. 14 የሰማይ ጭፍራዎች

ይህን ዮሐንስ እያየ ነበረ:: የሰማይ ጭፍራዎች በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጠው ቀጭን የነጻ የተልባ እግር ልብስ ለብሰው ጌታን ይከተሉ ነበር:: እነዚህ የሰማይ ጭፍራዎች የተባሉት:–

1ኛ ቅዱሳን ጉባኤ ከጌታ ጋር በሞት የተገናኙት፣
2ኛ ቅዱሳን አልፍ አእላፋት መላእክት፣
3ኛ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ይሆናሉ:: እነርሱም በትንሳኤ ከጌታ ጋር ይሆናሉና ነው::

## ቁ. 15 አጥፊው መሣሪያ

የመጨረሻው የአርማጌዶን ጦርነትን የሚመታ ከባድ መሣሪያ ምን እንደሆነ በዚህ ቁጥር ተገልጿል:: ይህ ጦርነት ጠቅላላ በፍልስጥኤም ወይም በእስራኤል አገር የሚሆን ሳይሆን አይቀርም:: ምክንያቱም የአርማጌዶን ጦርነት ቦታ በእስራኤል አገር 200 ማይልስ ስፋት ያለበት ቦታ እንደሚሆን ራእይ 14:20 ላይ የቦታው መለኪያ ተጽፎ ይገኛል:: እንዲሁም የወይን መጭመቂያ ቦታ ይልና የደሙ መፍሰስ ወደ ፈረሶች ልጓም ድረስ እንደሚደርስ አይተን ነበር:: በዚህ ጦርነት የሰማይ ሠራዊት በመሣሪያ አይዋጉም:: ነገር ግን ጌታ ራሱ ከአፉ የሚወጣ ሰይፍ ታላቅ የማጥፊያ መሣሪያ ይሆናል:: ጦርነቱ የአንድ በኩል ሠራዊት ብቻ ይሆናል:: ያውም በአንድ በኩል ለጦርነት የሚቆሙት የዓለም ሕዝብ በሞላ ሆኖ፣ በሌላ በኩል የሰማይ ሠራዊት ለሰልፍ ሳይቆሙ ጌታ ብቻ ይቆማል:: የሰማይ ሠራዊት በጌታ በኩል ቆመው ይመለከታሉ:: ጌታም ከአፉ በሚወጣ ሰይፍ አህዛብን ይመታቸዋል:: ከአፉ የሚወጣው ቃል ትልቅ ሥራ ይሠራል::

በመጀመሪያ በዘፍጥረት 1:3–6 ቁጥር 9, 11, 14, 20, 24, 26 በእነዚህ ቁጥሮች 8 ጊዜ እግዚአብሔር በቃሉ ይሁን አለ ይላል:: ሆኖም በመዝሙር 33:6–9 እግዚአብሔር በቃሉ ሰማይንና ምድርን ሌሎችንም ፍጥረታት እንደፈጠረ እናያለን:: እንዲሁም በዓለም መጨረሻ ጌታችን በቃሉ በሚወጣ ቃል ምድርን ይፈርዳል:: በብረት በትርም በቃሉ በሚወጣ ብቻ ይገዛቸዋል፣ ራእይ 1:16 ተመልከት::

ቁ. 16 በልብሱና በጭኑ የተጻፈው ስም አስደናቂ ነው:: የነገሥታት ንጉሥ የጌቶችም ጌታ:: ጌታ በሁለተኛው መምጣት ጊዜ ከሁሉ በላይ አጠቃላይ ባለ ሥልጣን ይሆናል:: አልፋና ኦሜጋ፣ መጀመሪያና መጨረሻ፣ ሁሉን የሚወስን ሆኖ እናያለን፣ ራእይ 1:8::

በጦርነቱ የሚሳተፉ እነማን ናቸው? መልሱ ራእይ 19:19 ተመልከት:: ምዕራፍ 16:12–19 ተመልከት:: ራእይ 19:17–20:: ይህም ሆኖ በጉ ድል ያደርጋቸዋል፣ ዕብ. 12:25–27 ተመልከት::

## ቁ. 17–18 የአርማጌዶን የመጨረሻ ውጊያ

ዲያቢሎስ ከነጭፍሮቹ እንዲሁም የምድር ነገሥታትና ገዢዎች ከሐሰተኛ ነብይና ሐሳዊ መሢህ ጋር አንድ ወገን ሆነው ጌታ ኢየሱስና የሰማይ ሠራዊት ሊዋጉ የሚሰበሰቡበት ጦርነትና የጦር ሜዳው አርማጌዶን ጦርነት ይባላል:: በዚያ ጦርነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአፉ በሚወጣ ስለታም ሰይፍ (ቃል) ሲመታቸው የሰው ሬሳና የከብት ሬሳ በሜዳ ስለሚወድቅ የሰማይ አሞራዎችን ለግብዣ የሚጠራ መልአክ ጥሪ ይሰማል:: እንግዲህ ጌታ ለብዙ ዓመታት በሰው ልጆች ላይ ምሕረቱንና ትዕግሥቱን እያሳየ ቆይቷል:: አሁን ግን የፍርድ ሰዓት ደረሰ:: ሰው ሁሉ በሕይወቱ ዘመን የዘራውን የሚያጭድበት ጊዜ ደረሰ:: ስለዚህ ይጨክናል፣ ገላ. 6:7–8:: የፍርድ ጊዜ ደረሰ::

ቁ. 19 አውሬው ምንም እንኳ ከጌታ ጋር ጦርነት ሊያደርግ የምድር ሠራዊት ቢያከማችም መጨረሻቸው ጥፋት ይሆናል:: ዛሬም ቢሆን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ጠላት የተሸነፈ ነው፣ ያዕ. 4:7–8፤ 1ኛ ጴጥ. 5:9:: ያም ዲያቢሎስ ነው:: ዲያቢሎስና ሰዎች ራሳቸው ባዘጋጁት መሣሪያ እግዚብሔርን የሚያሸንፉ መስሏቸው ነበር::

## ቁ. 20 የአውሬውና የሐሰተኛ ነብይ መጠረሻቸው

የተሸነፉ የምድር ሠራዊትና አውሬው ምን እንደሚሆኑ ጌታ ሲገልጽ ድንቅና ተአምራትን ያደረገው ሐሰተኛው ነቢይ በሕይወታቸው በዲን ወደሚቃጠሉበት ወደ እሳት ባህር ተጣሉ። አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ራሳቸውን የሰይጣን መጠቀሚያ አድርገው ስለሰጡ ወደ እሳት ባህር ይጣላሉ፣ ራእይ 20:10። ያሳታቸው ዲያቢሎስም ከእነርሱ ጋር ወደ እሳት ባህር ይጣላሉ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት ሐሳዊ መሢህና ሐሰተኛው ነቢይ የመጀመሪያው የእሳት ባህር እራት ናቸው። በኋላ የሚቀጥለው ዲያቢሎስ ምዕ. 20:10–15 እንዲሁም በጌታ ያላመኑት ሁሉ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው እሳት ባህር ይጣላሉ፣ ማቴ. 25:41። እስከዚያ ድረስ ሲያል ላላመኑትና ለከፉዎች ማረፊያ ነው፣ ሉቃስ 16:19–31። በዚያን ጊዜ በመዝ. 2:1–4 የተጻፈው ቃል ይፈጸማል። ክርስቶስ ድል አድራጊ ይሆናል።

## ቁ. 21 የቀሩት ሰዎች መጠረሻቸው

በፈረስ ላይ ከተቀመጠው አፍ ከሚወጣ ሰይፍ የተገደሉትን በቁጥር 15 አይተን ነበር። እንዲሁም በምዕራፍ 14:19–20 ፍርዳቸውን ተመልክተናል። ከዚህ ከአርማጌዶን ጦርነት ቀጥለን የታላቁ መከራ ዘመን ማለቁንና ማብቃቱን እንድንገነዘብ ያስፈልጋል። ከዚህ በኋላ በጥናታችን ከታላቁ መከራ በኋላ ምን እንደሚሆን እንመለከታለን።

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 20

## እግዚብሔር በሰይጣን ላይ ያለው የመጨረሻ ውሳኔ የሚለውን እንመርምር

ቁ. 1–3 እንዲሁም ቁ. 7–10

አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ዓቢይ ወቅትና ምዕራፍ ደርሰናል:: የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን:: ይህ ምዕራፍ እንደሚያመለክተው ክርስቶስ ለሺህ ዓመት በምድር ላይ የሚነግሥበት ጊዜ መጣ:: ሰይጣን ለሺህ ዓመት በጥልቅ ታስሮ ተዘግቶበት እናያለን:: ይህ የሰይጣን የመጨረሻው ውጤት ነው:: እንዲሁም የመከራ ዘመን ቅዱሳንና ትንሣኤያቸውን የምድርን ሁኔታ እንዲሁም ትልቅ ነጭ ዙፋንን እንመለከታለን:: ክርስቶስ ለሺህ ዓመት በምድር ላይ ይነግሣል:: ያውም ጌታ በጸሎቱ ያስተማረን መንግሥት ወደ ምድር መምጣቱ ነው፤ ማቴ. 6:10–13:: «መንግሥትህ ትምጣ» የሚለው እንዲሁም መንግሥትህን ለእሥራኤል መቼ ትመልሳለህ? የተባለለት የሐዋ.ሥራ 1:6::

በዚህ በራእይ ምዕራፍ 20 ላይ የተዘረዘሩት የአምስቱን ክንውኖች ቅደም ተከተል እንመለከታለን:: እነዚህ:–

1. ሰይጣን ለሺህ ዓመት መታሰሩ፤ ቁ. 1–3
2. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገደሉትን ቅዱሳን፤ ቁ. 4:–6
3. ከሺህ ዓመት በኋላ የሰይጣን መለቀቅን፤ ቁ. 7–9
4. ሰይጣን ወደ ዘላለም የእሳት ባህር መጣሉን፤ ቁ. 19::
5. ታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድና ያላመኑት የየዘመናቱን ሕዝቦች ቁ. 11–15

ለጥናታችን እንዲረዳን ይህን ምዕራፍ በትልልቅ አርእስት እንከፍለዋለን:: ይኸውም የሚከተለው ነው::

1. እግዚአብሔር በሰይጣን ላይ ያለው የመጨረሻ ውሳኔ
2. የእግዚአብሔር መንግሥት ከክርስቶስና ከቅዱሳኑ ጋር
3. የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ ባላመኑት ላይ::

ዮሐንስ ራእይ ምዕ. 20ን ቁጥር በቁጥር ስንመለከት ማስታወስ የሚገባን ዋና ነገር ምዕ. 20 ከምዕ. 19 የሚቀጥል ተከታታይ መሆኑን ነው::

ሐዋርያው ዮሐንስ የሚጠቀመው ታላቅ ቃል ሰማይ ተከፍቶ አየሁ የሚለውን ቃል ከምዕ. 19 እስከ ምዕ. 21 ድረስ አስር ጊዜ እናገኛለን:: ለምሳሌ ምዕራፍ 19:11 ቁጥር 17 ,19፣ ምዕ. 20:1,4,11,12፤ ምዕ. 21:1,2,3 ተመልከት::

## ቁ. 1–3 የሰይጣን መታሰር

ዮሐንስ የምድር ጦር ሠራዊትና ጦርነት በጌታ ቅጣትን ከተቀበሉና ከጠፉ በኋላ የሰይጣንን መታሰር አየሁ ይላል:: ሰይጣን ለምን ለሺህ ዓመት በጥልቅ ይታሠራል? መልሱ በኢሳያስ 14:12–16 ላይ ይገኛል:: ሰይጣን በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ላይ ካመጸበት ጊዜ አንስቶ ራሱን ከፍ አደረገ:: የዚህ ዓለምም ገዢ ሆነ:: ስለዚህ አሁን እግዚአብሔር ሰይጣንን ዝቅ ያደርጋል:: የእግዚብሔር ኃይል ከሰይጣን ኃይል እጅግ ይበልጣል:: በዚህ ምዕራፍ የሰይጣንን መታሰር እናያለን:: ሰይጣን ምንም ኃይለኛ መስሎ ቢታይም እግዚአብሔር ከተናገረ ተራ መልአክ ሊያስረውና ወደ ጥልቅ ሊወረውረው ይችላል ማለት ነው:: እስከዚያ ድረስ የመላእክት አለቃ የሆነው መልአኩ ሚካኤል እንኳን በራሱ ሥልጣን ምንም ማድረግ አልፈለገም:: ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ፣ ይሁዳ ቁጥር 9፣ ራእይ 12:7–9::
ደግሞም የሚገርመው ነገር ይህ በዮሐንስ ራእይ 20:1–3 ያለው ሰይጣንን ያሰረ መልአክ በሰይጣን ላይ 6 ነገሮችን ለማድረግ ሥልጣን እንዳለው እናያለን:: እነርሱም:–

1. እጁን ለመጫን
2. ሺህ ዓመት ለማሰር
3. ወደጥልቅ ለመጣል
4. ጉድጓዱን ለመዝጋት
5. ለማተም
6. እንደገና ከሺህ ዓመት በኋላ ይፈታ ዘንድ

ሰይጣን የታሰረበት ጥልቅ የሚለውን ከዚህ በፊት በምዕ. 9:2 ላይ አምስተኛው መለከት በተነፋ ጊዜ ተመልክተን ነበር:: ይህ ጥልቅ ጉድጓድ በጥናታችን የከፉ መላእክት መጥፊያ እንደሆነ እናገኛለን:: ስለዚህ ነው ሰይጣንን ያሰረው መልአክ ወደ ጥልቅ ጉድጓድ የወረወረው::

ይህ መልአክ እንደ ክርስቶስ በሥልጣን ሲሠራ ይታያል:: ኢየሱስ በዮሐንስ 14:12 ያለውንና ሐዋርያው ጳውሎስም በክርስቶስ ኃይል ያደረገውን ያሳስበናል፣ ፊልጵ. 4:13:: ስለዚህ የክርስቶስ ኃይል ይህን መልአክ ኃይለኛ ያደረገው ይመስላል::

ለሺህ ዓመት በሰይጣን መታሰር ምክንያት ክርስቶስ በዲያቢሎስ ተበላሽቶ የነበረውን ፍጥረት ለሺህ ዓመት መንግሥት መለወጥና ለማደስ እንደሆነና ለመንፈሳዊ እድሳት የሆነ ይመስላል:: ደግሞ ሰይጣን ሳይታሰር ሺህ ዓመት ከክርስቶስ ጋር በሰላም መንገሥ የት ይኖራል? እንዴትስ ይሆናል? የሚገርመው ነገር በክርስቶስ ሺህ ዓመት መንግሥት ጊዜ ሰይጣን አንድም ጊዜ ስሙ ተጠቅሶ አናይም:: ሺህ ዓመት ሲፈጸም ግን ሰይጣን ከእሥር ይወጣል:: ከዚያም የሚያደርገውን ቁ. 7–10 አንብብ:: ሰይጣን ከእሥር ሲወጣ እግዚአብሔርን በመቃወም የሚያደርገውን ተመልከት:: ይህ ተቃውሞ የሰይጣን የመጨረሻ ተቃውሞ ነው:: ከዚያ በኋላ የሰይጣን መጨረሻ ይሆናል:: ቁጥር 3 ላይ ሰይጣን ለጥቂት ጊዜ ይፈታል ይላል:: ለምን እንደሚፈታ የሚያሳስቡ ሁለት ነገሮች አሉ::

1. ሰይጣን ሺህ ዓመት ታስሮ ጠባዩ የተለወጠ እንደሆነ ለማረጋገጥ:: ይሁን እንጂ ሺህ ዓመት ቀርቶ ከዚያ በላይ ቢሆን ጠባዩ አይሻሻልም፣ አይለወጥም፣ ንስሐም አይገባም::

2. በሰይጣን ላይ የመጨረሻ ፍርድ የፈረደው እግዚአብሔር እውነተኛ ጻድቅ እንደሆነ ያስመሰክራል::

እንዲሁም የሰው ክፉ ጠባይ እንደማይለወጥ እናያለን፣ ሮሜ 7:15–17፤ ራእይ 8:9:: በክርስቶስ ሺህ ዓመት መንግሥ ጊዜ ሰውና ሁሉም ነገር ተስተካክሉለት በሰላም ተገዛ፤ ያላመኑት ሁሉ ተገዙ:: ነገር ግን ሰይጣን ሲፈታ ሰው ቶሎ ብሎ በእርሱ ግዛት ለጦርነት ተከተተ:: በምድር ማዕዘን ያለው ሕዝብ እርሱን ይከተላል:: ዛሬ በመንፈስ ቅዱስ ልቡ ያልተለወጠ ሕዝብ ሁልጊዜም ያው ነው:: በክርስቶስ ሺህ ዓመት መንግሥ ልባቸው ባይለወጥም ይገዙለታል:: ሰይጣን ሲመጣ ግን እርሱን ይመርጡና ይከተሉታል:: የሰው ልብ ክፉ ነው፣ ኤር. 17:9–10::

## ቁ. 8 ስለ ጎግና ማጎግ

ስለ ጎግና ማጎግ በሕዝቅኤል 38 እና 39 በሰፊው ተጽፏል:: እነዚያ ቦታዎች ስለ ጦርነት ነው የሚያወሩት:: በዮሐንስ ራእይም በምድር ላይ በሰፊው ጦርነት እንደሚሆን ያወራል:: ስለዚህ ጎግና ማጎግ ጦርነት አንድ ጊዜ ሳይሆን፣ በዚያ ቦታ ሁለት እና ሦስት ጦርነቶች የሚሆን ይመስላል:: ለምሳሌ 1ኛው ወይም 2ኛው የዓለም ጦርነት እንደሚባል:: የመጨረሻ የጎግና ማጎግ ጦርነት በራእይ 20:8 ይሆናል:: የዓለምን ሕዝብ ሰይጣን ለጦርነት ያስከትታቸዋል:: ከጌታና ከተከታዮቹ ጋር ሲዋጋ ግን እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጠፋቸዋል:: የመጨረሻ ጦርነት ቦታ ነው:: እነዚህ ሙታን እንኳን በመጨረሻ በነጭ ዙፋን ፊት ለፍርድ መቅረባቸው አይቀርም፣ ቁ. 11 እና 12:: ይሁን እንጂ እንደ ሰዶምና ጎሞራ ይሆናሉ:: ከምድርም ይጠፋሉ:: ከጌቶች ጌታና ከነገሥታት ንጉሥ አፍ በወጣ ስለታም ሰይፍ ይመታሉ:: ከሰማይ በሚወርድ እሳት ይጠፋሉ::

ቁ. 9 የቅዱሳንን ከተማ ሊዋጉ ከበቡ:: ለሰዎች የመጨረሻ የንስሐ ጊዜ እንኳን ቢሰጣቸውም መመለስ አልፈለጉም:: በአመጽ ላይ አመጽን፣ በኃጢአት ላይ ኃጢአትን መጨመር ይፈልጋሉ እንጂ:: ከዚህ ቦታ ሰዎች ከሰይጣን ጋር ሲሆኑ የመመለስና የንስሐ ልብ ሳይሆን፣ የእምቢተኝነትና የወንጀለኛነት ልብና አእምሮ እንደሚሞላባቸው እናያለን፣ ሮሜ 1:28–32:: ስለዚህ መጨረሻቸው እንደ ሰዶምና ገሞራ ይሆናል::

## ቁ. 10 የሰይጣን መጨረሻ

ሰይጣን ለእርሱና ለተከታዮቹ ወደ ተዘጋጀላቸው ወደ እሳት ባሀር ተጣሉ፣ ማቴ. 25:41:: ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 12:31–33 የዚህ ዓለም ገዥ ተፈረደበት ያለው ጊዜ ደረሰ:: ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ ሰይጣን ተፈርዶበታል::

መንፈስ ቅዱስም መጥቶ ዓለምን ስለ ኃጢአት ሲወቅስ ሰይጣን ተፈረደበት ነበር፣ ዮሐ. 16:11 አሁን ግን በራእይ 20:10 ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ ሰይጣን አገኘ:: እግዚአብሔር እስከዚያ ድረስ ሰይጣንንና ክፉ መልአኩችን ያቆያቸው የእግዚአብሔር ዓላማና እቅድ እስኪፈጸም ድረስ ነበር::

ሰይጣን ወደ እሳት ባህር ሲጣል ከዚያ ቀደም ብሉ የተጣሉት ሐሳዊ መሲህና ሐሰተኛ ነቢይ ተጥለው ነበር። ኃያሉ እግዚአብሔር የርኩሳን ሥላሴን ዘንዶ፣ አውሬውን፣ ሐሰተኛ ነቢይን ሦስቱንም በኋላም በጌታ አምነው ያልጸኑት ሁሉ ወደዚያ ይገባሉ። ከዘላለም እስከ ዘላለም ይቃጠላሉ።

ራእይ 20:4–6 የእግዚአብሔር መንግሥት ከክርስቶስና ከቅዱሳን ጋር

ከዚህ ምዕራፍ በቁጥሮች ከደረስንበት ወደ ኋላ ተመልሰን እንመለከታለን። ዮሐንስ የሰይጣንን ለሺህ ዓመት መታሰር ካየ በኋላ ዙፋኖችን አየሁ ይላል። በእነዚህ ቁጥሮች የክርስቶስን ሺህ ዓመት በምድር መንግሥ ይገልጻል። ይህም የሚሆነው ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመለስ ነው። ክርስቶስ ከቅዱሳኖቹ ጋር በምድር ሲነግሥ ስለሚመጣ ነው። የእግዚብሔር መንግሥት ከቅዱሳን ጋር የተባለው በዚህ በሺህ ዓመት መንግሥት በምድር ላይ ከክርስቶስ ጋር ምን ምን ነገሮች እንደሚሆን አንድ በአንድ ተዘርዝሮ ባይገለጽም እንኳ የጸጋ ዘመን መጨረሻ እንደሆነ እናያለን፤ ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ባለው በሁለቱ ምዕራፎች 21 እና 22 የዘላለም መንግሥት እንደሚሆን ይናገራል። በዚህ መንግሥት ክርስቶስ ለሺህ ዓመት በምድር ላይ ይነግሣል። ከዚህ መንግሥት ቀጥሎ የዘላለም መንግሥት ለእርሱ ይሆናል። «መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን…» ብለን የጸለይነው ጸሎት መልስ ይሆናል፣ ማቴ. 6:10።

ከዚያን ጊዜ አንስቶ ለዘላለም የሰማይና የምድር ግዛት በሙሉ የሰውና የሰይጣን መሆኑ ቀርቶ የእግዚአብሔር ይሆናል።

እግዚአብሔር የምድርን አገዛዝ ከዘፍጥረት 1:26 ጀምሮ ያለውን ዓይነት ግዛ፣ ንገሥ ሁሉን ሰጥቼሃለሁ ያለውን በብሉይ ኪዳን በሰፊው ማጥናት ይቻላል። ሰው ግን በተሰጠው ሥልጣን ሲወድቅና ሲያበላሽ እግዚብሔርንም ሲያሳዝን እንደ ነበረ ታሪክ ይመሰክራል፣ ዘፍጥ. 6:5–7። ነገር ግን እግዚአብሔር ለመልካም አገዛዝ የሚበቃ ሰውና አምላክ የሆነ ልጁ እንዲሆን ስለ ወሰነ በኢሳ. 9:6–7 በተጻፈው መሠረት መምጣት አስፈለገው። ስለዚህ ነቢያት ሁሉ ስለዚህ ስለሚመጣው ፍጹም መንግሥት እንዲህ እያሉ በብዙ ከጻፉት በጥቂቱ እንጥቀስ:–

ኢሳ. 2:2–4 ከዳዊት ቅርንጫፍ ቁጥቋጦ ተነስቶ በሰላም እንደሚገዛ
ኤር. 23:3–6 ተመልከት።

ዳንኤልም 2:44–45 የሚኒሳ የሰማይ መንግሥት ተጠቅሷል። እንዲሁም ስለ ዘላለም መንግሥት ትንቢት ዘካ. 12:10–14:21 ተመልክት። እነዚህና የመሳሰሉትን የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ስንመለከት ራእይ 20:4–6 ያለውን የክርስቶስን ሺህ ዓመት መንግሥ እውነት ያደርገዋል።

## የክርስቶስን ለሺህ ዓመት መንግሥ መከድ

በመጽሐፍ ቅዱስና በጌታ ዳግም መምጣት የሚያምኑት ስለ ጌታ መመለስ በሦስት ይከፈላሉ።

1. Amillennialism (ኤ ሚሊኒዝም) ይባላሉ። እምነታቸው ጌታ መጥቶ በምድር ላይ ለሺህ ዓመት አይነግስም። ይህ ሺህ ዓመት አባባል ምሳሌያዊ አነጋገር ነው እንጂ እርግጠኛ አይደለም ይላሉ።
2. postmillennialism (ፖስት ሚሊኒዝም) ይባላሉ። እምነታቸው ክርስቶስ ወደ ምድር የሚመጣው ሺህ ዓመት ካለፈ በኋላ ነው ይላሉ። ሺህ ዓመት በምድር ላይ ሰላም ጸጥታ ጥሩ አገዛዝ ይሆናል። ይህም የሚሆነው እኛ በርትተን ወንጌልን ከሠራን ነው። ከዚያ በኋላ ጌታ ዳግም ይመለሳል ይላሉ።
3. premillennialism(ፕሪ ሚሊኒዝም) ይባላሉ። እነዚህ የሚያምኑት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እምነት ይመስላል። እርሱም ጌታ ድንገት ባየር ላይ ይገለጥና ቤተ ክርስቲያንን ይወስዳል። ከዚያም 7 ዓመት የመከራ ዘመን ይሆናል። ከ7 ዓመት የመከራ ዘመን በኋላ ጌታ ወደ ምድር ይመለሳል። ሺህ ዓመት በምድር ላይ ይነግሣል። ከዚያም መንግሥቱ የእርሱ ይሆናል። ሰይጣን ይታሠራል። ከሺህ ዓመት በኋላ ሰይጣን ይለቀቅና ጦርነት ይደረጋል፤ ፍርድ በእርሱና በተከታዮቹ ላይ ይሆናል ይላሉ።

ይህ የራእይ መጽሐፍ ትርጉምም በዚህ በሦስተኛው ዓይነት እምነት የተተረጐመና የተቀመጠ ነው። እኔም ይህን አምናለሁ። ጌታ ለሺህ ዓመት በምድር ሊነግሥ ይመጣል። ከሺህ ዓመት መንግሥት በኋላ በምድር ላይ የመጨረሻ ፍርድ ይሆናል።

## የሺህ ዓመት የክርስቶስ መንግሥት ምን ይመስላል?

ምን እንደሚመስል በዮሐንስ ራእይ በግልጽ ባይጻፍም እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ዘመን የተጻፈውን እናንብብ። ለምሳሌ ኢሳ.2፡2–4፤ 11፡3–5 ተመልከት። በታውም ጽዮን ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነግሥባት ከተማ ኢየሩሳሌም ይሆናል። ግዛቱና መንግሥቱ የኢየሱስ ይሆናል፣ ዘካ. 14፡9–11።

ራእይ 20፡1–3 በክርስቶስ ሺህ ዓመት መንገሥ ጊዜ

1. ፍጹም ሰላም የሞላበት መንፈሳዊ ቁጥጥር ይሆናል። ጠላት ሰይጣን በጥልቅ ጉድጓድ ታስሮ ስለተዘጋበት አካባቢውን የሚያውክ እንቅፋት አይኖርም፣ ዘካ. 14፡16–17 ተመልከት።

2. ፍጹም የሆነ የሞራል እረፍት የተሞላበት ቁጥጥር ይሆናል። ክርስቶስ የሰላም ገዢ ስለሆነና የጌታ ተከታዮች የመንግሥቱ ገዢዎች ይሆናሉ። ስለዚህ መዝ. 2፡6–9፤ መዝ.(72)፡8–11 እንኳን ምድርና ሰማይ ይባረካሉ፣ ራእይ 12፡5፤ 19፡15።

ቁ. 4–6 ዙፋኖች የሚለው ለነማን ነው?

ኢየሱስ ከእኔ ጋር ትነግሣላችሁ ብሎ ተስፋ የሰጣቸው፡–

1. ቤተ ክርስቲያንን ነው፣ ራእይ 2፡26፣ 27፤ ምሳሌ 3፡21፣
2. የዳኑት የእሥራኤል ቤተሰብን ነው፣ ማቴ. 19፡27–28፣
3. የብሉይ ኪዳን ቅዱሳንን ነው፣ ኢሳ. 1፡25–26፣
4. በመከራው ዘመን የአውሬውን ምልክት ያልወሰዱትንና ለጌታ ስም የተገደሉትን ሁሉ፣ ቁ. 4 ተመልከት።

እነዚህ ሁሉ ከጌታ ጋር ለሺህ ዓመት ይነግሣሉ። የሰላም መንግሥት ይሆናል፣ መዝ. (72)፡1–7)።

3. ፍጹም ሥጋዊ ዕረፍት የሞላበት አካባቢ ይሆናል፣ ኢሳ.11፡6–9 ደግሞ ኢሳ. 35፡1–2።

ቁ. 5–7 ሚክያስ 4፡4–5 አሞጽ 9፡13፤ ዘካ. 10፡1 እነዚህ ቁጥሮች የሚያሳዩት ክርስቶስ ሺህ ዓመት ሲነግሥ ብቻ ሊሆን የሚችል ጸጥታና ሰላም ለዓለም ይሆናል። ፍጥረት ሁሉ ያቺን ጊዜ ይጠባበቃል፣ ሮሜ 8፡9–23። ኢየሱስ በምድር ላይ ሺህ ዓመት እንደሚነግሥ

በዚሁ መጽሐፍ ስድስት ጊዜ ተደጋግሞ ይናገራል:: ስለዚህ የመንገሡ ዘመን ልክ በግልጽ የታወቀ ነው::

ቁ. 5–6 ራእይ 20:5–6 ስለትንሣኤ ይናገራል:: ስንት ትንሣኤ አለ?

ኢየሱስ በዚህ ምድር በሥጋው በነበረ ጊዜ ስለ ጻድቃን ትንሳኤ በብዙ ተናግሯል:: ሉቃስ 14:14፤ ዮሐ. 5:28–29 እንዲሁም ራእይ 20 ላይ በሰፊው እናገኛለን::

1ኛ ትንሣኤ የክርስቶስ የራሱ ትንሣኤ ነው:: ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኩር ሆኖ ተነስቷል ይላል፣ 1 ቆሮ. 15:20፤ ሮሜ 6:9::

2ኛ ትንሣኤ የመነጠቅ ጊዜ የሚሆን የአማኞች ትንሣኤ ነው፣ 1ኛ ተሰሎ. 4:16:: በክርስቶስ የሞቱት አስቀድመው ይነሳሉ:: ይህ ትንሣኤ ሳይባል የቤተ ክርስቲያን በአየር ላይ መነጠቅ ይባላል:: በአየር ላይ ከጌታ ጋር ይገናኛሉ፣ 1ኛ ተሰሎ. 4:13–18::

3ኛትንሣኤ በዮሐንስ ራእይ 20:6 ላይ ያለው ከክርስቶስ ጋር ሊነግሡ የሚነሱ የመከራ ዘመን ቅዱሳኖች ትንሣኤ ነው:: ይህ ትንሣኤ ፊተኛው ትንሣኤ ተብሏል:: ይህን ትንሣኤ ያገኙት ለሺህ ዓመት ከክርስቶስ ጋር በምድር ይነግሣሉ:: እነርሱም የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ:: በእነዚህ ትንሣኤ በጌታ ያላመኑት አይነሱም:: መጽሐፉ የክርስቶስ ሺህ ዓመት መንግሥት በምድር ላይ እስኪፈጸም ድረስ የቀሩት ሙታን በሕይወት አልኖሩም ይላልና::

4ኛ ትንሣኤ በጌታ ያላመኑት ከሺህ ዓመት መንግሥት በኋላ በነጭ ዙፋን ፊት ለፍርድ ሊቆሙ የሚነሱት ትንሣኤ ነው፣ ራእይ 20:12–15:: ዮሐ. 5:29፤ በ3ኛ ትንሣኤና በ4ኛ ትንሣኤ መካከል ሺህ ዓመት ልዩነት አላቸው ማለት ነው::

ቁ. 6 ስለ ሁለተኛው ሞት ይናገራል:: ይህን ሁለተኛ ሞት ምዕ. 21:8 ተመልከት፤ምዕ. 20:14 :: በጌታ የማያምኑትን የሚጠብቅ የእሳት ባህር ነው፣ ምዕ. 20:15::

## በክርስቶስ ሺህ ዓመት መንግሥት የሚከፈሉት

1. ወደ ሰማይ የተነጠቀች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ ራእይ 2:26–27፤ 3:21:: ዙፋኖች ተዘርግተው ዳኝነት ይሰጣቸዋል:: በሌሎች ላይ የምንፈርድ እንሆናለን፣ 1 ቆሮ. 6:2–3:: እንዲሁም 2 ጢሞ. 2:12 ከእርሱ ጋር መከራ ብንቀበል ከእርሱ ጋር እንነግሣለን ይላል:: ያኔ የተስፋ ቃሉ ይፈጸማል::

2. በመከራ ዘመን ስለ ክርስቶስ ስም የአውሬውን ምልክት በእጃቸውና በግምባራቸው አንቀበልም ብለው የሚታረዱ ቅዱስ ይሆናሉ።

3. በመከራ ዘመን ወደ ጌታ የተመለሱት አይሁዶች

4. በመከራ ዘመን ወደ ጌታ የተመለሱት ከአህዛብ ወገን

5. የብሉይ ኪዳን ዘመን ቅዱሳን በመንግሥቱ ተካፋዮች ይሆናሉ።

## ቁ. 11–15 የእግዚአብሔር መጨረሻ ፍርድ ባላመኑት ላይ

በዕብራውያን 9:27 ላይ ለሰው እንደ ተመደበ ይሞቱ ዘንድ ከሞት በኋላ ፍርድ ተመድበባቸዋል ይላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሰባት ዓይነት ፍርድ ይናገራል።

1. በኃጢአት ምክንያት በአዳም ላይ የተላለፈው ፍርድ፣ ዘፍጥ. 3:23–24።

2. ክርስቶስ ለዓለም በመስቀል ላይ የወሰደው ፍርድ ነው፣ 2ቆሮ. 5:21።

3. ክርስቲያኖች በየዕለቱ በራሳቸው ላይ የሚፈርዱት ፍርድ፣ 1 ቆሮ. 11:3132። ከዚያም ንስሐ ሲገቡ ይነጻሉ፣ 1 ዮሐ. 1:9።

4. በእሥራኤል ልጆች ላይ የሚሆን ፍርድ በራእይ 20 ስለ ፍርድ ስናጠና እንመለከታለን።

5. የክርስቲያኖች የሥራቸው ፍርድ ጊዜ ይሆናል፣ 1 ቆሮ. 5:10፤ 3:12–15።

6. በአህዛብ ላይ የሚሆን ፍርድ በመጨረሻው ዘመን፣ ማቴ. 25:31–46። የእግዚአብሔርን ሕዝብ እሥራኤል ምን እንዳደረጉ፣ ክርስቲያንን ምን እንዳደረጉ፣ ክርስቶስን ምን እንዳደረጉ ሁሉ ወደ ፍርድ ይመጣል።

7. በዮሐንስ ራእይ 20:11–15 ላይ ያለው የነጭ ዙፋን ፍርድ ነው። ይህ ዓይነት ፍርድ ከዚህ በፊት ሆኖ አያውቅም። ምክንያቱም የአሁኑ ዳኛ በነጭ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ታይቷልና ነው። በዚህ ጊዜ ክርስቲያኖች ፍርድ አይኖርባቸውም። ምክንያቱም ክርስቲያኖች የሥራቸውን ፍርድ ከዚህ በፊት በሰማይ ተቀብለዋልና ዋጋቸውንም ተቀብለዋልና። ይህ ፍርድ ግን ያላመኑት የሚቀበሉት

የመጨረሻ ፍርድ ነው:: ሙታን ሁሉ ለፍርድ ይነሳሉ፣ ኢዮብ 14:14:: ሰው ከሞተ በኋላ ሕያው ይነሳልን? ብሎ ይጠይቃል:: መልሱ አዎን ነው::

## ቁ. 11 ታላቅና ነጭ ዙፋን

ይህ ታላቅና ነጭ ዙፋን የሚመስል ስፍራ የትም አይገኝም:: ዮሐንስ ይህንን ነጭ ዙፋን ነው አየሁ የሚለው:: ይህ ዙፋን ልዩ ነበረ:: ልዩ የሆነበት ምክንያት በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ልዩ ነበረ:: ከፊቱ ሰማይና ምድር ሸሽተው ሄደው ቦታው በባዶ አየር ላይ ነበረ:: በዙፋን ላይ የተቀመጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነበረ፣ዮሐ. 3:3–5::

ይህ ነጭ ዙፋን በመልካም ተግባር የሚያመልጡበት ቦታ አይደለም:: ምክንያቱም በዙፋኑ የተቀመጠ እግዚአብሔረ የተከፈተ መጽሐፍ እያሳየ በተግባር ያደረግኸው ለደህንነት በቂ አይደለም የሚልበት ቦታ ነው:: በዙፋኑ የተቀመጠው ጻድቅ እውነተኛ ፈራጅ የሆነ፣ ሁሉን ቻይ የሆነ እግዚአብሔር ነው:: የፍርዱ ዙፋን ታላቅ የሚሆንበት ሌላ ምክንያት ቅዱሳንና ጻድቃን ቃሬዊት በዙሪያው ስለሚሆኑ ነው:: የዚህ ፍርድ ውጤት ለዘላለም ወደ ገሃነመ እሳት ባህር ለመጨረሻ መጣል ስለሚሆን ታላቅ ነው:: ማምለጫ ስለማይገኝ፣ ዕብ. 2:3::

ዙፋኑ ነጭ የሆነበት ምክንያት ፈራጁ ቅዱስና ጻድቅ ፍጹም ንጹሕ እንደሆነ ያሳያል:: ደግሞ ሰው በኃጢአት የተበላሸ ጨለማ መሆኑን ይገልጻል:: ስለዚህ በታላቁ ዙፋን ፊት መቆም አይችልም:: ሌላ ዙፋኖች እንዳሉ ማሰብ አለብን:: ዮሐንስ ያየው የዘላለም ግዛት ዙፋን ነበረ፣ ራእይ 4:22:: ደግሞ ድል አድራጊዎች ሊቀመጡ ተስፋ የተሰጣቸው ዙፋንም አለ ራእይ 3:21:: ደግሞ የበጉ ዙፋን የተባለው አለ፣ ምዕ. 22:3:: እንዲሁም ዳኛው የሚቀመጥበት ዙፋን የክብር ዙፋን ተብሏል፣ ማቴ. 25:31:: የዮሐንስ ራእይ ዙፋን የክብር ዙፋን ነው:: ዓለም ከተፈጠረበት ጀምሮ ያለው ያላመነ የሰው ዘር የሚፈረድበት ዙፋን ነው:: በዚያ የዓለም ነገሥታት ነበርን የሚሉ ሁሉ፣ ገዢ ነበርን የሚሉ ሁሉ፣ ታላላቅ ሰዎች ነበርን የሚሉ ሁሉ ፍርዳቸውን ይቀበላሉ:: በዙፋኑ ፊት ለፍርድ ይቆማሉ፣ ማምለጫ የላቸውም::

ቁ. 11 ዳኛው ክርስቶስ ነው፣ ዮሐ. 5:22፤ የሐዋ. ሥራ 17:31፤ 2ጴጥ. 3:10:: ፈራጅ ኢየሱስ ነውና ጉልበት ሁሉ ለእርሱ በግድ

ይንበረከካል፣ ፊልጵ.2፡6–11። ታላቁ ነጭ ዙፋን የምህረት መሆኑ ቀርቶ የፍርድ ዙፋን ይሆናል፣ዮሐ. 3፡36፤ ዳን. 7፡9–11 ያለው ትንቢት ይፈጸማል።

ቁ. 12 ስለሞቱ

ስለ ሞቱ ሙታን ይናገራሉ። ሦስት ዓይነት ሞት እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

1ኛ ሞት በኃጢአት ውስጥ መግባት የእግዚአብሔር ትእዛዝ መተላለፍ አንደኛው ሞት ነው። አዳም በኃጢአት በወደቀ ቀን ሞተ። መንፈሳዊ መለየት ነው። ከእግዚአብሔር ሕብረት ተለየ፣ ዘፍጥ. 3፡3፤ 2፡16–17፤ ኢሳ. 59፡2፤ ኤፌ. 2፡1። በአባታችን በአዳም ምክንያት እኛ ሁላችን ተለየን፤ ሞትን፤ ሮሜ 5፡12–14። መንፈሳዊ ሞት ነው።

2ኛው ሞት ሥጋዊ ሞት ነው። ሥጋና ነፍስ ስትለያይ ሥጋ ወደ መቃብር ሲሄድ፣

3ኛው ሞት ነፍስ በጌታ ፊት ፍርድ ስትቀበል። ወደ ገሃነመ እሳት ስትጣል። ይህን ሞት መጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛ ሞት ይለዋል፣ ራእይ 20፡6–14 ምዕ. 21፡8። ይህ ሞት በጌታ በኢየሱስ አናምንም ብለው ጌታን የናቁትና የጠሉት የሚገቡበት የመጨረሻ ሥፍራ ነው። በዳንኤል 12፡2 በእፍረት ትንሳኤ ይላል። በሐዋ.ሥራ 2፡15 የአመጸኞች ትንሣኤ ይላል። እዚያ ይደርሳሉ፤ ጌታ ኢየሱስንም ያላመኑት ለፍርድ ትንሣኤ ይነሳሉ አለ፣ ዮሐ. 5፡29።

ቁ 13 ሐዋርያው ዮሐንስ ሲያይ ሙታን ለፍርድ የሚነሱ ነበር። ያላመኑት ከየት እንደመጡ ሲናገር ባህርም በእርሱ ያለውን ሙታን ሰጠ፣ ሞትም በእርሱ ዘንድ ያለውን ሙታን ሰጠ። ሲዖልም በእርሱ ያሉትን ሙታን ሰጠ፣ ለሁሉም እንደሥራቸው መጠን ተከፈለ ተፈረደ። ሰው ሞቶ በስብሶ የተረሳ ይመስላል። ግን እግዚአብሔር አይረሳውም። ሞት ቢሆን፣ ሲዖል፣ ባህርም ቢሆን ሌላም ለጌታ ይታዘዛል። ሙታንን ይሰጣል። ከጌታ ማምለጫ አይገኝም። ማምለጫው ዛሬ በሕይወት እያለን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ከእርሱ ጋር መታረቅ ብቻ ነው።

## ሞትና ሲኦል

ሞት ነፍስና ሥጋ ተለይቶ ሥጋ ይሞታል ይበሰብሳል። ሲኦል ነፍስ ከሥጋ ተለይቶ የሚቀመጥበት ሥፍራ ነው። በጌታ ያላመነ ነፍስ የሚቆይበት አሰቃቂ ሥፍራ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት እስኪነሳ ድረስ ሲኦል በሁለት ይከፈል ነበር። 1ኛው ሲኦል የቅዱሳን ነፍስ የሚቆይበት ወይም የሚያርፍበት ላይኛው ሲኦል ይባል ነበር። እንደ ገነት ማረፊያ ነበር። አብርሃምና ድሃው አልአዛር በዚያ ነበሩ። 2ኛው ሲኦል ወይም ታችኛው ሲኦል የኃጢአተኞች ነፍሳት የሚቆዩበት የሥቃይ ሥፍራ ነው። በዚያ ባለ ጸጋው (ሐብታሙ) ሰው በእሳት ነበልባል ይሰቃይ ነበር፣ ሉቃስ 16፡19–31። በላይኛውና በታችኛው ሲኦል መካከል መገናኘት እንደማይቻል ትልቅ ገደል ነበር። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ በሞተ ጊዜ ነፍሱ ወደ ሲኦል ሄዶ ሰበከ፣ 1ጴጥ. 3፡18–19። ክርስቶስ ከሞት በተነሳ ጊዜ ግን በላይኛው ሲኦል ወይም በእረፍት ስፍራ የነበሩትን ምዕመናን ማለትም እነ አብርሃምን ይዞ ተነሳ። ምርኮ ማረከ። ከእርሱ ጋር ወሰደ፣ ኤፌ. 4፡8–10። ኢየሱስም እንዲህ አለ፣ ራእይ 1፡18 ከዚያ በኋላ የአማኞች ነፍስ ወደ ጌታ ይሄዳል፣ ፊልጵ. 1፡23፤ 3፡20፤ 2 ቆሮ. 5፡1–5። ቤታችን በሰማይ ነው። እስጢፋኖስ ሲሞት ወደ ሰማይ ሄደ፣ የሐዋ. ሥራ 7፡55–56። ከዚያን ጊዜ አንስቶ የቅዱሳን ነፍስ ወደ ሰማይ ወደ ጌታ ይሄዳል።

ያላመኑት ሰዎች ነፍስ ግን እስከ ነጩ ዙፋን ፍርድ ጊዜ ወይም እስከ ሙታን ትንሣኤ በሲኦል ይቆያል። ለመጨረሻው ፍርድ ከዚያ ይወጣል ወይም ይነሳል። ከነጩ ዙፋን ፍርድ በኋላ ወደ እሳት ባህር (ገሃነመ እሳት) ይገባሉ፣ ይጣላሉ።

## ቁ. 12 የፍርድ መጻሕፍት መከፈት

እነዚህ መጻሕፍት አንዱ የሕይወት መጽሐፍ ሲሆን፣ ሌላው በሕይወት ዘመናቸው ያደረጉትን የሥራ መጠን የሚገልጽ ነው። ማንም በክርስቶስ ቢሆን ኩነኔ የለበትም፣ ሮሜ 8፡1። ኢየሱስም እንዲህ አለ፣ በእኔ ያላመነ አሁን ተፈርዶበታል፣ ዮሐ. 3፡18–36። ኢየሱስ እኔ አልፈርድባችሁም ነገር ግን ከእኔ የሰማችሁት ቃል እርሱ ይፈርድባችኋል። በእኔ ማመን እምቢ ስላላችሁ፣ ዮሐ. 12፡47–48።

አንድ ሰው ወደ እዚህ ምድር በሚወለድበት ጊዜ ስሙ በሕይወት መጽሐፍ እንደሚጻፍና በምድር በሚኖርበት ዘመን ሁሉ ጌታን ሳይቀበል እምቢ ሲል በመጨረሻው ስሙ ከሕይወት መጽሐፍ የሚፋቅ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምር ይመስለኛል፣ ዘጸ. 29:20:: በሞት ጊዜ የእርሱ ስም በሕይወት መጽሐፍ ሳይኖር ሲቀር ይታያል:: በዚህ ምክንያት ፍርድ ይደርስበታል:: ለጌታ ኃጢአቱን ስላልተናዘዘ ኃጢአቱ ያገኘዋል፣ ዘኁ. 32:23:: ኃጢአቱን ለጌታ ቢናዘዝ ይለማል:: ቢደብቅ ግን አይለማም፣ ምሳሌ 28:13:: መጻሕፍቱ በሚከፈቱበት ጊዜ እንኳን በልብና በሃሳብ ውስጥ የተደበቀ ኃጢአት እንኳን ቢሆን ይታያል፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ወንድሙን በልቡ የሚጠላ እንኳን ነፍሰ ገዳይ ነው፣ 1ዮሐ. 3:15:: ወደ ሴት አይቶ የተመኘ አመንዝራ ነው፣ ማቴ. 5:28:: በታላቁ ነጭ ዙፋን ፊት ኃጢአትን መደበቅ አይቻልም:: ዛሬ የክርስቶስ ደም ኃጢአትን እንደሚደመስስ በእምነት ካልተቀበልን ወዮ፣ 1 ዮሐ. 1:7–9::

ያላመኑት ሰዎች ሥራ የሚገልጽ መጽሐፍ ለእያንዳንዱ አላቸው:: አንዱ መጽሐፍ የሕይወት መጽሐፍ ሲሆን ሌላው ደግሞ በሕይወታቸው ዘመን ያደረጉትን ሥራ የሚገልጽ ነው:: ሁሉም እያንዳንዳቸው እንደ ሥራቸው መጠን ይከፈላቸዋል:: የአንተስ ሥራ እንደምን ይሆን? ክርስቶስ ለአንተ የሠራውን ካልተቀበልክ አንተም ከፍርድ አታመልጥም:: ክርስቶስ ይወድሃል፣ እርሱ ሊያድንህ መጣ፣ ዮሐ. 3:16:: አንዳንድ ሰው በሥራዬ እድናለሁ ይላል:: ይህ አይሆንም:: በጌታ ፊት፣ኢሳ. 64:6፤ ሮሜ 3:23፤ ገላ. 2:16–21:: ጽድቅ በሥራ አይገኝም ይላል:: መዳን በእምነት ነው:: በአንተ መጽሐፍ ውስጥ ምን ተጽፎ ይሆን? በደል ይሆን? ኃጢአት ይሆን? ወይም በክርስቶስ ደም የታጠበ ንጹህ የሆነ የደህንነት ሥራ?

## ቁ. 13–14 የፍርድ መጠን

በዚህ ቦታ ሁሉም እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈላቸው ይላል:: ምናልባት አንድ ጥያቄ በልብህ ይመጣ ይሆናል:: የጌታን ቃል ያልሰሙት እንዴት ይፈረድባቸዋል? የሚል ይሆናል፣ ሮሜ 2:11–12:: ሕግ ያላቸው እንደ ሕግ፣ የሌላቸው ያለ ሕግ ይፈረድባቸዋል:: መጠኑ የሚበዛም አለ፣ ማቴ. 11:21–23፤ ሉቃስ 20:46–47:: የፍርድ ልዩነት መኖሩን አስታውስ፣ ሉቃስ 12:47–48::

ቁ. 14 <u>ስለ ፍርድ</u>

በታላቁ ነጭ ዙፋን ፊት የሚሰጠው ፍርድ ሁለተኛው ሞት ነው:: ቅጣቱ የዘላለም ጥፋት ነው:: በጌታ ፊት የሚደርሰው 2ኛ ተሰሎ. 1:9 ወይም ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለዘለዓለም ሥቃይ መቀበልና መጥፋት ነው:: ኢየሱስም መፍራት ወደ ገሃነም የሚሰደውን ነው አለ፣ ሉቃስ 12:5:: የጥፋት መሣሪያ ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ ዕብራውያን 10:30–31 ተመልከት:: ዕብ. 12:29 አምላካችን የሚባላ እሳት ነው:: ሞትና ሲኦልም ይቀጣሉ::

ቁ. 15 የእሳት ባህር የዘላለም ቅጣት ቦታ ነው:: በዘላለም እሳት ባህር የሚገቡት እረፍት በጭራሽ አያገኙም:: ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ፣ ምዕ. 20:10፤ ማቴ. 25:46:: ሰው ሁሉ ራሱን መጠየቅ አለበት:: እኔስ ከእግዚአብሔር ፍርድ አመልጣለሁ ወይ ብሎ? መልሱ አዎን ዛሬ በጌታ ብታምንና እርሱን ብትከተል ታመልጣለህ፣ ዮሐ. 1:12:: የእግዚብሔር ልጅ ሁን፣ ዮሐ. 11:25–26:: እኔ ሕይወትና ትንሣኤ ነኝ፣ የሚያምንብኝ ቢኖር ይድናል፣ ዮሐ. 5:24:: ባመንክበት ቀን ከሞት ወደ ሕይወት ትሻገራለህ:: ስለዚህ ዕድልህ በዚህ ዓለም በሕይወትህ ሳለህ ብቻ ነው:: ከሞትህ በኋላ ምንም ማድረግ አትችልም፣ አይፈቀድልህም፣ ዕብ. 9:27:: ጌታን የመቀበል ጊዜ ሰዓቱ አሁን ነው፣ ምሳሌ 29:1:: ድምጹን ስትሰማ ልብህን አታጠንክር ወደ ጌታ ና፣ ዕብ. 3:7–8፤ ምዕ. 2:3::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 21

## ለዘላለም መኖር ተገለጸ

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 21 ላይ እግዚአብሔር ለዘለዓለም መኖርን በፊታችን ግልጽ ሲያደርግ እንመለከታለን። በዚህ ምዕራፍ ቁልፍ የሆነው 5 ቁጥር ነው። «እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ» የሚል ነው። በዚህ ምዕራፍ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ ያለው ነገሮች የሚቀጥሉ ናቸው። አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፣ አዲስ ኢየሩሳሌም በሰውና በእግዚብሔር መካከል አዲስ ሕብረትና ግንኙነት፣ ለዳኑት ሰዎች አዲስ የምቾት ሁኔታ፣ አዲስ የዘለዓለም ቤት፣ ለሙሽራው አዲስ ክብር፣ አዲስ መቅደስ፣ አዲስ ብርሃን፣ አዲስ ፍጹም የሆነ ሕይወትና አዲስ የመኖር ዘዴዎች ናቸው።

ቁ. 1–2 በዚህ በሁለቱ ቁጥሮች ከእነዚያ አዲስ ነገሮች ሦስቱ ተጽፈዋል። እነርሱም አዲስ ሰማይ፣ አዲስ ምድርና አዲስ ኢየሩሳሌም ናቸው።

### ቁጥር 1 <u>አዲስ ሰማይ</u>

በዚህ ቦታ ላይ ዮሐንስ አዲስ ሰማይን አየሁ ይላል። ፊተኛው ሰማይ አልፏል ይላል። በመጽሐፍ ቅዱሳችን በመጀመሪያው መጽሐፍ ማለት በዘፍጥ. 1፡1 ላይ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ይላል። ይህ ሰማይ የተባለው ምን እንደሆነ እንድናስታውስ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰማይን በሦስት ይከፍላል። ወይም ሦስት ሰማይ እንዳለ ይናገራል፣ 2 ዜና. 2፡6።

1ኛው ሰማይ ጠፈር ይባላል።

ቀዝቃዛ አየርና ውኃ ያለበት ጠፈርን እግዚአብሔር ሰማይ አለው፣ ዘፍ.1፡6–8። በኖኅ ዘመን በጥፋት ውኃ ጊዜ የሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ፣ ዝናቡም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በምድር ላይ ሆነ፣ ዘፍ. 7፡11። እንደገና የሰማይ መስኮቶች ተደፈኑ፣ ዘፍ. 8፡1። ለኛ ለመሬታችን ቅርብ ዙሪያ የሆነ ጠፈርን ሰማይ ሲል፣ አንደኛ ሰማይ መሆኑን እናስብበት።

2ኛው ሰማይ በዘፍጥ. 1፡14 በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይሁን አለ።

እግዚአብሔር አብርሃምን ወደ ሰማይ ተመልከት፣ ከዋክብትንም ልትቆጥራቸው ትችል እንደሆነ ቁጠር አለው። ዘፍጥ. ~~15፡5፤~~ መዝ.

8:3 የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ ጨረቃንና ከዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን ይላል። ከዋክብትና ጨረቃ ፀሐይ ያለው ሁለተኛው ሰማይ መሆኑን እንድናስታውስ ይገባል።

3ኛው ሰማይ መጽሐፍ ገነት ይላል

ጳውሎስ ስለዚህ 3ኛ ሰማይ ወይም ገነት ያለውን ተመልከት፣ 2ቆሮ. 12:2–4። ንጉሥ ሰለሞን በጸለየ ጊዜ ሦስቱን ሰማይ ጠቅሷል። እንዲህ እያለ፣ እነሆ ሰማይ ከሰማይም በላይ ያለው ሰማይ አለ፣ 2 ዜና 6:18 ተመልከት። ይህ ሦስተኛው ሰማይ የልዑል እግዚአብሔር ዙፋን መሆኑ ነው። ኢየሱስም ስትጸልዩ የሰማይ አባታችን ብላችሁ ጸልዩ አለ፣ ማቴ. 6:9። ሦስተኛው ሰማይ የእግዚብሔር ከተማ መንግሥተ ሰማያት ነው። ስለዚህ ራእይ 21:1 ስለ ሦስተኛው ሰማይ ሳይሆን ሰማይና ምድር አልፈዋል ያለው ሌሎች እንደሆኑ ከራእይ ምዕራፍ 6 እስከ ምዕራፍ 19 ያለውን በጥናታችን ማስተዋል እንችላለን። ጴጥሮስም 2 ጴጥ 3:10–13 ስለዚሁ በእሳት እንደሚያልፉ ተናግሯል። ዳዊት በመዝሙር (102):25 ላይ ስለ ሁለቱ ሰማይ ሲናገር «ሰማያት የእጅህ ሥራ ናቸው፤ እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ» ይላል። ራእይ 20:11፤ ኢሳ. 65:17 እግዚአብሔር የሚለውን ስሙ። እግዚአብሔር አንደኛውን ሰማይ የሚያጠፋው የሰይጣን ዙፋን ያለበት ስለሆነ ነው፣ ኤፌ. 6:11–12፤ ዮሐ. 14:30። ስለዚህ በእሳት ያልፋል፣ 2ኛ ጴጥ. 3:6–7። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል ሰማይ ያልፋል ስላለ ሰማያት ያልፋሉ የምንለው።

ቁ. 1 <u>አዲስ ምድር</u>

ዮሐንስ አዲስ ምድርን አየሁ ይላል። የፊተኛው ምድር አልፏል። ይህ የፊተኛው የተባለው በዘፍ. 1:1 የተፈጠረውን ነው። ዳዊት በመዝ. (104):5 እንዳትናወጥ ምድርን መሠርተሃል ሲል ስለ አዲስ ምድር የሚናገር ይመስላል። እንደዚህ ባይሆን ምድር አልፎ አየሁ አይልም ነበር። በዘፍጥ.1:2 ምድርም ባዶ ነበረች፣ አንዳችም አልነበረባትም ሲል ምድርን ባዶ ያደረገው የሉሲፈር (የሰይጣንና የሠራዊቱ) መውደቅ ነው።

1. የእርሱ መውደቅ ምድርን አበላሸ
2. በአዳም ምክንያት ምድር በተረገመች ጊዜ ምድር እሾህና አሜኬላ እንድታበቅልተረገመች።

አዳምን በላብህ ወዝ እንጀራ ትበላለህ፣ ወደ ተፈጠርክበት ምድር ትመለሳለህ፤ ስለ አንተ ምድር የተረገመች ትሁን፣ ዘፍጥ. 3:17–19:: ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ሮሜ 8:22–23 በዚህ ምድር ስንኖር እንቃትታለን ያለው:: ነገር ግን ጌታ በምድር ሺህ ዓመት ሲነግሥ የምድር ለውጥ ይጀምራል:: የተሰጠንን ተስፋዎች እንብብ፤ ኢሳ. 35:1፤ 55:12–13:: ሐዋርያው ዮሐንስ ሲመለከት ግን ያልፍ ነበር፣ ራእይ 20:11 ምዕ. 21:1:: ጴጥሮስም 2ኛ ጴጥ. 3:7–10:: ጳውሎስም በዕብ. 1:10–12፤ ቆላ. 1:17 ሁሉ በእርሱ ተጋጥሟል አለ:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሁሉን ሊያድስ ሁሉን ያጠፋል፣ ኢሳ. 65:17::

## ቁ. 2 <u>አዲስ ኢየሩሳሌም</u>

ስለ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሐዋርያው ዮሐንስ እግዚአብሔር በራእይ ያሳየውን ይገልጽልናል:: ቅድስቲቱ ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባሏ እንደ ተዘጋጀች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ስትወርድ አየሁ ይላል:: ይህች ከላይ የምትወርድ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አሁን በምድር ካለችው ኢየሩሳሌም ልዩ ነች:: በመከራ ዘመን ከምትሠራዋ ኢየሩሳሌም የተለየች ነች:: በመከራ ዘመንና ጊዜ ኢየሱስ ሺህ ዓመት ሲነግሥ የምትኖረዋ ኢየሩሳሌም በራእይ 11:8 ላይ ሰዶምና ግብጽ ተብላለች:: ከሰማይ የምትወርደዋ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ግን ኢየሱስ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ ያለው፣ ለሙሽራው የተዘጋጀች ከሰማይ የምትወርድ ነች፣ ዮሐ. 14:2–3:: አንድ ሰው እንዳለው አዲሲቷ ኢየሩሳሌም የተዘጋጀችው ለሰማይ ለተዘጋጁ ቅዱሳን ሰዎች ነው ብሏል:: እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ለአዲስ ልደትና ደህንነት የተዘጋጁ ማለት ነው፣ ዮሐ. 3:3–7:: ክርስቶስ ለሙሽራይቱ ተመልሶ ይመጣና ወደ እርሱ ይወስዳታል፤ ያቺም ቤተ ክርስቲያን ናት፣ 1 ተሰሎ. 4:16–17::

በቁጥር 2 የተገለጸችው አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በቁጥር 10 በረጅም ተራራ ላይ ያለችውን ቅድስቲቱን፣ አዲሲቷን ኢየሩሳሌምን ና እይ ሲል እናገኛለን:: ይህች አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ቅዱሳን በሆኑ ሕዝብ መሃከል ሆና እግዚአብሔር በመካከላቸው የሚያድርባት ከተማ ሳትሆን አትቀርም፣ ዕብ. 11:10:: በዚህች ከተማ የምትኖረዋ የክርስቶስ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ይህች ከተማ ዛሬ በሰማይ፣ በኋላ በአዲሲቷ ምድር የምትሆን ናት:: ይህች አዲሲቷ ኢየሩሳሌም

የጸድቃንየእረፍት ቦታ ሳትሆን አትቀርም። ይህች አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በሮቿ ሁልጊዜ አይዘጉም። ብርሃኗ ከአዲሱ ኢየሩሳሌም ወደ ምድር ያበራል። መብራቷም በጉ ይሆናል።

## ቁ. 3 አዲስ ሕብረትና ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር

በዚህ ቦታ ሐዋርያው ዮሐንስ አዲስ ሕብረትን እግዚአብሔር ከሰው ጋር እንደሚያደርግ ድምጽ ከሰማይ ሰማሁ ይላል። የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱ ጋር ያድራል። በድንኳን ማደር በዮሐ. 1፡14 ላይ ኢየሱስ ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ በእኛ አደረ የተባለው የእግዚአብሔርን ክብር አየነው። ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በእኛ መካከል አደረ። ስለዚህ ኢየሱስ ከዚያ አንስቶ ለዘላለም በከበረው ሥጋው በቤተ ክርስቲያኑ (ሙሽራይቱ) ያድራል። እርሱ ሙሉ እግዚአብሔርና ሙሉ ሰው ነው፣ 1 ጢሞ. 2፡5። በዚህ ቦታ ሦስቱ ሥላሴ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በመካከላችን ያድራሉ ማለት ነው። በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር በሙሴ ጊዜ በቤተ መቅደስ የእግዚብሔር ክብር እንደ ተገለጸ፣ ዘጸ. 40፡34፤ 1ኛ ነገ. 8፡10–11 ተመልከት። እንዲሁም የእግዚአብሔር ክብር በራሱ ሕዝብ መካከል ይሆናል። ኢየሱስ የጸለየው ጸሎቱ ይፈጸማል፣ዮሐ. 17፡24 ። ይህ ማለት ሥላሴ ዙፋኑን ትቶ በምድር ይኖራል ማለት ሳይሆን እርሱ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ቦታ የሚገኝ አምላክ እንደሆነ አንርሳ፣ መዝ. (139)፡7–12። ይህ ነገር ለእኛ አሁን በሙሉ አይገባንም። በኋላ ግን ይገባናል፣ 1 ቆሮ. 13፡12።

ቁ. 4 በዚያ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም እግዚአብሔር እንባዎችን ስለሚጠርግ እንባ የለም። ሞት አይገኝም። ሐዘን፣ ጩኸት ወይም ስቃይ የለም። የሚገርመው ነገር ዮሐንስ ሲገልጽ በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም የሌለውን ነገር ይገልጻል እንጂ ያለውን ነገር አይናገርም። ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ. 12፡4 ወደ ሦስተኛው ሰማይ ተወስዷል። ያያቸውን ነገሮች ለመግለጽ አልሞከረም ነበር። ቢነግረንም እንኳ አይገባንም። ስለዚህ 1ቆሮ. 2፡9 ላይ ያለውን ተመልከትና አስብ። ዮሐንስ ስለ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ያለውን ያህል ካወቅን በቂ ነው።

## ቁ. 5 ነገሮች ሁሉ አዲስ

በዙፋኑ የነበረው ለዮሐንስ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለውና ይህን ጻፍ አለው:: የቀድሞ ፍጥረት ሁሉ በቀድሞ አባታችን በአዳም ኃጢአት ምክንያት ተበላሽቷል:: አርጌም ሆኗል:: አሁን ግን በሁለተኛው አዳም በክርስቶስ ምክንያት ሁሉም አዲስ ይሆናል፣ ኢሳ. 65:17:: በክርስቶስ በማመን ሕይወታቸውን የሰጡት በክርስቶስ ስለሚሰጥ አዲስ ፍጥረት መሆን ይገባቸዋል፣ 2ቆሮ.5:17:: ጳውሎስም በኤፌሶን 2:10 ኢየሱስም ለኒቆዲሞስ አዲስ ስለ መሆን ይገልጽለታል፣ ዮሐ. 3:3:: በጌታ ሁለተኛ መመለስ ላይ የክርስቲያን ሥጋ እንኳ ይለወጣል፤ አዲስ ይሆናልም፣1ኛቆሮ. 15:53::

ቁ. 6 ከሚሰጣቸው ነገሮች አንዱ ለተጠማ የሕይወት ውሃ ነው:: አልፋና ኦሜጋ መጀመሪያና መጨረሻ የሆነ ጌታ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ ይላል:: በዘፍጥረት የተፈጠረ ምድርና ሰማይ በጊዜ የተወሰነ ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስም በጊዜ ይፈጽማል:: በዮሐንስ ራእይ 21 ዘላለማዊነት ይጀምርና በሰዓት መወሰን ያበቃል:: ክርስቶስ ዘለአለማዊ ስለሆነ በአዲስ ሰማይና ምድር ዘላለማዊነት ይጀምራል:: መጨረሻም አይኖረውም:: ክርስቶስ በፍቅር የመረጠን ለዚሁ ነው፣ ኤፌ. 1:4፤ ቁ.10ና11:: ኤፌ. 2:7::

ቁ. 7 ስለዚህ በክርስቶስ ሆኖ ድል የሚነሳ ይህን ይወርሳል:: አዲስ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ይወርሳል:: እግዚአብሔር አምላኩ ይሆናል:: ድል የሚያደርግ ልጁ ይሆናል:: ድል ማድረግ ከቃልና ከእምነት የተነሳ የሚመጣ እንደሆነ አንደኛ ዮሐንስ 5:4–5 ተገልጿል:: ለክርስቲያን ምን ዓይነት አስደናቂ የተባረከ ተስፋ ነው የተሰጠው:: ክርስቲያን በምትመጣዋ በአዲሲቱ ከተማ በኢየሩሳሌም ከንጉሡ ከኢየሱስ ጋር ለመሆን በርታና ጠላትህን ዲያቢሎስን ተዋጋ:: ድል አድራጊ ሆነህ ተገኝ እንጂ ድል አትሁን፤ የሚረዳህ ጌታ ከአንተ ጋር ነውና::

## ቁ. 8 ለእምቢተኞች ማሳሰቢያ

ዮሐንስ በጌታ ድል አድራጊዎችን የወደፊት ዕጣ ከገለጸ በኋላ በአንፃሩ ለክርስቶስ ወንጌል እምቢተኞች ላይ የሚደርሰውን ያሳስባቸዋል:: በኃጢአት ጸንተው ለጌታ ቃል እምቢ የሚሉት እድላቸው ምን ዓይነት እንደሚሆን ያሳስበናል:: መልሰህ ቁጥር 8ን አንብብ::

ለማያምኑት የሚጠብቃቸው የእሳት ባህር ይኼውም ሁለተኛው ሞት ነው። ምናልባት አንዳንዶች እኔ አይደለሁም፣ እነዚህን ኃጢአቶች አላደረግሁም፣ ለእኔ አይደርስብኝም ትሉ ይሆናል። ሌላ ኃጢአት ባታደርግ ውሸትና ሐሰት ተናግረህ አታውቅምን? ማነው ሐሰተኛ? ራእይ 21:22 ላይ አንብብና ወልድን የሚክድ፣ የማይቀበልና የማያምን ኃጢአተኛ ነው ይላል። በ1ኛ ዮሐ. 5:10 ራእይ 21:8 ስንመለከት እጅግ የሚገርመው ነገር አዲስ ሰማይና ምድር ሲፈጠር ወይም አዲሲቱ ኢየሩሳሌምና ሌላም አዲስ ነገሮች ሲሆን ነው። ነገር ግን የእሳት ባህር ወይም ገሃነም የማይለወጥና ዘላለማዊ መሆኑን ማየት ትችላለህ። እርሱ አይለወጥም። ስለዚህ በጌታ ያላመኑት እድላቸው ለዘላለም በዚያ ይሆናል። በጌታ ያላመነ በበደልና በኃጢአት የሞተ ነው። ኤፌ.2:1 በጌታ ሲያምን ግን ወዲያውኑ ሕያው ይሆናል። ኤፌ. 2:5 በኃጢአት ለጸና ሰው በአዲስ ሰማይና ምድር ወይም በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ቦታ የለውም፤ ለመግባትም አይፈቀድለትም።

## ቁ. 9–10 የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ገለጻ

ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ሲገልጽ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምና የክርስቶስ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ያሳያል። መልአኩ ከሰማይ የምትወርድ ቅድስቲቱ ኢየሩሳሌም ከሰማይ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ስትወርድ 21:2 እንዲሁም 21:9 ላይ ሙሽራይቱ ተሸልማ ከቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩተሳሌም ጋር ያላቸውን ግንኙነት አጥብቀህ ተመልከት። የተሸለመ ሙሽራና የተሸለመ ከተማ። ይህች ከተማ ጌታ ለሙሽራይቱ ለቤተ ክርስቲያን ሄጄ ሥፍራ አዘጋጅላችኋለሁ፣ መጥቼም እወስዳችኋለሁ ያለውን የዮሐንስ ወንጌል 14:2 ያሳስበናል። ይህች ከተማ ለሙሽራይቱ እንደ ተዘጋጀ አድርጎ ስለሚገልጽ፣ በቁጥር 10ና 11 ላይ ያሉትን ቆንጃጅት አትኩረህ ተመልከት። ይህች ከተማ በምዕራፍ 4:3 ላይ እግዚአብሔር በዙፋን ላይ ምን እንደሚመስል ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሁሉ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መልክ አንድ እንደሆነ የእግዚአብሔር ክብር የሚታይበት ነው። በዚያች ከተማ መብራት አያስፈልግም። ብርሃን ከበጉ ይወጣል፣ 21:23 ተመልከት። ከተማዋ የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን አያስፈልጋትም። የእግዚአብሔር ክብር ያላት ናት። በጉ ብርሃኗ ነው። እንደዚሁም አማኞች የዓለም ብርሃን ናቸው፣ ማቴ. 5:14። እንግዲህ ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት ያብራ፣ ማቴ. 5:16።

## ቁ. 16 የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ቅርጽና መልክ

ዮሐንስ ሲገልጽ በራእይ ያያት ከተማ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ተሸልማ የወረደች አራት ማዕዘን ቅርጽ አላት ይላል። ርዝመቷ ስፋቷና ከፍታዋ እኩል ነበር። አስራ ሁለት ሺህ ምዕራፍ ያህላል። መልአኩ ሲለካት ሁለት ሺህ አራት መቶ ኪሎ ሜትር ያህል ሆነ ይላል። በአዲሱ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከተማይቱ የት ልትሆን ነው? ለሚል ጥያቄ መልሱ ክርስቶስ የማዕዘኗ ራስ፣ ኤፌ.2:20 ሲሆን፣ ከእርሱ ዙሩን አንስቶ ንጹህ የሕይወት ውኃ የሚፈስበት ድረስ አካባቢ እንደሚሆን ይመስላል፣ ራእይ 22:1። ይህም ሆኖ የዚያች ከተማ መሠረት የተጣለው በእግዚአብሔር ነው። እነ አብርሃም ያችን ከተማ ይናፍቁ ነበር፣ ዕብ. 11:10። ያቺ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በአሁኑ ምድር ላይ ሳይሆን በአዲሲቱ ምድር ላይ የምትሆን መስሉ ይታያል። ቁ. 10 ተመልከት። አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከታላቅና ረዥም ተራራ ላይ ዮሐንስ በነበረበት ተራራ ስትወርድ አያት፣ ከኢሳ. 2:1–4 ጋር አመዛዝኑት።

## ቁ. 17–18 የከተማይቱ ግንብ

በአዲሱ ትርጉም ብታነብ በጣም ገልጽ ያደርገዋል። መልአኩ የግንቡን አጥር ሲለካ ሰባ ሁለት ሜትር ሆነ። ውፍረቱና ቁመቱ የግንቡ ድንጋዮች ልዩ ልዩ ዓይነት የከበሩ ድንጋዮች ናቸው። ከተማይቱ በንጹሕ ወርቅ ነበረ የተሠራችው። እንደ መስታወት ንጹሕ ነበረች። ከእነዚህ ከከበሩ ድንጋዮች የሚወጣው ብርሃን ለአካባቢውና ለፍጥረት ሁሉ ያበራ ነበር። በቁጥር 19 እና 20 አንብብ። የከተማይቱ መሠረቶች ተገልጸዋል። መሠረቶቿ የከበሩ ድንጋዮች ሲሆኑ ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው ናቸው። አስራ ሁለት የመሠረት ድንጋዮች ሲሆኑ የእግዚአብሔርን ክብር የተሞላ ብርሃን ከእነርሱ ይወጣ ነበር።

ቁ.14 የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም በመሠረቶችዋ ላይ ተጽፎ ነበረ፣ ኤፌ. 2:19–20። የመሠረቱ ድንጋይ ራስ ክርስቶስ ስለሆነ እናንተ ከእንግዲህ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም ይላል። ለዚህ ነው አማኞችን በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል-የሚለው።

## ቁ. 12–13 የቅድስቲቱ ከተማ የኢየሩሳሌም ደጆች

ዮሐንስ በራእይ ያያት አዲሲቱ ከተማ አስራ ሁለት ደጆች አሏት ይላል። በእያንዳንዳቸው ደጆች መልአክት አሉባቸው። ቁጥራቸው

አሥራ ሁለት ነበሩ፤ ደጆቹም በአሥራ ሁለት ዕንቁዎች የተሠሩ ነበሩ:: ቁ.21 አንብብ:: እነዚህ አሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች ስም በየደጆቻቸው ተጽፈው ነበር:: እነርሱም የእሥራኤል ቅዱሳን አባቶች ስም ነበር:: ይህን ዕንቁ የገዛው ክርስቶስ ነው:: ዕንቁም ቤተ ክርስቲያን ናት፣ (ማቴ. 13:45-46):: ቤተ ክርስቲያን በውድ ዋጋ የተገዛች እንቁ ናት፣ 1ኛ ጴጥ. 1:18-19:: የተከፈለውም ዋጋ የክርስቶስ የከበረ ደም ነው:: ያቺ ከሰማይ የወረደችው ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም የቅዱሳን መኖሪያ ናት:: የቤተ ክርስቲያን ከተማ ናት:: እነዚያ በዕንቁ ያጌጡ ደጆች የሚያሳስቡን የማይጠቅሙ ጠጠሮችና አሸዋዎች ተሰብስበው ዕንቁ ሆኑ:: እኛ በጌታ እምነን የዳንን ለክርስቶስ የማንመች፣ የምንቆረቁር ድንጋይና አሸዋ ነበርን:: ግን ክርስቶስ በደሙ አበጀን:: በጸጋ ድነናል፣ ኤፌ. 2:8:: በእግዚአብሔር ዙፋን የነጻንና ያማርን ሆነናል ስሙ ይባረክ:: በክርስቶስ ጸጋ የተሸፈንን ሆነናል:: ክርስቶስ ለእኛ ሲል የከበረ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጥቶናል:: ስለዚህ በእርሱ ፊት ከዕንቁ በላይ መሆናችንን ያሳስበናል::

ቁ. 18 ከተማይቱ በወርቅ የነጻች ናት ይላል:: ቁ. 21 ደግሞ የከተማይቱ አደባባዮች ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበር ይላል:: በዚህች ከተማ እግዚአብሔር ራሱ ብርሃን ሆኖ ይኖርባታል:: የምድራዊ ከተሞቻችን በሲሚንቶና በአስፋልት ይሸፈናሉ:: ሰማያዊው ከተማ ግን በንጥር ወርቅ ይሸፈናል:: ወርቅ ኃጢአት የሌለበት ንጽሕናን ያሳስበናል:: ስለዚያች ከተማ አስበንም ተናግረንም አንችልም ከሰው ግምት ሁሉ በላይ ነውና::

## ሦስት ዓይነት ሰዎች

በጣም የሚገርመው ነገር በዚህች በአዲሲቷ ቅድስት ከተማ ኢየሩሳሌም ሦስት ዓይነት ሰዎች ይኖራሉ::

ቁ. 9 አንብብ 1. የበጉ ሚስት ሙሽራይቱ ከልዩ ልዩ ወገን የዳኑት
ቁ.12 አንብብ 2. ከአሥራ ሁለቱ ወገኖች የእሥራኤል ልጆች የዳኑት
ቁ.24 አንብብ 3. ከአሕዛብ ማለት ከልዩ ልዩ ወገኖች የዳኑት
በዚያች ከተማ እንደሚገኙ እናስተውል::

ቁ. 22-23 በዚያች ከተማ አዲስ መቅደስ ይሆናል፤ አዲስም መብራት:: ጌታ አምላክና በጉ መቅደስና መብራቷ ናቸው:: ፀሐይና ጨረቃ አያስፈልጋትም:: ሌላ መቅደስም የለም:: በብሉይ ኪዳን ቅዱስተ ቅዱሳን የተባለ የእግዚአብሔር ድንኳንና መቅደስ ተሠርቶ ነበር::

በአዲሷ ኢየሩሳሌም ግን አያስፈልግም። ጌታ እግዚአብሔር አምላክ በሕዝቡ መካከል ይኖራልና። በብሉይ ኪዳን ዘመን መቅደስ በመካከል ሆኖ የእሥራኤል ሕዝብ በዚያ ይሠፍሩ ነበር፣ ዘኁልቁ ምዕራፍ 2። ሊቀ ካህን ደም ይዞ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ ነበር። በአዲሲቷ ከተማ ግን አያስፈልግም። ምክንያቱም የእኛ ሊቀ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን ደም ይዞ ለዘለዓለም ወደ ሰማያዊው መቅደስ ስለገባ፣ ዕብ. 9፡11–26። በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከተማ ዙሪያ የመኖር ሥርዓትና አሰላለፍ እጅግ የሚያስገርም ነው፣ ቁ 13 ተመልከት። አዲሲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ቅድስተ ቅዱሳን ያለባት ቦታ ናት። ቅድስተ ቅዱሳን የልዑል እግዚአብሔር ማደሪያ ሲሆን ጌታ ራሱ መቅደስና ቅድስተ ቅዱሳን ሆኖ በሕዝቡ መካከል እንደሚያድር በቁጥር 22 ላይ ተመልከት። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን (እኛ አማኞች) የእግዚአብሔር ማደሪያ ቅድስተ ቅዱሳን ነን፣ 1ኛ ቆሮ. 6፡19–20። የቤተ ክርስቲያኑ የውስጥ ደንብ ኢየሱስ እኛን ቅዱስ ቅዱሳን ነገሥታትና ካህናት ስለ አደረገን ለስሙ ክብር ምስጋና ይሁን። ራእይ 1፡6።

የሌዊ ልጆች ካህናት በመገናኛ ድንኳን እንደሠሩ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከተማ ይሠፍራሉ። ሙሽራው ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ንግሥትና ካህናት አድርጐ በዚያች ከተማ ያገለግለናል። በዚያች ከተማ ያሉት አሕዛብና እሥራኤል በዚያች ከተማ ብቻ መኖር አይገደዱም። ነገር ግን ይገባሉ ይወጣሉም። መሰማሪያም ያገኛሉ። አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለፍጥረት ሁሉ መሃከለኛ ሥፍራ ትሆናለች።

## የቤተ ክርስቲያን ዘለዓለማዊነት

የእግዚአብሔር እቅድ ለቤተ ክርስቲያን ማለት ለሙሽራይቱ እና ለዳኑት እሥራኤላውያን እንዲሁም ለዳኑት አሕዛብ መኖሪያቸውና ቤታቸው በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከተማ እንደሚሆን ራእይ 21፡2, 9, 10 ተመልከት። በዕብራውያን 12፡22–23 ወደ እግዚአብሔር ከተማ... ወደ በኵራት ማህበር ደርሳችኋል እያለ ለቤተ ክርስቲያን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ልዩ ሥፍራ ላይ ያስቀምጣቸዋል። ከክርስቶስ ጋር ለዘለዓለም ያስቀምጣቸዋል። ይህም ዛሬ በእምነት ክርስቶስን ለሚከተሉትና የክርስቶስ አካል ለሚሆኑት ምዕመናን ነው። አንተም አንቺም ለዚህ ተጠርታችኋል። 1ኛ ተሰሎ. 4፡18።

ቁ. 23 <u>በጉ ራሱ ብርሃን ነው</u>
በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ለማብራት ፀሐይና ጨረቃ አያስፈልጋትም። ምክንያቱም በጉ ራሱ የእግዚአብሔር ክብር ሆኖ ለከተማይቱ ያበራል። በዚህ ቦታ ፀሐይና ጨረቃ አይኖሩም አላለም። ነገር ግን ለከተማይቱ አያስፈልጓትም አለ እንጂ።

ቁ. 24 አህዛብ በብርሃኗ ይመላለሳሉ። ክብራቸውንም ወደ እርሷ ያመጣሉ። ዛሬም ቢሆን ክርስቶስ የዓለም ሁሉ ብርሃን ነው። ለፍጥረት ሁሉ የሚያበራ ብርሃን እርሱ ነው። ለአዲሱ ዓለምና ፍጥረት ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር መሆኑ ብቻ በቂ ነው።

ጥንት በፍጥረት ዘመን ሰው በኃጢአት ሲወድቅ የእግዚአብሔር ከእነርሱ መለየት ከባድ ጨለማ እንደ አመጣ ዘፍ. 1:3–5:14–18 አንብብ። ስለ አሁኑ አዲስ ፍጥረት ግን የኃጢአት መወገድና እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር መሆኑ፣ የብርሃን ምንጭ ይሆናል፣ ራእይ 21:3። ዛሬ ግን ሰው በምድር ከብርሃን ይልቅ ጨለማን እንደሚወድ ኢየሱስ ተናግሯል፣ ዮሐ. 3:19። እንዲሁም ኢየሱስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚያምንብኝ በጨለማ አይመላለስም፣ ዮሐ. 8:12 የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ አለ። ዛሬ በብርሃን ብንመላለስ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፣ 1ኛ ዮሐ. 1:7። ስለዚህ በአዲሲቷ ኢየሩሳሌምና በፍጥረቱ ኃጢአት አይገኝም።

ቁ. 25–26 በዚያች ከተማ ኃጢአት ስለሌለ ጨለማ አይኖርም። ሌሊትም የለም። በጉ ብርሃኗ ነው። በሮችዋም ቀንና ሌሊት አይዘጋም። ምክንያቱም ጨለማና ኃጢአት የለምና ነው። በዚያ በዘላለም ቤት የጸኑት ሁሉ አይናቸውን አንሥተው ወደ ጌታ ክብር የሚመለከቱበት እንጂ ችግር የለም። ጌታም በመካከላቸው ስለሆነ ያመልኩታል።

ቁ. 27 በዚያ ቦታ በበጉ ደም የነጹት በሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ከተጻፉት በስተቀር ሌላ አይገባም። በቁጥር 8 ያሉት ሁሉ ቦታ የላቸውም። ከቶም አይገቡም። ወዳጄ ሆይ ለዚያች አዲሲቷ ከተማ ዛሬ ተዘጋጅ። ወደ ጌታ ተመለስ። ዛሬ ነው እድልህ ወደ ጌታ ተመለስ።

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 22:1–5 ያለው ሃሳብ ከምዕራፍ 21 ጋር አብሮ የሚሄድና ሃሳቡም አንድ ስለሆነ በምዕራፍ 21 ሥር እንመለከታለን።

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 22

## አዲሲቷ ገነት

ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ አዲሲቷ ገነት ሲናገር መልአኩ እንዲህ አለኝ ይላል::

ቁ. 1–5 በአዲሲቱ ገነት መካከል በጣም ንጹሕ የሆነ ውኃ ወንዝ አሳየኝ ይላል:: እንዲሁም ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ:: ዛፊቷም በየወሩ ፍሬ ትሰጣለች:: አንዳንድ ሰው በዘለዓለም ቤት እንበላለን ወይ ብለው ጥያቄ የሚጠይቁ አይጠፉም:: መልሱ አዎን ነው:: ለዘላለም ለመኖር ባንበላም እንኳን ኢየሱስ ከሞት በክብር ከተነሳ በኋላ የክብር ሥጋ ለብሶ ነበር:: ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ መብላት አስፈላጊ ባይሆንም እንኳን በልቷል፣ ሉቃስ 24:28–43 ተመልከት:: በዘለዓለማዊ ቤት ሌሊት የለም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ብርሃንዋ ነውና:: በዚያ ቦታ ድካምና እረፍት የለም:: ጌታን ከማገልገል አያቋርጡም::

ቁ. 2 የሕይወት ዛፍ ቅጠል እንኳን ሕዝቡን የሚፈውስ ነው:: ማለት በዚያ ሕመም አለ ማለት አይደለም:: ቅጠሉ ለፈውስ ነው የሚለው ቃል በዚያ ለዘለዓለም ፈውስ ይቀጥላል ለማለት ነው:: ፈውስና ጤንነት ሁልጊዜ ስለሚኖር ሕዝብዋ ሁልጊዜም ደስተኞች ናቸው:: በዚያ መርገም ስለሌለ ሕመም የለም:: ቁ. 3:: መርገምና ኃጢአት ተወግዷል:: በዚያ ከተማ የሚኖሩ ሁሉ መልካቸው እግዚአብሔርን ይመስላል፣ ቁ. 4 አንብብ:: በ1ኛ ዮሐ. 3:2 ላይ የተባለው የሚፈጸምበት ዘመን ይሆናል::

ቁ. 5 ሐዋርያው ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ሲያሳይ:–

1. የኢየሱስን ሰብአዊ ክብርና በአባቱ ዘንድ አሁን ያለው ክብር፣
2. የኢየሱስን የማያልቀውን ጸጋ ለቤተ ክርስቲያኑ ያለውን፣ ቁጥር 4ን አንብብ፣
3. የኢየሱስ ክርስቶስን ዘለዓለማዊ ንጉሥነቱን ያሳያል፣ ቁጥር 5ን አንብብ:: ኢየሱስ ጌታነው!!

የመጨረሻ ቃል ማረጋገጫና ጥሪ፤ ቁ. 6–21 አንብብ።

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዮሐንስ በራእይ የተናገረውን የገለጸውን ያረጋግጥለታል

2. ዮሐንስ በመጽሐፉ የጻፈውን ጽሑፍ እንዲህ እያለ ያረጋግጥለታል።

ቁ. 6 ቃሎቹ

እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞች ናቸው። በዮሐንስ ራእይ የተባለውና የተጻፉት ቃሎች እርግጠኞች ናቸው ይላል። የቃሉ ታማኝነት እውነት ብቻ የሞላበት ነው። የተባለው ቃል ሁሉ ዋጋ ያለው ቃል ነው። ሰዎች ሊታመኑበት የሚገባ ነው። እግዚአብሔር ያለው ነገር እውነተኛ ታማኝነት ያለበት ቃል ስለሆነ እኛ ማመንና መደገፍ አለብን። ቃሉ እውነት ከሆነ ወደ መታየት ይመጣል ወይም ውጤት አለው። በእግዚአብሔር ዘንድ እውነት በቃል ይሰማል። እውነት በድርጊት ይፈጸማል። እውነት ያው እውነት ነው። እግዚአብሔር ለእኛ በጣም አድርጐ ሊገልጽልን የሚፈልገው ኢየሱስ ለዮሐንስ የገለጸው ነገር እውነት መሆኑን ነው። ስለዚህ ማንም ከተገለጠው እውነትና እርግጠኝነት ጨምሮ፣ አጋንኖና አሳንሶ፣ ወይም አጉድሎ መገኘት የለበትም።

የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ በብዛት ከብሉይ ኪዳን ጋር የሚጠጋና ብዙ የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎች የሚታይበት መጽሐፍ ነው። ብዙ የራእይን ትርጉሞች ለማግኘት ወደ ብሉይ ኪዳን ታሪኮችና ምሳሌዎች መሄድ አለብን ማለት ነው።

የዮሐንስ ራእይ በተለይ በመንፈስ ቅዱስ አዲስ ለተወለዱት መንፈስ ቅዱስ ገለጻ የሚሰጥበት መጽሐፍ ነው። የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ለፍጥረታዊ ወይም ሥጋዊ ሰው አይገባውም። ለእርሱ አልተጻፈለትምና።

በክርስቶስ አዲስ ልደት ላገኙት ነው የተጻፈው። ምክንያቱም በቃሉ ይሄዱበታል በቃሉም ይኖሩበታል። ለእነርሱ ይገባቸዋል። ስለዚህ ነው ይህን ቃል ለሚጠብቁት የበረከት ተስፋ የሰጣቸው፣ ቁጥር 7 አንብብ። የተሰጠው የበረከት ተስፋ ቃሉ የታመነ ነው። ማንበብና መታዘዝ በረከትንም መቀበል የእኛ ጉዳይ ነው።

## ቁ. 7 እነሆ በቶሎ እመጣለሁ

ጌታችን እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ይላል፡፡ ይህ ማረጋገጫ ቃል በዚህ መጽሐፍ እየተደጋገመ የተጻፈ ቃል ነው፡፡ በቶሎ እመጣለሁ የሚለው ቃል በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ሰባት ጊዜ ተደጋግሞ ተጽፎአል፡፡ ይህ በቶሎ ማለት በፍጥነት፣ በቅርብ ጊዜ ማለት እንዳልሆነ ማሰብ አለብን፡፡ ቶሎ የሚለው ቃል ሰዓት ወይም ደቂቃን የሚመዝን አይደለም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እመጣለሁ ሲል፣ በጊዜው እመጣለሁ፣ በሰዓቱ እመጣለሁ፣ ወይም በተወሰነ በዚያች ሰዓት እመጣለሁ ማለቱ ነው፡፡ ከተወሰነው ሰዓት አያልፍም፡፡ በቀጠሮው ሰዓት የማይቀር ነገር ነው ማለት ነው፡፡ እርግጠኛው ቀን መቼ እንደሆነ ባናውቅም እንኳ በዚያ በተወሰነው ቀን አልቀርም ይላል፡፡ ለዚህ ምሳሌ አስቡ፡፡ በመጀመሪያ ሥጋ ለብሼ እመጣለሁ ብዬ በነቢያቶች በተናገርሁ ጊዜ፣ ጊዜው ሳያልፍ በወሰንሁት ዘመንና ወር፣ ቀን መምጣቴን አስታውሱ ይለናል፣ (ገላ. 4፡4)፡፡ ይህ ምሳሌ ምልክት ይሁንላችሁ፡፡ በዚህ መጣሁ እንጂ አልቀረሁም፡፡ አሁንም ለዳግም መምጣቴ እምነት ይኑራችሁ፣ ንቁና ጠብቁኝ ይላል፡፡

ሌላም ምልክት አስታውሱ፣ መንፈስ ቅዱስን እኔ ሄጄ እሰድላችኋለሁ ያልኩትን አስቡ፣ ዮሐ. 16፡7–10 ተስፋውን አንብቡ፡፡ ደግሞ የተናገርኩት እንደ ተፈጸመ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2ን አንብቡ፡፡ ሁሉም በጊዜው ሆኗል፡፡ አሁንም ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጌታ በሰዓት ታማኝ ነው ከተባለ ከሰዓት ወደ ፊት አይሄድም፡፡ ከሰዓቱም ወደ ኋላ አይቀርም ልክ በሰዓቱ እመጣለሁ ማለቱ ነው፡፡

## ቁ. 7 የበረከት ተስፋ

እግዚአብሔር በግለሰብ ወይም በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ከዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ለሚያነቡና የተባለውንም ለሚጠብቁት በረከት ሊሰጥ ተስፋ የገባበት ቃል ያረጋግጣል፡፡ ምዕ. 1፡3 ላይ ከዚህ በፊት ትምህርት ወስደናል፡፡ እግዚአብሔር በመጽሐፉ መጀመሪያ ተናገረ፡፡ አሁንም ሁለተኛ በምዕራፉ መጨረሻ ላይም ያረጋግጥልናል፡፡ ቃሉን የሚያነብና የሚሰማ የሚጠብቅ ወይም የሚፈጽም የተባረከ ነው ይላል፡፡ አሁንም በምዕ. 22፡7 ተደገመ፡፡ ስለዚህ ቃሉቹን መጠበቅ ወይም መደጋገም ያስፈልጋል እንጂ መርሳት አያስፈልገንም፡፡ ክርስቲያን በየጊዜው የራሱን ሕይወት በዚህ መጽሐፍ ቃል መለካትና መመዘን ያስፈልገዋል፡፡

የዚህ መጽሐፍ ጥቅም እኛ ለእግዚብሔርና ለእግዚአብሔር ክብር ለመገዛትና ለመታዘዝ ፈቃደኞች ሆነን እጅ ስንሰጥ ብቻ ነው:: ያኔ ነው በረከቱን ሁሉ እንደ ተስፋ ቃሉ የምንቀበለው::

ቁ. 8–9 እኛ በመጽሐፍ ቅዱሳችን በጠቅላላ የታዘዝነው ለእግዚብሔር ብቻ እንድንሰግድና እንድናመልክ ነው::ዮሐንስ በዚህ ቦታ ለመልአክ ሊሰግድ እንደ ሞከረና መልአኩ አትስገድልኝ እኔ እንደ አንተ የእግዚአብሔር ባሪያ ነኝ አለው:: ይህ ቃል የተደጋገመ ነው:: ምዕ. 19:10 ላይ መመልከት እንችላለን:: መልአኩም ለእግዚአብሔር ብቻ ስገዱ ይላል:: ማርያምም ኢየሱስ የሚለውን አድርጉ አለች፣ ዮሐ. 2:5 ተመልከት:: ለመላእክት እንድንሰግድ ትእዛዝ አልተሰጠንም:: እግዚአብሔርን እንድናመልክ ነው እንጂ:: እግዚአብሔርን ማምለክና ለእርሱ ብቻ መስገድ ስንጀምር፣ ዮሐ. 4:23–24 በእውነትና በመንፈስ ስንሰግድ፣ እግዚአብሔር ሆይ አንተ ሊሰገድልህና ልትመለክ የሚገባህ ነህ ማለታችን ነው:: ስለ እግዚአብሔር ብዙ መማር ስንጀምር ብዙ እናውቃለን:: ብዙ ማወቅ ስንጀምር እርሱን ብቻ እናመልካለን::

## ቁ. 10 የትንቢትን ቃል በማኅተም አትዝጋው

ዮሐንስ ሲናገረኝ ዘመኑ ቀርቧልና የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል በማኅተም አትዝጋው ተባልኩኝ ይላል:: ዘመኑ ወይም ሰዓቱ ደርሷል ይላል:: ክርስቶስ በወሰነው ወይም በተባለለት ሰዓት ሊመጣ ነው:: ቃሉን እንዳትዘጋ:: በማኅተም አትዝጋው ይላል:: ይህ ቃል በዳንኤል 12:4 ላይ ከሚገኘው ቃል ተቃራኒ ነው:: በዳንኤል ትንቢት ዝጋው፣ አትመው ይላል:: ይህ ማለት ለዳንኤል ትንቢቱን ዝጋው፣ አትም የተባለበት ምክንያት የትንቢቱን ቃል ዝጋ ለሰው አይገባምና የትንቢት መጨረሻ እስኪመጣ አይገባም:: ስለዚህ ዝጋው አለው:: ለዮሐንስ ግን ክፈት ነው ያለው:: በትንቢት መፈጸሚያ ዘመን ስለሆነ ዮሐንስ የትንቢት ፍጻሜ እንዲከፍትና ትርጉሙን እንዲፈታ ተናገረ:: ትንቢቱ በሚፈጸምበት ጊዜ ወይም ዘመን ላይ የሚያነበው ግለሰብ ይገባዋል:: የሚያነበው ቤተ ክርስቲያን ይገባዋል:: ትርጉሞቹ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ይገባዋል:: በራእይ 1:1 ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባ ነው ይላል:: ቶሎ ያልፋል ማለት ነው:: የመጽሐፉ እውነት ወደ ፍጻሜ ይደርሳል ይፈጸማል ነው::

## ቁ. 11 የጠፉት ሰዎች ሁኔታ

አስፈሪ የሆነ የጠፉት የነፍሳት ሁኔታ፣ በዚህ ቦታ የሚያመለክተው በነጭ ዙፋን ፊት ፍርድን ያገኙት ጠፍተው ለዘላለም በዚያ በጥፋት ባህር ማለት በዘለዓለም እሳት ባህር እንደሚጠፉ ያሳስብናል:: የጸደቁትና የዳኑትም በቦታቸው ጸንተው እንደሚቀጥሉ እያሳሰበ አሁንም ይህ እውነት የማይለወጥና የማይሻር የእግዚብሔር ቃል ነውና ተጠንቀቁ የሚልየአምላካችንን ምክር እንስማ:: እግዚአብሔር ማስታወቅ የሚፈልገው ክፉ ክፋቱን ይቀጥላል:: ከዘላለም ፍርድ በኋላ የሚቀየር ነገር የለም:: የሚሻሻል ነገር ምንም አይኖርም:: ለዘለዓለም እንደ ተፈረደበት ይቀጥላል:: እየባሰ ይሄዳል እንጂ የሚቀንስ ፍርድ ወይም አስተያየት፣ ምህረት አይኖርም ነው:: በአመጽና በእርኩሰት ያሉት ለዘለዓለም በዚያው ይቀጥላሉ ማለት ነው:: በክርስቶስ መምጫና ወይም ከሞት በኋላ ወደ ሕይወት መንገድ ወደ ጌታ መመለስ አይቻልምና ዛሬውኑ ወደ ጌታ ና:: ከሞት በኋላ መንፈስ ቅዱስ ሊረዳህ አይችልም:: የመጽሐፍ ቅዱስንም ቃል ለመስማት እድል አይኖርህም:: ኢየሱስ ያለውን አስብ፣ ማቴ. 7:21–23 ስለዚህ ከፍርድ ለመዳን ጊዜው አሁን ነው::

## የዳኑት ሰዎች ሁኔታ

ቁ. 11 «ጻድቁ ወደፊት ይጽደቅ ቅዱሱም ወደ ፊት ይቀደስ::» ይህ የጌታ ትእዛዝ ነው:: በጽድቅና በቅድስና ማደግ አለበት ማለት ነው:: ወደ ፊት የሚል ቃል ከዳኑ በኋላ ወደ አዲሲቱ ሰማይና ምድር ከደረሱ በኋላ ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከገቡ በኋላም መንፈሳዊ እድገት ይቀጥላል ማለት ነው:: በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መጽደቅ ማቀደስ እግዚአብሔርን በመምሰልና በማወቅ እድገት ይቀጥላል:: ክርስቲያኖች ወደ አዲሱ ሰማይና ምድር ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሲደርሱ እያደጉ መንፈሳዊነት ይቀጥላል እንጂ በምድር ከሞት በፊት በነበሩበት ሁኔታ እንዲቆዩ አይደረጉም:: ሁልጊዜ በመንፈስ መጽደቅና መቀደስ ይቀጥላል:: በጌታ የሆናችሁ ስለዚህ አደራረግና ሥራ ጌታን ሁልጊዜ አመስግኑ::

## ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ

ቁ. 12 ክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ለመገናኘት እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ይላል፣ 2ኛ ቆሮ. 5:10:: ዋጋዬም ከእኔ ጋር ነው ይላል::

ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው ይከፍል ዘንድ ነው። ይህ የክርስቲያኖች የሥራቸው ወይም የአገልግሎታቸውን ዋጋ መከፈያ ቦታ እንጂ የዮሐንስ ራእይ 20፡11 ታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ቦታ አይደለም። የነጩ ዙፋን ፍርድ ላላመኑት ሲሆን ላመኑት ግን በፍርድ ወንበር ፊት ነው። የክርስቲያን ዋጋ የሚከፈልበት ቦታ ክርስቶስ በአየር ሲመጣ ክርስቲያኖች በአየር ከተገናኙ1ኛተሰሎ. 4፡16–17 መሠረት ቤተ ክርስቲያን ስትነጠቅ ጌታ በሰማይ ዋጋ ለክርስቲያን የሚከፍልበት ጊዜ ነው።

ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ምን እንዳለ በ2ኛ ቆሮ. 5፡10–11 ተመልከት። ደግሞ በ1ኛ ቆሮ. 3፡13–15 ክርስቲያን ዋጋው ውጤታማ የሚሆነው በእሳት ተፈትኖ ሲወጣ ነው። የክርስቲያን ሥራ ቢቃጠልበት ግን ክርስቲያን ይጐዳበታል። ነፍሱ ግን በጌታ ስላመነ ይድናል። ስለዚህ ክርስቲያን ሆይ ዋጋህ በጌታ እጅ ነው፤ ና በጌታ አምነህ ከዳንክ ለአገልግሎት በርታ። 1ኛ ቆሮ. 15፡58፤ ገላ. 6፡9–10። ተመልከት።

## መጀመሪያና መጨረሻ

ቁ. 13 ክርስቶስ አልፋና ኦሜጋ መጀመሪያና መጨረሻ እኔ ነኝ ይላል። ይህ ማለት ክርስቶስ ከእኔ በፊት ማንም የለም፣ ከእኔም በኋላ ማንም የለም እያለ የመጨረሻ ማረጋገጫ ሲሰጥ ነው። በዘመንና በጊዜ ሁኔታም ከሄድን እርሱ ነበረ፣ በኤደን ገነት እርሱ ነበረ፣ አሁንም በአዲሲቷ ቅድስቲቱ ከተማም እርሱ ነው። ለዘለዓለም የሚኖር ፈጣሪ እርሱ ነው። ወይም ወደ መታየት አምጪውም የፈለገውን የሚፈጽምም የሚጨርስም እርሱ ነው። እርሱ መጀመሪያና መጨረሻ ነው።

## ሌላ የበረከት ተስፋ

ቁ. 14 በዚህ ቁጥር ሌላ የበረከት ተስፋ ተሰጥቶናል። ይህም የእርሱን ፈቃድ ለማድረግ ፈቃደኞ የሆኑ ብጹአን ናቸው ይላል። እነርሱ የሕይወት ዛፍ ያለበትን ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸውና ወደ ከተማይቱ እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብጹአን ናቸው። ልብሳቸውን ማጠብ ትእዛዝ ነው። ይህ ልብስ ማጠብ ማለት ትእዛዝን መጠበቅ ነው፣ መዝ.(119)፡9። ልብስን ማጠብ ንጹህ ያደርጋል፣ 1ዮሐ. 1፡7። የክርስቶስ ደምና ቃሉ ኃጢአትን ያጥባል ያነጻል።

የእርሱን ትእዛዝ መጠበቅ 1 ዮሐ. 3:23 በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን፣ ትእዛዝን መፈጸም ማለት ነው:: ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ በሮቹን የሚጠቀሙ ብጹአን ናቸው:: ኢየሱስ በሩ እኔ ነኝ አለ፣ ዮሐ. 10:9:: በእኔ የሚገባ ይድናል:: ወደ ከተማይቱ የሚወስደው መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ ዮሐ. 14:6:: ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ በሮቹን መጠቀም አለብን:: እርሱም ኢየሱስነው:: ትክክለኛውን መንገድ ይዘው ወደ እውነተኛው በር የሚጓዙ እነርሱ አሸናፊዎች ናቸው ተብለዋል፣ 1 ዮሐ. 5:5:: ከሕይወት ዛፍ ለመብላት ሥልጣን ያላቸው በበጉ ደም ብቻ ልብሳቸውን ያጠቡት ናቸው:: ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ለመድረስ የሚችሉት እውነተኛውን መንገድ ክርስቶስን ይዘው የሚጓዙት ብቻ ናቸው:: ስለዚህ ጉዳይ በራእይ 21:17 የተጠቀሰውን ተመልከት:: በበጉ መጽሐፍ ስሞቻቸው የተጻፉት ብቻ በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምኑ አማኞች ይደርሳሉ፣ 1 ዮሐ. 5:10–13 ተመልከት::

ቁ. 15 ሌሎች በኃጢአት እርኩሰት የሚመላለሱ ውሾች፣ አስማተኞች፣ ሴሰኞች፣ ነፍስ ገዳዮችና ጣዖትን የሚያመልኩ ውሸታሞች ወደዚያ አይገቡም:: ቦታ ወይም ሥፍራ ለእነርሱ በእግዚአብሔር ከተማ የላቸውም:: እነርሱ ወደ ውጭ ማለትም ወደ እሳት ባሀር ይጣላሉ::

<u>የዳዊት ሥርና ዘር</u>

ቁ. 16 አሁን ኢየሱስ ለዮሐንስ የሚገልጸው ነገር ነው:: አብያተ ክርስቲያናት የሚለው ቃል ወይም ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በራእይ ምዕ. 3 ላይ ከተገለጸው እስካሁን ድረስ በዚህ በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ በዚህ ቦታ ለመጀመሪያ መናገሩ ነው:: ኢየሱስ ይህን ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲመሰክርላቸው መልአኩን ላከሁ ይላል:: ለዮሐንስ ሲናገር ኢየሱስ ለራሱ እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ ይላል::

<u>የዳዊት ዘር</u> ኢየሱስ ራሱን ከእሥራኤል ዘር ከዳዊት ቤተሰብ እንደሆነ ይመሰክራል:: ዳዊት ንጉሥ ነበረ:: ኢሳ. 11:1:: የተሰጠው ተስፋ እንደ ተፈጸመ በትንቢት ተመልከት:: እርሱ የዘላለም ንጉሥ ነው:: እንዲሁም ኢየሱስ ራሱን ከቤተ ክርስቲያን ጋር አንድነት እንዳለው ይመሰክራልም:

የንጋት ኰከብ ነኝ ሲል የቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ መነጠቅን ያሳስበናል። ክርስቶስ እንደ ንጋት ኰከብ በአየር ለቤተ ክርስቲያንና ለእሥራኤል እንደሚመጣ ያሳስበናል። ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ክብር መገለጽ እንድትዘጋጅ ጥሪ ያቀርባል። የንጋት ኰከብ በጨለማ እንደሚያበራ እንዲሁም የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ለዚህ በኃጢአት ጨለማ ላለው ዓለም ታላቅ ተስፋ ነው። በተለይም በዚህ ጨለማ ለምትንከራተት ቤተ ክርስቲያን ትልቅ እድል ነው። እርሷን ለመውሰድ ይመጣል። በኋላም እንደ ፀሐይ ሆኖ የእሥራኤልን ነገድ ሊረዳ ይመጣል፣ ሚልክ. 4:1–3።

ለሁሉም የጥሪ ቃል

ቁ. 17 ሁሉንም የሚያጠቃልል ጥሪ

ሦስት የጥሪ ግብዣ ተመልከት

1. መንፈስና ሙሽራይቱ ና ይላሉ።
2. የሚሰማም ና ይበል።
3. የተጠማ ይምጣ ከወደደ የሕይወት ውኃ እንዲያው ይውሰድ።

መንፈስ ቅዱስና ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ና ብለው ይጋብዛሉ። የተዘጋጁት ሁሉ የክርስቶስን ድንገት መገለጥ ይጋብዛሉ። የትንቢት ቃል እንደሚለው የጌታ መምጣትን ይጠራል። በዮሐንስ ወንጌል 5:24 የጥሪ ቃል ስላለ ስምተን መልስ መስጠት አለብን። ኢሳ. 55:1 ለሚሰማ ሁሉ ጥሪ አለ፤ ለተጠማና ውኃ ለሚፈልግ ማለት የውስጥ የልብ የነፍስ እረፍትና እርካታ ያጣ ወደ ኢየሱስ ይምጣ፣ ዮሐ. 7:37። ፍጹም እረፍትና እርካታ ታገኛለህ። በሕይወቱ ባዶነት የሚሰማው ሁሉ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይምጣ፣ ዮሐ. 3:16፤ 5:40፤ ሮሜ 10:13። ፍጹም እረፍትና እርካታ ይገኛልና።

ጥብቅ ማስጠንቀቂያ

ቁ. 18–19 በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚጨምሩ ወይም ለሚቀንሱት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

1. በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ወይም በትንቢት ማለት የእግዚብሔር ቃል በሙሉ ትንቢት ነውና ለሚጨምር ሁሉ በመከራ ዘመን ያየናቸው መቅሰፍቶች ሁሉ ይጨመርበታል።

2. በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ወይም በትንቢት መጽሐፍ ማለት የእግዚብሔር ቃል በሙሉ የትንቢት ቃል ነውና ከእርሱ አንዳች ቢቀንስ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።

እንግዲህ በእግዚአብሔር ትንቢት ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን የማያስተምር ምን ይውጠው ይሆን?

እንዲሁም በእግዚአብሔር ትንቢት ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለውን እያስተማሩ ሰውን ከእግዚአብሔር ጎዳና የሚያሳስቱ ምን ይውጣቸው ይሆን?

የሰው ጥበብ የእግዚአብሔርን ፍርድ ሊቀንስ አይችልም።

ቁ. 20 ኢየሱስ ቶሎ እመጣለሁ እያለ ትልቅ ማሳሰቢያ አስቀምጦልናል። ይህን የሚመሰክር እመጣለሁ ይላል። ይህ የመጨረሻ ድግግሞሽ ነው። ቶሎ እመጣለሁ የሚለው የኢየሱስ ቃል የኢየሱስ ዳግም መምጣት የመጨረሻ ማረጋገጫ ቃል ነው ቶሎ እመጣለሁ።

ዮሐንስም አዎን አሜን ይሁንልን እያለ ይመልሳል። ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያንን ወክሎ አዎን ጌታ ሆይ ቶሎ ና ይላል። ዛሬ የቤተ ክርስቲያን ጩኸት ና ጌታ ሆይ ቶሎ ና የሚል ነው። አንባቢ ሆይ አንተስ ጌታ ኢየሱስ ሆይ እባክህ ቶሎ ና ለማለት ተዘጋጅተሃልን?

## ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን

ቁ. 21 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን አሜን። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ ጥቅስ ነው። የመዝጊያ ጥቅስ ከዚህ የሚቀጥል አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አይገኝም። አሜን ነው። በዚህ ጥቅስ የምናየው ነገር አሁንም በመጨረሻ እንኳን የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰዎች እንዳለ የሚገልጥ ነው። የእግዚአብሔር የማዳኑ መንገድ ለኃጢአተኞች እስካሁን ክፍት መሆኑን ነው። ወደ ጸጋው መምጣት ይችላሉ። ጸጋ ነጻ ስጦታ ነው። መዳን በሥራ ሳይሆን በክርስቶስ በማመን እንደሆነ እየገለጸ ነው፣ ኤፌ. 2:8። መጽሐፍ ቅዱስ ሰው በሥራው ለመዳን ቢሞክር እዳ እንዳለውና በክርስቶስ በማመን ከሆነ ግን እምነት ጽድቅ ሆኖ እንደሚቆጠርለት በግልጽ ይገልጽልናል፣ ሮሜ 4:4–5። ደህንነት በጸጋ እንጂ በተግባር እንዳልሆነ ኤፌ. 2:8–9 ተመልከት። መዳን በእግዚአብሔር የጸጋ

ስጦታ ብቻ በማመን ይገኛል:: ጸጋ ለክርስቲያን መንፈሳዊ እድገት የሚሰጥ ነጻ ስጦታ ነው:: እግዚአብሔር ለበጎ ሥራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል፣ 2ቆሮ. 9:9::

ዛሬ ይህን ማስታወሻ የምታነብ ሁሉ ጌታ ኢየሱስን በእምነት ብትቀበል ጸጋ ለአንተ እንደሚሆንልህ እወቅ:: የእግዚአብሔር የምህረት እጁ አሁንም ተዘርግቶ እንደሚጠብቅህ እወቅ:: ወደ ጌታ ና:: የክርስቶስን ጸጋ በእምነት ተቀበል:: ልብህን ለጌታ ስጠው፣ ሮሜ 10:9–13:: ለነፍስህ እረፍት ታገኛለህ፣ ማቴ. 11:28:30::

## በተጠማሪ የምትመለከታቸው ጥቅሶች

1. ስለ መንግሥተ ሰማያት ወይም የእረፍት ሥፍራ

    ማቴ. 25:34፤ ራእይ 21:1–7፤ 22:1–5፤ ዕብ. 4:14፤ 2 ቆሮ. 12:2፤ ዮሐ. 14:1–3፤ ዕብ. 12:22–24፤ ራእይ 21:1–27፤ ማር. 12:25፤ ራእይ ምዕራፍ 4 ና 5 በሙሉ፤ ኢሳ. 66:24፤ ማቴ. 8:11፤ 2 ቆሮ. 5:1–8፤ ቆላ. 3:1–4፤ ፊልጵ. 1:20–23፤ 3:20::

2. ስለ እሳት ባህር ወይም የቅጣት ሥፍራ

    ማቴ. 25:42፤ ማር. 9:42–48፤ ራእይ 20:7–15፤ መዝ. (30):9፤ ዘኍ. 16:33፤ ኢሳ. 38:10፤ ኢዮብ 24:19፤ 2 ጴጥ. 2:4፤ ማቴ. 8:12፤ ራእይ 4:10–11፤ ዕብ. 6:4–8፤ ራእይ 14:11፤ ማቴ. 25:46፤ ዮሐ. 5:29፤ ዳን. 12:2፤ ሮሜ 2:8–10፤ ራእይ 20:10–15፤ ዕብ. 10:27፤ ዕብ. 9:27::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 19
## የክርስቶስ ዳግም መመለስ

**ቁጥር 1**

ይህ ምዕራፍ ሲጀምር «ከዚህ በኋላ» ብሎ ይጀምራል። ምን ማለት ነው? ያቺ ነጋዴዋ ባቢሎን ፍርድ ከተቀበለች በኋላ የሚቀጥል ነገር ነው ማለት ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ እየሰማና እያየ በሰማይ የብዙ ሰዎች ድምጽ ሰማ። እንዲህ እያሉ ነበር፦

**ቁጥር 2**

ሃሌሉያ ማዳንና ክብር ኃይልም የአምላካች ነው። ምክንያቱም ምድርን በዝሙቷ ያጠፋችውን ያችን ታላቂቷን ጋለሞታ ሴት እግዚአብሔር ስለፈረደባት፣ የባሪያዎቹንም ደም ከእጅዋ ስለተበቀለ ፍርዶቹ እውነትና ጽድቅ ነው አሉ። ይህ 19ኛው ምዕራፍ የመከራ ዘመን ማለቂያ እንደሆነና ደስ ብሏቸው በሰማይ ዝማሬ እንዳደረጉ ያሳየናል፣ ራእይ 18፡20። በምዕራፍ 19፡1 በደስታቸው ምክንያት ለጥሪው መልስ ሲሰጡ እንመለከታለን። አሸናፊና የፍጥረት ገገር የሆነው ኢየሱስ በአውሬውና በዘንዶው የሚፈርድበት፣ ለሺህ ዓመትም የሚገዛበት ዘመን ስለ ደረሰ ነው። ያቺ ክፉ ባቢሎን ተፈረደባት። ጨለማው ወደብርሃን ተለወጠ፣ ፍርድ ወደ በረከት መለወጡ ነው።

በምዕራፍ 19 የምንመለከታቸው ሁለት ትልልቅ ነገሮች፣ የበጉ ሠርግና የጌታ ዳግም መምጣት ጉዳይ ነው። እንዲሁም በዚህ ምዕራ ሁለት ትልልቅ ግብዣዎችን እናያለን። ያውም የበጉ ሠርግ ግብዣና በአርማጌዶን ጦርነት ለሰማይ አሞራዎችና ወፎች የተሰጠ የሥጋ ግብዣ ነው። ያም ማለት በሮሜ 8፡18–23 ድረስ የተጻፈው የተስፋችን ዘመን መጣ፣ የእግዚአብሔር ልጆች የነጻነት ዘመን ስለ መጣ በሰማይ ደስታ ሆነ ማለት ነው።

**ቁጥር 2–3 በሰማይ ታላቅ ሃሌሉያ**

እነዚህ ምስጋና የሚያቀርቡ ቅዱሳን አሁን ነገሮችን ከእግዚአብሔር አቅጣጫ እግዚአብሔር እንደሚያይ ዓይነት አድርገው ስለሚያዩ ነገሮቹ ልዩ ሆነዋል። እነዚህ ቅዱሳን ለእግዚአብሔር ማዳንና ክብር ኃይልም ይሁን ሲሉ፣ ምክንያት አላቸው። እርሱ እግዚአብሔር እውነተኛ፣ ጻድቅ ፈራጅ ስለሆነና ያቺን ጋለሞታ በርኩሰቷ ምድርን በሞላ ያበላሸችውን እንዲሁም ጌታ የቅዱሳንን ደም ስለ ተበቀለ

ምስጋናና እልልታ በሰማይ ስለሆነ ነው። ደግሞ የፍርዷ ጢስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ስለ ወጣ ነው።

ታላቅ ሃሌሉያ የሆነበት ምክንያት

1. ጋለሞታዋ ሴት ስለ ተፈረደባት
2. ጌታ ማንም ሊቃወም በማይችል ሁኔታ ስለሚነግሥ ነው።
3. የቅዱሳን ደም በከንቱ የፈሰሰውን ስለ ተበቀለላቸው ነው።
4. የበጉ ሠርግ ሥፍራውን ስለሚወስድና የሐሰት ሙሽራይቱ መንገድ ስለለቀቀችና ስለ ተወገደች ነው። በቁጥር 3 ላይ የጢስ መውጣት ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚለው በራእይ 14:9–11 ስለተገለጸ ተመልከት።

ቁ. 4 ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በሰማይ ሠራዊት ደስታ አብረው ተደሳቾች ሆነው በታላቅ ዝማሬ ውስጥ ሲገኙ እናያለን። ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ወደ ሰማይ የተነጠቁ ቤተ ክርስቲያንን የሚወክሉት ናቸው። 4ቱ እንስሳትና ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ሃሌ ሉያ ብለው ለእግዚአብሔር ሲሰግዱ ይታያሉ። በዮሐንስ ራእይ ስለ 24ቱ ሽማግሌዎች የሚያወራው የመጨረሻ ቦታ ራእይ 19:4 ነው። ከዚህ በኋላ ስለ ቤተ ክርስቲያን በተለይም የተነጠቁትን ምዕመናን የሚወክል 24 ሽማግሌዎች የሚለው ይቀርና ሙሽራይቱ ወይም ሚስቱ በሚል ቃል ተተክቶ እናያለን።

ቁ. 5–6 ድምጽ ከዙፋኑ ወጣ፣ እንዲህ እያለ፣ እግዚአብሔርን የምትፈሩ ባሪያዎች ሁሉ አምላካችንን አመስግኑ የሚል ኃይለኛ ድምጽ፣ ከባድ ድምጽ፣ ሃሌ ሉያ ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላካችን ነግሦአልና፣ ኃይል ሁሉ ብርታት ሁሉ የእርሱ የሆነ ጌታ ነግሦአልና ይሉ ነበረ። እንግዲህ ሙሽራው ከነገሠ ሙሽራይቱም የመንገሥዋ ጊዜ መጥቷል ማለት ነው። እንግዲህ የበጉ ሠርግ ደርሦአልና፤ ይህ የበጉ ሠርግ ከጌታ ወደ ምድር መመለስ ቀደም ብሎ በሰማይ ይሆናል።

ቁ. 7–10 የበጉ ሠርግ ሥነ ሥርዓት

ከሃሌ ሉያ ኳየር (መዘምራን) ቀጥሎ የተሰጠ መግለጫ። መግለጫውም የበጉን ሠርግና እራት የሚመለከት ጉዳይ ነበረ። ስለ ሠርግ አይሁዶች የሚያደርጉት ሥርዓት ነበሯቸው። ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ጭምር ስለ ሠርግ እንመለከታለን።

1. ሠርግ ሁልጊዜ በአባት ማለት በሁለቱ ሙሽራና ሙሽራይቱ ወላጆች የሚደረጉ ሥርዓቶችን ያሳስበናል። ለምሳሌ ያህል የማርያምና የዮሴፍ ጋብቻ ጉዳይ በማቴ. 1:19–25 ላይ ያለውን ማንበብ ነው። ስለ ሁለቱ እጮኛሞች ጉዳይ በጥልቅ ማየት ይቻላል። ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳለች፣ ይህ መታጨት ማለት በወላጆቻቸውና በቤተሰባቸው እንዲሁም በሕብረተሰባቸው የመታጨት ፕሮግራም ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ ማርያም የዮሴፍ ሚስት ትባል ነበረ። ወንዱ እጮኛዋ ለሴቷ ባልዋ ይባል ነበረ። ሠርግ ተደርጐ ሳይጋቡ ወይም በግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳይኖራቸው እንኳን ባልና ሚስት ይባሉ ነበር። ይህን ከማቴዎስ ወንጌል ልንገነዘብ እንችላለን። በዚህ መካከል ሳሉ መልአክ መጥቶ ለዮሴፍ ስለ እጮኛው ወይም በአይሁድ ሕግ ስለ ሚስቱ ከመንፈስ ቅዱስ ማርገዟን ገለጸለት።

2. በዚሁ ዓይነት ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምዕመናን በ2ኛ ቆሮ. 11:2 ላይ ለክርስቶስ ለአንድ ባል ለማቅረብ እንደ አጫቸው ይናገራል። ስለዚህ ይህች የታጨች ድንግሊቱ ለወንዱ ሚስት ናት። ያም ክርስቶስ ባል ሆኖ፣ ቤተ ክርስቲያን ሚስቱ ድንግሊቱ ሆና እናገኛለን።

3. በኤፌሶን 1:3–4 ላይ ስንመለከት እግዚአብሔር አብ ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ሚስት እንድትሆን እንደ መረጣት እንመለከታለን። እኛ አማኞች ሳንወለድ በፊት ተመርጠናል፣ ታጭተናል፣ እንግዲህ በአይሁድ ሕግ ወንድ ልጁ ለአባቱ እጮኛዬን አምጣልኝ ብሎ ሲናገር፣ አሁን አገባለሁ ብሎ ራሱን አዘጋጅቶ ሲቀርብ ሙሽራይቱ ትመጣለች። የሙሽራይቱ መቅረብ ጊዜ ይባላል። የልጅቷ አባት ወደ ልጁ ወይም ወደ ሙሽራው የሚስቱን ወይም የሙሽራይቱን እጅ ይዞ ይመጣና ለልጁ አባት ሲያስረክብ፣ የልጁ አባት ተቀብሎ ለልጁ ለሙሽራው ሙሽራይቱን ይሰጣል። ወይም ያስረክባል። ያኔ ሙሉ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ተፈጸመ ይባላል።

4. የሙሽራይቱ ወደ ሙሽራው መቅረብ ጉዳይ በኤፌሶን 5:25–27 ባሎች ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ይላል። ራሱን ለቤተ ክርስቲያን አሳልፎ ሰጥቷል። በውኃ አንጽቷት ቤተ ክርስቲያንን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ ይላል። እንግዲህ ይህ ወደ ራሱ ማቅረብ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ

በአየር ስትወሰድ 1ኛ ተሰሎ. 4፡16–17 ላይ እንደተገለጸው ይፈጸማል። በዚያም በሰማይ የሠርጉ ቃል ኪዳን የሚደረግና የሚፈጸም ይመስላል። በዚያ በሠርጉ ጊዜ ምናልባት ቶሎ ወደ ሠርጉ እራት መሄድ ሳይሆን ሙሽራው ሙሽራይቱን ለተጋበዙት ጉባኤ የማስተዋወቅና የሽርሽር ፕሮግራም ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። ከዚያም ሁልጊዜ ሙሽራይቱ ከሙሽራው ጋር ትሆናለች፣ 1ኛ ተሰሎ. 4፡17–18። ይህ የደስታ ጊዜያቸው ይሆናል። ስለዚህ ፕሮግራም አንተ ራስህን አዘጋጅተሃል ወይ?

ቁ. 8–9 የበጉ ሠርግ

ሚስቱ ራስዋን ስለ አዘጋጀች ደስ ይበለን ይላል። ቤተ ክርስቲያን ምን ጊዜም ራስዋን በቅድስና መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ርኩሰትን መጸየፍ አለባት፣ ዕብ. 12፡14፤ ይሁዳ 1፡24–25። ሚስቱ ምን ጊዜም ያማረና ያጌጠ ልብስ መልበስ ያስፈልጋታል። ቀጭን ያጌጠ ልብስ የተባለው የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ ነው። በክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ከነጻን በኋላ ለመልካም ሥራ ተጠርተናል። የጽድቅ ሥራ እንሥራ፣ መልካም ሥራ ሁልጊዜም ያስፈልገናል፣ ማቴ. 5፡16፤ ኤፌ. 2፡10።

ቁ. 9 ወደ በጉ ሠርግ እራት መጠራት።

የዓለም ሕዝብ ሁሉ ተጠርቷል። በወንጌል እየተጠራ ነው። እናንተ ደካሞች ወደ እኔ ኑ ይላል፣ ማቴ. 11፡28–30።

የግብዣው ሁኔታ

ሰው ሁሉ እንደ አቅሙ፣ እንደ ባለጠግነቱ መጠን ነው የሚያደርገው። ድግሱ ለአጭር ጊዜ ሊሆን ይችላል ወይም ለሙሉ ሳምንት ወይም ከዚያም በላይ ለረጅም ወራት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ በዮሐንስ 2፡1–12 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ተጠርተው ነበረ። ከዚያም ድግስ እንደነበረና በዚያ እንደ ተካፈለ እናያለን።

## 5. ስለ በጉ ሠርግ ግብዣ

ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 22፡1–14 ያለውን መርምር። ይህ ንጉሥ ያዘጋጀው የልጁ ሠርግና ግብዣ፣ እግዚአብሔር ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያዘጋጀው ሠርግና ድግሥ ይመስላል። ደግሞ ወደ ሠርጉ አንመጣም ብለው የቀሩትን አይሁዳውያንን ያመለክታል፣ በማቴ. 25፡1–13 ድረስ ያለውን የሠርግ ቦታ ተመልከትና አመዛዝን።

ሙሽራው ከሙሽራይቱ ጋር ስለሚመጣ ተዘጋጅተው ይጠባበቁ ነበር። የተዘጋጁት ከሙሽራው ጋር ሺህ ዓመት ሊነግሡ ወደ ሠርጉ ገቡ። ያልተዘጋጁት አይሁዶች ግን በውጭ ቀሩ። ዘይቱ መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል፣ (ሮሜ 8:9)።

## ልዩ ልብስ

ሙሽራው የለበሰው የራሱን ቅድስና የተባለውን ልብስ ሲሆን፣ ሙሽራይቱ የለበሰችው የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ ይባላል። ስለዚህ ነው በቁጥር 9 ላይ ወደ በጉ ሠርግ የተጠሩ ብፁአን ናቸውና ጻፍ የተባለው። ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው ይላል። የበጉ ሠርግ ግብዣ ጊዜ እንደ ራእይ 21:9–10 መሠረት ከክርስቶስ ጋር ለሺህ ዓመት ስንነግሥ የሚሆን ይመስላል። ደስ ይበላችሁ፣ በታውም ከሰማይ የምትወርድ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ይሆን ይሆናል። በበጉ ሠርግ እራት የሚገኙት እንግዶች በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት:–

1. ዮሐንስ መጥምቁ እንደ ዮሐንስ 3:29
2. እንደ ሉቃስ፣ 13:28–29 የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ሁሉ ነው።
3. እንደ ራእይ 20:4 መሠረት በመከራ ዘመን ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም የታረዱትና የተገደሉት ቅዱሳን ሁሉ፣
4. በመከራ ዘመን የሚድኑ ሕዝብ በሙሉ፣
5. ምናልባት ቅዱሳን መላእክት በሙሉ፣ ዕብ.1:6።

ቁ. 10 የዮሐንስን ሁኔታ እንመልከት፤ ስለ በጉ ሠርግ እራት ገለጻ ላደረገው መልእክት መስገድ ሲሞክር መልአኩ መልሶ፣ አታድርገው አለ። ማለት አትስገድልኝ፣ እኔም አንተም የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነን። ለእግዚአብሔር ስገድ። የሚሰገድለት እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኔ ቅዱስ መልአክ ስግደትን ከእግዚአብሔር ልወስድና ለራሴ ለማድረግ አልችልም። እኔም ለእግዚአብሔር ብቻ እሰግዳለሁ። እኔም ፍጡር ነኝ። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ስገድ አለው መልአኩ፣ ራእይ 22:8–9። ክብር ምስጋና ስግደት የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ቁ.11 <u>የሰማይ መከፈት</u>

ሐዋርያው ዮሐንስ ሰማይ ተከፍቶ አየሁ ይላል በዮሐንስ ራእይ 4:1–2። ሰማይ ተከፍቶ ዮሐንስን ወደላይ ሲያስወጣው ወይም ሲያስገባ ነበረ። አሁን ግን ልዩ ነበረ። ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ምድር የሚመልስ ሰማይ ተከፍቶ ነበረ። ዮሐንስ ወደ ሰማይ ሊገባ ሲሆን፣ በዚህ በታ

ግን ኢየሱስ ከሰማይ ሲወጣ ወደ ምድር ሲወርድ ይታያል። ቁ. 11ን አንብብ። ጌታ ከሰማይ ወደ ምድር ከቅዱሳንና ከመላእክት ጋር ሲወርድ ይህን ምድር ባበላሸው በሐሳዊ መሲህና በምድር ነገሥታት ላይ ልክ በዳንኤል መጽሐፍ ምዕ. 2:34–45 እንደተጻፈ ከሰማይ የተወረወረ ድንጋይ ይወርድባቸዋል። የጌታ መውረድ ለሰይጣንና ለሐሳዊ መሲህ፣ እንዲሁም ለክፉ ሰዎች የመጨረሻ ጥፋታቸው ይሆናል። ክርስቶስ ሺህ ዓመት መንገሥ ከመጀመሩ በፊት የክፋት ሠራዊት በሞላ መንገድ መልቀቅ አለባቸው። ከዚያ በኋላ ነው የጽድቅ መንግሥት የሚቋቋመው።

<u>ነጭ ፈረስ፡</u>– ክርስቶስ በነጭ (አምባላይ) ፈረስ ላይ፣ ፈረስ የጦርነት ምሳሌ ነው። ከዚህ በፊት በምዕ. 6:2 ላይ ሐሳዊ መሲህ ክርስቶስን መስሎ ሕዝቡን ሊያስት በነጭ ፈረስ ተቀምጦ መጣና አታለላቸው። ክርስቶስ ግን እውነተኛ ነው። በመጀመሪያ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ ራሱን ዝቅ አድርጐ፣ አዋርዶ፣ ሠላማዊ ሆኖ፣ በአህያ ላይተቀምጦ ነበር፣ ማቴ.21:1–11። አሁን ግን በፈረስ ላይ ተቀምጦ ሲመጣ በጦርነትና በድል አድራጊነት ይመጣል፣ ቁጥር 11 ተመልከት። በነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠው ታማኝና እውነተኛ ይባላል። ፊልጵ. 2:8–11። በመጀመሪያ መምጣት ራሱን አዋርዶ፣ በሁለተኛው መምጣት ግን ራሱን ከፍ ያደረገ፣ ኃያሉ እግዚአብሔር እርሱ ብቻ ነው። እርሱ ከሁሉ በላይ ነው። እርሱ ክብር ይገባዋል። እርሱ ሊነግሥ ይገባዋል። እርሱ ድል አድራጊ ነው። እርሱ እውነተኛና ታማኝ ነው። በእውነትም ይፈርዳል።

ቁ. 12 ዓይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ናቸው።

በምዕራፍ 1:14 ላይ አይተናል። ማለት አንዳችም ነገር ከዓይኖቹ ማምለጥ አይችልም። ማንም ከእርሱ መደበቅ አይችልም፣ ምዕ. 6:12–17 ተመልከተናል።

- በራሱ ላይ ብዙ ዘውዶች አሉ ይላል። ከዚህ ጊዜ አንስቶ ክርስቶስ ወሰን የሌለው የምድር ሁሉ ገዢዎ ባለ ሥልጣን እርሱ መሆኑን ያሳያል። እስከዚያ ድረስ ሰይጣን ሁልጊዜ እየተቃወመው ነበር። አሁን ግን ክርስቶስ ሰይጣንን ስለፈረደበት የዘላለም የምድርና የሰማይ ገዢ ይሆናል።
- ደግሞ ከራሱ በቀር ማንም ሊያውቅ የማይችል የተጻፈ ስም አለው።

## ቁ. 13 በደም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፎል

ለዓለም ሕዝብ ደሙን አፈሰሰ፣ ኢሳ. 63:2–6:: እርሱ በዓለም ሊፈርድ ይመጣል:: ስሙም የእግዚአብሐር ቃል ተብሏል፣ ዮሐ. 1:1:: እስከዚህ ድረስ ክርስቶስ በዙፋኑ ሆኖ ፍርድን ወደ ምድር ይልክ ነበር:: አሁን ግን ወደ ምድር ይወርዳል:: ኢየሱስ ወደ ምድር ሲወርድ ወደ ሰማይ ሲያርግ ባረገበት፣ የሐዋ. ሥራ 1:10–12 ወደ ደብረ ዘይት ተራራ እግሮቹ ይወርዳል፣ ዘካ. 14:4:: ከዚያም የተከማቸውን የምድር ገዢዎችን ሠራዊት በሥልጣኑ ይዋጋል፣ ድልም ያደርጋል::

## ቁ. 14 የሰማይ ጭፍራዎች

ይህን ዮሐንስ እያየ ነበረ:: የሰማይ ጭፍራዎች በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጠው ቀጭን የነጻ የተልባ እግር ልብስ ለብሰው ጌታን ይከተሉ ነበር:: እነዚህ የሰማይ ጭፍራዎች የተባሉት:-

1ኛ ቅዱሳን ጉባኤ ከጌታ ጋር በሞት የተገናኙት፣
2ኛ ቅዱሳን እልፍ አእላፋት መላእክት፣
3ኛ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ይሆናሉ:: እነርሱም በትንሳኤ ከጌታ ጋር ይሆናሉና ነው::

## ቁ. 15 አጥፊው መሣሪያ

የመጨረሻው የአርማጌዶን ጦርነትን የሚመታ ከባድ መሣሪያ ምን እንደሆነ በዚህ ቁጥር ተገልጿል:: ይህ ጦርነት ጠቅላላ በፍልስጥኤም ወይም በእስራኤል አገር የሚሆን ሳይሆን አይቀርም:: ምክንያቱም የአርማጌዶን ጦርነት ቦታ በእስራኤል አገር 200 ማይልስ ስፋት ያለበት ቦታ እንደሚሆን ራእይ 14:20 ላይ የቦታው መለኪያ ተጽፎ ይገኛል:: እንዲሁም የወይን መጭመቂያ ቦታ ይልና የደሙ መፍሰስ ወደ ፈረሶች ልጓም ድረስ እንደሚደርስ አይተን ነበር:: በዚህ ጦርነት የሰማይ ሠራዊት በመሣሪያ አይዋጉም:: ነገር ግን ጌታ ራሱ ከአፉ የሚወጣ ሰይፍ ታላቅ የማጥፊያ መሣሪያ ይሆናል:: ጦርነቱ የአንድ በኩል ሠራዊት ብቻ ይሆናል:: ያውም በአንድ በኩል ለጦርነት የሚቆሙት የዓለም ሕዝብ በሞላ ሆኖ፣ በሌላ በኩል የሰማይ ሠራዊት ለሰልፍ ሳይቆሙ ጌታ ብቻ ይቆማል:: የሰማይ ሠራዊት በጌታ በኩል ቆመው ይመለከታሉ:: ጌታም ከአፉ በሚወጣ ሰይፍ አህዛብን ይመታቸዋል:: ከአፉ የሚወጣው ቃል ትልቅ ሥራ ይሠራል::

በመጀመሪያ በዘፍጥረት 1:3–6 ቁጥር 9, 11, 14, 20, 24, 26 በእነዚህ ቁጥሮች 8 ጊዜ እግዚአብሔር በቃሉ ይሁን አለ ይላል:: ሆኖም በመዝሙር 33:6–9 እግዚአብሔር በቃሉ ሰማይንና ምድርን ሌሎችንም ፍጥረታት እንደፈጠረ እናያለን:: እንዲሁም በዓለም መጨረሻ ጌታችን በቃሉ በሚወጣ ቃል ምድርን ይፈርዳል:: በብረት በትርም በቃሉ በሚወጣ ብቻ ይገዛቸዋል፣ ራእይ 1:16 ተመልከት::

ቁ. 16 በልብሱና በጭኑ የተጻፈው ስም አስደናቂ ነው:: የነገሥታት ንጉሥ የጌቶችም ጌታ:: ጌታ በሁለተኛው መምጣት ጊዜ ከሁሉ በላይ አጠቃላይ ባለ ሥልጣን ይሆናል:: አልፋና ኦሜጋ፣ መጀመሪያና መጨረሻ፣ ሁሉን የሚወስን ሆኖ እናያለን፣ ራእይ 1:8::

በጦርነቱ የሚሳተፉ እነማን ናቸው? መልሱ ራእይ 19:19 ተመልከት:: ምዕራፍ 16:12–19 ተመልከት:: ራእይ 19:17–20:: ይህም ሆኖ በጉ ድል ያደርጋቸዋል፣ ዕብ. 12:25–27 ተመልከት::

## ቁ. 17–18 የአርማጌዶን የመጨረሻ ውጊያ

ዲያቢሎስ ከነጭፍሮቹ እንዲሁም የምድር ነገሥታትና ገዢዎች ከሐሰተኛ ነብይና ሐሳዊ መሢህ ጋር አንድ ወገን ሆነው ጌታ ኢየሱስና የሰማይ ሠራዊት ሊዋጉ የሚሰበሰቡበት ጦርነትና የጦር ሜዳው አርማጌዶን ጦርነት ይባላል:: በዚያ ጦርነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአፉ በሚወጣ ስለታም ሰይፍ (ቃል) ሲመታቸው የሰው ሬሳና የከብት ሬሳ በሜዳ ስለሚወድቅ የሰማይ አሞራዎችን ለግብዣ የሚጠራ መልአክ ጥሪ ይሰማል:: እንግዲህ ጌታ ለብዙ ዓመታት በሰው ልጆች ላይ ምሕረቱንና ትዕግሥቱን እያሳየ ቆይቷል:: አሁን ግን የፍርድ ሰዓት ደረሰ:: ሰው ሁሉ በሕይወቱ ዘመን የዘራውን የሚያጭድበት ጊዜ ደረሰ:: ስለዚህ ይጨክናል፣ ገላ. 6:7–8:: የፍርድ ጊዜ ደረሰ::

ቁ. 19 አውሬው ምንም እንኳ ከጌታ ጋር ጦርነት ሊያደርግ የምድር ሠራዊት ቢያከማችም መጨረሻቸው ጥፋት ይሆናል:: ዛሬም ቢሆን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ጠላት የተሸነፈ ነው፣ ያዕ. 4:7–8፤ 1ኛ ጴጥ. 5:9:: ያም ዲያቢሎስ ነው:: ዲያቢሎስና ሰዎች ራሳቸው ባዘጋጁት መሣሪያ እግዚብሔርን የሚያሸንፉ መስሏቸው ነበር::

## ቁ. 20 የአውሬውና የሐሰተኛ ነብይ መጠረሻቸው

የተሸነፉ የምድር ሠራዊትና አውሬው ምን እንደሚሆኑ ጌታ ሲገልጽ ድንቅና ተአምራትን ያደረገው ሐሰተኛው ነቢይ በሕይወታቸው በዲን ወደሚቃጠሉበት ወደ እሳት ባህር ተጣሉ:: አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ራሳቸውን የሰይጣን መጠቀሚያ አድርገው ስለሰጡ ወደ እሳት ባህር ይጣላሉ፣ ራእይ 20:10:: ያሳታቸው ዲያቢሎስም ከእነርሱ ጋር ወደ እሳት ባህር ይጣላሉ:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት ሐሳዊ መሢህና ሐሰተኛው ነቢይ የመጀመሪያው የእሳት ባህር እራት ናቸው:: በኋላ የሚቀጥለው ዲያቢሎስ ምዕ. 20:10–15 እንዲሁም በጌታ ያላመኑት ሁሉ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው እሳት ባህር ይጣላሉ፣ ማቴ. 25:41:: እስከዚያ ድረስ ሲያል ላላመኑትና ለከፉዎች ማረፊያ ነው፣ ሉቃስ 16:19–31:: በዚያን ጊዜ በመዝ. 2:1–4 የተጻፈው ቃል ይፈጸማል:: ክርስቶስ ድል አድራጊ ይሆናል::

## ቁ. 21 የቀሩት ሰዎች መጠረሻቸው

በፈረስ ላይ ከተቀመጠው አፍ ከሚወጣ ሰይፍ የተገደሉትን በቁጥር 15 አይተን ነበር:: እንዲሁም በምዕራፍ 14:19–20 ፍርዳቸውን ተመልክተናል:: ከዚህ ከአርማጌዶን ጦርነት ቀጥለን የታላቁ መከራ ዘመን ማለቁንና ማብቃቱን እንድንገነዘብ ያስፈልጋል:: ከዚህ በኋላ በጥናታችን ከታላቁ መከራ በኋላ ምን እንደሚሆን እንመለከታለን::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 20

## እግዚብሔር በሰይጣን ላይ ያለው የመጨረሻ ውሳኔ የሚለውን እንመርምር

ቁ. 1–3 እንዲሁም ቁ. 7–10

አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ዓቢይ ወቅትና ምዕራፍ ደርሰናል:: የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን:: ይህ ምዕራፍ እንደሚያመለክተው ክርስቶስ ለሺህ ዓመት በምድር ላይ የሚነግሥበት ጊዜ መጣ:: ሰይጣን ለሺህ ዓመት በጥልቅ ታስሮ ተዘግቶበት እናያለን:: ይህ የሰይጣን የመጨረሻው ውጤት ነው:: እንዲሁም የመከራ ዘመን ቅዱሳንና ትንሣኤያቸውን የምድርን ሁኔታ እንዲሁም ትልቅ ነጭ ዙፋንን እንመለከታለን:: ክርስቶስ ለሺህ ዓመት በምድር ላይ ይነግሣል:: ያውም ጌታ በጸሎቱ ያስተማረን መንግሥት ወደ ምድር መምጣቱ ነው፣ ማቴ. 6:10–13:: «መንግሥትህ ትምጣ» የሚለው እንዲሁም መንግሥትህን ለእሥራኤል መቼ ትመልሳለህ? የተባለለት የሐዋ.ሥራ 1:6::

በዚህ በራእይ ምዕራፍ 20 ላይ የተዘረዘሩት የአምስቱን ክንውኖች ቅደም ተከተል እንመለከታለን:: እነዚህ:–

1. ሰይጣን ለሺህ ዓመት መታሰሩ፣ ቁ. 1–3
2. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገደሉትን ቅዱሳን፣ ቁ. 4:–6
3. ከሺህ ዓመት በኋላ የሰይጣን መለቀቅን፣ ቁ. 7–9
4. ሰይጣን ወደ ዘላለም የእሳት ባህር መጣሉን፣ ቁ. 19::
5. ታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድና ያላመኑት የየዘመናቱን ሕዝቦች ቁ. 11–15

ለጥናታችን እንዲረዳን ይህን ምዕራፍ በትልልቅ አርእስት እንከፍለዋለን:: ይኸውም የሚከተለው ነው::

1. እግዚአብሔር በሰይጣን ላይ ያለው የመጨረሻ ውሳኔ
2. የእግዚአብሔር መንግሥት ከክርስቶስና ከቅዱሳኑ ጋር
3. የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ ባላመኑት ላይ::

የሐንስ ራእይ ምዕ. 20ን ቁጥር በቁጥር ስንመለከት ማስታወስ የሚገባን ዋና ነገር ምዕ. 20 ከምዕ. 19 የሚቀጥል ተከታታይ መሆኑን ነው::

ሐዋርያው ዮሐንስ የሚጠቀመው ታላቅ ቃል ሰማይ ተከፍቶ አየሁ የሚለውን ቃል ከምዕ. 19 እስከ ምዕ. 21 ድረስ አስር ጊዜ እናገኛለን:: ለምሳሌ ምዕራፍ 19:11 ቁጥር 17 ,19፣ ምዕ. 20:1,4,11,12፤ ምዕ. 21:1,2,3 ተመልከት::

## ቁ. 1–3 የሰይጣን መታሰር

ዮሐንስ የምድር ጦር ሠራዊትና ጦርነት በጌታ ቅጣትን ከተቀበሉና ከጠፉ በኋላ የሰይጣንን መታሰር አየሁ ይላል:: ሰይጣን ለምን ለሺህ ዓመት በጥልቅ ይታሠራል? መልሱ በኢሳያስ 14:12–16 ላይ ይገኛል:: ሰይጣን በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ላይ ካመጸበት ጊዜ አንስቶ ራሱን ከፍ አደረገ:: የዚህ ዓለምም ገዢ ሆነ:: ስለዚህ አሁን እግዚአብሔር ሰይጣንን ዝቅ ያደርጋል:: የእግዚብሔር ኃይል ከሰይጣን ኃይል እጅግ ይበልጣል:: በዚህ ምዕራፍ የሰይጣንን መታሰር እናያለን:: ሰይጣን ምንም ኃይለኛ መስሎ ቢታይም እግዚአብሔር ከተናገረ ተራ መልአክ ሊያስረውና ወደ ጥልቅ ሊወረውረው ይችላል ማለት ነው:: እስከዚያ ድረስ የመላእክት አለቃ የሆነው መልአኩ ሚካኤል እንኳን በራሱ ሥልጣን ምንም ማድረግ አልፈለገም:: ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ፣ ይሁዳ ቁጥር 9፣ ራእይ 12:7–9::
ደግሞም የሚገርመው ነገር ይህ በዮሐንስ ራእይ 20:1–3 ያለው ሰይጣንን ያሰረ መልአክ በሰይጣን ላይ 6 ነገሮችን ለማድረግ ሥልጣን እንዳለው እናያለን:: እነርሱም:–

1. እጁን ለመጫን
2. ሺህ ዓመት ለማሰር
3. ወደጥልቅ ለመጣል
4. ጉድጓዱን ለመዝጋት
5. ለማተም
6. እንደገና ከሺህ ዓመት በኋላ ይፈታ ዘንድ

ሰይጣን የታሰረበት ጥልቅ የሚለውን ከዚህ በፊት በምዕ. 9:2 ላይ አምስተኛው መለከት በተነፋ ጊዜ ተመልክተን ነበር:: ይህ ጥልቅ ጉድጓድ በጥናታችን የከፉ መላእክት መጥፊያ እንደሆነ እናገኛለን:: ስለዚህ ነው ሰይጣንን ያሰረው መልአክ ወደ ጥልቅ ጉድጓድ የወረወረው::

ይህ መልአክ እንደ ክርስቶስ በሥልጣን ሲሠራ ይታያል:: ኢየሱስ በዮሐንስ 14:12 ያለውንና ሐዋርያው ጳውሎስም በክርስቶስ ኃይል ያደረገውን ያሳስበናል፣ ፊልጵ. 4:13:: ስለዚህ የክርስቶስ ኃይል ይህን መልአክ ኃይለኛ ያደረገው ይመስላል::

ለሺህ ዓመት በሰይጣን መታሰር ምክንያት ክርስቶስ በዲያቢሎስ ተበላሽቶ የነበረውን ፍጥረት ለሺህ ዓመት መንግሥት መለወጥና ለማደስ እንደሆነና ለመንፈሳዊ እድሳት የሆነ ይመስላል:: ደግሞ ሰይጣን ሳይታሰር ሺህ ዓመት ከክርስቶስ ጋር በሰላም መንገሥ የት ይኖራል? እንዴትስ ይሆናል? የሚገርመው ነገር በክርስቶስ ሺህ ዓመት መንግሥት ጊዜ ሰይጣን አንድም ጊዜ ስሙ ተጠቅሶ አናይም:: ሺህ ዓመት ሲፈጸም ግን ሰይጣን ከእሥር ይወጣል:: ከዚያም የሚያደርገውን ቁ. 7–10 አንብብ:: ሰይጣን ከእሥር ሲወጣ እግዚአብሔርን በመቃወም የሚያደርገውን ተመልከት:: ይህ ተቃውሞ የሰይጣን የመጨረሻ ተቃውሞ ነው:: ከዚያ በኋላ የሰይጣን መጨረሻ ይሆናል:: ቁጥር 3 ላይ ሰይጣን ለጥቂት ጊዜ ይፈታል ይላል:: ለምን እንደሚፈታ የሚያሳስቡ ሁለት ነገሮች አሉ::

1. ሰይጣን ሺህ ዓመት ታስሮ ጠባዩ የተለወጠ እንደሆነ ለማረጋገጥ:: ይሁን እንጂ ሺህ ዓመት ቀርቶ ከዚያ በላይ ቢሆን ጠባዩ አይሻሻልም፣ አይለወጥም፣ ንስሐም አይገባም::
2. በሰይጣን ላይ የመጨረሻ ፍርድ የፈረደው እግዚአብሔር እውነተኛ ጻድቅ እንደሆነ ያስመሰክራል::

እንዲሁም የሰው ክፉ ጠባይ እንደማይለወጥ እናያለን፣ ሮሜ 7:15–17፤ ራእይ 8:9:: በክርስቶስ ሺህ ዓመት መንገሥ ጊዜ ሰውና ሁሉም ነገር ተስተካክሎለት በሰላም ተገዛ፤ ያላመኑት ሁሉ ተገዙ:: ነገር ግን ሰይጣን ሲፈታ ሰው ቶሎ ብሎ በእርሱ ግዛት ለጦርነት ተከተተ:: በምድር ማዕዘን ያለው ሕዝብ እርሱን ይከተላል:: ዛሬ በመንፈስ ቅዱስ ልቡ ያልተለወጠ ሕዝብ ሁልጊዜም ያው ነው:: በክርስቶስ ሺህ ዓመት መንገሥ ልባቸው ባይለወጥም ይገዙለታል:: ሰይጣን ሲመጣ ግን እርሱን ይመርጡና ይከተሉታል:: የሰው ልብ ክፉ ነው፣ ኤር. 17:9–10::

## ቁ. 8 ስለ ጎግና ማጎግ

ስለ ጎግና ማጎግ በሕዝቅኤል 38 እና 39 በሰፊው ተጽፏል:: እነዚያ ቦታዎች ስለ ጦርነት ነው የሚያወሩት:: በዮሐንስ ራእይም በምድር ላይ በሰፊው ጦርነት እንደሚሆን ያወራል:: ስለዚህ ጎግና ማጎግ ጦርነት አንድ ጊዜ ሳይሆን፣ በዚያ ቦታ ሁለት እና ሦስት ጦርነቶች የሚሆን ይመስላል:: ለምሳሌ 1ኛው ወይም 2ኛው የዓለም ጦርነት እንደሚባል:: የመጨረሻ የጎግና ማጎግ ጦርነት በራእይ 20:8 ይሆናል:: የዓለምን ሕዝብ ሰይጣን ለጦርነት ያስከትታቸዋል:: ከጌታና ከተከታዮቹ ጋር ሲዋጋ ግን እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጠፋቸዋል:: የመጨረሻ ጦርነት ቦታ ነው:: እነዚህ ሙታን እንኳን በመጨረሻ በነጭ ዙፋን ፊት ለፍርድ መቅረባቸው አይቀርም፣ ቁ. 11 እና 12:: ይሁን እንጂ እንደ ሰዶምና ጎሞራ ይሆናሉ:: ከምድርም ይጠፋሉ:: ከጌቶች ጌታና ከነገሥታት ንጉሥ አፍ በወጣ ሰለታም ሰይፍ ይመታሉ:: ከሰማይ በሚወርድ እሳት ይጠፋሉ::

ቁ. 9 የቅዱሳንን ከተማ ሊዋጉ ከበቡ:: ለሰዎች የመጨረሻ የንስሐ ጊዜ እንኳን ቢሰጣቸውም መመለስ አልፈለጉም:: በአመጽ ላይ አመጽን፣ በኃጢአት ላይ ኃጢአትን መጨመር ይፈልጋሉ እንጂ:: ከዚህ ቦታ ሰዎች ከሰይጣን ጋር ሲሆኑ የመመለስና የንስሐ ልብ ሳይሆን፣ የእምቢተኝነትና የወንጀለኛነት ልብና አእምሮ እንደሚሞላባቸው እናያለን፣ ሮሜ 1:28–32:: ስለዚህ መጨረሻቸው እንደ ሰዶምና ገሞራ ይሆናል::

## ቁ. 10 የሰይጣን መጨረሻ

ሰይጣን ለእርሱና ለተከታዮቹ ወደ ተዘጋጀላቸው ወደ እሳት ባህር ተጣሉ፣ ማቴ. 25:41:: ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 12:31–33 የዚህ ዓለም ገዥ ተፈረደበት ያለው ጊዜ ደረሰ:: ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ ሰይጣን ተፈርዶበታል::

መንፈስ ቅዱስም መጥቶ ዓለምን ስለ ኃጢአት ሲወቅስ ሰይጣን ተፈረደበት ነበር፣ ዮሐ. 16:11 አሁን ግን በራእይ 20:10 ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ ሰይጣን አገኘ:: እግዚአብሔር እስከዚያ ድረስ ሰይጣንንና ክፉ መልአኩችን ያቆያቸው የእግዚአብሔር ዓላማና እቅድ እስኪፈጸም ድረስ ነበር::

ሰይጣን ወደ እሳት ባሀር ሲጣል ከዚያ ቀደም ብሎ የተጣሉት ሐሳዊ መሲሀና ሐሰተኛ ነቢይ ተጥለው ነበር። ኃያሉ እግዚአብሔር የርኩሳን ሥላሴን ዘንዶ፣ አውሬውን፣ ሐሰተኛ ነቢይን ሦስቱንም በኋላም በጌታ አምነው ያልጸኑት ሁሉ ወደዚያ ይገባሉ። ከዘላለም እስከ ዘላለም ይቃጠላሉ።

ራእይ 20፡4–6 የእግዚአብሔር መንግሥት ከክርስቶስና ከቅዱሳን ጋር

ከዚህ ምዕራፍ በቁጥሮች ከደረስንበት ወደ ኋላ ተመልሰን እንመለከታለን። ዮሐንስ የሰይጣንን ለሺህ ዓመት መታሰር ካየ በኋላ ዙፋኖችን አየሁ ይላል። በእነዚህ ቁጥሮች የክርስቶስን ሺህ ዓመት በምድር መንግሥ ይገልጻል። ይህም የሚሆነው ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመለስ ነው። ክርስቶስ ከቅዱሳኖቹ ጋር በምድር ሲነግሥ ስለሚመጣ ነው። የእግዚብሔር መንግሥት ከቅዱሳን ጋር የተባለው በዚህ በሺህ ዓመት መንግሥት በምድር ላይ ከክርስቶስ ጋር ምን ምን ነገሮች እንደሚሆን አንድ በአንድ ተዘርዝሮ ባይገለጽም እንኳ የጸጋ ዘመን መጨረሻ እንደሆነ እናያለን፣፡ ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ባለው በሁለቱ ምዕራፎች 21 እና 22 የዘላለም መንግሥት እንደሚሆን ይናገራል። በዚህ መንግሥት ክርስቶስ ለሺህ ዓመት በምድር ላይ ይነግሣል። ከዚህ መንግሥት ቀጥሎ የዘላለም መንግሥት ለእርሱ ይሆናል። «መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን...» ብለን የጸለይነው ጸሎት መልስ ይሆናል፣ ማቴ. 6፡10።

ከዚያን ጊዜ አንስቶ ለዘላለም የሰማይና የምድር ግዛት በሙሉ የሰውና የሰይጣን መሆኑ ቀርቶ የእግዚአብሔር ይሆናል።

እግዚአብሔር የምድርን አገዛዝ ከዘፍጥረት 1፡26 ጀምሮ ያለውን ዓይነት ግዛ፣ ንገሥ ሁሉን ሰጥቼሃለሁ ያለውን በብሉይ ኪዳን በሰፊው ማጥናት ይቻላል። ሰው ግን በተሰጠው ሥልጣን ሲወድቅና ሲያበላሽ እግዚብሔርንም ሲያሳዝን እንደ ነበረ ታሪክ ይመሰክራል፣ ዘፍጥ. 6፡5–7። ነገር ግን እግዚአብሔር ለመልካም አገዛዝ የሚበቃ ሰውና አምላክ የሆነ ልጁ እንዲሆን ስለ ወሰነ በኢሳ. 9፡6–7 በተጻፈው መሠረት መምጣት አስፈለገው። ስለዚህ ነቢያት ሁሉ ስለዚህ ስለሚመጣው ፍጹም መንግሥት እንዲህ እያሉ በብዙ ከጻፉት በጥቂቱ እንጥቀስ፡–

ኢሳ. 2፡2–4 ከዳዊት ቅርንጫፍ ቁጥቋጦ ተነስቶ በሰላም እንደሚገዛ
ኤር. 23፡3–6 ተመልከት።

ዳንኤልም 2፡44–45 የሚነሳ የሰማይ መንግሥት ተጠቅሷል። እንዲሁም ስለ ዘላለም መንግሥት ትንቢት ዘካ. 12፡10–14፡21 ተመልከት። እነዚህና የመሳሰሉትን የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ስንመለከት ራእይ 20፡4–6 ያለውን የክርስቶስን ሺህ ዓመት መንግሥ እውነት ያደርገዋል።

## የክርስቶስን ለሺህ ዓመት መንግሥ መከድ

በመጽሐፍ ቅዱስና በጌታ ዳግም መምጣት የሚያምኑት ስለ ጌታ መመለስ በሦስት ይከፈላሉ።

1. Amillennialism (ኤ ሚሊኒዝም) ይባላሉ። እምነታቸው ጌታ መጥቶ በምድር ላይ ለሺህ ዓመት አይነግስም። ይህ ሺህ ዓመት አባባል ምሳሌያዊ አነጋገር ነው እንጂ እርግጠኛ አይደለም ይላሉ።
2. postmillennialism (ፖስት ሚሊኒዝም) ይባላሉ። እምነታቸው ክርስቶስ ወደ ምድር የሚመጣው ሺህ ዓመት ካለፈ በኋላ ነው ይላሉ። ሺህ ዓመት በምድር ላይ ሰላም ጸጥታ ጥሩ አገዛዝ ይሆናል። ይህም የሚሆነው እኛ በርትተን ወንጌልን ከሠራን ነው። ከዚያ በኋላ ጌታ ዳግም ይመለሳል ይላሉ።
3. premillennialism(ፕሪ ሚሊኒዝም) ይባላሉ። እነዚህ የሚያምኑት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እምነት ይመስላል። እርሱም ጌታ ድንገት ባየር ላይ ይገለጥና ቤተ ክርስቲያንን ይወስዳል። ከዚያም 7 ዓመት የመከራ ዘመን ይሆናል። ከ7 ዓመት የመከራ ዘመን በኋላ ጌታ ወደ ምድር ይመለሳል። ሺህ ዓመት በምድር ላይ ይነግሣል። ከዚያም መንግሥቱ የእርሱ ይሆናል። ሰይጣን ይታሠራል። ከሺህ ዓመት በኋላ ሰይጣን ይለቀቅና ጦርነት ይደረጋል፤ ፍርድ በእርሱና በተከታዮቹ ላይ ይሆናል ይላሉ።

ይህ የራእይ መጽሐፍ ትርጉምም በዚህ በሦስተኛው ዓይነት እምነት የተተረጐመና የተቀመጠ ነው። እኔም ይህን አምናለሁ። ጌታ ለሺህ ዓመት በምድር ሊነግሥ ይመጣል። ከሺህ ዓመት መንግሥት በኋላ በምድር ላይ የመጨረሻ ፍርድ ይሆናል።

## የሺህ ዓመት የክርስቶስ መንግሥት ምን ይመስላል?

ምን እንደሚመስል በዮሐንስ ራእይ በግልጽ ባይጻፍም እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ዘመን የተጻፈውን እናንብብ። ለምሳሌ ኢሳ.2:2–4፤ 11:3–5 ተመልከት። በታውም ጽዮን ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነግሥባት ከተማ ኢየሩሳሌም ይሆናል። ግዛቱና መንግሥቱ የኢየሱስ ይሆናል፣ ዘካ. 14:9–11።

ራእይ 20:1–3 በክርስቶስ ሺህ ዓመት መንገሥ ጊዜ

1. ፍጹም ሰላም የሞላበት መንፈሳዊ ቁጥጥር ይሆናል። ጠላት ሰይጣን በጥልቅ ጉድጓድ ታስሮ ስለተዘጋበት አካባቢውን የሚያውክ እንቅፋት አይኖርም፣ ዘካ. 14:16–17 ተመልከት።

2. ፍጹም የሆነ የሞራል እረፍት የተሞላበት ቁጥጥር ይሆናል። ክርስቶስ የሰላም ገዢ ስለሆነና የጌታ ተከታዮች የመንግሥቱ ገዢዎች ይሆናሉ። ስለዚህ መዝ. 2:6–9፤ መዝ.(72):8–11 እንኳን ምድርና ሰማይ ይባረካሉ፣ ራእይ 12:5፤ 19:15።

ቁ. 4–6 ዙፋኖች የሚለው ለነማን ነው?

ኢየሱስ ከእኔ ጋር ትነግሣላችሁ ብሎ ተስፋ የሰጣቸው:–

1. ቤተ ክርስቲያንን ነው፣ ራእይ 2:26፣ 27፤ ምሳሌ 3:21፣
2. የዳኑት የእሥራኤል ቤተሰብን ነው፣ ማቴ. 19:27–28፣
3. የብሉይ ኪዳን ቅዱሳንን ነው፣ ኢሳ. 1:25–26፣
4. በመከራው ዘመን የአውሬውን ምልክት ያልወሰዱትንና ለጌታ ስም የተገደሉትን ሁሉ፣ ቁ. 4 ተመልከት።

እነዚህ ሁሉ ከጌታ ጋር ለሺህ ዓመት ይነግሣሉ። የሰላም መንግሥት ይሆናል፣ መዝ. (72):1–7)።

3. ፍጹም ሥጋዊ ዕረፍት የሞላበት አካባቢ ይሆናል፣ ኢሳ.11:6–9 ደግሞ ኢሳ. 35:1–2።

ቁ. 5–7 ሚክያስ 4:4–5 አሞጽ 9:13፤ ዘካ. 10:1 እነዚህ ቁጥሮች የሚያሳዩት ክርስቶስ ሺህ ዓመት ሲነግሥ ብቻ ሊሆን የሚችል ጸጥታና ሰላም ለዓለም ይሆናል። ፍጥረት ሁሉ ያቺን ጊዜ ይጠባበቃል፣ ሮሜ 8:9–23። ኢየሱስ በምድር ላይ ሺህ ዓመት እንደሚነግሥ

በዚሁ መጽሐፍ ስድስት ጊዜ ተደጋግሞ ይናገራል። ስለዚህ የመንገሡ ዘመን ልክ በግልጽ የታወቀ ነው።

ቁ. 5–6 ራእይ 20፡5–6 ስለትንሣኤ ይናገራል። ስንት ትንሣኤ አለ?

ኢየሱስ በዚህ ምድር በሥጋው በነበረ ጊዜ ስለ ጻድቃን ትንሳኤ በብዙ ተናግሯል። ሉቃስ 14፡14፤ ዮሐ. 5፡28–29 እንዲሁም ራእይ 20 ላይ በሰፊው እናገኛለን።

1ኛ ትንሣኤ የክርስቶስ የራሱ ትንሣኤ ነው። ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኵር ሆኖ ተነስቷል ይላል፣ 1 ቆሮ. 15፡20፤ ሮሜ 6፡9።

2ኛ ትንሣኤ የመነጠቅ ጊዜ የሚሆን የአማኞች ትንሣኤ ነው፣ 1ኛ ተሰሎ. 4፡16። በክርስቶስ የሞቱት አስቀድመው ይነሳሉ። ይህ ትንሣኤ ሳይባል የቤተ ክርስቲያን በአየር ላይ መነጠቅ ይባላል። በአየር ላይ ከጌታ ጋር ይገናኛሉ፣ 1ኛ ተሰሎ. 4፡13–18።

3ኛትንሣኤ በዮሐንስ ራእይ 20፡6 ላይ ያለው ከክርስቶስ ጋር ሊነግሡ የሚነሱ የመከራ ዘመን ቅዱሳኖች ትንሣኤ ነው። ይህ ትንሣኤ ፊተኛው ትንሣኤ ተብሏል። ይህን ትንሣኤ ያገኙት ለሺህ ዓመት ከክርስቶስ ጋር በምድር ይነግሣሉ። እነርሱም የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ። በእነዚህ ትንሣኤ በጌታ ያላመኑት አይነሱም። መጽሐፉ የክርስቶስ ሺህ ዓመት መንግሥት በምድር ላይ እስኪፈጸም ድረስ የቀሩት ሙታን በሕይወት አልኖሩም ይላልና።

4ኛ ትንሣኤ በጌታ ያላመኑት ከሺህ ዓመት መንግሥት በኋላ በነጭ ዙፋን ፊት ለፍርድ ሊቆሙ የሚነሱት ትንሣኤ ነው፣ ራእይ 20፡12–15። ዮሐ. 5፡29፤ በ3ኛ ትንሣኤና በ4ኛ ትንሣኤ መካከል ሺህ ዓመት ልዩነት አላቸው ማለት ነው።

ቁ. 6 ስለ ሁለተኛው ሞት ይናገራል። ይህን ሁለተኛ ሞት ምዕ. 21፡8 ተመልከት፤ምዕ. 20፡14 ። በጌታ የማያምኑትን የሚጠብቅ የእሳት ባህር ነው፣ ምዕ. 20፡15።

## በክርስቶስ ሺህ ዓመት መንግሥት የሚከፈሉት

1. ወደ ሰማይ የተነጠቀች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ ራእይ 2፡26–27፤ 3፡21። ዙፋኖች ተዘርግተው ዳኝነት ይሰጣቸዋል። በሌሎች ላይ የምንፈርድ እንሆናለን፣ 1 ቆሮ. 6፡2–3። እንዲሁም 2 ጢሞ. 2፡12 ከእርሱ ጋር መከራ ብንቀበል ከእርሱ ጋር እንነግሣለን ይላል። ያኔ የተስፋ ቃሉ ይፈጸማል።

2. በመከራ ዘመን ስለ ክርስቶስ ስም የአውሬውን ምልክት በእጃቸውና በግምባራቸው አንቀበልም ብለው የሚታረዱ ቅዱስ ይሆናሉ::

3. በመከራ ዘመን ወደ ጌታ የተመለሱት አይሁዶች

4. በመከራ ዘመን ወደ ጌታ የተመለሱት ከአህዛብ ወገን

5. የብሉይ ኪዳን ዘመን ቅዱሳን በመንግሥቱ ተካፋዮች ይሆናሉ::

## ቁ. 11–15 የእግዚአብሔር መጨረሻ ፍርድ ባላመኑት ላይ

በዕብራውያን 9:27 ላይ ለሰው እንደ ተመደበ ይሞቱ ዘንድ ከሞት በኋላ ፍርድ ተመድቦባቸዋል ይላል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሰባት ዓይነት ፍርድ ይናገራል::

1. በኃጢአት ምክንያት በአዳም ላይ የተላለፈው ፍርድ፣ ዘፍጥ. 3:23–24::

2. ክርስቶስ ለዓለም በመስቀል ላይ የወሰደው ፍርድ ነው፣ 2ቆሮ. 5:21::

3. ክርስቲያኖች በየዕለቱ በራሳቸው ላይ የሚፈርዱት ፍርድ፣ 1 ቆሮ. 11:3132:: ከዚያም ንስሐ ሲገቡ ይነጻሉ፣ 1 ዮሐ. 1:9::

4. በእሥራኤል ልጆች ላይ የሚሆን ፍርድ በራእይ 20 ስለ ፍርድ ስናጠና እንመለከታለን::

5. የክርስቲያኖች የሥራቸው ፍርድ ጊዜ ይሆናል፣ 1 ቆሮ. 5:10፤ 3:12–15::

6. በአህዛብ ላይ የሚሆን ፍርድ በመጨረሻው ዘመን፣ ማቴ. 25:31–46:: የእግዚአብሔርን ሕዝብ እሥራኤል ምን እንዳደረጉ፣ ክርስቲያንን ምን እንዳደረጉ፣ ክርስቶስን ምን እንዳደረጉ ሁሉ ወደ ፍርድ ይመጣል::

7. በዮሐንስ ራእይ 20:11–15 ላይ ያለው የነጭ ዙፋን ፍርድ ነው:: ይህ ዓይነት ፍርድ ከዚህ በፊት ሆኖ አያውቅም:: ምክንያቱም የአሁኑ ዳኛ በነጭ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ታይቷልና ነው:: በዚህ ጊዜ ክርስቲያኖች ፍርድ አይኖርባቸውም:: ምክንያቱም ክርስቲያኖች የሥራቸውን ፍርድ ከዚህ በፊት በሰማይ ተቀብለዋልና ዋጋቸውንም ተቀብለዋልና:: ይህ ፍርድ ግን ያላመኑት የሚቀበሉት

የመጨረሻ ፍርድ ነው። ሙታን ሁሉ ለፍርድ ይነሳሉ፣ ኢዮብ 14፡14። ሰው ከሞተ በኋላ በውኑ ይነሳልን? ብሎ ይጠይቃል። መልሱ አዎን ነው።

ቁ. 11 ታላቅና ነጭ ዙፋን

ይህ ታላቅና ነጭ ዙፋን የሚመስል ስፍራ የትም አይገኝም። ዮሐንስ ይህንን ነጭ ዙፋን ነው አየሁ የሚለው። ይህ ዙፋን ልዩ ነበረ። ልዩ የሆነበት ምክንያት በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ልዩ ነበረ። ከፊቱ ሰማይና ምድር ሸሽተው ሄደው ቦታው በባዶ አየር ላይ ነበረ። በዙፋን ላይ የተቀመጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነበረ፣ዮሐ. 3፡3–5።

ይህ ነጭ ዙፋን በመልካም ተግባር የሚያመልጡበት ቦታ አይደለም። ምክንያቱም በዙፋኑ የተቀመጠ እግዚአብሔረ የተከፈተ መጽሐፍ እያሳየ በተግባር ያደረግኸው ለደህንነት በቂ አይደለም የሚልበት ቦታ ነው። በዙፋኑ የተቀመጠው ጻድቅ እውነተኛ ፈራጅ የሆነ፣ ሁሉን ቻይ የሆነ እግዚአብሔር ነው። የፍርዱ ዙፋን ታላቅ የሚሆንበት ሌላ ምክንያት ቅዱሳንና ጻድቃን ሎራዊት በዙሪያው ስለሚሆኑ ነው። የዚህ ፍርድ ውጤት ለዘላለም ወደ ገሃነመ እሳት ባህር ለመጨረሻ መጣል ስለሚሆን ታላቅ ነው። ማምለጫ ስለማይገኝ፣ ዕብ. 2፡3።

ዙፋኑ ነጭ የሆነበት ምክንያት ፈራጁ ቅዱስና ጻድቅ ፍጹም ንጹሕ እንደሆነ ያሳያል። ደግሞ ሰው በኃጢአት የተበላሸ ጨለማ መሆኑን ይገልጻል። ስለዚህ በታላቁ ዙፋን ፊት መቆም አይችልም። ሌላ ዙፋኖች እንዳሉ ማሰብ አለብን። ዮሐንስ ያየው የዘላለም ግዛት ዙፋን ነበረ፣ ራእይ 4፡22። ደግሞ ድል አድራጊዎች ሲቀመጡ ተስፋ የተሰጣቸው ዙፋንም አለ ራእይ 3፡21። ደግሞ የበጉ ዙፋን የተባለው አለ፣ ምዕ. 22፡3። እንዲሁም ዳኛው የሚቀመጥበት ዙፋን የክብር ዙፋን ተብሏል፣ ማቴ. 25፡31። የዮሐንስ ራእይ ዙፋን የክብር ዙፋን ነው። ዓለም ከተፈጠረበት ጀምሮ ያለው ያላመነ የሰው ዘር የሚፈረድበት ዙፋን ነው። በዚያ የዓለም ነገሥታት ነበርን የሚሉ ሁሉ፣ ገገር ነበርን የሚሉ ሁሉ፣ ታላላቅ ሰዎች ነበርን የሚሉ ሁሉ ፍርዳቸውን ይቀበላሉ። በዙፋኑ ፊት ለፍርድ ይቆማሉ፣ ማምለጫ የላቸውም።

ቁ. 11 ዳኛው ክርስቶስ ነው፣ ዮሐ. 5፡22፤ የሐዋ. ሥራ 17፡31፤ 2ጴጥ. 3፡10። ፈራጅ ኢየሱስ ነውና ጉልበት ሁሉ ለእርሱ በግድ

ይንበረከካል፣ ፊልጵ.2፡6–11። ታላቁ ነጭ ዙፋን የምህረት መሆኑ ቀርቶ የፍርድ ዙፋን ይሆናል፣ዮሐ. 3፡36፤ ዳን. 7፡9–11 ያለው ትንቢት ይፈጸማል።

ቁ. 12 ስለሞቱ

ስለ ሞቱ ሙታን ይናገራሉ። ሦስት ዓይነት ሞት እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

1ኛ ሞት በኃጢአት ውስጥ መግባት የእግዚአብሔር ትእዛዝ መተላለፍ አንደኛው ሞት ነው። አዳም በኃጢአት በወደቀ ቀን ሞተ። መንፈሳዊ መለየት ነው። ከእግዚአብሔር ሕብረት ተለየ፣ ዘፍጥ. 3፡3፤ 2፡16–17፤ ኢሳ. 59፡2፤ ኤፌ. 2፡1። በአባታችን በአዳም ምክንያት እኛ ሁላችን ተለየን፤ ሞትን፤ ሮሜ 5፡12–14። መንፈሳዊ ሞት ነው።

2ኛው ሞት ሥጋዊ ሞት ነው። ሥጋና ነፍስ ስትለያይ ሥጋ ወደ መቃብር ሲሄድ፣

3ኛው ሞት ነፍስ በጌታ ፊት ፍርድ ስትቀበል። ወደ ገሃነመ እሳት ስትጣል። ይህን ሞት መጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛ ሞት ይለዋል፣ ራእይ 20፡6–14 ምዕ. 21፡8። ይህ ሞት በጌታ በኢየሱስ አናምንም ብለው ጌታን የናቁትና የጠሉት የሚገቡበት የመጨረሻ ሥፍራ ነው። በዳንኤል 12፡2 በእፍረት ትንሳኤ ይላል። በሐዋ.ሥራ 2፡15 የአመጸኞች ትንሣኤ ይላል። እዚያ ይደርሳሉ፤ ጌታ ኢየሱስንም ያላመኑት ለፍርድ ትንሣኤ ይነሳሉ አለ፣ ዮሐ. 5፡29።

ቁ 13 ሐዋርያው ዮሐንስ ሲያይ ሙታን ለፍርድ የሚነሱ ነበር። ያላመኑት ከየት እንደመጡ ሲናገር ባህርም በእርሱ ያለውን ሙታን ሰጠ፣ ሞትም በእርሱ ዘንድ ያለውን ሙታን ሰጠ። ሲዖልም በእርሱ ያሉትን ሙታን ሰጠ፣ ለሁሉም እንደሥራቸው መጠን ተከፈለ ተፈረደ። ሰው ሞቶ በስብሶ የተረሳ ይመስላል። ግን እግዚአብሔር አይረሳውም። ሞት ቢሆን፣ ሲዖል፣ ባህርም ቢሆን ሌላም ለጌታ ይታዘዛል። ሙታንን ይሰጣል። ከጌታ ማምለጫ አይገኝም። ማምለጫው ዛሬ በሕይወት እያለን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ከእርሱ ጋር መታረቅ ብቻ ነው።

## ሞትና ሲዖል

ሞት ነፍስና ሥጋ ተለይቶ ሥጋ ይሞታል ይበሰብሳል። ሲዖል ነፍስ ከሥጋ ተለይቶ የሚቀመጥበት ሥፍራ ነው። በጌታ ያላመነ ነፍስ የሚቆይበት አስቃቂ ሥፍራ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት እስኪነሳ ድረስ ሲዖል በሁለት ይከፈል ነበር። 1ኛው ሲዖል የቅዱሳን ነፍስ የሚቆይበት ወይም የሚያርፍበት ላይኛው ሲዖል ይባል ነበር። እንደ ገነት ማረፊያ ነበር። አብርሃምና ድሃው አልአዛር በዚያ ነበሩ። 2ኛው ሲዖል ወይም ታችኛው ሲዖል የኃጢአተኞች ነፍሳት የሚቆዩበት የሥቃይ ሥፍራ ነው። በዚያ ባለ ጸጋው (ሐብታሙ) ሰው በእሳት ነበልባል ይሰቃይ ነበር፣ ሉቃስ 16:19–31። በላይኛውና በታችኛው ሲዖል መካከል መገናኘት እንደማይቻል ትልቅ ገደል ነበር። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ በሞተ ጊዜ ነፍሱ ወደ ሲዖል ሄዶ ሰበከ፣1ጴጥ. 3:18–19። ክርስቶስ ከሞት በተነሳ ጊዜ ግን በላይኛው ሲዖል ወይም በእረፍት ስፍራ የነበሩትን ምዕመናን ማለትም እነ አብርሃምን ይዞ ተነሳ። ምርኮ ማረከ። ከእርሱ ጋር ወሰደ፣ ኤፌ. 4:8–10። ኢየሱስም እንዲህ አለ፣ ራእይ 1:18 ከዚያ በኋላ የአማኞች ነፍስ ወደ ጌታ ይሄዳል፣ ፊልጵ. 1:23፤ 3:20፤ 2 ቆሮ. 5:1–5። ቤታችን በሰማይ ነው። እስጢፋኖስ ሲሞት ወደ ሰማይ ሄደ፣ የሐዋ. ሥራ 7:55–56። ከዚያን ጊዜ አንስቶ የቅዱሳን ነፍስ ወደ ሰማይ ወደ ጌታ ይሄዳል።

ያላመኑት ሰዎች ነፍስ ግን እስከ ነጩ ዙፋን ፍርድ ጊዜ ወይም እስከ ሙታን ትንሣኤ በሲዖል ይቆያል። ለመጨረሻው ፍርድ ከዚያ ይወጣል ወይም ይነሳል። ከነጩ ዙፋን ፍርድ በኋላ ወደ እሳት ባህር (ገሃነመ እሳት) ይገባሉ፣ ይጣላሉ።

## ቁ. 12 የፍርድ መጻሕፍት መከፈት

እነዚህ መጻሕፍት አንዱ የሕይወት መጽሐፍ ሲሆን፣ ሌላው በሕይወት ዘመናቸው ያደረጉትን የሥራ መጠን የሚገልጽ ነው። ማንም በክርስቶስ ቢሆን ኩነኔ የለበትም፣ ሮሜ 8:1። ኢየሱስም እንዲህ አለ፣ በእኔ ያላመነ አሁን ተፈርዶበታል፣ ዮሐ. 3:18–36። ኢየሱስ እኔ አልፈርድባችሁም ነገር ግን ከእኔ የሰማችሁት ቃል እርሱ ይፈርድባችኋል። በእኔ ማመን እምቢ ስላላችሁ፣ ዮሐ. 12:47–48።

አንድ ሰው ወደ እዚህ ምድር በሚወለድበት ጊዜ ስሙ በሕይወት መጽሐፍ እንደሚጻፍና በምድር በሚኖርበት ዘመን ሁሉ ጌታን ሳይቀበል እምቢ ሲል በመጨረሻው ስሙ ከሕይወት መጽሐፍ የሚፋቅ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምር ይመስለኛል፣ ዘጸ. 29:20:: በሞት ጊዜ የእርሱ ስም በሕይወት መጽሐፍ ሳይኖር ሲቀር ይታያል:: በዚህ ምክንያት ፍርድ ይደርስበታል:: ለጌታ ኃጢአቱን ስላልተናዘዘ ኃጢአቱ ያገኘዋል፣ ዘኍ. 32:23:: ኃጢአቱን ለጌታ ቢናዘዝ ይለማል:: ቢደብቅ ግን አይለማም፣ ምሳሌ 28:13:: መጻሕፍቱ በሚከፈቱበት ጊዜ እንኳን በልብና በሃሳብ ውስጥ የተደበቀ ኃጢአት እንኳን ቢሆን ይታያል፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ወንድሙን በልቡ የሚጠላ እንኳን ነፍሰ ገዳይ ነው፣ 1ዮሐ. 3:15:: ወደ ሴት አይቶ የተመኘ አመንዝራ ነው፣ ማቴ. 5:28:: በታላቁ ነጭ ዙፋን ፊት ኃጢአትን መደበቅ አይቻልም:: ዛሬ የክርስቶስ ደም ኃጢአትን እንደሚደመስስ በእምነት ካልተቀበልን ወዮ፣ 1 ዮሐ. 1:7–9::

ያላመኑት ሰዎች ሥራ የሚገልጽ መጽሐፍ ለእያንዳንዱ አላቸው:: አንዱ መጽሐፍ የሕይወት መጽሐፍ ሲሆን ሌላው ደግሞ በሕይወታቸው ዘመን ያደረጉትን ሥራ የሚገልጽ ነው:: ሁሉም እያንዳንዳቸው እንደ ሥራቸው መጠን ይከፈላቸዋል:: የአንተስ ሥራ እንደምን ይሆን? ክርስቶስ ለአንተ የሠራውን ካልተቀበልክ አንተም ከፍርድ አታመልጥም:: ክርስቶስ ይወድሃል፣ እርሱ ሊያድንህ መጣ፣ ዮሐ. 3:16:: አንዳንድ ሰው በሥራዬ እድናለሁ ይላል:: ይህ አይሆንም:: በጌታ ፊት፣ኢሳ. 64:6፤ ሮሜ 3:23፤ ገላ. 2:16–21:: ጽድቅ በሥራ አይገኝም ይላል:: መዳን በእምነት ነው:: በአንተ መጽሐፍ ውስጥ ምን ተጽፎ ይሆን? በደል ይሆን? ኃጢአት ይሆን? ወይም በክርስቶስ ደም የታጠበ ንጹህ የሆነ የደህንነት ሥራ?

## ቁ. 13–14 የፍርድ መጠን

በዚህ ቦታ ሁሉም እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈላቸው ይላል:: ምናልባት አንድ ጥያቄ በልብህ ይመጣ ይሆናል:: የጌታን ቃል ያልሰሙት እንዴት ይፈረድባቸዋል? የሚል ይሆናል፣ ሮሜ 2:11–12:: ሕግ ያላቸው እንደ ሕግ፣ የሌላቸው ያለ ሕግ ይፈረድባቸዋል:: መጠኑ የሚበዛም አለ፣ ማቴ. 11:21–23፤ ሉቃስ 20:46–47:: የፍርድ ልዩነት መኖሩን አስታውስ፣ ሉቃስ 12:47–48::

ቁ. 14 ስለ ፍርድ

በታላቁ ነጭ ዙፋን ፊት የሚሰጠው ፍርድ ሁለተኛው ሞት ነው:: ቅጣቱ የዘላለም ጥፋት ነው:: በጌታ ፊት የሚደርሰው 2ኛ ተሰሎ. 1:9 ወይም ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለዘለዓለም ሥቃይ መቀበልና መጥፋት ነው:: ኢየሱስም መፍራት ወደ ገሃነም የሚሰደውን ነው አለ፣ ሉቃስ 12:5:: የጥፋት መሣሪያ ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ ዕብራውያን 10:30–31 ተመልከት:: ዕብ. 12:29 አምላካችን የሚባላ እሳት ነው:: ሞትና ሲዖልም ይቀጣሉ::

ቁ. 15 የእሳት ባህር የዘላለም ቅጣት ቦታ ነው:: በዘላለም እሳት ባህር የሚገቡት እረፍት በጭራሽ አያገኙም:: ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ፣ ምዕ. 20:10፤ ማቴ. 25:46:: ሰው ሁሉ ራሱን መጠየቅ አለበት:: እኔስ ከእግዚአብሔር ፍርድ አመልጣለሁ ወይ ብሎ? መልሱ አዎን ዛሬ በጌታ ብታምንና እርሱን ብትከተል ታመልጣለህ፣ዮሐ. 1:12:: የእግዚብሔር ልጅ ሁን፣ ዮሐ. 11:25–26:: እኔ ሕይወትና ትንሣኤ ነኝ፣ የሚያምንብኝ ቢኖር ይድናል፣ ዮሐ. 5:24:: ባመንክበት ቀን ከሞት ወደ ሕይወት ትሻገራለህ:: ስለዚህ ዕድልህ በዚህ ዓለም በሕይወትህ ሳለህ ብቻ ነው:: ከሞትህ በኋላ ምንም ማድረግ አትችልም፣ አይፈቀድልህም፣ ዕብ. 9:27:: ጌታን የመቀበል ጊዜ ሰዓቱ አሁን ነው፣ ምሳሌ 29:1:: ድምጹን ስትሰማ ልብህን አታጠንክር ወደ ጌታ ና፣ ዕብ. 3:7–8፤ ምዕ. 2:3::

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 21

## ለዘላለም መኖር ተገለጸ

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 21 ላይ እግዚአብሔር ለዘለዓለም መኖርን በፊታችን ግልጽ ሲያደርግ እንመለከታለን። በዚህ ምዕራፍ ቁልፍ የሆነው 5 ቁጥር ነው። «እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ» የሚል ነው። በዚህ ምዕራፍ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ ያለው ነገሮች የሚቀጥሉ ናቸው። አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፣ አዲስ ኢየሩሳሌም በሰውና በእግዚብሔር መካከል አዲስ ሕብረትና ግንኙነት፣ ለዳኑት ሰዎች አዲስ የምቾት ሁኔታ፣ አዲስ የዘለዓለም ቤት፣ ለሙሽራው አዲስ ክብር፣ አዲስ መቅደስ፣ አዲስ ብርሃን፣ አዲስ ፍጹም የሆነ ሕይወትና አዲስ የመኖር ዘዴዎች ናቸው።

ቁ. 1–2 በዚህ በሁለቱ ቁጥሮች ከእነዚያ አዲስ ነገሮች ሦስቱ ተጽፈዋል። እነርሱም አዲስ ሰማይ፣ አዲስ ምድርና አዲስ ኢየሩሳሌም ናቸው።

### ቁጥር 1 <u>አዲስ ሰማይ</u>

በዚህ ቦታ ላይ ዮሐንስ አዲስ ሰማይን አየሁ ይላል። ፊተኛው ሰማይ አልፏል ይላል። በመጽሐፍ ቅዱሳችን በመጀመሪያው መጽሐፍ ማለት በዘፍጥ. 1፡1 ላይ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ይላል። ይህ ሰማይ የተባለው ምን እንደሆነ እንድናስታውስ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰማይን በሦስት ይከፍላል። ወይም ሦስት ሰማይ እንዳለ ይናገራል፣ 2 ዜና. 2፡6።

1ኛው ሰማይ ጠፈር ይባላል።

ቀዝቃዛ አየርና ውኃ ያለበት ጠፈርን እግዚአብሔር ሰማይ አለው፣ ዘፍ.1፡6–8። በኖኅ ዘመን በጥፋት ውኃ ጊዜ የሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ፣ ዝናቡም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በምድር ላይ ሆነ፣ ዘፍ. 7፡11። እንደገና የሰማይ መስኮቶች ተደፈኑ፣ ዘፍ. 8፡1። ለኛ ለመሬታችን ቅርብ ዙሪያ የሆነ ጠፈርን ሰማይ ሲል፣ አንደኛ ሰማይ መሆኑን እናስብበት።

2ኛው ሰማይ በዘፍጥ. 1፡14 በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይሁን አለ።

እግዚአብሔር አብርሃምን ወደ ሰማይ ተመልከት፣ ከዋክብትንም ልትቆጥራቸው ትችል እንደሆነ ቁጠር አለው። ዘፍጥ. ~~15፡5፤~~ መዝ.

8:3 የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ ጨረቃንና ከዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን ይላል። ከዋክብትና ጨረቃ ፀሐይ ያለው ሁለተኛው ሰማይ መሆኑን እንድናስታውስ ይገባል።

3ኛው ሰማይ መጽሐፍ ገነት ይላል

ጳውሎስ ስለዚህ 3ኛ ሰማይ ወይም ገነት ያለውን ተመልከት፣ 2ቆሮ. 12:2–4። ንጉሥ ሰለሞን በጸለየ ጊዜ ሦስቱን ሰማይ ጠቅሷል። እንዲህ እያለ፣ እነሆ ሰማይ ከሰማይም በላይ ያለው ሰማይ አለ፣ 2 ዜና 6:18 ተመልከት። ይህ ሦስተኛው ሰማይ የልዑል እግዚአብሔር ዙፋን መሆኑ ነው። ኢየሱስም ስትጸልዩ የሰማይ አባታችን ብላችሁ ጸልዩ አለ፣ ማቴ. 6:9። ሦስተኛው ሰማይ የእግዚብሔር ከተማ መንግሥተ ሰማያት ነው። ስለዚህ ራእይ 21:1 ስለ ሦስተኛው ሰማይ ሳይሆን ሰማይና ምድር አልፈዋል ያለው ሌሎች እንደሆኑ ከራእይ ምዕራፍ 6 እስከ ምዕራፍ 19 ያለውን በጥናታችን ማስተዋል እንችላለን። ጴጥሮስም 2 ጴጥ 3:10–13 ስለዚሁ በእሳት እንደሚያልፉ ተናግሯል። ዳዊት በመዝሙር (102):25 ላይ ስለ ሁለቱ ሰማይ ሲናገር «ሰማያት የእጅህ ሥራ ናቸው፤ እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ» ይላል። ራእይ 20:11፤ ኢሳ. 65:17 እግዚአብሔር የሚለውን ስሙ። እግዚአብሔር አንደኛውን ሰማይ የሚያጠፋው የሰይጣን ዙፋን ያለበት ስለሆነ ነው፣ ኤፌ. 6:11–12፤ ዮሐ. 14:30። ስለዚህ በእሳት ያልፋል፣ 2ኛ ጴጥ. 3:6–7። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል ሰማይ ያልፋል ስላለ ሰማያት ያልፋሉ የምንለው።

ቁ. 1 <u>አዲስ ምድር</u>

ዮሐንስ አዲስ ምድርን አየሁ ይላል። የፊተኛው ምድር አልፏል። ይህ የፊተኛው የተባለው በዘፍ. 1:1 የተፈጠረውን ነው። ዳዊት በመዝ. (104):5 እንዳትናወጥ ምድርን መሥርተሃል ሲል ስለ አዲስ ምድር የሚናገር ይመስላል። እንደዚህ ባይሆን ምድር አልፎ አየሁ አይልም ነበር። በዘፍጥ.1:2 ምድርም ባዶ ነበረች፣ አንዳችም አልነበረባትም ሲል ምድርን ባዶ ያደረገው የሉሲፈር (የሰይጣንና የሠራዊቱ) መውደቅ ነው።

1. የእርሱ መውደቅ ምድርን አበላሸ
2. በአዳም ምክንያት ምድር በተረገመች ጊዜ ምድር እሾህና አሜከላ እንድታበቅልተረገመች።

አዳምን በላብህ ወዝ እንጀራ ትበላለህ፣ ወደ ተፈጠርክበት ምድር ትመለሳለህ፤ ስለ አንተ ምድር የተረገመች ትሁን፣ ዘፍጥ. 3፡17–19። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ሮሜ 8፡22–23 በዚህ ምድር ስንኖር እንቃትታለን ያለው። ነገር ግን ጌታ በምድር ሺህ ዓመት ሲነግሥ የምድር ለውጥ ይጀምራል። የተሰጠንን ተስፋዎች አንብብ፤ ኢሳ. 35፡1፤ 55፡12–13። ሐዋርያው ዮሐንስ ሲመለከት ግን ያልፍ ነበር፣ ራእይ 20፡11 ምዕ. 21፡1። ጴጥሮስም 2ኛ ጴጥ. 3፡7–10። ጳውሎስም በዕብ. 1፡10–12፤ ቆላ. 1፡17 ሁሉ በእርሱ ተጋጥሟል አለ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሁሉን ሊያድስ ሁሉን ያጠፋል፣ ኢሳ. 65፡17።

## ቁ. 2 <u>አዲስ ኢየሩሳሌም</u>

ስለ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሐዋርያው ዮሐንስ እግዚአብሔር በራእይ ያሳየውን ይገልጽልናል። ቅድስቲቱ ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባሏ እንደ ተዘጋጀች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ስትወርድ አየሁ ይላል። ይህች ከላይ የምትወርድ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አሁን በምድር ካለችው ኢየሩሳሌም ልዩ ነች። በመከራ ዘመን ከምትሠራዋ ኢየሩሳሌም የተለየች ነች። በመከራ ዘመንና ጊዜ ኢየሱስ ሺህ ዓመት ሲነግሥ የምትኖረዋ ኢየሩሳሌም በራእይ 11፡8 ላይ ሰዶምና ግብጽ ተብላለች። ከሰማይ የምትወርደዋ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ግን ኢየሱስ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ ያለው፣ ለሙሽራው የተዘጋጀች ከሰማይ የምትወርድ ነች፣ ዮሐ. 14፡2–3። አንድ ሰው እንዳለው አዲሲቷ ኢየሩሳሌም የተዘጋጀችው ለሰማይ ለተዘጋጁ ቅዱሳን ሰዎች ነው ብሏል። እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ለአዲስ ልደትና ደህንነት የተዘጋጁ ማለት ነው፣ ዮሐ. 3፡3–7። ክርስቶስ ለሙሽራይቱ ተመልሶ ይመጣና ወደ እርሱ ይወስዳታል፤ ያቺም ቤተ ክርስቲያን ናት፣ 1 ተሰሎ. 4፡16–17።

በቁጥር 2 የተገለጸችው አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በቁጥር 10 በረጅም ተራራ ላይ ያለችውን ቅድስቲቱን፣ አዲሲቷን ኢየሩሳሌምን ና እይ ሲል እናገኛለን። ይህች አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ቅዱሳን በሆኑ ሕዝብ መሃከል ሆና እግዚአብሔር በመካከላቸው የሚያድርባት ከተማ ሳትሆን አትቀርም፣ ዕብ. 11፡10። በዚህች ከተማ የምትኖረዋ የክርስቶስ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህች ከተማ ዛሬ በሰማይ፣ በኋላ በአዲሲቷ ምድር የምትሆን ናት። ይህች አዲሲቷ ኢየሩሳሌም

የጻድቃን የእረፍት ቦታ ሳትሆን አትቀርም። ይህች አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በሮቿ ሁልጊዜ አይዘጉም። ብርሃኗ ከአዲሱ ኢየሩሳሌም ወደ ምድር ያበራል። መብራቷም በጉ ይሆናል።

## ቁ. 3 አዲስ ሕብረትና ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር

በዚህ ቦታ ሐዋርያው ዮሐንስ አዲስ ሕብረትን እግዚአብሔር ከሰው ጋር እንደሚያደርግ ድምጽ ከሰማይ ሰማሁ ይላል። የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱ ጋር ያድራል። በድንኳን ማደር በዮሐ. 1:14 ላይ ኢየሱስ ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ በእኛ አደረ የተባለው የእግዚአብሔርን ክብር አየነው። ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በእኛ መካከል አደረ። ስለዚህ ኢየሱስ ከዚያ አንስቶ ለዘላለም በከበረው ሥጋው በቤተ ክርስቲያኑ (ሙሽራይቱ) ያድራል። እርሱ ሙሉ እግዚአብሔርና ሙሉ ሰው ነው፣ 1 ጢሞ. 2:5። በዚህ ቦታ ሦስቱ ሥላሴ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በመካከላችን ያድራሉ ማለት ነው። በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር በሙሴ ጊዜ በቤተ መቅደስ የእግዚብሔር ክብር እንደ ተገለጸ፣ ዘጸ. 40:34፤ 1ኛ ነገ. 8:10–11 ተመልከት። እንዲሁም የእግዚአብሔር ክብር በራሱ ሕዝብ መካከል ይሆናል። ኢየሱስ የጸለየው ጸሎቱ ይፈጸማል፣ዮሐ. 17:24 ። ይህ ማለት ሥላሴ ዙፋኑን ትቶ በምድር ይኖራል ማለት ሳይሆን እርሱ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉ ቦታ የሚገኝ አምላክ እንደሆነ አንርሳ፣ መዝ. (139):7–12። ይህ ነገር ለእኛ አሁን በሙሉ አይገባንም። በኋላ ግን ይገባናል፣ 1 ቆሮ. 13:12።

ቁ. 4 በዚያ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም እግዚአብሔር እንባዎችን ስለሚጠርግ እንባ የለም። ሞት አይገኝም። ሐዘን፣ ጩኸት ወይም ስቃይ የለም። የሚገርመው ነገር ዮሐንስ ሲገልጽ በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም የሌለውን ነገር ይገልጻል እንጂ ያለውን ነገር አይናገርም። ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ. 12:4 ወደ ሦስተኛው ሰማይ ተወስዷል። ያያቸውን ነገሮች ለመግለጽ አልሞከረም ነበር። ቢነግረንም እንኳ አይገባንም። ስለዚህ 1ቆሮ. 2:9 ላይ ያለውን ተመልከትና አስብ። ዮሐንስ ስለ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ያለውን ያህል ካወቅን በቂ ነው።

## ቁ. 5 ነገሮች ሁሉ አዲስ

በዙፋኑ የነበረው ለዮሐንስ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለውና ይህን ጻፍ አለው። የቀድሞ ፍጥረት ሁሉ በቀድሞ አባታችን በአዳም ኃጢአት ምክንያት ተበላሽቷል። አርጌም ሆኗል። አሁን ግን በሁለተኛው አዳም በክርስቶስ ምክንያት ሁሉም አዲስ ይሆናል፣ ኢሳ. 65:17። በክርስቶስ በማመን ሕይወታቸውን የሰጡት በክርስቶስ ስለሚሰጥ አዲስ ፍጥረት መሆን ይገባቸዋል፣ 2ቆሮ.5:17። ጳውሎስም በኤፌሶን 2:10 ኢየሱስም ለኒቆዲሞስ አዲስ ስለ መሆን ይገልጽለታል፣ ዮሐ. 3:3። በጌታ ሁለተኛ መመለስ ላይ የክርስቲያን ሥጋ እንኳ ይለወጣል፤ አዲስ ይሆናልም፣1ኛቆሮ. 15:53።

ቁ. 6 ከሚሰጣቸው ነገሮች አንዱ ለተጠማ የሕይወት ውሃ ነው። አልፋና ኦሜጋ መጀመሪያና መጨረሻ የሆነ ጌታ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ ይላል። በዘፍጥረት የተፈጠረ ምድርና ሰማይ በጊዜ የተወሰነ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስም በጊዜ ይፈጽማል። በዮሐንስ ራእይ 21 ዘላለማዊነት ይጀምርና በሰዓት መወሰን ያበቃል። ክርስቶስ ዘለአለማዊ ስለሆነ በአዲስ ሰማይና ምድር ዘላለማዊነት ይጀምራል። መጨረሻም አይኖረውም። ክርስቶስ በፍቅር የመረጠን ለዚሁ ነው፣ ኤፌ. 1:4፤ ቁ.10ና11። ኤፌ. 2:7።

ቁ. 7 ስለዚህ በክርስቶስ ሆኖ ድል የሚነሳ ይህን ይወርሳል። አዲስ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ይወርሳል። እግዚአብሔር አምላኩ ይሆናል። ድል የሚያደርግ ልጁ ይሆናል። ድል ማድረግ ከቃልና ከእምነት የተነሳ የሚመጣ እንደሆነ አንደኛ ዮሐንስ 5:4–5 ተገልጿል። ለክርስቲያን ምን ዓይነት አስደናቂ የተባረከ ተስፋ ነው የተሰጠው። ክርስቲያን በምትመጣዋ በአዲሲቱ ከተማ በኢየሩሳሌም ከንጉሡ ከኢየሱስ ጋር ለመሆን በርታና ጠላትህን ዲያቢሎስን ተዋጋ። ድል አድራጊ ሆነህ ተገኝ እንጂ ድል አትሁን፤ የሚረዳህ ጌታ ከአንተ ጋር ነውና።

## ቁ. 8 ለእምቢተኞች ማሳሰቢያ

ዮሐንስ በጌታ ድል አድራጊዎችን የወደፊት ዕጣ ከገለጸ በኋላ በአንፃሩ ለክርስቶስ ወንጌል እምቢተኞች ላይ የሚደርሰውን ያሳስባቸዋል። በኃጢአት ጸንተው ለጌታ ቃል እምቢ የሚሉት እድላቸው ምን ዓይነት እንደሚሆን ያሳስበናል። መልሰህ ቁጥር 8ን አንብብ።

ለማያምኑት የሚጠብቃቸው የእሳት ባህር ይኼውም ሁለተኛው ሞት ነው:: ምናልባት አንዳንዶች እኔ አይደለሁም፣ እነዚህን ኃጢአቶች አላደረግሁም፣ ለእኔ አይደርስብኝም ትሉ ይሆናል:: ሌላ ኃጢአት ባታደርግ ውሸትና ሐሰት ተናግረህ አታውቅምን? ማነው ሐሰተኛ? ራእይ 21:22 ላይ እንብብና ወልድን የሚክድ፣ የማይቀበልና የማያምን ኃጢአተኛ ነው ይላል:: በ1ኛ ዮሐ. 5:10 ራእይ 21:8 ስንመለከት እጅግ የሚገርመው ነገር አዲስ ሰማይና ምድር ሲፈጠር ወይም አዲሲቱ ኢየሩሳሌምና ሌላም አዲስ ነገሮች ሲሆን ነው:: ነገር ግን የእሳት ባህር ወይም ገሃነም የማይለወጥና ዘላለማዊ መሆኑን ማየት ትችላለህ:: እርሱ አይለወጥም:: ስለዚህ በጌታ ያላመኑት እድላቸው ለዘላለም በዚያ ይሆናል:: በጌታ ያላመነ በበደልና በኃጢአት የሞተ ነው:: ኤፌ.2:1 በጌታ ሲያምን ግን ወዲያውኑ ሕያው ይሆናል:: ኤፌ. 2:5 በኃጢአት ለጸና ሰው በአዲስ ሰማይና ምድር ወይም በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ቦታ የለውም፤ ለመግባትም አይፈቀድለትም::

## ቁ. 9–10 የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ገለጻ

ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ሲገልጽ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምና የክርስቶስ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ያሳያል:: መልአኩ ከሰማይ የምትወርድ ቅድስቲቱ ኢየሩሳሌም ከሰማይ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ስትወርድ 21:2 እንዲሁም 21:9 ላይ ሙሽራይቱ ተሸልማ ከቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩተሳሌም ጋር ያላቸውን ግንኙነት አጥብቀህ ተመልከት:: የተሸለመ ሙሽራና የተሸለመ ከተማ:: ይህች ከተማ ጌታ ለሙሽራይቱ ለቤተ ክርስቲያን ሄጄ ሥፍራ አዘጋጅላችኋለሁ፣ መጥቼም እወስዳችኋለሁ ያለውን የዮሐንስ ወንጌል 14:2 ያሳስበናል:: ይህች ከተማ ለሙሽራይቱ እንደ ተዘጋጀ አድርጎ ስለሚገልጽ፣ በቁጥር 10ና 11 ላይ ያሉትን ቆንጃጅት አትኩረህ ተመልከት:: ይህች ከተማ በምዕራፍ 4:3 ላይ እግዚአብሔር በዙፋን ላይ ምን እንደሚመስል ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሁሉ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መልክ አንድ እንደሆነ የእግዚአብሔር ክብር የሚታይበት ነው:: በዚያች ከተማ መብራት አያስፈልግም:: ብርሃን ከበጉ ይወጣል፣ 21:23 ተመልከት:: ከተማዋ የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን አያስፈልጋትም:: የእግዚአብሔር ክብር ያላት ናት:: በጉ ብርሃኗ ነው:: እንደዚሁም አማኞች የዓለም ብርሃን ናቸው፣ ማቴ. 5:14:: እንግዲህ ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት ያብራ፣ ማቴ. 5:16::

## ቁ. 16 የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ቅርጽና መልክ

ዮሐንስ ሲገልጽ በራእይ ያያት ከተማ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ተሸልማ የወረደች አራት ማዕዘን ቅርጽ አላት ይላል:: ርዝመቷ ስፋቷና ከፍታዋ እኩል ነበር:: አስራ ሁለት ሺህ ምዕራፍ ያህላል:: መልአኩ ሲለካት ሁለት ሺህ አራት መቶ ኪሎ ሜትር ያህል ሆነ ይላል:: በአዲሱ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከተማይቱ የት ልትሆን ነው? ለሚል ጥያቄ መልሱ ክርስቶስ የማዕዘኗ ራስ፣ ኤፌ.2:20 ሲሆን፣ ከእርሱ ዙፋን አንስቶ ንጹህ የሕይወት ውኃ የሚፈስበት ድረስ አካባቢ እንደሚሆን ይመስላል፣ ራእይ 22:1:: ይህም ሆኖ የዚያች ከተማ መሠረት የተጣለው በእግዚአብሔር ነው:: እነ አብርሃም ያችን ከተማ ይናፍቁ ነበር፣ ዕብ. 11:10:: ያቺ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በአሁኑ ምድር ላይ ሳይሆን በአዲሲቱ ምድር ላይ የምትሆን መስሉ ይታያል:: ቁ. 10 ተመልከት:: አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከታላቅና ረዥም ተራራ ላይ ዮሐንስ በነበረበት ተራራ ስትወርድ አያት፣ ከኢሳ. 2:1–4 ጋር አመዛዝኑት::

## ቁ. 17–18 የከተማይቱ ግንብ

በአዲሱ ትርጉም ብታነብ በጣም ገልጽ ያደርገዋል:: መልአኩ የግንቡን አጥር ሲለካ ሰባ ሁለት ሜትር ሆነ:: ውፍረቱና ቁመቱ የግንቡ ድንጋዮች ልዩ ልዩ ዓይነት የከበሩ ድንጋዮች ናቸው:: ከተማይቱ በንጹሕ ወርቅ ነበረ የተሠራችው:: እንደ መስታወት ንጹሕ ነበረች:: ከእነዚህ ከከበሩ ድንጋዮች የሚወጣው ብርሃን ለአካባቢውና ለፍጥረት ሁሉ ያበራ ነበር:: በቁጥር 19 እና 20 አንብብ:: የከተማይቱ መሠረቶች ተገልጸዋል:: መሠረቶቿ የከበሩ ድንጋዮች ሲሆኑ ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው ናቸው:: አስራ ሁለት የመሠረት ድንጋዮች ሲሆኑ የእግዚአብሔርን ክብር የተሞላ ብርሃን ከእነርሱ ይወጣ ነበር::

ቁ.14 የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም በመሠረቶችዋ ላይ ተጽፎ ነበረ፣ ኤፌ. 2:19–20:: የመሠረቱ ድንጋይ ራስ ክርስቶስ ስለሆነ እናንተ ከእንግዲህ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም ይላል:: ለዚህ ነው አማኞችን በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል-የሚለው::

## ቁ. 12–13 የቅድስቲቱ ከተማ የኢየሩሳሌም ደጆች

ዮሐንስ በራእይ ያያት አዲሲቱ ከተማ አስራ ሁለት ደጆች አሏት ይላል:: በእያንዳንዳቸው ደጆች መልአክት አሉባቸው:: ቁጥራቸው

አሥራ ሁለት ነበሩ፤ ደጆቹም በአሥራ ሁለት ዕንቁዎች የተሠሩ ነበሩ። ቁ.21 አንብብ። እነዚህ አሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች ስም በየደጆቻቸው ተጽፈው ነበር። እነርሱም የእሥራኤል ቅዱሳን አባቶች ስም ነበር። ይህን ዕንቁ የገዛው ክርስቶስ ነው። ዕንቁም ቤተ ክርስቲያን ናት፣ (ማቴ. 13:45-46)። ቤተ ክርስቲያን በውድ ዋጋ የተገዛች እንቁ ናት፣ 1ኛ ጴጥ. 1:18-19። የተከፈለውም ዋጋ የክርስቶስ የከበረ ደም ነው። ያቺ ከሰማይ የወረደችው ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም የቅዱሳን መኖሪያ ናት። የቤተ ክርስቲያን ከተማ ናት። እነዚያ በዕንቁ ያጌጡ ደጆች የሚያሳስቡን የማይጠቅሙ ጠጠሮችና አሸዋዎች ተሰብስበው ዕንቁ ሆኑ። እኛ በጌታ አምነን የዳንን ለክርስቶስ የማንመች፣ የምንቆረቁር ድንጋይና አሸዋ ነበርን። ግን ክርስቶስ በደሙ አበጀን። በጸጋ ድነናል፣ ኤፌ. 2:8። በእግዚአብሔር ዙፋን የነጻንና ያማርን ሆነናል ስሙ ይባረክ። በክርስቶስ ጸጋ የተሸፈንን ሆነናል። ክርስቶስ ለእኛ ሲል የከበረ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጥቶናል። ስለዚህ በእርሱ ፊት ከዕንቁ በላይ መሆናችንን ያሳስበናል።

ቁ. 18 ከተማይቱ በወርቅ የነጻች ናት ይላል። ቁ. 21 ደግሞ የከተማይቱ አደባባዮች ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበር ይላል። በዚህች ከተማ እግዚአብሔር ራሱ ብርሃን ሆኖ ይኖርባታል። የምድራዊ ከተሞቻችን በሲሚንቶና በአስፋልት ይሸፈናሉ። ሰማያዊው ከተማ ግን በንጥር ወርቅ ይሸፈናል። ወርቅ ኃጢአት የሌለበት ንጽሕናን ያሳስበናል። ስለዚያች ከተማ አስበንም ተናግረንም አንችልም ከሰው ግምት ሁሉ በላይ ነውና።

## ሦስት ዓይነት ሰዎች

በጣም የሚገርመው ነገር በዚህች በአዲሲቷ ቅድስት ከተማ ኢየሩሳሌም ሦስት ዓይነት ሰዎች ይኖራሉ።

ቁ. 9 አንብብ 1. የበጉ ሚስት ሙሽራይቱ ከልዩ ልዩ ወገን የዳኑት
ቁ.12 አንብብ 2. ከአሥራ ሁለቱ ወገኖች የእሥራኤል ልጆች የዳኑት
ቁ.24 አንብብ 3. ከአሕዛብ ማለት ከልዩ ልዩ ወገኖች የዳኑት
በዚያች ከተማ እንደሚገኙ እናስተውል።

ቁ. 22-23 በዚያች ከተማ አዲስ መቅደስ ይሆናል፤ አዲስም መብራት። ጌታ አምላክና በጉ መቅደስና መብራቷ ናቸው። ፀሐይና ጨረቃ አያስፈልጋትም። ሌላ መቅደስም የለም። በብሉይ ኪዳን ቅዱስተ ቅዱሳን የተባለ የእግዚአብሔር ድንኳንና መቅደስ ተሠርቶ ነበር።

በአዲሷ ኢየሩሳሌም ግን አያስፈልግም:: ጌታ እግዚአብሔር አምላክ በሕዝቡ መካከል ይኖራልና:: በብሉይ ኪዳን ዘመን መቅደስ በመካከል ሆኖ የእሥራኤል ሕዝብ በዚያ ይሠፍሩ ነበር፣ ዘኁልቁ ምዕራፍ 2:: ሊቀ ካህን ደም ይዞ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ ነበር:: በአዲሲቷ ከተማ ግን አያስፈልግም:: ምክንያቱም የእኛ ሊቀ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን ደም ይዞ ለዘለዓለም ወደ ሰማያዊው መቅደስ ስለገባ፣ ዕብ. 9:11–26:: በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከተማ ዙሪያ የመኖር ሥርዓትና አሰላለፍ እጅግ የሚያስገርም ነው፣ ቁ 13 ተመልከት:: አዲሲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ቅድስተ ቅዱሳን ያለባት ቦታ ናት:: ቅድስተ ቅዱሳን የልዑል እግዚአብሔር ማደሪያ ሲሆን ጌታ ራሱ መቅደስና ቅድስተ ቅዱሳን ሆኖ በሕዝቡ መካከል እንደሚያድር በቁጥር 22 ላይ ተመልከት:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን (እኛ አማኞች) የእግዚአብሔር ማደሪያ ቅድስተ ቅዱሳን ነን፣ 1ኛ ቆሮ. 6:19–20:: የቤተ ክርስቲያኑ የውስጥ ደንብ ኢየሱስ እኛን ቅዱስ ቅዱሳን ነገሥታትና ካህናት ስለ አደረገን ለስሙ ክብር ምስጋና ይሁን:: ራእይ 1:6::

የሌዊ ልጆች ካህናት በመገናኛ ድንኳን እንደሠሩ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከተማ ይሠፍራሉ:: ሙሽራው ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ንግሥትና ካህናት አድርጐ በዚያች ከተማ ያገለግለናል:: በዚያች ከተማ ያሉት አሕዛብና እሥራኤል በዚያች ከተማ ብቻ መኖር አይገደዱም:: ነገር ግን ይገባሉ ይወጣሉም:: መሰማሪያም ያገኛሉ:: አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለፍጥረት ሁሉ መሃከለኛ ሥፍራ ትሆናለች::

## የቤተ ክርስቲያን ዘለዓለማዊነት

የእግዚአብሔር እቅድ ለቤተ ክርስቲያን ማለት ለሙሽራይቱ እና ለዳኑት እሥራኤላውያን እንዲሁም ለዳኑት አሕዛብ መኖሪያቸውና ቤታቸው በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከተማ እንደሚሆን ራእይ 21:2, 9, 10 ተመልከት:: በዕብራውያን 12:22–23 ወደ እግዚአብሔር ከተማ... ወደ በኵራት ማህበር ደርሳችኋል እያለ ለቤተ ክርስቲያን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ልዩ ሥፍራ ላይ ያስቀምጣቸዋል:: ከክርስቶስ ጋር ለዘለዓለም ያስቀምጣቸዋል:: ይህም ዛሬ በእምነት ክርስቶስን ለሚከተሉትና የክርስቶስ አካል ለሚሆኑት ምዕመናን ነው:: አንተም አንቺም ለዚህ ተጠርታችኋል:: 1ኛ ተሰሎ. 4:18::

ቁ. 23 በጉ ራሱ ብርሃን ነው

በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ለማብራት ፀሐይና ጨረቃ አያስፈልጋትም። ምክንያቱም በጉ ራሱ የእግዚአብሔር ክብር ሆኖ ለከተማይቱ ያበራል። በዚህ ቦታ ፀሐይና ጨረቃ አይኖሩም አላለም። ነገር ግን ለከተማይቱ አያስፈልጓትም አለ እንጂ።

ቁ. 24 አህዛብ በብርሃኗ ይመላለሳሉ። ክብራቸውንም ወደ እርሷ ያመጣሉ። ዛሬም ቢሆን ክርስቶስ የዓለም ሁሉ ብርሃን ነው። ለፍጥረት ሁሉ የሚያበራ ብርሃን እርሱ ነው። ለአዲሱ ዓለምና ፍጥረት ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር መሆኑ ብቻ በቂ ነው።

ጥንት በፍጥረት ዘመን ሰው በኃጢአት ሲወድቅ የእግዚአብሔር ከእነርሱ መለየት ከባድ ጨለማ እንደ አመጣ ዘፍ. 1፡3–5፡14–18 እንብብ። ስለ አሁኑ አዲስ ፍጥረት ግን የኃጢአት መወገድና እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር መሆኑ፣ የብርሃን ምንጭ ይሆናል፣ ራእይ 21፡3። ዛሬ ግን ሰው በምድር ከብርሃን ይልቅ ጨለማን እንደሚወድ ኢየሱስ ተናግሯል፣ ዮሐ. 3፡19። እንዲሁም ኢየሱስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚያምንብኝ በጨለማ አይመላለስም፣ ዮሐ. 8፡12 የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ አለ። ዛሬ በብርሃን ብንመላለስ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፣ 1ኛ ዮሐ. 1፡7። ስለዚህ በአዲሲቷ ኢየሩሳሌምና በፍጥረቱ ኃጢአት አይገኝም።

ቁ. 25–26 በዚያች ከተማ ኃጢአት ስለሌለ ጨለማ አይኖርም። ሌሊትም የለም። በጉ ብርሃኗ ነው። በሮችዋም ቀንና ሌሊት አይዘጋም። ምክንያቱም ጨለማና ኃጢአት የለምና ነው። በዚያ በዘላለም ቤት የጸኑት ሁሉ አይናቸውን አንሥተው ወደ ጌታ ክብር የሚመለከቱበት እንጂ ችግር የለም። ጌታም በመካከላቸው ስለሆነ ያመልኩታል።

ቁ. 27 በዚያ ቦታ በበጉ ደም የነጹት በሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ከተጻፉት በስተቀር ሌላ አይገባም። በቁጥር 8 ያሉት ሁሉ ቦታ የላቸውም። ከቶም አይገቡም። ወዳጄ ሆይ ለዚያች አዲሲቷ ከተማ ዛሬ ተዘጋጅ። ወደ ጌታ ተመለስ። ዛሬ ነው እድልህ ወደ ጌታ ተመለስ።

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 22፡1–5 ያለው ሃሳብ ከምዕራፍ 21 ጋር አብሮ የሚሄድና ሃሳቡም አንድ ስለሆነ በምዕራፍ 21 ሥር እንመለከታለን።

# የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 22

# አዲሲቷ ገነት

ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ አዲሲቷ ገነት ሲናገር መልአኩ እንዲህ አለኝ ይላል።

ቁ. 1–5 በአዲሲቱ ገነት መካከል በጣም ንጹሕ የሆነ ውኃ ወንዝ አሳየኝ ይላል። እንዲሁም ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ። ዛፊቷም በየወሩ ፍሬ ትሰጣለች። አንዳንድ ሰው በዘለዓለም ቤት እንበላለን ወይ ብለው ጥያቄ የሚጠይቁ አይጠፉም። መልሱ አዎን ነው። ለዘላለም ለመኖር ባንበላም እንኳን ኢየሱስ ከሞት በክብር ከተነሳ በኋላ የክብር ሥጋ ለብሶ ነበር። ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ መብላት አስፈላጊ ባይሆንም እንኳን በልቷል፣ ሉቃስ 24፡28–43 ተመልከት። በዘለዓለማዊ ቤት ሌሊት የለም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ብርሃንዋ ነው። በዚያ ቦታ ድካምና እረፍት የለም። ጌታን ከማገልገል አያቋርጡም።

ቁ. 2 የሕይወት ዛፍ ቅጠል እንኳን ሕዝቡን የሚፈውስ ነው። ማለት በዚያ ሕመም አለ ማለት አይደለም። ቅጠሉ፻ ለፈውስ ነው የሚለው ቃል በዚያ ለዘለዓለም ፈውስ ይቀጥላል ለማለት ነው። ፈውስና ጤንነት ሁልጊዜ ስለሚኖር ሕዝብዋ ሁልጊዜም ደስተኞች ናቸው። በዚያ መርገም ስለሌለ ሕመም የለም። ቁ. 3። መርገምና ኃጢአት ተወግዷል። በዚያ ከተማ የሚኖሩ ሁሉ መልካቸው እግዚአብሔርን ይመስላል፣ ቁ. 4 አንብብ። በ1ኛ ዮሐ. 3፡2 ላይ የተባለው የሚፈጸምበት ዘመን ይሆናል።

ቁ. 5 ሐዋርያው ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ ሲያሳይ፡–

1. የኢየሱስን ሰብአዊ ክብርና በአባቱ ዘንድ አሁን ያለው ክብር፣
2. የኢየሱስን የማያልቀውን ጸጋ ለቤተ ክርስቲያኑ ያለውን፣ ቁጥር 4ን አንብብ፣
3. የኢየሱስ ክርስቶስን ዘለዓለማዊ ንጉሥነቱን ያሳያል፣ ቁጥር 5ን አንብብ። ኢየሱስ ጌታነው!!

የመጨረሻ ቃል ማረጋገጫና ጥሪ፤ ቁ. 6–21 አንብብ።

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዮሐንስ በራእይ የተናገረውን የገለጸውን ያረጋግጥለታል

2. ዮሐንስ በመጽሐፉ የጻፈውን ጽሑፍ እንዲህ እያለ ያረጋግጥለታል።

ቁ. 6 ቃሎቹ

እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞች ናቸው። በዮሐንስ ራእይ የተባለውና የተጻፉት ቃሎች እርግጠኞች ናቸው ይላል። የቃሉ ታማኝነት እውነት ብቻ የሞላበት ነው። የተባለው ቃል ሁሉ ዋጋ ያለው ቃል ነው። ሰዎች ሊታመኑበት የሚገባ ነው። እግዚአብሔር ያለው ነገር እውነተኛ ታማኝነት ያለበት ቃል ስለሆነ እኛ ማመንና መደገፍ አለብን። ቃሉ እውነት ከሆነ ወደ መታየት ይመጣል ወይም ውጤት አለው። በእግዚአብሔር ዘንድ እውነት በቃል ይሰማል። እውነት በድርጊት ይፈጸማል። እውነት ያው እውነት ነው። እግዚአብሔር ለእኛ በጣም አድርጉ ሊገልጽልን የሚፈልገው ኢየሱስ ለዮሐንስ የገለጸው ነገር እውነት መሆኑን ነው። ስለዚህ ማንም ከተገለጠው እውነትና እርግጠኝነት ጨምሮ፣ አጋንኖና አሳንሶ፣ ወይም አጉድሎ መገኘት የለበትም።

የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ በብዛት ከብሉይ ኪዳን ጋር የሚጠጋና ብዙ የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎች የሚታይበት መጽሐፍ ነው። ብዙ የራእይን ትርጉሞች ለማግኘት ወደ ብሉይ ኪዳን ታሪኮችና ምሳሌዎች መሄድ አለብን ማለት ነው።

የዮሐንስ ራእይ በተለይ በመንፈስ ቅዱስ አዲስ ለተወለዱት መንፈስ ቅዱስ ገለጻ የሚሰጥበት መጽሐፍ ነው። የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ለፍጥረታዊ ወይም ሥጋዊ ሰው አይገባውም። ለእርሱ አልተጻፈለትምና።

በክርስቶስ አዲስ ልደት ላገኙት ነው የተጻፈው። ምክንያቱም በቃሉ ይሄዱበታል በቃሉም ይኖሩበታል። ለእነርሱ ይገባቸዋል። ስለዚህ ነው ይህን ቃል ለሚጠብቁት የበረከት ተስፋ የሰጣቸው፣ ቁጥር 7 አንብብ። የተሰጠው የበረከት ተስፋ ቃሉ የታመነ ነው። ማንበብና መታዘዝ በረከትንም መቀበል የእኛ ጉዳይ ነው።

## ቁ. 7 እነሆ በቶሎ እመጣለሁ

ጌታችን እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ይላል:: ይህ ማረጋገጫ ቃል በዚህ መጽሐፍ እየተደጋገመ የተጻፈ ቃል ነው:: በቶሎ እመጣለሁ የሚለው ቃል በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ሰባት ጊዜ ተደጋግሞ ተጽፎአል:: ይህ በቶሎ ማለት በፍጥነት፣ በቅርብ ጊዜ ማለት እንዳልሆነ ማሰብ አለብን:: ቶሎ የሚለው ቃል ሰዓት ወይም ደቂቃን የሚመዝን አይደለም:: ነገር ግን እግዚአብሔር እመጣለሁ ሲል፣ በጊዜው እመጣለሁ፣ በሰዓቱ እመጣለሁ፣ ወይም በተወሰነ በዚያች ሰዓት እመጣለሁ ማለቱ ነው:: ከተወሰነው ሰዓት አያልፍም:: በቀጠሮው ሰዓት የማይቀር ነገር ነው ማለት ነው:: እርግጠኛው ቀን መቼ እንደሆነ ባናውቅም እንኳ በዚያ በተወሰነው ቀን አልቀርም ይላል:: ለዚህ ምሳሌ አስቡ:: በመጀመሪያ ሥጋ ለብሼ እመጣለሁ ብዬ በነቢያቶች በተናገርሁ ጊዜ፣ ጊዜው ሳያልፍ በወሰንሁት ዘመንና ወር፣ ቀን መምጣቴን አስታውሱ ይለናል፣ (ገላ. 4:4):: ይህ ምሳሌ ምልክት ይሁንላችሁ:: በዚህ መጣሁ እንጂ አልቀረሁም:: አሁንም ለዳግም መምጣቴ እምነት ይኑራችሁ፣ ንቁና ጠብቁኝ ይላል::

ሌላም ምልክት አስታውሱ፣ መንፈስ ቅዱስን እኔ ሄጄ እሰድላችኋለሁ ያልኩትን አስቡ፣ ዮሐ. 16:7-10 ተስፋውን አንብቡ:: ደግሞ የተናገርኩት እንደ ተፈጸመ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2ን አንብቡ:: ሁሉም በጊዜው ሆኗል:: አሁንም ይሆናል ማለት ነው:: ስለዚህ ጌታ በሰዓት ታማኝ ነው ከተባለ ከሰዓት ወደ ፊት አይሄድም:: ከሰዓቱም ወደ ኋላ አይቀርም ልክ በሰዓቱ እመጣለሁ ማለቱ ነው::

## ቁ. 7 የበረከት ተስፋ

እግዚአብሔር በግለሰብ ወይም በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ከዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ለሚያነቡና የተባለውንም ለሚጠብቁት በረከት ሊሰጥ ተስፋ የገባበት ቃል ያረጋግጣል:: ምዕ. 1:3 ላይ ከዚህ በፊት ትምህርት ወስደናል:: እግዚአብሔር በመጽሐፉ መጀመሪያ ተናገረ:: አሁንም ሁለተኛ በምዕራፉ መጨረሻ ላይም ያረጋግጥልናል:: ቃሉን የሚያነብና የሚሰማ የሚጠብቅ ወይም የሚፈጽም የተባረከ ነው ይላል:: አሁንም በምዕ. 22:7 ተደገመ:: ስለዚህ ቃሉቹን መጠበቅ ወይም መደጋገም ያስፈልጋል እንጂ መርሳት አያስፈልገንም:: ክርስቲያን በየጊዜው የራሱን ሕይወት በዚህ መጽሐፍ ቃል መለካትና መመዘን ያስፈልገዋል::

የዚህ መጽሐፍ ጥቅም እኛ ለእግዚብሔርና ለእግዚአብሔር ክብር ለመገዛትና ለመታዘዝ ፈቃደኞች ሆነን እጅ ስንሰጥ ብቻ ነው:: ያኔ ነው በረከቱን ሁሉ እንደ ተስፋ ቃሉ የምንቀበለው::

ቁ. 8–9 እኛ በመጽሐፍ ቅዱሳችን በጠቅላላ የታዘዝነው ለእግዚብሔር ብቻ እንድንሰግድና እንድናመልክ ነው::ዮሐንስ በዚህ ቦታ ለመልአክ ሊሰግድ እንደ ሞከረና መልአኩ አትስገድልኝ እኔ እንደ አንተ የእግዚአብሔር ባሪያ ነኝ አለው:: ይህ ቃል የተደጋገመ ነው:: ምዕ. 19:10 ላይ መመልከት እንችላለን:: መልአኩም ለእግዚአብሔር ብቻ ስገዱ ይላል:: ማርያምም ኢየሱስ የሚለውን አድርጉ አለች፣ ዮሐ. 2:5 ተመልከት:: ለመላእክት እንድንሰግድ ትእዛዝ አልተሰጠንም:: እግዚአብሔርን እንድናመልክ ነው እንጂ:: እግዚአብሔርን ማምለክና ለእርሱ ብቻ መስገድ ስንጀምር፣ ዮሐ. 4:23–24 በእውነትና በመንፈስ ስንሰግድ፣ እግዚአብሔር ሆይ አንተ ሊሰገድልህና ልትመለክ የሚገባህ ነህ ማለታችን ነው:: ስለ እግዚአብሔር ብዙ መማር ስንጀምር ብዙ እናውቃለን:: ብዙ ማወቅ ስንጀምር እርሱን ብቻ እናመልካለን::

## ቁ. 10 የትንቢትን ቃል በማኅተም አትዝጋው

ዮሐንስ ሲናገረኝ ዘመኑ ቀርቧልና የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል በማኅተም አትዝጋው ተባልኩኝ ይላል:: ዘመኑ ወይም ሰዓቱ ደርሷል ይላል:: ክርስቶስ በወሰነው ወይም በተባለለት ሰዓት ሊመጣ ነው:: ቃሉን እንዳትዘጋ:: በማኅተም አትዝጋው ይላል:: ይህ ቃል በዳንኤል 12:4 ላይ ከሚገኘው ቃል ተቃራኒ ነው:: በዳንኤል ትንቢት ዝጋው፣ አትመው ይላል:: ይህ ማለት ለዳንኤል ትንቢቱን ዝጋው፣ አትም የተባለበት ምክንያት የትንቢቱን ቃል ዝጋ ለሰው አይገባምና የትንቢት መጨረሻ እስኪመጣ አይገባም:: ስለዚህ ዝጋው አለው:: ለዮሐንስ ግን ክፈት ነው ያለው:: በትንቢት መፈጸሚያ ዘመን ስለሆነ ዮሐንስ የትንቢት ፍጻሜ እንዲከፍትና ትርጉሙን እንዲፈታ ተናገረ:: ትንቢቱ በሚፈጸምበት ጊዜ ወይም ዘመን ላይ የሚያነበው ግለሰብ ይገባዋል:: የሚያነበው ቤተ ክርስቲያን ይገባዋል:: ትርጉሞቹ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ይገባዋል:: በራእይ 1:1 ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባ ነው ይላል:: ቶሎ ያልፋል ማለት ነው:: የመጽሐፉ እውነት ወደ ፍጻሜ ይደርሳል ይፈጸማል ነው::

ቁ. 11 የጠፉት ሰዎች ሁኔታ

አስፈሪ የሆነ የጠፉት የነፍሳት ሁኔታ፣ በዚህ ቦታ የሚያመለክተው በነጭ ዙፋን ፊት ፍርድን ያገኙት ጠፍተው ለዘላለም በዚያ በጥፋት ባህር ማለት በዘለዓለም እሳት ባህር እንደሚጠፉ ያሳስብናል:: የጸደቁትና የዳኑትም በቦታቸው ጸንተው እንደሚቀጥሉ እያሳሰበ አሁንም ይህ እውነት የማይለወጥና የማይሻር የእግዚብሔር ቃል ነውና ተጠንቀቁ የሚልየአምላካችንን ምክር እንስማ:: እግዚአብሔር ማስታወቅ የሚፈልገው ክፉ ክፋቱን ይቀጥላል:: ከዘላለም ፍርድ በኋላ የሚቀየር ነገር የለም:: የሚሻሻል ነገር ምንም አይኖርም:: ለዘለዓለም እንደ ተፈረደበት ይቀጥላል:: እየባሰ ይሄዳል እንጂ የሚቀንስ ፍርድ ወይም አስተያየት፣ ምህረት አይኖርም ነው:: በአመጽና በእርኩሰት ያሉት ለዘለዓለም በዚያው ይቀጥላሉ ማለት ነው:: በክርስቶስ መምጫና ወይም ከሞት በኋላ ወደ ሕይወት መንገድ ወደ ጌታ መመለስ አይቻልምና ዛሬውኑ ወደ ጌታ ና:: ከሞት በኋላ መንፈስ ቅዱስ ሊረዳህ አይችልም:: የመጽሐፍ ቅዱስንም ቃል ለመስማት እድል አይኖርህም:: ኢየሱስ ያለውን አስብ፣ ማቴ. 7:21–23 ስለዚህ ከፍርድ ለመዳን ጊዜው አሁን ነው::

የዳኑት ሰዎች ሁኔታ

ቁ. 11 «ጻድቁ ወደፊት ይጽደቅ ቅዱሱም ወደ ፊት ይቀደስ::» ይህ የጌታ ትእዛዝ ነው:: በጽድቅና በቅድስና ማደግ አለበት ማለት ነው:: ወደ ፊት የሚል ቃል ከዳኑ በኋላ ወደ አዲሲቱ ሰማይና ምድር ከደረሱ በኋላ ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከገቡ በኋላም መንፈሳዊ እድገት ይቀጥላል ማለት ነው:: በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መጽደቅ ማቀደስ እግዚአብሔርን በመምሰልና በማወቅ እድገት ይቀጥላል:: ክርስቲያኖች ወደ አዲሱ ሰማይና ምድር ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሲደርሱ እያደጉ መንፈሳዊነት ይቀጥላል እንጂ በምድር ከሞት በፊት በነበሩበት ሁኔታ እንዲቆዩ አይደረጉም:: ሁልጊዜ በመንፈስ መጽደቅና መቀደስ ይቀጥላል:: በጌታ የሆናችሁ ስለዚህ አደራረግና ሥራ ጌታን ሁልጊዜ አመስግኑ::

ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ

ቁ. 12 ክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ለመገናኘት እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ይላል፣ 2ኛ ቆሮ. 5:10:: ዋጋዬም ከእኔ ጋር ነው ይላል::

ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው ይከፍል ዘንድ ነው። ይህ የክርስቲያኖች የሥራቸው ወይም የአገልግሎታቸውን ዋጋ መከፈያ ቦታ እንጂ የዮሐንስ ራእይ 20፡11 ታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ቦታ አይደለም። የነጩ ዙፋን ፍርድ ላላመኑት ሲሆን ላመኑት ግን በፍርድ ወንበር ፊት ነው። የክርስቲያን ዋጋ የሚከፈልበት ቦታ ክርስቶስ በአየር ሲመጣ ክርስቲያኖች በአየር ከተገናኙ1ኛተሰሎ. 4፡16–17 መሠረት ቤተ ክርስቲያን ስትነጠቅ ጌታ በሰማይ ዋጋ ለክርስቲያን የሚከፍልበት ጊዜ ነው።

ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ምን እንዳለ በ2ኛ ቆሮ. 5፡10–11 ተመልከት። ደግሞ በ1ኛ ቆሮ. 3፡13–15 ክርስቲያን ዋጋው ውጤታማ የሚሆነው በእሳት ተፈትኖ ሲወጣ ነው። የክርስቲያን ሥራ ቢቃጠልበት ግን ክርስቲያን ይጐዳበታል። ነፍሱ ግን በጌታ ስላመነ ይድናል። ስለዚህ ክርስቲያን ሆይ ዋጋህ በጌታ እጅ ነው፤ ና በጌታ አምነህ ከዳንክ ለአገልግሎት በርታ። 1ኛ ቆሮ. 15፡58፤ ገላ. 6፡9–10። ተመልከት።

## መጀመሪያና መጨረሻ

ቁ. 13 ክርስቶስ አልፋና ኦሜጋ መጀመሪያና መጨረሻ እኔ ነኝ ይላል። ይህ ማለት ክርስቶስ ከእኔ በፊት ማንም የለም፣ ከእኔም በኋላ ማንም የለም እያለ የመጨረሻ ማረጋገጫ ሲሰጥ ነው። በዘመንና በጊዜ ሁኔታም ከሄድን እርሱ ነበረ፣ በኤደን ገነት እርሱ ነበረ፣ አሁንም በአዲሲቷ ቅድስቲቱ ከተማም እርሱ ነው። ለዘለዓለም የሚኖር ፈጣሪ እርሱ ነው። ወይም ወደ መታየት አምጪውም የፈለገውን የሚፈጽምም የሚጨርስም እርሱ ነው። እርሱ መጀመሪያና መጨረሻ ነው።

## ሌላ የበረከት ተስፋ

ቁ. 14 በዚህ ቁጥር ሌላ የበረከት ተስፋ ተሰጥቶናል። ይህም የእርሱን ፈቃድ ለማድረግ ፈቃደኞ የሆኑ ብጹአን ናቸው ይላል። እነርሱ የሕይወት ዛፍ ያለበትን ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸውና ወደ ከተማይቱ እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብጹአን ናቸው። ልብሳቸውን ማጠብ ትእዛዝ ነው። ይህ ልብስ ማጠብ ማለት ትእዛዝን መጠበቅ ነው፣ መዝ.(119)፡9። ልብስን ማጠብ ንጹህ ያደርጋል፣ 1ዮሐ. 1፡7። የክርስቶስ ደምና ቃሉ ኃጢአትን ያጥባል ያነጻል።

የእርሱን ትእዛዝ መጠበቅ 1 ዮሐ. 3:23 በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን፣ ትእዛዘን መፈጸም ማለት ነው:: ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ በሮቹን የሚጠቀሙ ብጹአን ናቸው:: ኢየሱስ በሩ እኔ ነኝ አለ፣ ዮሐ. 10:9:: በእኔ የሚገባ ይድናል:: ወደ ከተማይቱ የሚወስደው መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ ዮሐ. 14:6:: ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ በሮቹን መጠቀም አለብን:: እርሱም ኢየሱስነው:: ትክክለኛውን መንገድ ይዘው ወደ እውነተኛው በር የሚጓዙ እነርሱ አሸናፊዎች ናቸው ተብለዋል፣ 1 ዮሐ. 5:5:: ከሕይወት ዛፍ ለመብላት ሥልጣን ያላቸው በበጉ ደም ብቻ ልብሳቸውን ያጠቡት ናቸው:: ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ለመድረስ የሚችሉት እውነተኛውን መንገድ ክርስቶስን ይዘው የሚጓዙት ብቻ ናቸው:: ስለዚህ ጉዳይ በራእይ 21:17 የተጠቀሰውን ተመልከት:: በበጉ መጽሐፍ ስሞቻቸው የተጻፉት ብቻ በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምኑ አማኞች ይደርሳሉ፣ 1 ዮሐ. 5:10–13 ተመልከት::

ቁ. 15 ሌሎች በኃጢአት እርኩሰት የሚመላለሱ ውሾች፣ አስማተኞች፣ ሴሰኞች፣ ነፍስ ገዳዮችና ጣዖትን የሚያመልኩ ውሸታሞች ወደዚያ አይገቡም:: ቦታ ወይም ሥፍራ ለእነርሱ በእግዚአብሔር ከተማ የላቸውም:: እነርሱ ወደ ውጭ ማለትም ወደ እሳት ባህር ይጣላሉ::

የዳዊት ሥርና ዘር

ቁ. 16 አሁን ኢየሱስ ለዮሐንስ የሚገልጸው ነገር ነው:: አብያተ ክርስቲያናት የሚለው ቃል ወይም ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በራእይ ምዕ. 3 ላይ ከተገለጸው እስካሁን ድረስ በዚህ በመጨሻው ምዕራፍ ላይ በዚህ ቦታ ለመጀመሪያ መናገሩ ነው:: ኢየሱስ ይህን ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲመሰክርላቸው መልአኩን ላክሁ ይላል:: ለዮሐንስ ሲናገር ኢየሱስ ለራሱ እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ ይላል::

የዳዊት ዘር ኢየሱስ ራሱን ከእሥራኤል ዘር ከዳዊት ቤተሰብ እንደሆነ ይመሰክራል:: ዳዊት ንጉሥ ነበረ:: ኢሳ. 11:1:: የተሰጠው ተስፋ እንደ ተፈጸመ በትንቢት ተመልከት:: እርሱ የዘላለም ንጉሥ ነው:: እንዲሁም ኢየሱስ ራሱን ከቤተ ክርስቲያን ጋር አንድነት እንዳለው ይመሰክራልም፡

የንጋት ኮከብ ነኝ ሲል የቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ መነጠቅን ያሳስበናል:: ክርስቶስ እንደ ንጋት ኮከብ በአየር ለቤተ ክርስቲያንና ለእሥራኤል እንደሚመጣ ያሳስበናል:: ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ክብር መገለጽ እንድትዘጋጅ ጥሪ ያቀርባል:: የንጋት ኮከብ በጨለማ እንደሚያበራ እንዲሁም የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ለዚህ በኃጢአት ጨለማ ላለው ዓለም ታላቅ ተስፋ ነው:: በተለይም በዚህ ጨለማ ለምትንከራተት ቤተ ክርስቲያን ትልቅ እድል ነው:: እርሷን ለመውሰድ ይመጣል:: በኋላም እንደ ፀሐይ ሆኖ የእሥራኤልን ነገድ ሊረዳ ይመጣል፣ ሚልክ. 4:1–3::

ለሁሉም የጥሪ ቃል

ቁ. 17 ሁሉንም የሚያጠቃልል ጥሪ

ሦስት የጥሪ ግብዣ ተመልከት

1. መንፈስና ሙሽራይቱ ና ይላሉ::
2. የሚሰማም ና ይበል::
3. የተጠማ ይምጣ ከወደደ የሕይወት ውኃ እንዲያው ይውሰድ::

መንፈስ ቅዱስና ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ና ብለው ይጋብዛሉ:: የተዘጋጁት ሁሉ የክርስቶስን ድንገት መገለጥ ይጋብዛሉ:: የትንቢት ቃል እንደሚለው የጌታ መምጣትን ይጠራል:: በዮሐንስ ወንጌል 5:24 የጥሪ ቃል ስላለ ሰምተን መልስ መስጠት አለብን:: ኢሳ. 55:1 ለሚሰማ ሁሉ ጥሪ አለ፤ ለተጠማና ውኃ ለሚፈልግ ማለት የውስጥ የልብ የነፍስ እረፍትና እርካታ ያጣ ወደ ኢየሱስ ይምጣ፣ ዮሐ. 7:37:: ፍጹም እረፍትና እርካታ ታገኛለህ:: በሕይወቱ ባዶነት የሚሰማው ሁሉ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይምጣ፣ ዮሐ. 3:16፤ 5:40፤ ሮሜ 10:13:: ፍጹም እረፍትና እርካታ ይገኛልና::

ጥብቅ ማስጠንቀቂያ

ቁ. 18–19 በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚጨምሩ ወይም ለሚቀንሱት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል::

1. በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ወይም በትንቢት ማለት የእግዚብሔር ቃል በሙሉ ትንቢት ነውና ለሚጨምር ሁሉ በመከራ ዘመን ያዩናቸው መቅሰፍቶች ሁሉ ይጨመርበታል::

2. በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ወይም በትንቢት መጽሐፍ ማለት የእግዚብሔር ቃል በሙሉ የትንቢት ቃል ነውና ከእርሱ አንዳች ቢቀንስ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።

እንግዲህ በእግዚአብሔር ትንቢት ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን የማያስተምር ምን ይውጠው ይሆን?

እንዲሁም በእግዚአብሔር ትንቢት ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለውን እያስተማሩ ሰውን ከእግዚአብሔር ጎዳና የሚያሳስቱ ምን ይውጣቸው ይሆን?

የሰው ጥበብ የእግዚአብሔርን ፍርድ ሊቀንስ አይችልም።

ቁ. 20 ኢየሱስ ቶሎ እመጣለሁ እያለ ትልቅ ማሳሰቢያ አስቀምጦልናል። ይህን የሚመሰክር እመጣለሁ ይላል። ይህ የመጨረሻ ድግግሞሽ ነው። ቶሎ እመጣለሁ የሚለው የኢየሱስ ቃል የኢየሱስ ዳግም መምጣት የመጨረሻ ማረጋገጫ ቃል ነው ቶሎ እመጣለሁ።

ዮሐንስም አዎን አሜን ይሁንልን እያለ ይመልሳል። ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያንን ወክሎ አዎን ጌታ ሆይ ቶሎ ና ይላል። ዛሬ የቤተ ክርስቲያን ጩኸት ና ጌታ ሆይ ቶሎ ና የሚል ነው። አንባቢ ሆይ አንተስ ጌታ ኢየሱስ ሆይ እባክህ ቶሎ ና ለማለት ተዘጋጅተሃልን?

ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን

ቁ. 21 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን አሜን። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ ጥቅስ ነው። የመዝጊያ ጥቅስ ከዚህ የሚቀጥል አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አይገኝም። አሜን ነው። በዚህ ጥቅስ የምናየው ነገር አሁንም በመጨረሻ እንኳን የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰዎች እንዳለ የሚገልጥ ነው። የእግዚአብሔር የማዳኑ መንገድ ለኃጢአተኞች እስካሁን ክፍት መሆኑን ነው። ወደ ጸጋው መምጣት ይችላሉ። ጸጋ ነጻ ስጦታ ነው። መዳን በሥራ ሳይሆን በክርስቶስ በማመን እንደሆነ እየገለጸ ነው፣ ኤፌ. 2:8። መጽሐፍ ቅዱስ ሰው በሥራው ለመዳን ቢሞክር እዳ እንዳለውና በክርስቶስ በማመን ከሆነ ግን እምነት ጽድቅ ሆኖ እንደሚቆጠርለት በግልጽ ይገልጽልናል፣ ሮሜ 4:4–5። ደህንነት በጸጋ እንጂ በተግባር እንዳልሆነ ኤፌ. 2:8–9 ተመልከት። መዳን በእግዚአብሔር የጸጋ

ስጦታ ብቻ በማመን ይገኛል። ጸጋ ለክርስቲያን መንፈሳዊ እድገት የሚሰጥ ነጻ ስጦታ ነው። እግዚአብሔር ለበጎ ሥራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል፣ 2ቆሮ. 9:9።

ዛሬ ይህን ማስታወሻ የምታነብ ሁሉ ጌታ ኢየሱስን በእምነት ብትቀበል ጸጋ ለአንተ እንደሚሆንልህ እወቅ። የእግዚአብሔር የምህረት እጁ አሁንም ተዘርግቶ እንደሚጠብቅህ እወቅ። ወደ ጌታ ና። የክርስቶስን ጸጋ በእምነት ተቀበል። ልብህን ለጌታ ስጠው፣ ሮሜ 10:9-13። ለነፍስህ እረፍት ታገኛለህ፣ ማቴ. 11:28:30።

## በተጠማሪ የምትመለከታቸው ጥቅሶች

1. ስለ መንግሥተ ሰማያት ወይም የእረፍት ሥፍራ

ማቴ. 25:34፤ ራእይ 21:1-7፤ 22:1-5፤ ዕብ. 4:14፤ 2 ቆሮ. 12:2፤ ዮሐ. 14:1-3፤ ዕብ. 12:22-24፤ ራእይ 21:1-27፤ ማር. 12:25፤ ራእይ ምዕራፍ 4 ና 5 በሙሉ፤ ኢሳ. 66:24፤ ማቴ. 8:11፤ 2 ቆሮ. 5:1-8፤ ቆላ. 3:1-4፤ ፊልጵ. 1:20-23፤ 3:20።

2. ስለ እሳት ባህር ወይም የቅጣት ሥፍራ

ማቴ. 25:42፤ ማር. 9:42-48፤ ራእይ 20:7-15፤ መዝ. (30):9፤ ዘኍ. 16:33፤ ኢሳ. 38:10፤ ኢዮብ 24:19፤ 2 ጴጥ. 2:4፤ ማቴ. 8:12፤ ራእይ 4:10-11፤ ዕብ. 6:4-8፤ ራእይ 14:11፤ ማቴ. 25:46፤ ዮሐ. 5:29፤ ዳን. 12:2፤ ሮሜ 2:8-10፤ ራእይ 20:10-15፤ ዕብ. 10:27፤ ዕብ. 9:27።